# በአህሉልበይት መንሐጅ ዙርያ የሚነሱ ጥያቄዎች

ሰይድ ሙስጠፋ አል-ቀዝዊኒ

ትርጉም፡- ጣሂር መሐመድ ዓሊ አል-ጎዳነምቢ

አብዱልዓዚዝ ኢብራሂም

*ነሓሴ 2004*

www.bookshia.com
knowledge enlivens the soul

# በአህሉልበይት መንሐጅ ዙርያ የሚነሱ ጥያቄዎች

ሰይድ ሙስጠፋ አል-ቀዝዊኒ

www.bookshia.com
knowledge enlivens the soul

**ማውጫ** **ገጽ**

መግቢያ ........ 2

ሺዓዎች ማን ናቸው? ........ 8

አምስቱ የኢስላም መዝሐቦች ........ 12

ጃዕፈሪ ........ 12

ሐነፊ ........ 14

ማሊኪ ........ 15

ሻፊዒ ........ 16

ሐንበሊ ........ 17

ኢማማህ (ኢማምነት/መሪነት) ........ 19

1. የንግስና አያህ ........ 23
2. የመፍረድ ስልጣን አያህ ........ 23
3. የማዘዝ ስልጣን አያህ ........ 23
4. የመሪነት ስልጣን አያህ ........ 24
5. የመከተል አያህ ........ 25
6. የመምረጥ ስልጣን አያህ ........ 25
7. ፍርድ የመስጠት ስልጣን አያህ ........ 26

ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ........ 29

የማስጠንቀቂያው ቀን አያህ ........ 31

የሩኩዕ አያህ (ሩኩዕ ውስጥ በመሆን ምጽዋት መስጠትን አስመልክቶ የወረደ የቁርአን አያህ) ........ 33

የመሪነት ስልጣን የተሰጡትን የመታዘዝ አያህ............................ 34
የዓሊ ኸሊፋነትን አስመልክቶ ከቅዱሱ ነቢይ
(ሰ.ዐ.ወ) የተያዙ ሐዲሶች ............................................................ 35
ሁሉም ከቁሬይሽ ጎሳ የሆኑ አሥራ ሁለት ኢማሞች
(መሪዎች) የነቢዩ ኸሊፋዎች ሆነው እንደሚነሱ
የሚጠቅሱ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተያዙ ሐዲሶች በጥቂቱ ................. 38
አህለልቤይት(ዐ) .................................................................................. 40
የፍጹም መጥራራት አያህ (አያት አል-ጠሓራህ) ........................... 40
የውዴታ አያህ (አያት አል-መወድዳህ)......................................... 42
የሙባሐላ አያህ (የመፈታተኛ/መረጋገሚያ አያህ) ........................ 44
የሰለዋት አንቀጽ .......................................................................... 48
የማብላት አንቀጽ ....................................................................... 50
የመሪነት አያህ ............................................................................. 53
የሰቀለይን ሐዲስ (የሁለቱ የከበሩ ነገሮች ሐዲስ) ........................ 54
እንከን-የለሽነት (ዕስማህ)..................................................................... 57
ምልጃ (ሺፋዓ) ........................................................................... 63
ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ኢማሞችን (ዐ.ሰ)
ለኢስቲጋሳ (እርዳታ) መጥራት .................................................. 67
ኢማም መህዲ (ዐ.ሰ)...................................................................... 71
ተቂያ (ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ አቋምን
ደብቆ የመኖር ጥበብ) ................................................................. 74

አላህን ስለ ማየት (ሩእየቱላህ)...................................................... 77
በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት ማውረድ
(ሰለዋት አላ አል-ነቢ) ............................................................................ 82
ሰላት ጋር ተያዥነት ያላቸው ድርጊቶችን በተመለከተ.................................. 84
ውዱእ ሲደረግ እግር ማበስ ...................................................... 84
ሰላትን ማጣመር (ጀምዕ ማድረግ) ............................................. 86
አዛንና ሀያ ዐላ ኸይረል ዐመል (ወደበለጠ/ወደ የተሻለ)
ተግባር ኑ ..................................................................................... 90
በሰላት ውስጥ እጆችን ማጣመር (ተክፊር) ................................. 93
ሰላት ተሰግዶ ሲያልቅ በሦስት ተክቢራ
ማጠናቀቅ (ሰላትን ሦስት ጊዜ 'አላሁ አክበር'
በማለት ማጠናቀቅ) ...................................................................... 93
አፈር ላይ ሱጁድ ማድረግ............................................................... 93
በከርበላ አፈር ላይ ለምን ሱጁድ ይደረጋል? .............................. 99
በሙታን ላይ መስገድ (ሰላት አል-መይት) .................................. 102
የተራዊህ ሰላቶች ......................................................................... 102
የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባዎች ........................................................................... 104
የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች........................................................................... 114
ታሪካዊ እውነታዎች......................................................................................... 117
የሐሙሱ ቀን አሳዛኝ ክስተት ...................................................................... 119
በእሜቴ ፋጢማ አል-ዘሕራ (ዐ.ሰ) ላይ የደረሰው ጭቆናና በደል................. 121

እውን ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው በፊት
የመጀመሪያውን ኸሊፋ ሰላት እንዲመራ አዘውታልን?............................ 124
ጀነት የተመሰከረላቸው አሥሩ ሰሃቦች....................................................... 127
አቡ ሑረይራ.............................................................................................. 128
በሺዓና በሌሎች መዝሐቦች መካከል የሚነሱ
ልዩነቶችና አለመግባባቶች........................................................................ 133
የነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) አባትና የኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) አባት.................... 135
የቅዱስ ቁርአን መበረዝ አሉባልታ............................................................ 137
የፋጢማ ሙስሐፍ..................................................................................... 139
በነቢያትና በኢማሞች አቆራኝቶ ስም ማውጣት......................................... 140
የነቢያትንና የኢማሞችን መካነ መቃብሮች መንባኘት................................ 142
ሰደቀላሁል ዓዚም ወይስ ሰደቀላሁል ዓሊዩል ዓዚም?............................ 145
በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በቤተሰባቸው ላይ በደረሰው
አሳዛኝ ክስተት ማዘንና ማልቀስ................................................................ 146
በአንድ ጊዜ ሦስት ፍቺዎች? ..................................................................... 151
ኩምስ (አንድ አምስተኛ) በኢስላም ............................................................ 152
ጊዜያዊ ጋብቻ (ሙትዓ)............................................................................. 154
ሙተዓተል ሐጅ.......................................................................................... 158

**بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ(١)**
**الْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ(٢) الرَّحْمَٰنِ الرَّحِيمِ(٣) مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ(٤)**
**إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ(٥) اهْدِنَا الصِّرَاطَ الْمُسْتَقِيمَ(٦) صِرَاطَ الَّذِينَ**
**أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ الْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا الضَّالِّينَ(٧)**

«*በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡*
*ምስጋና ለአላህ ነው፤ የዓለማት ጌታ ለኾነው፤ እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ፤ የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው፡፡ አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፡፡ የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያላፈነገጡትን ሰዎች መንገድ ምራን፡፡*»

ይህችን ትንሽ ሥራዬን ለኃያሉ አላህ - ፈጣሪ፣ አምላክ፣ የሰማያትና ምድር ጌታ፣ የሁሉ ነገር አስተናባሪ ለሆነው ሁሉን ቻይ ጌታ ለማገልገል ይሁንልኝ ዘንድ አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም ለተወዳጁ አገልጋዩና መልዕክተኛው ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ለቅዱሳን ቤተ-ዘሩና መልካም ሰሃቦቹ መታሰቢያ እንዲሆንልኝ አቀርባለሁ፡፡

**الَّذِينَ يَسْتَمِعُونَ الْقَوْلَ فَيَتَّبِعُونَ أَحْسَنَهُ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ هَدَاهُمُ اللَّهُ**
**وَأُولَٰئِكَ هُمْ أُولُو الْأَلْبَابِ(١٨)**

«***እነዚያን ንግግርን የሚያዳምጡትንና መልካሙን የሚከተሉትን (አብስር) ፡፡ እነዚያ እነርሱ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ እነዚያም እነርሱ ባለአእምሮዎቹ ናቸው፡፡***»**(39:18)**

## መግቢያ

የሺዓና የሱኒ መዝሐቦች የሙስሊሙ ህዝብ የኢስላምን የተቀደሰ ዓላማ የሚያራምዱበትና የሚተገብሩበት የኢስላማዊው ህዝብ ሁለት ክንፎች ናቸው፡፡ አንድ ታላቅ የሙስሊም ሊቅ እንደተናገረው በሺዓና ሱኒ መካከል መለያየትና መከፋፈል እንዲኖር ለማድረግ የሚሞክሩ ወገኖች ሺዓም ሱኒም አይደሉም፡፡ ይህንን ዓላማ አንግቦ የተጻፈ ይህ መጽሐፍ የሺዓን ፍልስፍናና ተግባራትን በተመለከተ የሚነሱ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለማብራራትና ለመግለጽ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡ የሺዓና ሱኒ መዝሐቦች በዋናነት የሚለያዩት በፊቅህ ነክ ጉዳዮች (በህግጋትና መመሪያዎች) ላይ ሲሆን ከልዩነታቸው ይልቅ በርካታ የሆኑ ተመሳሳይና የጋራ ነገሮች አሏቸው፡፡ ሁሉም የኢስላም መዝሐቦች ህዝቡን ወደ ደህንነት ለመምራት የራሳቸው ድርሻ ስላላቸው ሊከበሩ ይገባል፡፡

ትክክለኛ መረጃ ከማጣት የተነሳ ኢማሚያህ መዝሐብ ለብዙ ሙስሊሞች እንቆቅልሽ ሆኖ ሰንብቷል፡፡ በርካታ ሙስሊሞች የሺዓ ኢስላምን እውነታዎች ከታማኝ ምንጮች ለማወቅ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን የኢስላም ጠላቶች ኢስላምን የማጠልሸትና በሙስሊሙ ህዝብ መካከል ያለውን ሰላም የማደፍረስና የመረበሽ ብቸኛው ስልት መከፋፈልንና ህዝቡን በተለያዩ ቡድኖች መለያየትን ማበረታታት መሆኑን ደርሰውበታል፡፡ በመሆኑም በሺዓ መዝሐብ ታማኝ መጽሐፍት ውስጥ ምንም መሠረት የሌላቸው አፍራሽና ጭፍን አሉባልታዎችን ለማሰራጨት በቅተዋል፡፡ እነዚህ አሉባልታዎች ከሁለት ነገሮች የመነጨ ናቸው፡- የአሉባልታውና የቅጥፈቱ ፈጣሪዎች ለኢስላም ያላቸው ጥላቻና ጠላትነት አንደኛው ሲሆን እነዚህን አሉባልታዎችና ቅጥፈቶች አምነው የሚያሰራጩ ሰዎች ድንቁርናና አላዋቂነት ሌላኛው ነው፡፡

በሌላ አባባል የዚህ ችግር ዋና መንስዔ አሉባልታ ፈጣሪዎች ለኢስላም ያላቸው የጠለቀ ጥላቻና ከነሱ ተቀብለው አሉባልታውን አምነው የሚያሰራጩ ወገኖች የተዘፈቁበት መኃይምነት ናቸው፡፡

ይህ መጽሐፍ ለሙስሊሞች አንድነት ይጣራል፡፡ እውነተኛ አንድነት የሚመጣው ደግሞ ያለንን ፍልስፍናና አስተሳሰብ ሚስጥር አድርገን በመያዝ ሳይሆን በግልጽ መረዳዳት ሲቻል ነው፡፡ ከሺዓ ምሁራን አብዛኛዎቹ እንዲያውም አማካይ ዕውቀት ያላቸውን ግለሰቦች ጨምሮ የሌሎችን መዝሐቦች በርካታ መጽሐፍት በአብያተ መጽሐፍታቸው ውስጥ አካተው ሲጠቀሙ፣ ከሺዓ ታማኝ ምንጮች ስለ ሺዓ ፍልስፍና ለማንበብ ጊዜ የሚወስዱት ሌሎች ሙስሊሞች ግን በጣም ጥቅት ናቸው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሺዓ ኢስላም የሚለይባቸውን እጅግ አነጋጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን ሁሉም ሰው በቀላሉ መረዳት በሚችለው መልኩ፣ በተለይም ደግሞ በምዕራቡ ዓለም የሚገኙ ወጣቶች በቀላሉ በሚረዱት መልኩ ለማቅረብ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ የመዝሐብ ልዩነት ሳይኖር በሁሉም አንባቢ እጅ እንዲደርስ በማሰብ በዋና ምንጭነት የተጠቀምኩት ቁርዓንንና በሐዲስ መጽሐፍት ውስጥ የተዘገቡትን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ነው፡፡ በሁሉም መዝሐቦች የጋራ ተቀባይነት ያላቸውን ኢስላማዊ ምንጮች በመጠቀም የመረጃ አቀራረቤ ትክክለኛና ሳይንሳዊ እንዲሆን ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ የሙስሊሙ ህዝብ ቁርአን ለአንድነት ባደረገው ጥሪ ትኩረት ይሰጡ ዘንድ ሙስሊሞች ያላቸውን ጉጉትና ምኞት እጋራለሁ፡፡

إِنَّ هَٰذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاعْبُدُونِ(٩٢)

*«በእርግጥ ይህች ኡመታችሁ አንዷት ኡመት ናት፤ እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ።» (21:92)*

ሌላው ዓላማ ደግሞ በመላው ዓለም ጠንካራ የሆነ፣ የተቀናጀ፣ እርስ በርስ የተሳሰረና የተባበረ የሙስሊም ማህበረሰብ መፍጠርና መገንባት ነው። ለዚህ ደግሞ ሙስሊሙ ህዝብ ተከብሮ እንዲኖር አንድነት መፍጠርና መስማማት የግድ ይላል። ሙስሊሞች የርስ በርሳቸውን አቋምና መርህዎች መረዳትና መቀበል አለባቸው። በተለያዩ መዝሐቦች መካከል ያሉትን አለመረዳዳቶችና አለመግባባቶች ለመመከት ያለው ብቸኛው መንገድ አልሚ፣ እውነተኛና በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ከስሜታዊነት የራቀ ውይይትና ክርክር ማድረግ ሲቻል ነው። የተከበረው ቁርአን የሦስቱን ሰማያዊ ኃይማኖቶች (አይሁድ፣ ክርስትናና ኢስላም) ተከታዮች የሰለጠነ ውይይት በማድረግ ስምምነት ላይ መድረስ እንዲችሉ

**قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْا إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَاءٍ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا اللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِنْ دُونِ اللَّهِ فَإِنْ تَوَلَّوْا فَقُولُوا اشْهَدُوا بِأَنَّا مُسْلِمُونَ(٦٤)**

«*የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው።*» (3:64) እያለ የሚጣራ ከሆነ በእርግጥ የተለያዩ ኢስላማዊ መዝሐቦችም በቁርአንና በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ትክክለኛ ሐዲሶች ላይ በመመርኮዝ ልዩነቶቻቸውን

በተመለከተ ተቀራርበው የመወያየትና የመነጋገር ግዴታ አለባቸው፡፡ የተለያዩ መዝሐቦች ፊቂህ ነክ ልዩነቶች ሊኖራቸው እንደሚችል የሚካድ ነገር ባይሆንም እነዚህ ልዩነቶች ግን የየመዝሐቡ ተከታዮች እርስ በርሳቸው ከመከባበርና የተለያየ ሐሳቦቻቸውን ከመረዳዳትና ከመቻቻል ሊያግዳቸው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የነዚህ መዝሐቦች መሪዎችና መሥራቾች ዕውቀታቸውን የቀሰሙት ከአንድ ምንጭ ነውና፡፡ ይኸውም ዕውቀቱን የቀሰሙት ከቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሆን በተዘዋዋሪ ደግሞ ከአላህ በመሆኑ ነው፡፡

ኃያሉ አላህ የሰው ልጆችን የፈጠረው ከውስጣዊ መልዕክተኛና ውጫዊ መልዕክተኛ ጋር ነው፡፡ ውስጣዊ መልዕክተኛ ማለትም አዕምሮና ነገሮችን በምክንያታዊነት የማየት ፋኩልቲ እንዲሁም ውጫዊው መልዕክተኛ ማለትም መለኮታዊ መመሪያ (ወህይ)፣ ሁለቱም የሰው ልጅ አዕምሮአዊ ችሎታውን በመጠቀም እውነትን እንዲፈልግና ባህሎችን፣ ልማዶችንና የቤተሰባዊ ባህሪያትን እንደ ቅዱስ እምነት አድርገው እንዳይዙ ጥሪ ያቀርባሉ፡፡ ይህ ጥሪ ሁሉንም የኢስላም ቅርንጫፎች ተከታዮችን የሚመለከት ነው፡፡ ሁሉም ሙስሊሞች ታሪካቸውን ማጥናትና መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡ ግልጽ መነሻ በሌላቸው የቅድመ አያቶቻቸው ልማዶችና ባህሎች ላይ መመርኮዝ የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ቅድመ-አያቶቻቸውን በጭፍን የሚከተሉ ወገኖችን አስመልክቶ የተከበረው ቁርአን በሚከተለው መልኩ ይኮንናልና፡-

**وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا إِلَىٰ مَا أَنْزَلَ اللَّهُ وَإِلَى الرَّسُولِ قَالُوا حَسْبُنَا مَا وَجَدْنَا عَلَيْهِ آبَاءَنَا أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ شَيْئًا وَلَا يَهْتَدُونَ(١٠٤)**

«*ለእነርሱም አላህ ወደ አወረደውና ወደ መልክተኛው ኑ በተባሉ ጊዜ «አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበት ነገር ይበቃናል» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና የማይመሩ ቢኾኑም* » (5:104)

وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ اتَّبِعُوا مَا أَنْزَلَ اللَّهُ قَالُوا بَلْ نَتَّبِعُ مَا أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ آبَاءَنَا أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْئًا وَلَا يَهْتَدُونَ(١٧٠)

«*ለእነርሱም «አላህ ያወረደውን ተከተሉ» በተባሉ ጊዜ «አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን» ይላሉ፡፡ አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ እውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋልን?)*» (2:170)

የዚህ መጽሐፍ አንባቢዎች በሙሉ ገለልተኛ ሆነው፣ አዕምሮአቸውን ከፍተው ለመዝሐብና ለቡድን ከፍፍል ሳያዳሉ ለአንድ ቡድን ብቻ ጭፍን የሆነ ዝንባሌ ሳይኖራቸው ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ እንዲያነቡ እጠይቃለሁ፡፡ ለማንኛውም አስተያየት፣ ትችትና ጥያቄ ምንጊዜም በሬ ክፍት ነው፡፡

እውነትና ሐቅን ለመፈለግ በምናደርገው ትግል ውስጥ አላህ እንዲመራንና ብርኃኑን እንዲለግሰን እማፀናለሁ፡፡ አላህ ለእውነት ልቦናችንና አዕምሮችንን ይከፈትልን፡፡ ሁሉን የሚሰጠው አምላክ ቅኑን እንዲመራንና ምህረቱን እንዲለግሰን የዘወትር ፀሎቴ ነው፡፡

رَبَّنَا لَا تُزِغْ قُلُوبَنَا بَعْدَ إِذْ هَدَيْتَنَا وَهَبْ لَنَا مِنْ لَدُنْكَ رَحْمَةً إِنَّكَ أَنْتَ الْوَهَّابُ(٨)

«*(እነሱም ይላሉ)፦ «ጌታችን ሆይ! ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኋላ ልቦቻችንን አታዘምብልብን፡፡ ከአንተ ዘንድ የኾነን ችሮታም ለኛ ስጠን፡፡ አንተ በጣም ለጋስ ነህና፡፡»*» (3፡8)

በዚች ትንሽ ሙከራዬ የአላህን ምህረት፣ ፀጋና በረከት እከጅላለሁ፡፡ የአላህ ኃይማኖትን በቅንነት በማገልገል ውስጥ ሁላችንም እንዘወትር ዘንድ አንባቢዎች በፀሎቶቻቸው እንዲያስቡን እጠይቃለሁ፡፡

ሰይድ ሙስጠፋ አል-ቀዝዊኒ
አውገስት 13፣ 1999
አሬንጅ ካውንቲ፣ ካሊፎርኒያ

## ሺዓዎች ማን ናቸው?

ኢማም ሙሐመድ አል-ባቂር (ዐ.ሰ) የተሰኙት አምስተኛው የአህለልቤይት ኢማም በአንድ ወቅት ጃቢር የተባለውን ተማሪያቸውን እንዲህ በማለት ተናገሩት፡-

*«ጃቢር ሆይ! አንድ ሰው ለኛ ለአህለል-ቤይት ያለውን ፍቅር በመግለጹ ብቻ የኛ ሺዓ (ተከታይ/ወገን) የሚሆን ይመስለሃል?* በፍጹም! *በአላህ እምላለሁ፣ አንድ ሰው አላህን ከፈራና ከታዘዘ በስተቀር የኛ ተከታይ ሊሆን አይችልም፡፡ ጃቢር ሆይ! የኛ ተከታዮች መገለጫ መተናነስ፣ መታዘዝ፣ ሐቀኝነትና ቅንነት፣ አላህን በብዙ ማወደስ፣ መጾምና መስገድ፣ ለወላጆች መልካም መሆንና በጎ መዋል፣ ለተቸገሩትና ለደሃዎች ትኩረት መስጠት፣ በዕዳ ለተያዙና በአካባቢያችን ለሚኖሩ ወላጅ አልባ ህፃናት (የቲሞች) ማሰብ፣ እውነት መናገር፣ ቁርአን መቅራትን ማዘውተር፣ ለመልካም ንግግር በስተቀር ምላስን መያዝና መቆጣጠር፣ እንዲሁም በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለዘመድ አዝማድ ታማኝና ቅን መሆን... ናቸው፡፡» (አል-ካፊ፣ አል-ኩለይኒ፣ 2፡74)*

«ሺዓ» ማለት ‘ተከታዮች’ ወይም ‘ወገን’ ማለት ሲሆን እንደ ነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ)፣ እና ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) የመሳሰሉ ቀደምት ነቢያት ጋር ተያይዞ በቁርአን ውስጥ በርካታ ቦታዎች ላይ ተጠቅሷል፡፡

وَدَخَلَ الْمَدِينَةَ عَلَىٰ حِينِ غَفْلَةٍ مِنْ أَهْلِهَا فَوَجَدَ فِيهَا رَجُلَيْنِ يَقْتَتِلَانِ هَٰذَا مِنْ شِيعَتِهِ
وَهَٰذَا مِنْ عَدُوِّهِ فَاسْتَغَاثَهُ الَّذِي مِنْ شِيعَتِهِ عَلَى الَّذِي مِنْ عَدُوِّهِ فَوَكَزَهُ مُوسَىٰ
فَقَضَىٰ عَلَيْهِ قَالَ هَٰذَا مِنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ إِنَّهُ عَدُوٌّ مُضِلٌّ مُبِينٌ(١٥)

«***ከተማይቱንም ሰዎቿ በዝንጋቴ ጊዜ ላይ ሆነው ሳሉ ገባ፡፡ በእርሷም ውስጥ የሚጋደሉን ሁለት ሰዎችን አገኘ፡፡ ይህ ከወገኑ (ከሺዓው) ነው፤ ይህም ከጠላቱ ነው፡፡ ያም ከወገኑ (ከሺዓው) የሆነው ሰው በዚያ ከጠላቱ በሆነው ሰው ላይ እርዳታን ጠየቀው፡፡ ሙሳም በጡጫ መታው፡፡ ገደለውም፡፡ ይህ ከሰይጣን ሥራ ነው፡፡ እርሱ ግልጽ አሳሳች ጠላት ነውና አለ፡፡***» (28፡15)

በአሁኑ ወቅት ሺዓ የሚለው ቃል በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በአህለልቤይቱ አስተምህሮ ላይ የተመሠረተ ኢስላማዊ መዝሐብ የሚከተሉ ወገኖችን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡ ይህ መዝሐብም የአህለልቤይት መዝሐብ በመባል ይታወቃል፡፡ መዝሐብ የሚባል ነገር ባልነበረበት በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን፣ ነቢዩ ራሳቸው የተወሰኑ የሰዎች ቡድንን ***የዓሊ ሺዓ*** በማለት ሰይመዋል፡፡

ቅዱሱ ነቢይ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) «የዓሊ ሺዓ» በማለት የተናገሩት ሐዲሶችን በጥቂቱ ለማየት ያህል፡-

- *የዓሊ ምሳሌ እንደዛፍ ነው፡፡ የዛፉ ሥር እኔ ስሆን ዓሊ ደግሞ ቅርንጫፉ ነው፣ ሐሰንና ሁሴን ፍሬዎቹ ሲሆኑ ሺዓዎቹ ደግሞ ቅጠሎቹ ናቸው፡፡ (ሊሳን አል-ሚዛን፣ ኢብን ሐጀር፣ 2፡354)*

- ጃቢር ቢን አብደላህ አል-አንሳሪ እንደተረከው፡-
  በአንድ ወቅት ሰብሰብ ብለን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በነበርን ወቅት ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ ወደኛ መጣ፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡ - «*እውነት እላችኋለሁ፣ ወንድሜ ወደ እናንተ እየመጣ ነው፡*» ከዚያም

እጃቸውን በካዕባ ላይ አስቀመጡና እንዲህ ሲሉ ቀጠሉ፡- «*ነፍሴ በእጁ ውስጥ በሆነችው (አላህ) እምላለሁ፣ ነገ በቂያማ ቀን ስኬት የሚጎናጸፉት ይህ ሰውና ሺዓዎቹ (ተከታዮቹ) ናቸው፡፡*» *(ተውዚህ አል-ደላኢል ፊተስሂህ አል-ፈዳኢል፣ ገጽ 505)*

- በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት ኡሙ ሰለማህ በተወራ ሐዲስ መሠረት ደግሞ፡- «*እሜቴ ፋጢማ ከባለቤታቸው ዓሊ ጋር በመሆን ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመዘየር በመጡ ጊዜ እኔ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ነበርኩ፡፡*» በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸውን ቀና በማድረግ እንዲህ አሉ፡- «*ዓሊ ሆይ! ደስ ይበልህ! አንተና ሺዓዎችህ ጀነት ውስጥ ናችሁ፡፡*» *(ተውዚህ አል-ደላኢል ፊተስሂህ አል-ፈዳኢል፣ ገጽ 507)*

- እንዲሁም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) እንዲህ ብለዋል፡- «*አንተና ሺዓዎችህ የጀነት ናችሁ (ጀነት ውስጥ ናችሁ)፡፡*» *(ታሪክ መዲነቱ ድመሽቅ/ የደማስቆ ከተማ ታሪክ፣ ኢብን አሳከር፣ የኢማም ዓሊ የህይወት ታሪክ በሚለው ክፍል ውስጥ)*

ከነዚህ ሐዲሶች መረዳት እንደሚቻለው ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በህይወት ዘመናቸው ሺዓ የሚለውን ስያሜ ራሳቸው እንደቆረቆሩና እንደተጠቀሙበት በግልጽ መናገር ይቻላል፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላም ለኢማም ዓሊ ታማኝ የነበሩ ወገኖች *የዓሊ ሺዓዎች* በመባል ይታወቁ ነበር፡፡

በሁለተኛው የሂጅራ ምዕተ-ዓመት (ማለትም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከመካ ከተማ ወደ መዲና ከተማ ከተሰደዱ በኋላ ባሉት ሁለት ምዕተ-ዓመታት)

የአባሲያ ኸሊፋዎች አራቱን የሱኒ መዝሐቦች አፊሴላዊ በሆነ መልክ ያበረታቱና ይደግፉ ነበር፡፡ በአንዳንድ መሪዎቻቸው መነሳሳትና ማነቃቃት የተነሳ መዝሐቦቹ ዕውቅና እንዲቸራቸው ተደርጎ ነበር፡፡ ሺዓዎችን በተመለከተ ደግሞ ከኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) መገደል በኋላ የልጁ ሐሰንን (ዐ.ሰ) ኢማምነት በመቀበል በሱ መመራት ጀመሩ፡፡ ከዚያም በወንድሙ በሁሴይን (ዐ.ሰ) እና ከኢማም ሁሴይን ዝርያ ከሆነ ዘጠኝ ተከታታይ ኢማሞችን በመከተል ታወቁ፡፡ ኢማሞቹን ለመከተል የበቁት የቁርአን ማስረጃዎችንና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲሶችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ይኸውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተለያዩ አጋጣሚዎች በተደጋጋሚ በግልጽ እንዳስቀመጡት ከሳቸው በኋላ አሥራ ሁለቱ ኢማሞች እንደሚተኩአቸውና ሁላቸውም ከቁሬይሽ ጎሳ እንደሚሆኑ በተደጋጋሚ የተናገሩትን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ፣ ሰሂህ ሙስሊም፡ 2፡191፣ ሰሂህ ቲርሚዚ፡ 2፡45፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል፡ 5፡106፣ ሱነን አቡ ዳውድ፡ 2፡207 (ገጽ 23 ይመልከቱ)*

ስለዚህ ሺዓነት የተከበረውን ቁርአንን መከተል መሠረት ያደረገና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመረጧቸው ቤተ-ዘራቸው (አህለል-ቤይት) የተላለፉትን የቅዱሱ ነቢይን (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ማስረጃ ባደረገ መልኩ የተገኘ ነው ማለት ነው፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ሺዓዎች የሚከተሉት በመለኮታዊ መገለጥ የተመረጡና የተሾሙ የነቢዩ ተተኪ ኢማሞችን ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ቀጥሎ በሚመጡት ክፍሎች ውስጥ ይዳሰሳል፡፡

## አምስቱ የኢስላም መዝሐቦች

መዝሐቦች የሰው ልጆች ቁርአንንና ቅዱሱ ነቢይን (ሰ.ዐ.ወ) ለመከተል የሚወስዱት ጎዳናዎች ናቸው፡፡ በእርግጥ እነዚህ መዝሐቦች በተለይ የተፈጠሩት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህልፈት በኋላ ሲሆን እስከ በኒ ኡመያ ኸሊፋዎች ዘመን ድረስ ቅርጽ አልያዙም ነበር፡፡ ለምሳሌ አህለ ሱናህ ወል ጀማዓህ የተሰኘው የታወቀ ስያሜ እስከ 3ኛው ሂጅራ ምዕተ ዓመት ድረስ በግልጽ የሚታወቅ አልነበረም፡፡ በዚህ ጊዜ ነው በግልጽ መታወቅ የጀመረው፡፡ በ250 ዓመተ-ሂጅራ አራቱ የሱኒ መዝሐቦች በአባሲያዎች የኸሊፋነት ዘመን በህዝቡ ውስጥ እንዲስፋፉና ዕውቅና እንዲያገኙ ይበረታቱና ድጋፍ ይሰጣቸው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሺዓ መዝሐብ ዕድገቱንና ጥንካሬውን ከኢማም ዓሊ በኋላ ከሱ ዝርያ በሆኑ ሙተዋትር በሆኑ ሐዲሶችና አሳማኝ ማስረጃን መሰረት በማድረግ የተያዙ ኢማሞች አማካይነት ቀጠለ፡፡ ቅዱሱ ነቢይና ተመራጭ ኢማሞቹ ከማንኛውም ኃጢአት፣ ስህተትና መዘናጋት በአላህ የተጠበቁ እንከን-የለሾች ናቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በሁሉም ሙስሊሞች ተቀባይነት ያገኙ አምስቱ የኢስላም መዝሐቦች ጃዕፈሪ 23% ሙስሊሞችን ያቀፈ፣ ሐነፊ 31% ሙስሊሞችን ያቀፈ፣ ማሊኪ 25% ሙስሊሞችን ያቀፈ፣ ሻፊዒ 16% ሙስሊሞችን ያቀፈና ሀንበሊ 4% ሙስሊሞችን ያቀፈ ናቸው፡፡ ሌሎች የተቀሩ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሙስሊሞችን ያቀፉ መዝሐቦች እንደ ዘይዲ እና ኢስማኢሊ ያሉ መዝሐቦች ናቸው፡፡

1. ***ጃዕፈሪ፡-*** የጃዕፈሪ መዝሐብ ይምመራ የነበረው ከ83 ሂጅራ እስከ 148 ሂጅራ በኖሩት በኢማም ጃዕፈር ቢን ሙሐመድ አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ነበር፡፡

የተወለዱትም ሆነ የሞቱት በቅድስቷ ከተማ በመዲና ሲሆን ከአህሉል ቤይት አሥራ ሁለቱ ኢማሞች ስድስተኛው ኢማም ናቸው፡፡ ምንም እንኳ የፊቅህ (ኢስላማዊ ህግጋትና መመሪያዎች) አስተምህሮ የተመሠረተውና ያደገው በነቢዩና በተተኪዎቻቸው (ኢማሞች) ቢሆንም በየጊዜው በነበረው የፖለቲካ ጫናና አህለልቤይቱ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ከነበረባቸው ጭቆናና ግፍ የተነሳ በሺዓ የሚሰጠው የፊቅህ ትምህርት በሚፈለገው ሁኔታና መጠን ሰፊው ህዝብ ጋር መድረስ አልቻለም ነበር፡፡ ለኡመያዎችና አባሲዎች ኸሊፋዎችና መንግስቶቻቸው ህጋዊ ዕውቅና መስጠት አሻፈረን በማለታቸው የአህለልቤይት ኢማሞችና ተከታዮቻቸው በእነዚህ ኸሊፋዎች እጅ ብዙ ጭቆናና እንግልት ደርሶባቸዋል፡፡ የኡመያዎች መንግስት እንደተዳከመ ኢማም ጃዕፈር ቢን መሐመድ አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ወርቃማ አጋጣሚውን በመጠቀም የነቢዩንና የአህለል ቤይቱን ሐዲሶች በመቀመርና በማስተላለፍ ተጠመዱ፡፡ በአንድ ወቅት አራት ሺህ የሚሆኑ ምሁራን፣ ሙፈሲሮች (ቁርአን ተንታኞች)፣ የታሪክ ጸሐፍትና ፈላስፋዎች በቅድስቷ ከተማ በመዲና በሳቸው የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትለዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ትክክለኛ ቁርአናዊ አስተምህሮዎችንና የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አስተምህሮዎችን ጠብቀው ማስተላለፍ ቻሉ፡፡ ይህንንም «አል-ፊቅህ አል-ጃዕፈሪ» በመባል ለመታወቅ የበቃ ህያው የሆነ መረጃ ትተው ለማለፍ በቁ፡፡ አስተምህሮዎቻቸው በ400 ኡሱሎች (መሠረታውያን) የተጠናቀሩ ሲሆኑ በተማሪዎቻቸው የተጻፉና ሀዲስ፣ ኢስላማዊ ፍልስፍና፣ ስነ-መለኮት፣ የቁርአን ተፍሲር (ትርጉም/ትንታኔ)፣ ስነ-ጽሑፍና ሥነ-ምግባር አስተምህሮዎችን ያካተቱ ነበሩ፡፡

ከጊዜ በኋላ ሦስት ታዋቂ ሙሁራን እነዚህን 400 ኡሱል በሺዓ በአራት ኪታቦች ደለደሉ፡፡ እነዚህም አል-ካፊ - በአል-ኩለይኒ (329 ሂጅራ)፣ መን ላ የህዱሩሁ አል-ፈቂህ -በአል-ሱዱቅ (381 ሂጅራ) እና አል-ተህዲብ አል-ኢስቲብሳር - በአል-ጡሲ (460 ሂጅራ) ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስት ምሁራን የሦስቱም የመጀመሪያ ስም ሙሐመድ ስለነበረ «ሦስቱ መሐመዶች» በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ እነዚህ ኪታቦች ለሺዓዎች የሐዲስ ዋና ምንጮች ሆነው ሳለ ጸሃፊዎቹ ግን ኪታቦቻቸውን «ሰሂህ» ብለው ሰይመው አያውቁም፡፡ ትክክለኛ ሐዲሶችን ብቻ ለመሰብሰብ የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደረጉ ቢሆንም አንድ ሐዲስ ከቁርአን ጋር የሚቃረን ሆኖ ከተገኘ ህጋዊና ትክክለኛ ሆኖ ሊወሰድ አይችልም፡፡ በጃዕፈሪ መዝሐብ መሠረት ሐዲሶች ተቀባይነት የሚኖራቸው ቁርአን ሲቀበላቸውና ሲያረጋግጣቸው ብቻ ነው፡፡ ብቸኛው አስተማማኝና እርግጠኛ የሚኮንበት የመመሪያ ምንጭ ቁርአን ብቻ ነውና፡፡

2. ***ሐነፊ፡-*** የሐነፊ መዝሐብ መሪ የነበሩት ኢማም አል-ኑዕማን ኢብን ሳቢት (አቡ ሐኒፋ) የነበሩ ሲሆን ከ80 ሂጅራ እስከ 150 ሂጅራ የኖሩ ናቸው፡፡ ኢማም አቡ ሐኒፋ አረብ ካልሆነ አባት ተወልደው ኩፋ ሀገር አድገው በግዳድ ውስጥ የሞቱ ምሁር ነበሩ፡፡ ይህ መዝሐብ ለመታወቅ የበቃው በአባሲዎች መንግስት ዘመን ሲሆን የኢማም አቡ ሐነፊ ተማሪ የነበረው አቡ ዩሱፍ አል-ቃዲ የፍርድ ቤት ወይም የህግ ክንፍ መሪና ከፍተኛ ዳኛ ሆኖ በተሾመበት ጊዜ ነበር፡፡ በተለይም ደግሞ ይህንን መዝሐብ ያስፋፋው በአል-መህዲ፣ አል-ሓዲ እና አል-ረሺድ የኸሊፋነት ዘመናት ውስጥ ነበር፡፡ ለአባሲዎች ኸሊፋ አል-ረሺድ ከአቡ ዩሱፍ አል-ቃዲ በላይ ቅርብ የሆነ ሰው አልነበረም፡፡ ነገር ግን የአባሲዎች ኸሊፋ የነበረው አል-መንሱርም የኢማም አቡ ሐኒፋን መዝሐብ ለማስፋፋትና ለማደራጀት

የተቻለውን እገዛ ሁሉ በማድረግ ይታወቃል፡፡ የኢማም ጃዕፈር ዝናና ዕውቅና እያደገ በነበረበት በዚሁ ወቅት ይህንን የአቡ ሐኒፋን መዝሐብ ለማስፋፋት የማይፈነቀል ድንጋይ አልነበረም፡፡ ኢማም አቡ ሐኒፋ ለሁለት ዓመታት ያህል ትምህርታቸውን የተከታተሉት በኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ሥር ነበር፡፡ (ሚን አመሊ አል ኢማም አል-ሳዲቅ፤ ከሊሊ፤4፡157) ይህንንም አስመልክቶ አቡ ሐኒፋ እንዲህ ብለው ***ነበር፡፡ «ከጃዕፈር ቢን መሐመድ የተሻለ እውቀት ያለው አንድም ሰው በህይወቴ አይቼ አላውቅም፡፡ በእርግጥም እሱ በዚህ ኡማ (ህዝብ) ውስጥ በዕውቀት እጅግ የተካነ ብቸኛው ሰው ነው፡፡»*** *(ተዘኪረተል ሂፋዝ 1፡166፣ አስና አል-መጣሊብ፡ ገጽ 55)*

3. **ማሊኪ፡-** የማሊኪ መዝሐብ መሪ የነበሩት ከ93 ሂጅራ እስከ 179 ሂጅራ የኖሩት ኢማም ማሊክ ኢብን አነስ አል-አስበሂ ሲሆኑ መዝሀቡ በመላው ሂጃዝ የተስፋፋው ከኢማም አቡ ሐኒፋ ጋር በተጣሉ ጊዜ ነበር፡፡ ይኸውም ኢማም ማሊክ የሐዲስ አስተምህሮ መሪ የነበሩ ሲሆን ኢማም አቡ ሐኒፋ ደግሞ በግል አስተያየት (ረዕይ) ላይ የተመሠረተ አስተምህሮ ያራምዱ ስለነበረ ነው፡፡ አብዛኞቹ የሙስሊም መንግሥታት ኢማም አቡ ሐኒፋን ይደግፉና ያበረታቱ ነበር፡፡ ኢማም ማሊክ የኢማም ዓሊ ዝርያ የነበሩት አለዊያዎችን (አለዊያን) በመቀላቀል ትምህርታቸውን ከኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ቀሰሙ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ህይወታቸው ምስቅልቅል የበዛበት ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ብዙ ጭቆናና እንግልት ይደርስባቸው ነበር፡፡ የዘመኑን መንግሥት ቁጣ በማትረፋቸው በአንድ ወቅት በየጎዳናው እየተጎተቱ ይገረፉ ነበር፡፡

በ148 ሂጅራ ደግሞ ዕድላቸው ተቀይሮ ዝናቸውና የበላይነታቸው ዳግም አንሰራራ፡፡ አባሲዎች ለህዝቡ ፍርድና ውሳኔ (ፈትዋ) ይሰጡ ዘንድ ኢማሙ በህዝቡ ውስጥ ዝናን እንዲያገኙ ለማድረግ ሞከሩ፡፡ የአባሲ ኸሊፋ የነበረው አል-መንሱር የማሊኪ መዝሐብ አስተምህሮዎችን ያቀፈውን ***«ሙወጠዕ»*** የተሰኘውን የፊቅህ መጽሐፍ እንዲጽፉ ጠየቃቸው፡፡ በተጨማሪም በአንድ የሐጅ ወቅት ላይ የመንግሥቱ አፊሴላዊ ቃል አቀባይ ከኢማም ማሊክ ውጭ ማንም ሰው ፈትዋ (ሐይማኖታዊ ፍርድ/ውሳኔዎች) መስጠት እንደማይችል በግልጽ አወጀ፡፡ ሌላው የአባሲ ኸሊፋ ሐሩን አል-ረሺድ ወለል ላይ በመቀመጥ ኢማሙን ያዳምጥ ነበር፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ ኸሊፋዎቹ ለኢማሙ ከፍተኛ ቦታ በመስጠት ከአላህ ቁርአን በኋላ እንደ ኢማሙ ማሊክ ሙወጠዕ ትክክለኛና አስተማማኝ የሆነ መጽሐፍ በምድር ላይ የለም እስከማለት ደረሱ፡፡ ኢብን ሐዝም አል-አንደሉሲ እንዳስቀመጡት ሁለት መዝሐቦች በዘመኑ መንግሥትና ሱልጣኖች የተነሳ ሊስፋፉ ችለዋል፡፡ ይኸውም አንደኛው መዝሐብ ሊስፋፋ የቻለው አቡ ዩሱፍ አል-ቃዲ የዳኝነት ሹመት የሚሰጠው ለሐነፊዎች ብቻ ስለነበረ የአቡ ሐኒፋ መዝሐብ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የኢማም ማሊክ ተማሪ የነበረው ያህያ ኢብን ያህያ በኸሊፋው ቤተ-መንግሥት ውስጥ ትልቅ ዕውቅናና ክብር ስነበረው የኢማም ማሊክ መዝሐብ ነበር፡፡ ያህያን ሳያማክሩና ሳይጠይቁ ማንም ዳኛ በአንደሉስ ውስጥ አይሾምም ነበር፡፡

4. **ሻፊዒ፡-** የሻፊዒ መዝሐብ መሪ የነበሩት ከ150 ሂጅራ እስከ 198 ሂጅራ የኖሩት ኢማም ሙሐመድ ኢብን ኢድሪስ አል-ሻፊዒ ሲሆን የተወለዱት በሂጃዝ ውስጥ ነው፡፡ የኢማም አል-ሻፊዒ መዝሐብ ጎልቶ የወጣው በግብጽ ሀገር ነበር፡፡ በፋጢሚያ ሥርወ-መንግሥት ዘመን ግብጻውያን

በዋናነት የአህለልቤይት ተከታዮች የነበሩ ሲሆን የአህለልቤይቶች አስተምህሮም በአል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲ በሰፊው ይሰጥ ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን ሰላህዲን አል-አዩቢ መጣና በአህለልቤይት ላይ ሰፊ የሆነ ጦርነት አወጀ፡፡ የአህለልቤይት መዝሐብ ትምህርት በአል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲ እንዳይሰጥ በማገድ በ198 ሂጅራ በግብጽ የተገደሉትን የኢማም አል-ሻፊዒን መዝሐብ ጨምሮ ሌሎች መዝሐቦች እንዲያንሰራሩና እንዲጠነክሩ አደረገ፡፡

5. **ሐንበሊ፡-** የሐንበሊ መዝሐብ ይምመራ የነበረው ከ164 ሂጅራ እስከ 241 ሂጅራ በኖሩት በኢማም አህመድ ኢብን ሐንበል ነበር፡፡ የተወለዱትም ሆነ የሞቱት በባግዳድ ነው፡፡ መዝሐባቸው ዕውቅና ያገኘው ግን በአረብ ባህረሰላጤ ክልል ውስጥ በሚገኘው በነጅድ ውስጥ ብቻ ነበር፡፡ ይህም የሆነው የወሓቢያ መሥራች በነበረው በሙሐመድ ኢብን አብደል ወሓብ አስተምህሮዎች ምክንያት ነበር፡፡ የሐንበሊ መዝሐብ በነጅድ ውስጥ መስፋፋት ዋና ምክንያቱ ከ661 ሂጅራ እስከ 728 ሂጅራ በኖሩት በአህመድ ኢብን አብዱልሐሊም አል-ዲመሽቂ ኢብን ተይሚያ አስተምህሮና በተማሪያቸው በኢብን አል-ቀይም አል-ጀውዚያህ አማካይነት ነበር፡፡

የእነዚህን መዝሐቦች ታሪክ በአንክሮ ስናጠናና የተፈጠሩበትን፣ የኖሩበትንና የተስፋፉበትን ምክንያቶች ስናጤን በጊዜው የነበሩ በርካታ መንግሥታት ለመዝሐቦቹ መፈጠርና መስፋፋት ዋነኛ መንስዔ እንደነበሩ እንረዳለን፡፡ መንግሥታዊ ዕርዳታዎችና ድጋፎች በቁሳቁስም ሆነ በገንዘብ የታገዘ እንደነበረ ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ይኸውም፡- ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም፣ የፊቂህ

መጽሐፍት እንዲስፋፉ ማድረግ፣ ኦፊሴላዊ መዝሐቦችን መመስረትና መደገፍ፣ የአንዳንድ «ኦፊሴላዊ» መዝሐቦች መሥራቾችና ምሁራን ነፃነት መስጠትና የመሳሰሉ ተግባራት ለመዝሐቦቹ ዕድገት የተሠሩ ሥራዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድና ስልት በሁሉም የዓለም ኃይማኖቶች ውስጥ የተከሰተ ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ ይህንን በኢስላም ውስጥ የነበረውን አካሄድ በ1534ዓ.ክ በእንግሊዝ ንጉስ ሄንሪ ስምንተኛው አማካይነት ከተፈጠረው ኤንጅሊካል ቸርች ጋር ማወዳደር የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ሄንሪ ስምንተኛው ይህንን ቤተክርስቲያን የግዛቱ ኦፊሴላዊ ኃይማኖታዊ ባህል በማድረግ 55 ሚሊዮን ተከታዮች እንዲኖሩት ለማድረግ በቅቷል፡፡

የአህለልቤይት መዝሐብን ስንመለከት በኡመያዎችና አባሲዎች የተለያዩ ኸሊፋዎች እጅ እጅግ መራር የሆነ ጭቆና፣ እንግልትና መድሎ ይደርስባቸው እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ነገር ግን ጭቆና እንዳለ ሆኖ በአል-መእሙን የኸሊፋነት ዘመን በአላህ ፈቃድ ከፍተኛውን ደረጃ በመጎናጸፍ ሺዓነት እስከ መንግሥት ባለስልጣናት ድረስ ደርሶ መእሙን እራሱ የዓሊ ዝርያ ለነበሩ አለዊዮች የጠለቀ ሐዘኔታ ለማሳየት ተገዶ ነበር፡፡ እንዲያውም ወደ ሺዓነት በማዘንበል የአህለልቤይት ስምንተኛው ኢማም የሆኑት ኢማም ዓሊ ኢብን ሙሳ አል-ሪዳ (ዐ.ሰ) ተተኪው ሆነው እንዲሾሙና የመሪነቱን ቦታ እንዲቀበሉ ጋብዞ ነበር፡፡ ነገር ግን ኢማሙ ሹመቱን አልተቀበሉም ነበር፡፡

## 3. ኢማማህ (ኢማምነት/መሪነት)

በአህለልቤይት መዝሐብና በሌሎች ኢስላማዊ መዝሐቦች መካከል ያለው ዋና ልዩነት በኢማማህ ወይም ነቢዩን ተክቶ የመሪነት ኃላፊነቱ ለማን እንደተሰጠ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ ነው፡፡ የአህለልቤይት መዝሐብ የኢማማህ ሹመት መለኮታዊ ሹመት ነው ብሎ ያምናል፡፡ ይህም ማለት ኢማም ወይም ኸሊፋ ቀጥታ በአላህ የሚመረጥ መሪ ነው ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የመሪነት ወይም ኸሊፋነት አስፋላጊነቱ የነቢይነት አስፈላጊነት ያህል ነው ተብሎ ስለሚታመን በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የሰው ልጆች የተወሰኑ የነቢዩ ተተኪዎችን (ኢማሞችን) እንዲከተሉ አላህ አዞአቸዋል ማለት ነው፡፡

ሌሎች መዝሐቦች ደግሞ ኢማማህ (የመሪነት ሹመት) የሚወሰነው በሹራ (በምርጫ) እንደሆነና የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋ ይህንን አካሄድ በመጠቀም ነው የተወሰነው ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን የሺዓ መዝሐብ የሹራ ጽንሰ ሐሳብ በተሟላ ሁኔታ ተሰርቶበት አያውቅም ብለው ያምናሉ፡፡ ኢብን ቁተይባህ እንደሚያስቀምጡት የመጀመሪያው ኸሊፋ የተመረጡት በዋናነት በሁለት ሰዎች ብቻ እንደነበረ ይጠቅሳሉ፡፡*(አል-ኢማማህ ወ አል-ሲያሳህ፣ ኢብን ቁተይባህ፣ 1፡6)* ኢብን ከሲር እንደሚለው ደግሞ የመጀመሪያው ኸሊፋ የኸሊፋነቱን ቦታ ለሁለት ሰዎች ማለትም ለዑመር ኢብን አል-ኸጣብና ዑበይዳህ ኢብን አል-ጀራህ ብቻ አድርገው ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ሰዎች እጩነቱን መቀበል ትተው እራሳቸውን (የመጀመሪያውን ኸሊፋ) መረጡ፡፡ ከዚያም ምርጫው በሁለተኛ ደረጃ በመዓዝ፣ ዑሰይድ፣ በሺርና ዘይድ ኢብን ሳቢት ድጋፍ አገኘ *(አል-ሲራህ አል-ነበውያህ፣ ኢብን ከሲር 2፡494)*፡፡

ጠበሪ እንደተረከው ደግሞ አንሷሮች በሰቂፋህ (ከነቢዩ በኋላ ኸሊፋ ማን መሆን ስላለበት ውይይት የተደረገበት ቦታ- ሰቂፈተ በኒ ሰዒዳህ/የበኒ ሰዒዳህ ጎጆ) ለመጀመሪያው ኸሊፋ በይዓ የሚያደርጉት (ቃል ኪዳን የሚገቡት) ለዓሊ ብቻ እንደሆነ ያወሳል፡፡ (ታሪክ አል-ጠበሪ፣ 2፡443)

የመጀመሪያው ኸሊፋ በሹመታቸው መመረቅያ ሥነ-ሥርዓት ላይ የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡፡ እንዲህ ነበር ያሉት፡- «*ሰዎች ሆይ! እነሆ በናንተ ላይ ለመሾም በቅቻለሁ፡፡ ሆኖም ግን ከእናንተ የተሻልኩ ሁኜ አይደለም፡፡*» *(ታሪክ አል-ኹለፋእ፣ አስ-ሱዩጢ - ገጽ 69)*

የታሪክ ምሁሩ ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ እንደዘገበው ደግሞ ሁለተኛው ኸሊፋ የአል-ሰቂፋህ ክስተትን በማስተባበርና በማቀናበር የነበራቸውን ሚና ካሙኑ በኋላ ላይ ለመጀመሪያው ኸሊፋ በይዓ ማድረጋቸው (ድምጽ መስጠታቸው) በድንገት ያመለጠ ስህተት (ፈልተህ) እንደነበረና አላህ ግን ጥፋቱ ሊያመጣው ከሚችለው አደጋና መዘዝ ህዝቡን እንደጠበቀ በፀፀት መናገራቸውን አስቀምጧል፡፡ *(ሸርህ ነህጁል በላጋህ፣ ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ 2፡29)*

የሹራ ጽንሰ ሐሳብ በሁለተኛው ኸሊፋ ሹመት ወቅትም ቢሆን በተግባር የታየበት ሁኔታ የለም፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው ኸሊፋ ከመሞታቸው በፊት የሁለተኛውን ኸሊፋ ሹመት አጽድቀው ነው ያለፉት፡፡ የሦስተኛው ኸሊፋ ሹመትም ቢሆን የተከናወነው በሁለተኛው ኸሊፋ የተመረጡና የተመሩ አምስት አባላትን ያቀፈ ሸንጎ አማካይነት ሲሆን በመሠረቱ በአንድ ሰው የተሰጠ ሹመት ነው ማለት ይቻላል፡፡

ይኸውም በሁለተኛው ኸሊፋ የጸደቀ ሹመት ነበር ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም እኚሁ ኸሊፋ ከሳቸው ህልፈት በኋላ ሁለት አስተዳዳሪዎች - በስም ለመጥቀስ ያህል ሰዕድ ኢብን አቢ ወቃስና
አቡ ሙሳ አል-አሽዐሪ በስልጣን ላይ እንዲቆዩ ተናዘው የሞቱበት ሁኔታ ነበር የነበረው፡፡ *(ሸርህ ነህጁል በላጋህ፣ ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ - 9:50)*

## የኢማምነት/ኸሊፋነት ሹመት በመለኮታዊ ውሳኔ (በአላህ ውሳኔ) ስለመሆኑ የሚያወሱ የቁርአን ማስረጃዎች

**وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَائِكَةِ إِنِّي جَاعِلٌ فِي الْأَرْضِ خَلِيفَةً**

- «***ጌታህ ለመላኢካዎቹ እንዲህ ባለ ጊዜ አስታውስ፡ 'እነሆ  በምድር ላይ ኸሊፋህ (ተተኪ) አድርጌ ላስቀምጥ ነው፡፡'***» (2:30)

**يَا دَاوُودُ إِنَّا جَعَلْنَاكَ خَلِيفَةً فِي الْأَرْضِ فَاحْكُمْ بَيْنَ النَّاسِ بِالْحَقِّ وَلَا تَتَّبِعِ الْهَوَىٰ فَيُضِلَّكَ عَنْ سَبِيلِ اللَّهِ إِنَّ الَّذِينَ يَضِلُّونَ عَنْ سَبِيلِ اللَّهِ**

- «***ዳውድ ሆይ! እኛ በምድር ላይ ኸሊፋ አድርገንሃልና በሰዎች መካከል በእውነት ፍረድ፡፡ ዝንባሌህንም አትከተል፤ ከአላህ መንገድ ያሳስትሃልና ፡፡***» (38:26)

**وَإِذِ ابْتَلَىٰ إِبْرَاهِيمَ رَبُّهُ بِكَلِمَاتٍ فَأَتَمَّهُنَّ قَالَ إِنِّي جَاعِلُكَ لِلنَّاسِ إِمَامًا قَالَ وَمِنْ ذُرِّيَّتِي قَالَ لَا يَنَالُ عَهْدِي الظَّالِمِينَ(١٢٤)**

- «*ኢብራሂምንም ጌታው በቃላት በፈተነውና በፈጸማቸው ጊዜ (አስታውስ)፤ «እኔ ለሰዎች ኢማም ላደርግህ ነው » አለው፡፡ ኢብራሂምም «ከዘሮቼስ?» አለ፡፡ ቃል ኪዳኔ በዳዮቹን አያገኝም አለው፡፡*» (2፡124)

وَجَعَلْنَا مِنْهُمْ أَئِمَّةً يَهْدُونَ بِأَمْرِنَا لَمَّا صَبَرُوا وَكَانُوا بِآيَاتِنَا يُوقِنُونَ(٢٤)

- «*በታገሱና በተዓምራቶቻችን የሚያረጋግጡ በሆኑም ጊዜ ከእነርሱ በትዕዛዛችን የሚመሩ ኢማሞችን አደረግን፡፡*» (32፡24)

እነዚህ የቁርአን አያዎች በግልጽ እንደሚያስቀምጡት የመሪነትን ወይም የኢማማህን ስልጣን አላህ ፈትኗቸው መስፈርቱን ያሟሉ ሰዎች ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ስልጣኑን ሊቆናጠጥ እንደማይችል ነው፡፡ የተከበረው ቁርአን በተለይም ደግሞ በ2፡124 ላይ እኩይ ተግባርና በደል ፈጻሚዎች (ዛሊሚን) ሙስሊሙን ህዝብ የመምራት ስልጣን ከመቆናጠጥ ፍጹም የታገዱና የተከለከሉ እንደሆነ አስረግጦ ያስቀምጣል፡፡ ነገር ግን የኢስላም ታሪክ ይህንን ትዕዛዝና መመሪያ ስለመተግበሩ ያሳየው ምስክርነት አለ ወይ? በኡመያዎችና አባሲዎች የስልጣን ዘመን ስንቱ ኸሊፋዎችና ሱልጣኖች ምግባረ ብልሹና ኢስላምን ያልተገበሩ ነበሩ! እንዲህም ሆነው ግን የሙስሊሙ ኡማህ መሪዎች ነበሩ፡፡

ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ተክቶ የመምራት ስልጣን - ኺላፋህ ወይም ኢማማህ - በቁርአን ውስጥ በተጠቀሰ ቁጥር በብቸኝነት ለአላህ ብቻ የተገነባ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ በአህለልቤይት መዝሐብ መሠረት ኺላፋህ የሚወክለው ጊዜያዊ ኃይልና የፖለቲካ ስልጣን በህዝቡ ላይ ያለው መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከዚህ

የበለጠ ወሳኙ ነገር ይህንንም የማድረግ ስልጣን ያለው መሪነትና ፍርድ አላህ የራሱ መገለጫ አድርጎ ያስቀመጣቸው ጉዳዮችን አስመልክቶ የቁርአን አያዎች በሰባት ክፍሎች ለአላህ ብቻ የተገባ ጉዳይ መሆኑን ያስረዳሉ፡-

1. **የንግስና አያህ**

- « *በል፡– «የንግስና ባለቤት የኾንክ አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግሥናን ትሰጣለህ፡፡ ከምትሻውም ሰው ንግሥናን ትገፍፋለህ፡፡* » (3፡26)
- *በል «በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ፡፡ የሰዎች ሁሉ ንጉሥ በኾነው፡፡ የሰዎች አምላክ በኾነው»፡፡(*114፡ 1–3)
- «*የሰማያትና የምድርም በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፡፡ መመለሻም ወደርሱ ብቻ ነው፡፡*» (5፡18)

2. **የመፍረድ ስልጣን አያህ**

- «*ፍርዱ ለአላህ ብቻ ነው፡፡ እውነትን ይፈርዳል፡፡ እርሱም ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው» በላቸው፡፡*» (6፡57)
- «*ንቁ! ፍርዱ ለእርሱ ብቻ ነው፡፡ እርሱም ከተቆጣጣሪዎች ሁሉ ይበልጥ ፈጣን ነው፡፡*» (6፡62)
- «*ከምንም ነገር ያ በእርሱ የተለያዩበት ፍርዱ ወደ አላህ ነው፡፡* (42፡10)

3. **የማዘዝ ስልጣን አያህ**

- *«ትዕዛዙ(አምሩ) ሁሉም ለአላህ ነው» በላቸው፡፡* » (3፡154)

- «*ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡*» (7፡54)
- *በእውነቱ የነገሩ ሁሉ ውሳኔ የአላህ ነው፡፡* » (13፡31)
- «*አላህና መልክተኛውም ነገርን በፈረዱ ጊዜ ለምእምናንና ለምእምናት ከነገራቸው ለእነርሱ ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም! የአላህንና የመልክተኛውንም ትእዛዝ የጣሰ ሰው ግልጽ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ፡፡*» (33፡36)

4. የመሪነት ስልጣን አያህ

إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ وَيُؤْتُون الزَّكَاةَ وَهُمْ رَاكِعُونَ(٥٥)

- «*መሪያችሁ(ወሊ ችሁ) አላህና መልክተኛው እነዚያም ያመኑት ብቻ ናቸው፡፡ (እነርሱ) እነዚያ ሶላትን በደንቡ የሚሰግዱ እነርሱም ያጎነበሱ ኾነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው፡፡*» (5፡55)

የቁርአን ሙፈሲሮች በሙሉ ያለ ምንም ልዩነት ይህ አያህ የወረደው ኢማም ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) አስመልክቶ እንደሆነ ዘግበዋል፡፡ ይኸውም ዓሊ በሰላት ውስጥ ሆኖ ሩኩዕ ላይ እያለ ቀለበቱን ለአንድ ለማኝ የሰጠበትን ክስተት በማስመልከት የወረደ መሆኑን ሙፈሲሮች በአንድነት የተስማሙበት ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡

- «*የምእምናን ቃል የነበረው ወደ አላህና ወደ መልክተኛው በመካከላቸው ሊፈርድ በተጠሩ ጊዜ ሰማን፤ ታዘዝንም ማለት ብቻ ነው። እነዚህም እነሱ የፈለጉትን የሚያገኙ ናቸው።*» (24:51)
- «*ማንንም መልክተኛ በአላህ ፈቃድ ሊታዘዙት እንጅ አልላክንም።*»(4:64)
- *በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ሙእሚን አይኾኑም)።* (4:65)

**5. የመከተል አያህ**

- «*በላቸው፦ «አላህን የምትወዱ እንደኾናችሁ ተከተሉኝ፤ አላህ ይወዳችኋልና። ኀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና። አላህም መሓሪ አዛኝ ነው።*»» (3:31)
- «*ከጌታችሁ ወደእናንተ የተወረደውን ተከተሉ። ከአላህም ሌላ ረዳቶችን አትከተሉ። ጥቂትን ብቻ ትገሰጻላችሁ።*» (7:3)

**6. የመምረጥ ስልጣን አያህ**

- «*ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል፤ ይመርጣልም። ለእነርሱ (ለሰዎቹ) ምርጫ የላቸውም። አላህ ከማይገባው ሁሉ ጠራ። ከሚያጋሯቸውም ላቀ።*» (28:68)

7. **ፍርድ የመስጠት ስልጣን አያህ**

- «***አላህም በእውነት ይፈርዳል፡፡ እነዚያም ከእርሱ ሌላ የሚግገዟቸው በምንም አይፈርዱም፡፡ አላህ እርሱ ሰሚው ተመልካቹ ነው፡፡***» (40፡20)

እነዚህ የቁርአን ምሳሌዎች ለአላህ ብቻ የተገባ የሆነ የመምራትና የማስተዳደር ባህሪያትን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በተደጋጋሚ የሚገለፀው «አላ ለሁል አምር ወል ሁክም» (እነሆ የማዘዝና የመፍረድ ስልጣን የሱ ነው) የሚለው ሐረግ ይህንኑን ጉዳይ ያመለክታል፡፡ የአላህ የመሪነት ስልጣን ዋነኞቹ መገለጫዎች የጥበቃና የማዘዝ ስልጣን ማለትም ህዝቡን በሁለንተናዊው የህይወት አውታር መምራትና ትዕዛዛትና መመሪያዎችን የማስተላለፍና የማስፈጸም ስልጣን ሲሆን ይህንን ደግሞ ለመረጠው ሰው ያጎናጽፋል፡፡ የኸሊፋው ባህርይ (ነቢዩን ተክቶ ህዝቡን የመምራት ስልጣን ባህርይ) ለኸሊፋው ህዝቡን የመጠበቅ፣ የመምራትና የማዘዝ መብት የሚያጎናጽፍና ህዝቡ ደግሞ ኸሊፋውን የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው የሚያስቀምጥ ነው፡፡ ፍጹም መታዘዝና መገዛት ለአላህ ብቻ እስከሆነ ድረስ ይህንን ስልጣንና ኃይል ለፈቀደው ሰው የማስተላለፍ መብት ያለው ኃያሉ አላህ ብቻ ነው፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي**
**الْأَمْرِ مِنْكُمْ فَإِنْ تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِنْ كُنْتُمْ**
**تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا(٥٩)**

«*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡ መልክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡ በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደ መልክተኛው መልሱት፡፡ ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡*» (4፡59)

ነገር ግን አንድ ሰው በኃይልና በጉልበት የመሪነትን ስልጣን በመቆናጠጥ ኸሊፋ ወይም ኢማም ለመሆን ከበቃ ህጋዊ የሙስሊም መሪ ብሎ መሰየም አግባብነት የለውም፡፡ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) የሚተካ ኸሊፋ ወይም ኢማም በአላህ መመረጥ እንዳለበት አመንክዮ ያስገድዳል፡፡ ለነሱ መታዘዝን ለነቢዩና ለራሱ (አላህ) በመታዘዝ ደረጃ ላይ ስላስቀመጠ ማንም ሰው የነቢዩ ኸሊፋ ሆኖ ሊመረጥ አይችልም፡፡ በኡመያዎችና አባሲዎች ሥርወ-መንግሥት ዘመን አንዳንድ ብልሹ ሰዎች የመሪነትንና የኸሊፋነትን ቦታ እንደያዙ የኢስላም ታሪክ ይነግረናል፡፡ ታዲያ ይህ የመታዘዝ ግዴታነት አያህ እነሱንም ይመለከት ይሆን? አማኝ ሙስሊሞች እነዚህን መሪዎች በጭፍን መከተል አለባቸው ?አላህ ብልሹ መሪና ጨቋኝን እንዲከተሉና እንዲታዘዙ ሙስሊሞችን ያዛልን ? በአንዳንድ የሐዲስ መጽሐፍት ውስጥ እነዚህ መሪዎች ሙስሊሙን እንዲያዙና እንዲገዙ እንዲሁም ሙስሊሞች መታዘዝ እንዳለባቸው የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

ኢማም ቡኻሪ በዘገቡት መሠረት የሚከተለውን ዓይነት ሐዲስ እናገኛለን፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል በማለት ይነግሩናል፡፡ ይኸውም፡-

«*ከኔ በኋላ መሪዎች (ዊላት) ይመጣሉ፡፡ ከነሱ ውስጥም ብልሹዎችና ጥሩዎች ታገኛላችሁ፡፡ እናንተ ሙስሊሞች ሁለቱንም ዓይነት መሪዎች መስማትና መታዘዝ አለባችሁ፡፡*

*የጀመዓውን አንድነት የሚሰብር ማንኛውም ሰው ከኢስላም እንደወጣ ተደርጎ ይቆጠራል»* *(ሰሂህ ቡኻሪ፡- ኪታብ አል-ኢማራህ፣ ሐዲስ ቁጥር 1096፣ ኪታብ አል-ፍተን - ሐዲስ ቁጥር 6530 እና 6531፣ ኪታብ አል-አህካም - ሐዲስ ቁጥር 6610፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ አል-ኢማራህ - ሐዲስ ቁጥር 3438፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - ቅጽ 1፡275፣ 297 እና 310፣ አል-ዳረሚ - ኪታብ አል-መናቅብ፡ ቁጥር 2407)፡፡*

እንዲህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች

**وَلَا تَرْكَنُوا إِلَى الَّذِينَ ظَلَمُوا فَتَمَسَّكُمُ النَّارُ وَمَا لَكُمْ مِنْ دُونِ اللَّهِ مِنْ أَوْلِيَاءَ ثُمَّ لَا تُنْصَرُونَ(١١٣)**

«***ወደ እነዚያም ወደ በደሉት አትጠጉ፡፡ እሳት ትነካችኋለችና፡፡ ከአላህም ሌላ መሪዎች (ጠባቂዎች) የላችሁም፡፡ ከዚያም አትረድዱም፡፡***» (11፡113) የሚለው የቁርአን አያህ ጋር የሚቃረኑ ናቸው፡፡ ቅዱስ ቁርአንማ አማኞች አንድን ጨቋኝ መሪ ወይም ማንንም በደል ሠሪ መደገፍ እንደሌለባቸውና ወደ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር ማዘንበል እርም እንደሆነ በአጽንኦት ያስቀምጣል፡፡ አንድን ጨቋኝና ፍትሓዊ ያልሆነን አካል የሙስሊሙ ኡማ መሪ ይሆን ዘንድ መንገድ መክፈትና ለእንዲህ ዓይነቱ መሪ ቃል ኪዳን መግባት (በይዓ ማድረግ) አስመልክቶ ምንም ህጋዊ ማስረጃ መቅረብ አይችልም፡፡ ይህንን ማድረግ ቁርአናዊ አስተምህሮን ሙሉ በሙሉ የሚጻረር ነው፡፡

አያህ 4፡59 አማኞች ኡሉል ዓምርን ወይም ህጋዊ መሪዎቻቸውን (እንከን-የለሽ የሆኑት ኢማሞችን) የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው ማዘዝ ብቻ ሳይሆን ማንም ብልሹ የሆነና እኩይ ተግባር ፈጻሚ ሰው ይህንን ቦታ ለመያዝ በአላህ ሊመረጥ ስለማይችል አያው የህጋዊ ኸሊፋዎችን እንከን-የለሽነት (ዕስማህ) የሚያረጋግጥ ነው፡፡

## ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ)

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ያለውን የመሪነት ስልጣን በማስመልከት ቁርአንና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊን (ዐ.ሰ) ኢማምነት በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡

**ገዲርኹም**፡- ይህ ክስተት የተፈጸመው በአሥራ ሁለተኛው የአረብኛ አቆጣጠር ወር በዙልሂጃ 18 ሲሆን በ110 የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች፣ በ84 ተከታይ ትውልዶች (ታቢኢን) እና ከሁሉም መዝሐብ የተውጣጡ 360 የሙስሊም ምሁራን ተዘግቧል፣ ተተርኳል፡፡ ቅዱሱ ነቢይና 114000 ገደማ የሚደርሱ ሰሃቦቻቸው የመሰናበቻውን ሐጅ አድርገው ወደየቤታቸው እየተመለሱ ነበር፡፡ በዛ ዓመት በሐጅ ወቅት አየሩ በጣም ሞቃት ነበር፡፡ ጠራራ ፀሐይ ወላፈኗን በሐጅ አድራጊው ህዝብ ላይ ያለመታከት ታወርዳለች፡፡ እንዲህም ሆኖ ግን ሙስሊሞችን ወደ ተለያዩ ሐገራት የሚለያየውን ገዲር ኹም የተባለ ጩፌያማ ቦታ ሲደርሱ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እኩለ ቀን አካባቢ የሙስሊሙን ጭፍራ ጉዞዋቸውን እንዲገቱ በማድረግ በሥፍራው የደረሱ እንዲቆዩ፣ አለፍ ብለው የሄዱት ደግሞ ወደ ኋላ እንዲመለሱ አደረጉ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ለህዝቡ መነገር ያለበት ከአላህ የሆነ አስቸኳይ መልዕክት እንደሚከተለው ስለደረሳቸው ነው፡-

**يَا أَيُّهَا الرَّسُولُ بَلِّغْ مَا أُنْزِلَ إِلَيْكَ مِنْ رَبِّكَ وَإِنْ لَمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُ وَاللَّهُ يَعْصِمُكَ مِنَ النَّاسِ**

«***አንተ መልክተኛ ሆይ! ከጌታህ ወዳንተ የተወረደውን አድርስ፡፡ ይህን ባታደርግ ግን መልዕክቱን በሙሉ አላደረስከም፡፡ አላህም ከሰዎች ሴራ ይጠብቅሃል፡፡ አላህ ከሓዲዎችን ሕዝቦች አያቀናምና፡፡***» (5፡67)

*(ለበለጠ ማብራሪያ የሚከተሉትን ሙፈሲሮች ይመልከቱ፡- ጠባሪ፣ ዋሂዲ፣ ሰዕለቢ፣ ቁርጡቢ፣ አል-ራዚ፣ ኢብን ከሲር፣ ነይሳቡሪ፣ ሱዩጢና አሉሲ አልብግዳዲ፡፡)*
*ከታሪክ ምሁራን ደግሞ፡- በላዘሪ፣ ኢብን ቁጠይባህ፣ ጠበሪ፣ አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ፣ ኢብን አብድልበር፣ ሸህርስታኒ፣ ኢብን አሳኪር፣ ኢብነል አሲር፣ ኢብን አቢል ሐዲድ፣ ያዕቁት አል-ሐመዊ፣ ኢብን ኸሊቃን፣ ያፊዕ፣ ኢብን ከሲር፣ ኢብን ኹልዱን፣ አል-ዘሐቢ፣ ኢብን ሐጀር አል-አስቀላኒ፣ ኢብን አል-ሰባግ አል-ማሊኪ፣ አል-መቅሪዚ እንዲሁም አል-ጀላለዲን አል-ሱዩጢ፡፡)*

*ከሐዲስ ዘጋቢ ምሁራን ደግሞ፡- አል-ሻፊዒ፣ አህመድ ኢብን ሐንበል፣ ኢብን ማጃህ፣ ቲርሚዚ፣ ኒሳኢ፣ አል-በገዊ፣ አል-ዱለቢ፣ አል-ጠሓዊ፣ አቡ የዕላ አል-ሙሰሊ፣ አል-ሐኪም አል-ነይሳቡሪ፣ ኸጢብ አል-ኽዋሪዝሚ፣ ሙሂብ አል-ዲን አል-ጠባሪ፣ አል-ዘሐቢ እንዲሁም አል-ሙተቂ አል-ህንዲ፡፡*)

በህዝቡ ላይ አጠቃላይ የሆነ ስልጣንና መብት እንዳላቸው የህዝቡን ምስክርነት ከመጠየቃቸው በፊት ጥቂት የመግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላ ይህንን ጥያቄ በአጽንኦት ጠየቁ፡፡ ህዝቡም በአንድነት፡- «*አዎ! የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በእርግጥም እርስዎ መሪያችን (መውላችን) ነዎት*» ብለው መለሱ፡፡ ይህንን ጥያቄ ሦስት ጊዜ መላልሰው ጠየቁ፡፡ ህዝቡም በተመሳሳይ መልኩ ደጋግመው ለመሪነታቸው ምስክርነታቸውን በአንድ ድምጽ ሰጡ፡፡ ከዚህ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊን ጠርተው የሁለቱ እጆች በሰዎች በፊት ከፍ ብሎ በሚታይ ሁኔታ የዓሊን እጅ ይዘው ከፍ በማድረግ ለህዝቡ እንዲህ አሉ፡- «*እነሆ እኔ መሪው (መውላው) ለሆንኩት ሰው ሁሉ ዓሊም መሪው (መውላው) ነው፡፡*»
በዚህ ጊዜ ዓሊ 33 ዓመታቸው ነበር፡፡ ህዝቡ ይህንን ዜና የተቀበለው በተለያየ ስሜት ነበር፡፡ ከፊሉ በደስታ፣ ከፊሉ ደግሞ በጥላቻ ነበር፡፡ ለዓሊ የእንኳን ደስ ያለህ ብስራት ለመግለጽ ቀዳሚውን ተራ የወሰዱት በኋላ ላይ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን የኸሊፋነት ቦታ ለመያዝ የበቁት ሁለቱ ሰዎች ነበሩ፡፡

ሁለተኛው ኸሊፋ ለዓሊ ደስታቸውን ሲገልጹ እንዲህ ነበር ያሉት፡- «*እሰይ! እሰይ! እንኳን ደስ ያለህ ዓሊ ሆይ! እነሆ የኔ መሪ (መውላ) እንዲሁም የመላው አማኞች (ሙእሚኒን) መሪ (መውላ) ለመሆን በቃህ፡፡*»

(*ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 4፡281፣ ሲረል ዓለሚን - አል-ገዛሊ - ገጽ 12፣ አል-ሪያድ አል-ነዲራህ፣ አል-ጠበሪ እንዲሁም ሌሎች...*)

ከዚያ በኋላ ለቅዱሱ ነቢይ ሌላ የቁርአን አያህ ወረደ፡-

**الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا**

« ***እነሆ ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡*** » (5፡3)

በዚህ የቁርአን አያህ መሠረት በዓሊ ኢማም ወይም ኸሊፋ ሆኖ መመረጥ የኢስላም ኃይማኖት ፍጹምና ምሉዕ ሆኖ ተጠናቀቀ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ዓሊ ኸሊፋ ሆኖ ባይመረጥ ኖሮ የኢስላም ኃይማኖት ጎደሎ ሆኖ ይቀር ነበር ማለት ነው፡፡

**የማስጠንቀቂያው ቀን አያህ፡-** የኢስላም ጎህ ከቀደደ ከሦስት ዓመታት በኋላ አላህ በነቢዩ ላይ የቁርአን አያህ በማውረድ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመካ ውስጥ ያሉትን የቅርብ ዘመዶቻቸውን ወደ ኢስላም እንዲጣሩ አዘዛቸው፡፡ እንዲህ አላቸው፡-

وَأَنْذِرْ عَشِيرَتَكَ الْأَقْرَبِينَ

«***የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ፡፡***» (26፡214)

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጎሳቸው ከበኒ ሓሺም የሆኑ 40 የሚሆኑ ሰዎችን በአጎታቸው አቡ ጧሊብ ቤት ውስጥ በመሰብሰብ ምግብ አሰናድተው ግብዣ አደረጉ፡፡ ተጋባዦቹ ምግብ በልተው ከጨራረሱ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሏቸው፡- «የአብደል ሙጠሊብ ልጆች ሆይ! በአላህ እምላለሁ - እኔ ካመጣሁላችሁ ነገር የተሻለ ነገር ለህዝቡ ያመጣ ከአረብ የሆነ አንድንም ወጣት አላውቅም፡፡ ለዚህ ዓለምም ሆነ ለወዲያኛው ዓለም እጅግ ምርጥ የሆነ ነገር አምጥቼላችኋለው፡፡ አላህም ወደዚህ ነገር እንድጋብዛችሁ አዞኛል፡፡ ታዲያ ማን ነው በዚህ ታላቅ ተግባር ላይ ረዳቴና ደጋፊ ሊሆነኝ የሚችል ሰው? ማነው ወንድሜ፣ ተተኪዬ (ኸሊፋዬ) እና ወራሼ የሚሆነኝ?» ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) ሲቀር ሁሉም መልስ ከመስጠት ታቀቡ፡፡ ዓሊ ግን «እኔ በዚህ ተግባር ላይ ረዳትዎ እሆናለሁ፡፡» ብሎ መለሰላቸው፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊ ቁጭ እንዲል አዘዙትና ጥያቄውን ለሁለተኛ ጊዜ ደገሙት፡፡ አሁንም ዓሊ ተነሳ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደገና እንዲቀመጥ ነገሩት፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ ጠይቀው ከሌሎች ሰዎች መልስ ባጡ ጊዜ ዓሊ አሁንም ተነስተው ድጋፋቸውን ደግመው ተናገሩ፡፡ ከዚያ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጃቸውን ትከሻው ላይ አድርገው የቅርብ ዘመዶቻቸው ለሆኑ ለአርባዎቹ ሰዎች እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-

*«ይህ ወንድሜ፣ ወራሼና በናንተ ላይ ኸሊፋዬ (ተተኪዬ) ነው፡፡ ስለዚህ እነሆ እሱ የሚላችሁን ስሙ፣ ታዘዙትም፡፡» ከዚያም ሰዎቹ ከተቀመጡበት በመነሳት እየተገረሙና እየተሳሳቁ ለዓሊ አባት እንዲህ አሏቸው፡- «የአጎትህ ልጅ ልጅህ የሚልህን እንድትሰማና እንድትታዘዘው አዞሃል»»* ብለው አፌዙ፡፡ *(ኢህቃቅ አል-ሀቅ 4፡62፣ ታሪክ አል-ጠበሪ 2፡117፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 1፡159፣ ታሪክ አቡል-ፊዳ 1፡116፣ ነዝም ዱረር አል-ሲምተይን - ገጽ 82፣ ኪፋየት አል-ጧሊብ - ገጽ 205፣ ታሪክ መዲነት ዲመሽቅ 1፡87፡ ሐዲስ ቁጥር 139 እና 143፣ ሸዋሂድ አል-ተንዚል - አል-ሐሰካኒ 1፡420፣ ጀሚዐል በያን - ሙሐመድ ኢብን ጀሪር አል-ጠበሪ 19፡131፣ አል-ዱረል መንሱር -*

*ጀላሉዲን አል-ሱዩጢ 5፡97፣ ተፍሲር ኢብን ከሲር 3፡350፣ ተፍሲር አል-ካዚን - አል-በግዳዲ 3፡371፣ ሩህ አል-መዓኒ - አል-አሉሲ አል-በግዳዲ 19፡122፣ ተፍሲር አል-ጀዋሒር - አል-ጠንጣዊ 13፡103፣ አል-ሙስተድረክ አላ አል-ሰሂሄይን - አል-ሓኪም አል-ኒይሳቡሪ 3፡135። ሌሎች እንደ ሲራህ አል-ሐለቢ ያሉ የታሪክ መዛግብት ምንጮች ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እላይ በተጠቀሰው በተጨማሪ፡ «**እነሆ እሱ የኔ ሚኒስትር (ወዚር) እና ወራሼ ይሆናል**» በማለት እንደተናገሩ ይጠቅሳሉ።)*

## *የሩኩዕ አያህ (ሩኩዕ ውስጥ በመሆን ምጽዋት መስጠትን አስመልክቶ የወረደ የቁርአን አያህ)*

«***ረዳታችሁ አላህና መልክተኛው እነዚያም ያመኑት ብቻ ናቸው። (እነርሱ) እነዚያ ሶላትን በደንቡ የሚሰግዱ እነርሱም ያጎነበሱ ኾነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው።***» (5፡55)

ከሁሉም መዝሐቦች የተውጣጡ በርካት ሙፈሲሮች ይህ የቁርአን አያህ የወረደው ዓሊ ኢብን አቢ አጧሊብ (ዐ.ሰ) መሆኑን በአንድነት ዘግበዋል። ታዋቂው የቁርአን መፈስር ዘመክሽሪ ይህንን አያህ በተመለከተ ሲናገሩ፡- «*ይህ አያህ የወረደው ዓሊን በማስመልከት ነው። ዓሊ ሰላት ውስጥ በሩኩዕ ላይ እያለ አንድ ለማኝ ምጽዋት በጠየቀው ጊዜ በዛ ሁኔታ ውስጥ እያለ ቀለበቱን አውጥቶ ሰጠው። በትንሽዋ ጣቱ ላይ በላላ መልኩ የተጠለቀ ቀለበት ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ቀለበቱን አውጥቶ ለመስጠት ሳይቸገር በቀላሉ የወጣ ስለሆነ። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ሰላቱ ሊበላሽ በቻለ ነበር። አያው የወረደው በብዙ ቁጥር አመልካች ሆኖ ሳለ እንዴት ዓሊን (ረ.ዐ) በተመለከተ ይሆናል ብለህ ብትጠይቅ፣ ሰዋሰዋዊ አቀራረቡ በብዙ ቁጥር አመልካች ቢሆንም ድርጊቱ የተፈጸመው በአንድ ሰው ነው እላለሁ። ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሎች ሰዎችም ይህንን አርአያ በመከተል ተመሳሳይ ሽልማት ማግኘት*

*እንዲችሉ ለማበረታታት አማኞች በሙሉ ለእንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ ትኩረት በመስጠት ደኅንና የተቸገሩትን በተመለከተ ጥልቅ አሳቢና ርህሩህ መሆን እንዳለባቸው ለማሳሰብ ጭምር ነው፡፡ እንዲሁም ጉዳዩ ፋታ የማይሰጥና ለሌላ ጊዜ መተላለፍ የማይችል ደረጃ ላይ ካለ ሶላት እስኪያልቅ ድረስ እንኳ - መዘግየት ላይኖርበት እንደማይችል ለማስተማርም ነው፡፡»* *(ተፍሲር አል-ከሻፍ - ዘመክሽሪ፡- የአምስተኛው ሱራህ፣ አያህ 55 ተፍሲር)*

በተጨማሪም **አስባብ አል-ኑዙል** የተሰኘው የቁርአን ተፍሲር የከልቢን ዘገባ በመጥቀስ ይህ አያህ የወረደበት ምክንያት ዓሊን (ዐ.ሰ) በተመለከተ እንደሆነ ያስቀምጣል፡- «*የዚህ አያህ የመጨረሻው ክፍል የወረደበት ምክንያት ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብን አስመልክቶ ነው፡፡ ምክንያቱም ሶላት ውስጥ ሆኖ በሩኩዕ ላይ እያለ ቀለበት ለአንድ ለማኝ በመስጠቱ ነው*» *(አስባብ አል-ኑዙል - ዋሂዲ፡- የ5ኛው ሱራህ፣ አያህ 55 ተፍሲር)*

ሌሎች በርካታ ተፍሲሮችም *ሱነን አል-ነሳኢ*፣ የሳዕለቢ *ተፍሲር አል-ከቢር*፣ *ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል*፣ *ሙስነድ ኢብን መርዱወይህ*፣ *ከንዝ አል-ዑማል*ና ሌሎችን ጨምሮ ይህ አያህ ዓሊን (ዐ.ሰ) አስመልክቶ እንደወረደ ጠቅሰዋል፡፡ *(ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 5፡38፣ ከንዝ አል-ዑማል - ሐዲስ ቁጥር 5991)*

- **የመሪነት ስልጣን የተሰጡትን የመታዘዝ አያህ**

ቅዱስ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በገለጹት መሠረት ይህ የቁርአን አያም የዓሊን (ዐ.ሰ) ኢማምነትና መሪነት ከሚያበስሩ የቁርአን አንቀጾች አንደኛው እንደሆነና ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ያለው የኸሊፋነት ስልጣን ለዓሊ (ዐ.ሰ) የተሰጠ መሆኑን በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

ይህ አያህ አማኞች በሙሉ ለአላህ፣ ለነቢዩና በህዝቡ ላይ የመሪነት ስልጣን የተሰጣቸውን *(ኡሉል አምር)* መታዘዝ ግዴታ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህ የቁርአን አያህ በወረደ ጊዜ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላላቅ ሰሃባዎች አንዱ የነበረው ጃቢር ኢብን አብደላህ አል-አንሳሪ እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

«*የአላህ ነቢይ ሆይ! አላህና መልዕክተኛውን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን እነዚህ እነሱን መታዘዝ አላህና መልዕክተኛውን ከመታዘዝ ጋር እኩል አድርጎ አላህ ያስቀመጣቸው «ከናንተ የሆኑ ስልጣን የተሰጣቸው» (ኡሉል አምር) የተባሉት ምንድን ናቸው?*»

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመልሱ፡-

«*እነዚህ የኔ ተተኪዎችና (ኸሊፋዎች) ከኔ በኋላ የሙስሊሙ መሪ የሚሆኑ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ፣ ከዚያም ሐሰንና ሁሴይን፣ ከዚያ ደግሞ ባቂር በመባል የሚታወቅ ሙሐመድ ኢብን ዓሊ፣ ጃቢር ሆይ! እሱን ታየዋለህ፡፡ ስታገኘው ሰላም በልልኝ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ አል-ሳዲቅ ጃዕፈር ኢብን ሙሐመድ፣ ቀጥሎ ሙሳ ኢብን ጃዕፈር፣ ከዚያ ዓሊ ኢብን ሙሳ፣ ቀጥሎ ሙሐመድ ኢብን ዓሊ፣ ከዚያ ዓሊ ኢብን ሙሐመድ፣ ቀጥሎ ሐሰን ኢብን ዓሊ፣ ቀጥሎ ደግሞ የኔ ሞክሼ የሆነው ሙሐመድ ሲሆን እሱ በምድር ላይ የአላህ ማስረጃ (ሁጃህ) ይሆናል*» በማለት መለሱለት፡፡

## *የዓሊ ኸሊፋነትን አስመልክቶ ከቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የተያዙ ሐዲሶች*

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከሳቸው በኋላ ኸሊፋዎች ሆነው የሙስሊሙን ህዝብ የመምራት ስልጣን የተጎናጸፉትን የአህሉልበይት አባል ጨምሮ (በሚቀጥለው ክፍል በሰፊው ይቀርባል) ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ኸሊፋና ኢማም የሚሆነውን ዓሊን አስመልክቶ በሙስሊሙ በርካታ መረጃዎችን ሰጥተዋል፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

- ለዓሊ እንዲህ ባሉበት ወቅት፡ **«አንተ ከኔ አንፃር ያለህ ቦታ ከኔ በኋላ ነቢይ ያለመኖሩ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ሐሩን ከሙሳ አንጻር ያለው ቦታ ዓይነት ነው፡፡»** *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አል-መናቅብ፣ ሐዲስ ቁጥር 3430፣ መጋዚ ሐዲስ ቁጥር 4064፣ ሰሂህ ሙስሊም፡- ኪታብ ፈዳኢል አል-ሰሓባህ - ሐዲስ ቁጥር 4418፣ አል-ቲርሚዚ - ኪታብ አል-መናቅብ፡ ሐዲስ ቁጥር 3664፣ ኢብን ማጀህ - Book on the Introduction: 112 እና 118፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 1፡173፣ 175፣ 177፣ 179፣ 182፣ 184፣ 185)*
- **«እኔ የኖርኩ ትን ህይወት መኖር የፈለገ፣ እኔ የምሞተውን ሞት መሞት የፈለገና አላህ ቃል የገባልኝን የዘለዓለማዊ ፍጹም ደስታ መጎናጸፊያ ጀነት መግባት የፈለገ ሰው ዓሊን መሪው (ዋሊ) አድርጎ ይቀበል፡፡ ምክንያቱም ዓሊ ከሐቁ ጎዳና በፍጹም አያርቃችሁም፣ ወደ ስህተትም በፍጹም አይወስዳችሁም፡፡»** *(አል-ሙስተድረክ አል-ሐኪም - 3፡128፣ ከንዝ አል-ዑማል፡- አል-መተቂ አል-ህንዲ፡ 6፡155)*
- **«ዓሊ ከኔ በኋላ በእያንዳንዱ አማኝ (ሙእሚን) ላይ የመሪነት ስልጣን የተሰጠው (ዋሊ) ነው፡፡»** *(ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል፣ 5፣25 ሰሂህ ቲርሚዚ - 5፡296)*
- **«ዓሊ የዕውቀቴ መግቢያ በር ነው፡፡ ከኔ በኋላ ወደኔ የተወረደውን ለተከታዮቼ ግልጽ የሚያደርግና የሚያብራራ እሱ ነው፡፡ ዓሊን መውደድ ከኢማን ነው፤ እሱን መጥላት ደግሞ ሙናፊቅነት ነው፡፡»** *(ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ህንዲ - 6፡170)*
- **«እኔ የዕውቀት ከተማ ነኝ፡፡ ዓሊ ደግሞ መግቢያ በሩ ነው፡፡ ወደ ከተማው መግባት የፈለገ ሰው በበሩ መግባት ይኖርበታል፡፡»** *(አል-ሙስተድረክ አል-ሐኪም - 3፡226፣ እንዲሁም ኢብን ጀሪር፣ ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ህንዲ - 15፡13፣ ታሪክ ኢብን ከሲር - 7፡358)*

- **«ዓሊ ከኔ ነው፤ እኔም ከዓሊ ነኝ፡፡ ከኔና ዓሊ በስተቀር ማንም ጉዳዩን ሊፈጽም አይችልም፡፡»** *(ሱነን ኢብን ማጃህ 1፡44፣ ቲርሚዚ 5፡300)*
- **«እኔን የሚታዘዝ አላህን የሚታዘዝ ነው፤ እኔን የማይታዘዝ አላህን የማይታዘዝ ነው፤ እንደዚሁ ዓሊን የሚታዘዝ እኔን የሚታዘዝ ነው፤ ዓሊን የማይታዘዝ ደግሞ እኔንም የማይተዘዝ ነው፡፡»** *(አል-ሐኪም 3፡221፡፡ እንዲሁም ዘሐቢን ይመልከቱ)፡፡*

በኸይበር ዘመቻ ወቀት ቤተሰባቸውና ኢስላማዊ ግዛቱን ይጠብቅ ዘንድ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ኋላ እንዲቀር የነገሩት ዓሊን ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህን ጊዜ እንዲህ አላቸው፡- ***«የአላህ መልዕክተኛ እየሄዱ እኔ ወደ ኋላ መቅረት አለብኝ?»* ስለዚህ ዓሊ ተነስቶ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሄደ፡፡ በዚህን ጊዜ ነቢዩ እንዲህ አሉ፡- *«ይህንን ባንዲራ አላህና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሚወዱት ሰው እሰጣለሁ፡፡»*** በሌላ ሪዋያህ (ትረካ) ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) *«አላህና ነቢዩን በሚወድ ሰው አማካይነት አላህ ድልን ያጎናጽፈናል»* ማለታቸው ተዘግቧል፡፡ ያም ሆነ ይህ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባንዲራቸውን ለዓሊ (ዐ.ሰ) ሰጡ፣ አላህም በሱ (ዐ.ሰ) እጅ ድል አጎናጸፋቸው፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አል-ጂሃድ ወል መጋዚ፣ ሐዲስ ቁጥር 2724፣ 2753፣ ጂሃድ - ሐዲስ ቁጥር 3888፣ ሰሂህ ሙስሊም - ፊዳኢል - አል-ሰሃባህ - ሐዲስ 4423 እና 4424፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - 5፡333)*

- ***ሁሉም ከቁሬይሽ ጎሳ የሆኑ አሥራ ሁለት ኢማሞች (መሪዎች)*** **የነቢዩ ኸሊፋዎች ሆነው እንደሚነሱ የሚጠቅሱ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተያዙ ሐዲሶች በጥቂቱ**

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ዓሊ (ዐ.ሰ) ተተኪ ኸሊፋቸው እንደሚሆን ከሚጠቅሱ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በርካታ ሐዲሶች በተጨማሪ ከጎሳቸው ማለትም ከቁሬይሽ የሆኑ አሥራ ሁለት ኢማሞች (መሪዎች) እንደሚተኳቸው በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደተናገሩ ተዘግቧል፡፡ ከሐዲሶቹ ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

- ***«የኸሊፋነት ስልጣኑ በምድር ላይ ሁለት ሰዎች ብቻ እንኳ ቢቀሩ ከቁሬይሾች አይወጣም፡፡»*** *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ ፈዳኢል - ሐዲስ 3240፣ ሰሂህ ሙስሊም፣ ኪታብ አል-ኢማራህ - ሐዲስ 3392፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 2፡29፣ 93፣ 128)*
- **«ከአባቴ ጋር ሁኜ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉበት ቦታ እንዳለሁ እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው፡-** «***በመካከላቸው አሥራ ሁለት ኸሊፋዎች እስኪነሱ ድረስ ይህ ኺላፋ አያበቃም፡፡***» ከዚያም ተራኪው እንዲህ አሉ፡- «***ከዚያ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እኔ በደንብ ያልሰማሁት ነገር ተናገሩ፡፡***» ከዚያም አባቴን ጠየቅኩት፡- «***ምን ነበር ያሉት አልኩትን***» እሱም፡- «***ሁላቸውም ከቁሬይሽ ነው የሚሆኑት***» በማለት መለሰልኝ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አል-አህካም፣ ሐዲስ 6682፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ አል-ኢማራህ፣ ሐዲስ 3393፣ አል-ቲርሚዚ (Book on Trials, ሐዲስ 2149፣ አቡ ዳውድ - ኪታብ አል-መህዲ፣ ሐዲስ 3731፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - 5፡ 87፣ 90, 92, 95, 97, 99, 100, 101, 106, 107, 108) ተመሳሳይ ሐዲሶችን ከሌሎች ምንጮች ውስጥም በሰፊው ማግኘት ይቻላል፡፡*

**እነዚህ አሥራ ሁለት ኢማሞች ማን ናቸው? ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡፡**

***«እኔና ዓሊ የዚህ ኡማ አባቶች ነን፡፡ በዚህ መልኩ ያወቀን በኃያሉ አላህ የሚያምን ነው፡፡ ከዓሊ ደግሞ ሁለት የልጅ ልጆቹ ሐሰንና ሁሴይን በጀነት ውስጥ የወጣቶች ሁሉ አለቃ የሆኑ አሉ፡፡ ከሁሴይን የዘር ሐረግ ደግሞ ዘጠኝ አሉ፡፡ ለነሱ መታዘዝ እኔን መታዘዝ ነው፤ እነሱን አለመታዘዝ ደግሞ እኔን አለመታዘዝ ነው፡፡ ከነሱ ዘጠነኛው የነሱ «ቃኢም» (በቋሚነት የተመሠረተ)፣ መህዲ - አስፈጻሚና ወደ ቅን የመምራት ኃይል ከሰማያዊው ጥበብ የተቸረ ነው፡፡»*** *(ኢክማል አል-ዲን)*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለልጃቸው ልጅ ሁሴይን ገና ከልጅነቱ እንዲህ ሲሉ ተሰምተዋል፡- ***«አንተ ሰይድ (አለቃ) እንዲሁም የሰይድ (አለቃ) ልጅ ነህ፡፡ አንተ ኢማምና የኢማም ልጅ፣ የኢማም ወንድም፣ የኢማሞች አባት ነህ፡፡ አንተ የአላህ ሁጃ (ማስረጃ) እና ማረጋገጫ እንዲሁም የአላህ ሁጃህ ልጅ ነህ፡፡ አንተ ከአንተ የዘር ሐረግ የሚገኙ የዘጠኝ የአላህ ሁጃዎች አባት ነህ፡፡ ዘጠነኛው ቃኢማቸው (በቋሚነት የተመሠረተና ጉዳይ አስፈጻሚያቸው) ነው፡፡»*** *(ኢክማል አል-ዲን)*

## አህለልቤይት(0)

የአህለልቤይትን ማንነትና ምንነት ለሙስሊሙ ህዝብ ለማስተዋወቅ ምርጥ የሆነ መንገድ ቁርአን ስለነሱ ያለውን ማስታወስ ነው፡፡ በርካታ የቁርአን አንቀጾች (አያዎች) የአህለልቤይትን ደረጃና በኢስላም ውስጥ ያላቸውን የመጠቀ ቦታ በተለያዩ ቦታዎች ይገልጻሉ፡፡ ቁርአን ስለ አህለልቤይት በሚያወሳበት ወቅት በደም የተገናኙ የተለዩ አንድ ቡድን ብቻ ሳይሆን በዐቂዳና በእምነት ከቅዱሱ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የተቆራኙ ቁርአን ለይቶ ያወጣቸውን የተወሰኑ ሰዎችን ነው፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የደም ትስስር ያላቸውን ሁሉንም አያካትትም፡፡ ሰሃቦቻቸውንም ሆነ ባለቤቶቻቸውን የሚያቅፍ ቡድን አይደለም፡፡ ቀጥለን እንደምናየው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው አህለልቤይት ማን እንደሆኑ በግልጽ ይነግሩናል፡፡

- **የፍጹም መጥራራት አያህ (አያት አል-ጠሓራህ)**

***إِنَّمَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنْكُمُ الرِّجْسَ أَهْلَ الْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِيرًا(٣٣)***

***»የነቢዩ ቤተሰቦች ሆይ! አላህ የሚሻው ከእናንተ ላይ እርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው፡፡«*** (33፡33)

በኢስላም ውስጥ አንቱ የተባሉ ምሁራንና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ዘጋቢዎችና አጠናቃሪዎች በአንድነት በተስማሙበት ግልጽ መረጃዎችና ማስረጃዎች መሠረት አላህ በቁርአኑ ውስጥ አህለልቤይት ብሎ የጠቀሳቸው ሰዎች የቅዱሱ ነቢይ ሴት ልጅ ፋጢማ አል-ዘሕራ (ዐ.ሰ)፣ የአጎታቸው ልጅ ዓሊ ኢብን አቢ

ጧሊብ (ዐ.ሰ) እና ልጆቻቸው ሐሰንና ሁሴይን (ዐ.ሰ) ናቸው፡፡ *(አል-ዱር አል-መንሡር - አል - ሱዩጢ)*

ጠበራኒ ከተከበሩ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች አንዷ ከሆነችው ከኡሙ ሰላማህ በዘገበው መሠረት፡- «አንድ ወቅት ቅዱሱ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጃቸው እሜቴ ፋጢማ ባለቤቷ ዓሊንና ሁለቱ ልጆቿን ሐሰንና ሁሴይን እንድትጠራ ነገሯት፡፡ ሁላቸውም በመጡ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአንድ ትልቅ ካባ ሸፈኗቸውና እጃቸውን እነርሱ ላይ አድርገው፡- «*አላህ ሆይ! እነሆ* ***ኣሊ ሙሐመድ*** *(የነቢዩ ቤተሰብ) እነዚህ ናቸው፡፡ በኢብራሂምና ቤተሰቡ ላይም በረከትና ፀጋህን እንዳወረድክ ሁሉ በኣሊ ሙሐመድ ላይም አዉርድ፡፡ አንተ ልትመሰገን የምትገባና ኃያል ነህና፡*» ኡሙ ሰላማህ በተናገረችው መሠረት ከባውን አንስታ ከነርሱ ጋር ለመቀላቀል ፈልጋ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግን ተቀበሏትና፡ «አንቺ ባለሽበት ጥሩ ነሽ - መልካም ላይ ነሽ» አሏት፡፡ *(መናቂብ አህለልበይት - ቲርሚዚ 2፡308)*

ምንም እንኳ ይህ የቁርአን አያህ መጀመሪያው ላይ የነቢዩን ባለቤቶች የሚመለከት (የሚያናግር) ቢሆንም እንዲሁም ለነቢዩ ባለቤቶች መመሪያና ትዕዛዝ በሚሰጡ ሐረጎች መሐል ላይ ገብቶ ቢመጣም፣ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶችን ከዚህ ውጭ ያደርጋቸዋል፡፡ ቀደም ብሎ የሚመጣወና ቀጥሎ ያለው የነቢዩ ባለቤቶችን የሚመለከተው ጉዳይ ያቀረበው በእንስታይ ተውላጠ ስምና በእንስት ጾታ አመልካች ግሦች ሲሆን አህለል ቤይትን የሚመለከተው ክፍል ግን በተባዕታይ ጾታ አመልካች ወይም በቅይጥ ጾታ አመልካች ሰዋሰው ነው የተገለጸው፡፡ ስለዚህ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶችን የማይመለከት መሆኑ ግልጽ ነው ማለት ነው፡፡ ከሰዋሰዋዊ አጠቃቀሙ ምንም ማስረጃ ባይኖር እንኳ በአንዳንድ የነቢዩ ባለቤቶች መካከል የነበረው ግንኙነት ሲጤን ከዚህ አካላዊ፣

አዕምሮአዊና መንፈሳዊ ንጽህና ከሚያበስረው የቁርአን አንቀጽ ጋር የመጣጣም ብቃት አልነበራቸውም፡፡

በዚህ የቁርአን አያህ ውስጥ አህለልቤይት የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው አምስት ሰዎችን ማለትም ሙሐመድ፣ ዓሊ፣ ፋጢማ፣ ሐሰንና ሁሴይን ስለመሆናቸው አጽንኦት ለመስጠትና ግልጽ ለማድረግ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሱብሂ ሰላት ወደ መስጂድ በሚሄዱበት ወቅት በፋጢማ ቤት አጠገብ ሲያልፉ ቆም ብለው፡- «አህለልቤይት ሆይ! ወደ ሶላት ወደ ሶላት፡፡ አላህ የሚሻው ከናንተ ርክሰትን ሁሉ ሊያስወግድና ፍጹም የሆነ ማጥራትን ሊያጠራችሁ ነው፤ አህለልቤይት ሆይ!» ይሉ እንደነበረ በርካታ ዘጋቢዎች ጠቅሰዋል፡፡ *(ኢብን መርደወይህ፣ አህመድ ኢብን ሐንበል፣ ቲርሚዚ፣ ኢብን ሙንድር፣ ጠበራኒ፡፡ ለተጨማሪ ማብራሪያ የጠባጠባኢን አል-ሚዛን-ተፍሲር ለ 33፡33 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ፡፡)*

ኢማም አነስ ኢብን ማሊክ አክለው ሲናገሩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሱብሂ ሰላት በዛ ሲያልፉ በየቀኑ ለስድስት ወራት እንደዛ እንዳደረጉ ተናግረዋል፡፡ *(ፈዳኢል አህለልቤይት - አል-ሚቅሪዚ ገጽ 21)*

- **የውዴታ አያህ (አያት አል-መወድዳህ)፡**

**قُلْ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا الْمَوَدَّةَ فِي الْقُرْبَىٰ**

***«በእርሱ ላይ ለቅርብ ዘረ-ሰቤ ውዴታን እንጂ ዋጋን አልጠይቃችሁም« በላቸው፡፡*** (42፡23)

በዚህ አያህ ውስጥ «ቁርባሀ» (የቅርብ ዘመድ) የሚለው ቃል የሚያመለክተው አህለልቤይትን ነው *(ሰዋኢቅ - ኢብን ሐጀር ዘ፡160፣ ጠበቃቱል ኩብራ - ኢብን ሰዓድ፣ እንዲሁም ሰሂህ ሙስሊም፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል፣ ተፍሲር አል-ዱር አል-መንሱር)*

ለዚህ አያህ ማብራሪያ ሲሰጡ ፈኽረዲን አል-ራዚ እንዲህ ብለዋል፡- «*ያለ ጥርጥር እንደ እሜቴ ፋጢማ፣ ዓሊ፣ ሐሰንና ሁሴይን ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቀረበ ማንም የለም፡፡ ይህ ከሁሉም የሐዲስ ትረካ ሰንሰለቶች የተረጋገጠ እጅግ ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «ኣል» (ቤተሰብ) እነዚህ ናቸው፡፡*» ስለዚህ «ኣል» ወይም «አህል» የሚያመለክተው የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) የቅርብ ቤተሰብ ሲሆን እነሱም ፋጢማ፣ ዓሊ፣ ሐሰንና ሁሴይን ናቸው፡፡

አንዳንድ ሰዎች ሐሰንና ሁሴይን የኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ልጆች ስለሆኑና በእናታቸው ፋጢማ አል-ዘህራ በኩል የዘር ሐረጋቸውን ቀጥታ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ስለሚቆራኝ ብቻ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጆች መባል አይችሉም እያሉ ይከራከራሉ፡፡ የአባሲ ኸሊፍ የነበረው ሓሩን አል-ረሺድ የአህለል ቤይት ስምንተኛው ኢማም የሆኑት ኢማም ሙሳ ኢብን ጃዕፈር በፋጢማ በኩል የተገኙ የዓሊ ልጅ ሆነው ሳሉ እንዴት ራሳቸውን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር እንደሚያቆራኙ ጠይቆ ነበር፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር እንዴት ይገናኛሉ? ከዚያም ኢማሙ (ዐ.ሰ) ስለነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) የሚያወሳውን የሚከተለውን የቁርአን አያህ ቀሩለት፡፡

«***ለርሱም ኢስሐቅን (የልጅ ልጁን) ያዕቁብንም ሰጠነው፡፡ ሁሉንም መራን፡፡ ኑሕንም በፊት መራን፡፡ ከዘሮቹም ዳውድን፣ ሱለይማንንም፣ አዩብንም፣ ዩሱፍንም፣ ሙሳንም፣ ሃሩንንም (መራን)፡፡ እንደዚሁም በጎ ሰሪዎችን እንመነዳለን፡፡***

*ዘከሪያንም፣ የሕያንም፣ ዒሳንም፣ ኢልያስንም (መራን)፡፡ ሁሉም ከመልካሞቹ ናቸው፡፡*» (6፡84 – 85)

ከዚያም ኢማሙ የዒሳ (ዐ.ሰ) አባት ማን እንደነበረ ኸሊፋውን ጠየቁት፡፡ ኸሊፋውም ዒሳ (ዐ.ሰ) ያለ አባት የተወለዱና አባት የሌላቸው እንደሆኑ መለሰ፡፡ በዚህ ወቅት ኢማሙ እንዲህ በማለት ተናገሩ፡-
»ስለዚህ አየህ አላህ በእናታቸው መርየም በኩል ከነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) ጋር አገናኛቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እኛንም በእናታችን እሜቴ ፋጢማ (ዐ.ሰ) በኩል ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር አቆራኘን፡፡ *(ኢህቲጃጅ - ጠበርሲ፣ 2፡ 335፣ የመነጋገሪያ ነጥብ ቁጥር 271)*

- *የሙባሐላ አያህ (የመፈታተኛ/መረጋገሚያ አያህ)*

**فَمَنْ حَاجَّكَ فِيهِ مِنْ بَعْدِ مَا جَاءَكَ مِنَ الْعِلْمِ فَقُلْ تَعَالَوْا نَدْعُ أَبْنَاءَنَا وَأَبْنَاءَكُمْ وَنِسَاءَنَا وَنِسَاءَكُمْ وَأَنْفُسَنَا وَأَنْفُسَكُمْ ثُمَّ نَبْتَهِلْ فَنَجْعَلْ لَعْنَتَ اللَّهِ عَلَى الْكَاذِبِينَ(٦١)**

**»ዕውቀቱም ከመጣልህ በኋላ በርሱ (በዒሳ) የተከራከሩህን ሰዎች ኑ፤ ልጆቻችንንና ልጆቻችሁን፣ ሴቶቻችንንና ሴቶቻችሁንም፣ ነፍሶቻችንንና ነፍሶቻችሁንም እንጥራ፡፡ ከዚያም አጥብቀን አላህን እንለምን፤ የአላህንም ቁጣ በውሸታሞቹ ላይ እናድርግ« በላቸው፡፡(2:61)**

በኢስላም ታሪክ ውስጥ መሠረታዊ የሆነ ይህ ክስተት በሁሉም የታሪክ ምሁራን፣ የሐዲስ ዘጋቢዎች ተራኪዎችና የቁርአን ሙፈሲሮች በሰፊው

የተዘገበና የተወራ ሲሆን የነቢዩን ቤተሰቦች (አህለልቤይት) ከፍ ያለ ደረጃ በግልጽ የተገለጸበት ክስተት ነው፡፡ ዘጋቢዎች ባስተላለፉበት መሠረት አንድ ወቅት ከነጅራን ሀገር የተውጣጡ የክርስቲያን ልዑካን ስለ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ነቢይነትና ስለመጣው አዲስ ኃይማኖት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ለመነጋገር ወደ መዲና ይመጣሉ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዒሳ (እየሱስ) የሰው ልጅ እንደነበረ፣ ነቢይ እንደሆነና የአላህ ባሪያ (አገልጋይ) እንደሆነ በቁርአን የተገለጸውን ሁሉ በማብራራት ከገለጹላቸው በኋላ የአምላክ ልጅ እንደሆነ አድርጎ ማሰብ በአምላክ ላይ እንደማላገጥና ኃይማኖትን ማንቋሸሽ እንደሆነ እንዲሁም አላህ ከእንዲህ ዓይነቱ ሰዋዊ ባህሪ የጠራና የላቀ እንደሆነ በግልጽ አስረዷቸው፡፡ እነዚህን ነጥቦች ሰፋ ባለ ሁኔታና አሳማኝ በሆነ መልኩ ካነጋገሯቸው በኋላ ልዑካኑ ሆን ብለው ሐቁን ወደ ኋላ በመተው ቀደም ሲል በያዙት አጉል እምነታቸውና ልማዳቸው ለመቀጠል እኝክ ማለቱን እንደመረጡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተረዱ ጊዜ አላህ ይህንን የቁርአን አያህ አወረደ፡፡ ይህ ደግሞ ለክርስቲያኖቹ እጅግ ፈታኝ ነገር የነበረ ነው፡፡ ይኸውም ሐቁን በመተው በሐሰት ላይ እጸናለሁ ባለው ወገን ላይ አላህ ቁጣውን እንዲያወርድ በመጸለይ ሐሰተኛው እንዲታወቅ ለሁለቱም ወገን የተሰጠ የመፈታተኛ መድረክን የሚጋብዝ ነበር፡፡ በአላህ ትዕዛዝ መሠረት በሚቀጥለው ቀን ጧት በጨረቃ ወር 24ኛው ዙልሂጃህ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሴይንን አቅፈው፣ ሐሰንን እጁን ይዘው፣ ፋጢማን ከኋላ አስከትለው፣ ከሷ ኋላ ደግሞ አማቻቸውና የአጎታቸው ልጅ የሆነውን ዓሊ ኢብን አሊ ጧሊብን በማስከተል የኢስላም ባንዲራ ይዘው ቀጠሮው ቦታ ደረሱ፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የቅርብ ዘመዶቻቸውን ይዘው እንደመጡ ክርስቲያኖቹ ባዩ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የምራቸው መሆናቸውን አመኑ፡፡ ጉዳዩ እርግጥ ባይሆን ኖሮ ውድና ቅርብ የቤተሰብ አባሎቻቸውን ይዘው እንደማይመጡ አስረገጡ፡፡

የክርስቲያን ልዑካኑ ከመረጋገሚያው (ሙባሐላ) መድረክ አፈግፍገው በፍራቻ ተውጠው ወደ ሐገራቸው ነጅራን ተመለሱ፡፡

በወቅቱ በነቢዩ ቤተሰብ ውስጥ ሌሎች ሴቶች የነበሩ ቢሆንም፣ ሙፈሲሮች፣ የሐዲስ ምሁራንና የታሪክ ጸሓፍት በሙሉ በተስማሙበት መሠረት በዚህ የቁርአን አያህ ውስጥ «ኒሳአና» (ሴቶቻችን) የሚለው ሐረግ የተጠቀሰው ለፋጢማ አል-ዘሐራ (ዐ.ሰ) ብቻ እንደሆነ፣ «አብናአና» (ልጆቻችን) የሚለው ደግሞ ሐሰንና ሁሴይንን (ዐ.ሰ) ብቻ የሚያቅፍ እንደሆነና «አንፈሱና» (ነፍሳችን/ራሳችን) የተባለው ደግሞ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ብቻ የተሰጠ እንደሆነ ሁሉም የኢስላም ምሁራን በአንድነት የተስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

***ተፍሲር አል-ከሻፍ*** በተባለው ተፍሲራቸው ውስጥ ዘመክሸሪ ይህንን ክስተት በሚከተለው መልኩ ይገልጹታል፡-

ይህ የቁርአን አንቀጽ በወረደ ጊዜ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ክርስቲያኖችን ለመፈታተኛ (መረጋገሚያ) ሥርዓቱ በመጋበዝ ሐሰተኛ በሆነው ወገን ላይ የአላህ እርግማን ይወርድ ዘንድ ፀሎት እንዲደረግ ቀጠሮ እንዲያዝ አደረጉ፡፡ ክርስቲያኖችም በመካከላቸው ውይይት አደረጉ፡፡ በውይይቱ ውስጥም መሪያቸው አብደልመሲሕ የሚከተለውን ሐሳቡን አቀረበ፡- «*እናንተ ክርስቲያኖች ሆይ! ሙሐመድ ከአምላክ የተላከ ነቢይ መሆኑንና የመጨረሻውን መልዕክት ወደናንተ ያመጣ መሆኑን እወቁ፡፡ እውነት እላችኋለሁ ማንም ትውልድ ነቢይን በመረጋገም መድረክ ተጋፍጦ አያውቅም፣ ይህን ካደረገ ግን የመከራ ጽዋ መቅመስ አይቀሬ ካልሆነ በስተቀር፡፡ የእነሱ መጥፋት ብቻ ሳይሆን እርግማኑ ለልጅ ልጆቻቸው የሚደርስ መሆኑን አትዘንጉ፡፡*» ይህን ካለ በኋላ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ያመጡትን እውነታ ተጋፍጦ ከመጥፋት ስምምነት ላይ መድረሱ እንደሚበጅ መከራቸው፡፡ አብደልመሲሕ ወገኖቹ

ተቃውሞቻቸውንና ጥላቻቸውን አስወግደው ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መመሪያዎች እጅ ሰጥተው ኃይማኖታቸውን ጠብቀው መቆየቱ እንደሚሻል አበክሮ መከራቸው፡፡ እንዲህም አላቸው፡- *«በዚሁ ቀጥለን እስከመጨረሻው እንጋፈጣለን የምትሉ ከሆነ ሁላችንም መጥፋታችን ነው፡፡ ነገር ግን እምነታችሁን ማስጠበቅ ከፈለጋችሁና መጋፈጡን እምቢ ብላችሁ ባላችሁበት መቆየት ከፈለጋችሁ ከዚህ ሰው ጋር (ከነቢዩ ጋር) ሠላም ፈጥራችሁ ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ፡፡»* በሚቀጥለው ቀን ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሴይንን አቅፈው፣ ሐሰንን እጁን ይዘው፣ እሜቴ ፋጢማን ከኋላቸው አስከትለውና ከሷ በኋላ ደግሞ ዓሊን አስከትለው በቀጠሮው ቦታ በመገኘት ለቤተሰባቸው (አህለል ቤይታቸው) እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል፡- *«እኔ ወደ አላህ ዱዓእ በማደርግበት ወቅት ከኔ በኋላ ደግማችሁ በሉ፡፡»* የነጅራኑ ጳጳስ  ነቢዩንና ቤተሰቦቹን ባየ ጊዜ ለክርስቲያኖቹ እንዲህ አላቸው፡- *«እናንተ ክርስቲያኖች ሆይ! እያየሁ ያለሁት ፊቶች አላህ ለነሱ ሲል ተራራን እንኳን የሚያንቀሳቅስላቸው ሰዎችን ነው፡፡ ይህንን ካደረጋችሁ ግን ሁላችሁም ትጠፋላችሁ፣ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስም አንድም ክርስቲያን በዚች በምድረ ገጽ ላይ እንደማይቀር እወቁ፡፡»* *(ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል 1፡ 185፣ ተፍሲር-ጠበሪ 3፡192፣ አል-ሙስተድረክ - አል-ሐኪም 3፡150፣ ደላኢል አል-ኑቡወህ - አል-ሐፊዝ አቡ ኑዔይም - ገጽ 297፣ አስባብ አል-ኑዙል - አል-ኔይሳቡሪ ገጽ 74፣ አህካም አል-ቁርአን - አቡበክር ኢብን አል-ዐረቢ 1፡115፣ ተፍሲር አል-ከቢር - አል-ፈኽር አል-ራዚ 8፡85፣ ኡስድ አል-ጋባህ - አል-ጁዝሪ 4፡25፣ ተዝኪራ ሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ ገጽ 17፣ አል-ጀሚዐል ሂከም አል-ቁርአን - ቁርጡቢ 3፡104፣ ተፍሲር ኢብን ከሲር 1፡370፣ አል-ቢዳያህ ወል ኒሃያህ - ኢብን ከሲር 5፡52፣ አል-ኢሳባህ - ኢብን ሐጀር አል-ዐስቀላኒ 2፡503፣ አል-ፉሱል አል-ሙሂምማ - ኢብን አል-ሰባግ አል-ማሊኪ - ገጽ 108፣ አል-ዱረል መንሱር - ጀላለዲን አስ-ሱዩጢ 4፡38፣ ታሪከል ኹለፋእ - ጀላለዲን አስሱዩጢ ገጽ 115፣ አስሰዋሂቀል ሙህሪቃ - ኢብን ሐጀር ገጽ 199 እንዲሁም ሌሎች ታዋቂ ምንጮች፡፡*

በአጠቃላይ ከአራቱም መዝሐቦች የተውጣጡት 47 ሙሐዲሶችና ሙፈሲሮች የነቢዩ የቅርብ ቤተሰቦች (አህሉልቤይት) እሜቴ ፋጢማ፣ ዓሊ፣ ሐሰንና ሁሴይን ብቻ እንደነበሩ ያወሳሉ፡፡

ይህንን ምክር በመስማት ክርስቲያኖቹ ለቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ተናገሩ፡- አቡል ቃሲም ሆይ! ይህንን የመረጋገሚያ ፈተና ላለመቀበል ወስነናል፡፡ አንተም ኃይማኖትህን ይዘህ ቀጥል፣ እኛም የራሳችንን ኃይማኖት ይዘን እንዘልቃለን፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለክርስቲያኖቹ ሲናገሩ፡- *የመፈታተኛ እርግማኑን ሥርዓት አንቀበልም ካላችሁ ለአላህ እጅ ስጡና ሙስሊሞቹ የሚቀበሉትን ትቀበላላችሁ፣ ሙስሊሞቹ የሚሰጡትንም ትሰጣላችሁ ወይም ሙስሊሞቹ የሚያበረክቱትን ታበረክታላችሁ አሏቸው፡፡* የክርስቲያኖቹ ልዑካንም ሙስሊሞችን የመዋጋት ፍላጎት እንደሌሉዋቸው በመግለጽ የሰላም ስምምነት ለማድረግ እንደሚፈልጉ ገለጹ፡፡ የኢስላም ነቢይም (ሰ.ዐ.ወ) ጥያቄውን ተቀበሉ፡፡

- **የሰለዋት አንቀጽ**

**إِنَّ اللَّهَ ومَلَائِكَتَهُ يُصَلُّونَ عَلَى النَّبِيِّ يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا صَلُّوا عَلَيْهِ وَسَلِّمُوا تَسْلِيمًا(٥٦)**

«***አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ ሰለዋት ያወርዳሉ፡፡ እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በእርሱ ላይ ሰለዋት አውርዱ፡፡ የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ፡፡*** » (33፡56)

በአምስቱ የግዴታ ሰላቶች ጊዜ በተሸሑድ ውስጥ ሲጋጆች በሙሉ በነቢዩና በቤተ-ዘሩ (አህለል ቤይቱ) ላይ ሰለዋት ማውረድ ግዴታ መሆኑ ይታወቃል፡፡

«ቤተ-ዘር» ወይም «ኣል» የሚለው ቃል ደግሞ ለእሜቴ ፋጢማ፣ ለዓሊ፣ ለሐሰንና ሁሴይን እንዲሁም ለዝርዮቻቸው የተሰጠ ብቸኛ መታወቂያቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በነቢዩ ቤተ-ዘር ላይ ሰለዋት ማውረድን አስመልክቶ የተቀመጠው አትኩሮት አህለልቤይት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ያላቸውን የተለየ ቦታ ከሚገልጹ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ሙዕሚኖች እንዲያከብሯቸውና ከፍ ያለ ቦታ እንዲሰጧቸው በማዘዝ የሙስሊሙን ኡማ ለመምራት የተመረጡ መሆናቸውን አላህ ሙስሊሞችን ያስታውሳል፣ ያሳስባል፡፡ ዕውቅ ከሆኑ የቁርአን ሙፈሲሮች አንዱ የሆኑት ፈኽረልዲን አል-ራዚ ሙስሊሞቹ እንዴት አድርገው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰላምታና ሰላት ማውረድ እንዳለባቸው አንዳንድ ሰሓባዎች ነቢዩን በጠየቋቸው ጊዜ የተሰጣቸውን መልስ እንደሚከተለው ዘግበዋል፡- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በሉ አሏቸው፡- «*አላህ ሆይ! በሙሐመድና ቤተሰቡ ላይ በረከትህን አውርድ፣ በኢብራሂምና በቤተሰቡ ላይ በረከትህን እንዳወረድክ ሁሉ፡፡ በሙሐመድና በቤተሰቡ ላይ ፀጋህን አብዛ፣ በኢብራሒምና በቤተሰቡ ላይ ፀጋህን እንዳበዛህ ሁሉ፡፡ አንተ ምሥጉንና ለክብርህም ወደር የለሽ ነህና፡፡*» *(ተፍሲር አል-ከቢር 3፡56)*

አል-ራዚ በመቀጠል አስተያየት ሲሰጡ አላህና መላኢኮቹ በነቢዩ ላይ ሰላትና በረከት እንዲወርድ የሚያደርጉ ከሆነ የኛ ሰለዋት ምን ሊፈይዳቸው ነው በማለት ይጠይቃሉ፡፡ ጥያቄውን በራሳቸው ሲመልሱም እኛ በነቢዩ ላይ ሰለዋት የምናወርደው ነቢዩ የኛ ሰለዋት ስለሚያስፈልጋቸው አይደለም፡፡ ቀድሞውኑ የአላህ ሰላትና በረከት ስላላቸው የመላኢኮዎቹም አያስፈልጋቸውም፡፡ በነቢዩ ላይ ሰለዋት የምናወርደው አላህን ለማላቅና ምሥጋናችንን በመግለጽ ምህረቱንና ፀጋውን ለማግኘት እንድንችል ነው፡፡ ይኸውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- «*በኔ ላይ ሰለዋት ያወረደ አላህ በሱ ላይ አሥር እጥፍ ሰለዋት ያወርዳል*» ብለዋል፡፡

ሌላም የቁርአን አንቀጽ ይህንኑን አስተምህሮ ያስረግጣል፡፡ ይኸውም አላህ በቁርአኑ በቅዱሱ ነቢይ ቤተሰብ (ኣል) ላይ ሰላሙን ባወረደ ጊዜ የምናገኘው ሲሆን ይኸውም በ37፡150

سَلَامٌ عَلَىٰ إِلْ يَاسِينَ(١٣٠)

«***በያሲን ቤተሰብ ላይ ሰላም ይሁን***» የሚለው የቁርአን አያህ ይጠቀሳል፡፡ በብዙ ሙፈሲሮች መሠረት ያሲን ከነቢዩ ስሞች አንዱ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይኸውም በሱራ ያሲን ውስጥ እንደተጠቀሰው፡-

**يس(١) وَالْقُرْآنِ الْحَكِيمِ(٢) إِنَّكَ لَمِنَ الْمُرْسَلِينَ(٣)**

«***ያሲን፣ ጥበብ በተሞላው ቁርአን፣ በእርግጥ አንተ ከመልዕክተኞቹ አንዱ ነህ***»

*(አስ-ሰዋእቅ - ኢብን ሐጀር ምዕ. 11)*

- **የማብላት አንቀጽ**

በቁርአን ውስጥ 76ኛው ሱራ የወረደው በአህለልቤይት የተፈጸመውን የተቀደሰ ተግባር ለማወደስ የተገለጠ ነው፡፡ አላህ ይህንን ሱራ ኢንሳን (የሰው ልጅ) ብሎ በመሰየም የሰው ልጆችን አዕምሮ ወደ ሰው ልጅ ድንቅና የተባረከ ተግባር ለመሳብና የሰው ልጆች ከራስ ወዳድነትና ስግብግብነት ጸድተው ለመሰል ፍጡሮቻቸው እንዲያስቡና እንዲያዝኑ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የወረደ ነው፡፡ ይህ የቁርአን አያህ የሚጀምረው፡-

**هَلْ أَتَىٰ عَلَى الْإِنْسَانِ حِينٌ مِنَ الدَّهْرِ لَمْ يَكُنْ شَيْئًا مَذْكُورًا(١) إِنَّا خَلَقْنَا الْإِنْسَانَ مِنْ نُطْفَةٍ أَمْشَاجٍ نَبْتَلِيهِ فَجَعَلْنَاهُ سَمِيعًا بَصِيرًا(٢) إِنَّا هَدَيْنَاهُ السَّبِيلَ إِمَّا شَاكِرًا وَإِمَّا كَفُورًا(٣)**

«*በሰው ላይ የሚታወስ ነገር ሳይኾን ከዘመናት የተወሰነ ጊዜ በእርግጥ አልፎበታል፡፡ እኛ ሰውን የምንሞከረው ስንኾን ቅልቅሎች ከኾኑ የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፡፡ ሰሚ ተመልካችም አደረግነው፡፡ እኛ ወይ አመስጋኝ ወይም ከሓዲ ሲኾን መንገዱን መራነው፤ (ገለጽንለት)፡፡* በማለት ነው፡፡

ይህ መግቢያ ለታላቁ የነቢዩ ቤተሰቦች (አህሉልቤይት) መስዋዕት አዕምሮአችንን ይከፍታል፡፡ ይኸውም ዓሊ፣ ፋጢማ፣ ሐሰንና ሁሴይን እንዲሁም ፊድዳህ የተባለችው ሠራተኛቸው የከፈሉትን ድንቅ መስዋዕት አስመልክቶ የሰው ልጆችን አዕምሮ ለትኩረት ይጠራል ማለት ነው፡፡
ከዚያም ከ 5-13 ባሉት አያዎች ይገልጻቸዋል፡-

**إِنَّ الْأَبْرَارَ يَشْرَبُونَ مِنْ كَأْسٍ كَانَ مِزَاجُهَا كَافُورًا(٥) عَيْنًا يَشْرَبُ بِهَا عِبَادُ اللَّهِ يُفَجِّرُونَهَا تَفْجِيرًا(٦) يُوفُونَ بِالنَّذْرِ وَيَخَافُونَ يَوْمًا كَانَ شَرُّهُ مُسْتَطِيرًا(٧) وَيُطْعِمُونَ الطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا(٨) إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ اللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنْكُمْ جَزَاءً وَلَا شُكُورًا(٩) إِنَّا نَخَافُ مِنْ رَبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا(١٠) فَوَقَاهُمُ اللَّهُ شَرَّ ذَٰلِكَ الْيَوْمِ وَلَقَّاهُمْ نَضْرَةً وَسُرُورًا(١١) وَجَزَاهُمْ بِمَا صَبَرُوا جَنَّةً وَحَرِيرًا(١٢) مُتَّكِئِينَ فِيهَا عَلَى الْأَرَائِكِ لَا يَرَوْنَ فِيهَا شَمْسًا وَلَا زَمْهَرِيرًا(١٣)**

*በጎ አድራጊዎች መበረዣዋ ካፉር ከኾነች ጠጅ ይጠጣሉ፡፡ ከእርሷ የአላህ ባሮች የሚጠጡላት (ወደፈለጉበት) ማንቧቧትን የሚያንቧቧት ከኾነች ምንጭ (ይጠጣሉ)፡፡ (ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ፡፡ መከራው ተሰራጪ የኾነንም ቀን ይፈራሉ፡፡ ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድኻ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ «የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ*

*ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ «እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን ከጌታችን እንፈራለንና፤» (ይላሉ)፡፡ አላህም የዚያን ቀን ክፋት ጠበቃቸው፡፡ (ፊታቸውን) ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው፡፡ በመታገሣቸውም ገነትንና የሐር ልብስን መነዳቸው፡፡*

እነዚህ አያዎች ስለ አህለልቤይት የሚያወሱ ስለመሆናቸውና በጽድቅና ያላቸውን ከፍተኛ ቦታ እንደሚያሳዩና ለሰው ልጆች ርህራሄን በማሳየትና በቸርነት ድንቅ ተምሳሌት መሆናቸውን አስመልክቶ የቁርአን ሙፈሲሮች በአንድነት የተስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ የሰው ልጅ በነሱ ተምሳሌትነት ወደ ቅን መንገድ ይመራል፡፡ ለዚህ የቁርአን አያህ መገለጥ ምክንያት የሆነው ክስተት የተጀመረው ሐሰንና ሁሴይን በጠና ታመው እሜቴ ፋጢማ ምን ማድረግ እንዳለባት አባቷን በጠየቀች ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለአላህ ነዝር መግባት እንዳለባትና አላህ ልጆቹን ካዳናቸው ቤተሰቡ በሙሉ ለሦስት ተከታታይ ቀናት መጾም እንዳለባቸው ለአላህ ቃል እንድትገባ መከሯት፡፡ ሐሰንና ሁሴይንም ከበሽታቸው ዳኑ፡፡ የጾም ሥርዓቱም ተጀመረ፡፡ በወቅቱ በቤታቸው ውስጥ የሚበላ ነገር ስላልነበረ ኢማም ዓሊ ወደ አንድ ሲሞአን የተባለ የኸይበር አይሁድ በመሔድ ሦስት ኩባያ ገብስ ተበደረ፡፡ እሜቴ ፋጡማ አንዱን ኩባያ ገብስ በመፍጨትና በማቡካት ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ ይደርስ ዘንድ አምስተ ቂጣ ሠራች፡፡ ዓሊ፣ እሜቴ ፋጢማ፣ ልጆቻቸው ሐሰንና ሁሴይን እንዲሁም ሠራተኛቸው ፊድዳ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ጾሙ፡፡ በመጀመሪያው ቀን የማፍጠር ወቅት በደረሰ ጊዜ አንድ የተቸገረ (ሚስኪን) ሰው በራቸው ላይ በመቆም ምግብ ለመነ፡፡ ለማፍጠሪያ ያዘጋጁትን ምግብ በሙሉ ሰጡት፡፡ ጾማቸውንም በውኃ ብቻ አፈጠሩ፡፡ በሁለተኛው ቀን ደግሞ ልክ የማፍጠሪያ ወቅት ሲደርስ አንድ ወላጅ አልባ የሆነ ልጅ መጥቶ

ሲለምናቸው አሁንም ማፍጠሪያቸውን ሰጡት፡፡ በሦስተኛው ቀንም እንዲሁ ኢስላምን ለመከላከል በተደረጉት ጦርነትን ወቅት የተያዘ በመዲና ውስጥ ይኖር የነበረ ምርኮኛ በማፍጠሪያ ወቅት በር ላይ ቆሞ ሲለምን ያለውን ምግብ ወስደው በመስጠት ለሦስት ተከታታይ ቀናት ጾማቸውን በውኃ ብቻ

አፈጠሩ፡፡ በዛን ወቅት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ልጃቸው ፋጢማ አል-ዘህራን ለማየት ሲሄዱ ሁለቱ ልጆቿ ሐሰንና ሁሴይን በረሃብ ገርጥተው መናገር የማይችሉበት ደረጃ ደርሰው እየተንቀጠቀጡ መሆናቸውን አዩ፡፡ ልጃቸው ፋጢማ እራሷ ዓይኖቿ ሰርጉደው፣ ሆዷ ከጀርባዋ ጋር ተጣብቆ መስገጃዋ ላይ ኩርምት ብላ ተቀምጣ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ የሆኑበትን ምክንያት በመጠየቅ ላይ ሳሉ ጂብሪል 76ኛውን የቁርአን ሱራ ይዞ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መጣ፡- «*ሙሐመድ ሆይ! ቤተሰቦችህ ለከፈሉት መስዋዕት አላህ ያበስረሃል*» እያለ ከአላህ የወረደውን የቁርአን ሱራ አመጣላቸው፡፡ *(ተፍሲር አል-ከሻፍ - ዘመክሸሪ 76፣ ተፍሲር አል-ከቢር-ፈኽር አል-ራዚ ሱራ 76፣ መጅመዐል በያን - ጠበርሲ ሱራ 76)* እነዚህ የቁርአን አያዎች የአህለል ቤይትን ቸርነትና ቁርጠኝነት ከመመስከር ባሻገር የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ (አህለልቤይት) ፍጹም ታዛዥነትና ወደር-የለሽ የሆነ ስብዕናቸውንና የላቀ ጥራታቸውን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡

- ***የመሪነት አያህ***

«***እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገዙ፡፡መልዕክተኛውንና ከእናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ፡፡በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑብትኾኑ (የተከራከራችሁበትን ነገር) ወደ አላህና ወደመልክተኛው መልሱት፡፡ይህ የተሻለ መጨረሻውም ያማረ ነው፡፡***» (4፡59)

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ የቁርአን አያህ የዓሊን ኢማምነትና የተቀሩትን የአህለል ቤይት አባላት መሪነት (ኢማምነት) የሚገልጽ አንቀጽ ነው፡፡ ከእናንተ ሥልጣን የተሰጡት» የሚለውን ሐረግ በማስመልከት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- «*እነዚህ የኔ ተተኪዎች ናቸው፣ ከኔ በኋላ የሙሲሊሙን ኡማ የሚመሩ ኸሊፋዎቼ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ፣ ቀጥሎ ደግሞ ሐሰንና ሁሴይን፣ በመቀጠል ደግሞ ዓሊ ኢብነል ሁሴይን፣ ከዚያ ደግሞ ባቂር በመባል የሚታወቀው ሙሐመድ ኢብን ዓሊ፣ ቀጥሎ አል-ሳዲቅ ጃዕፊር ኢብን ሙሐመድ፣ ከዚያም ሙሳ ኢብን ጃዕፈር፣ በመቀጠል ደግሞ ዓሊ ኢብን ሙሳ፣ ከዚያም ሙሐመድ ኢብን ዓሊ፣ ከዚያም ዓሊ ኢብን ሙሐመድ፣ ከዚያም ሐሰን ኢብን ዓሊና በመጨረሻም የኔን ስም የያዘው ሙሐመድ ሲሆን እሱም በምድር ላይ የአላህ ሁጃህ (ማስረጃ) ይሆናል፡፡*» ብለዋል፡፡ *(ተፍሲር አል-ቡርሓን)*

- ## *የሰቀለይን ሐዲስ (የሁለቱ የከበሩ ነገሮች ሐዲስ)*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «*በቅርቡ መጠራቴ አይቀርም፤ እኔም ለጥሪው ምላሽ መስጠቴ አይቀሬ ነው፡፡ ስለዚህ ከኔ በኋላ ሁለት ውድና የከበሩ ነገሮችን ትቼላችኋለው፡፡ እነዚህም ከሰማይ እስከ ምድር የተዘረጋውን ገመድ የአላህ ቁርአንና የኔ ዘረሰብ -አህለልቤይቴ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ በከውሰር ምንጭ ላይ እስከንገናኝ ድረስ ፍጹም እንደማይለያዩ እነሆ ቸሩና ሁሉን አዋቂው አላህ ነግሮኛል፡፡ ስለዚህ ከኔ በኋላ እነዚህን ሁለቱን ነገሮች እንዴት መያዝ እንዳለባችሁና ምን ማድረግ እንዳለባችሁ አስተውሉ፣ ተጠንቀቁ!*» *(ይህ ሐዲስ ከ20 በሚበልጡ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች የተወራ ሲሆን በሰሂህ ሙስሊም (2፡238)፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል (5፡181 – 182)፣ ሰሂህ ቲርሚዚ (2፡ 220) እና ሌሎች መጽሐፍት ውስጥ በተጠቀሱ ከ185 በላይ በሚሆኑ የሐዲስ ተራኪዎች ተጠቅሷል)፡፡*

ይህ ሐዲስ ቢያንስ በአምስት የተለያዩ ጊዜያትና አጋጣሚዎች እንደተነገረ ይታወቃል፡፡ የመጀመሪያው በመሰናበቻው ሐጅ ወቅት በመጨረሻው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ንግግር ወቅት፣ ሁለተኛው ደግሞ ከመሰናበቻው ሐጅ መልስ በገዲር ኹም፣ ሦስተኛው ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መካ አካባቢ የጧኢፍን ከተማ ሲለቁ፣ አራተኛው መዲና ምንበር ላይ ሆነው ሲሆን አምስተኛው ደግሞ ክፍላቸው ውስጥ ሆነው ብዙ ሰሃቦቻቸው በተሰበሰቡበት ከመሞታቸው በፊት ጥቂት ጊዜያት ሲቀር እንደሆነ ይነገራል፡፡

ቁርአን በታላቅነቱና አስፈላጊነቱ ወደር-የለሽ ሆኖ ሳለ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዴት አህለልቤይትን ከቁርአን ጋር በማቆራኘት በሁለተኛ ደረጃነት አስቀመጡ? የዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆነው የቁርአንን ትክክለኛ ትርጉምና ትንታኔ መስጠት የሚችሉት ብቸኛው አካል አህለል ቤይት ስለነበሩ ነው፡፡ ቁርአን ራሱን በራሱ በገለጸው መሠረት ግልጽ (ሙህከም) እና አሻሚ (ሙተሻቢህ) አያዎችን ያካተተ በመሆኑ የነዚህ አንቀጾች ትክክለኛ ትርጓሜ ከራሳቸው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ አህለልቤይት መተላለፍ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም አህለል ቤይት ለነቢዩ ከነበራቸው ልዩ ቀረቤታ የተነሳ ተወዳዳሪ የሌለው የነቢዩ ሐዲስና አኗኗር ዕውቀት ነበራቸው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ አህለል ቤይት ከተናገሩት ተመሳሳይ ሐዲሶች መካከል፡-

- ***«የኔ አህለልቤይት ምሳሌ እንደ የኑህ መርከብ ነው፡፡ በመርከቧ የተሳፈረ ማንኛውም ሰው የደህንነት ዋስትና ይጎናጸፋል፡፡ በመርከቧ መሳፈርን አሻፈረኝ ያለ ግን ሰጥሞ ይጠፋል፡፡*** *» (ይህ ሐዲስ በ8 የነቢዩ ሰሃቦች፣ በ8 ሰሃቦች ተከታዮች የተወራ ሲሆን፣ ዕውቅናን ባተረፈ 60 ምሁራን፣ የሱኒ ወንድሞች ከሆኑ 90 ጸሐፍት (እንደ ሚሽከቱል መሳቢህ - አህመድ ኢብን ሐንበል፣ ገጽ 523፣ ፈራኢደል ሲምተይን - 2፡242፣ አል-ሰዋኢቅ አል-መህሪቃ ገጽ 234፣ ዑዩን አል-አኽባር - 1፡211... ሌሎችም) ተዘግቧል፡፡*

- ***«ከዋክብት የሰው ልጆች በጉዞ ላይ ሲሆኑ መንገድ እንዳይጠፋቸው እንደመሪ እንደሚያገለግሉ ሁሉ የኔ አህለልቤይትም ሰዎች ኃይማኖታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ፈር እንዳይለቁ የሚጠበቁ ናቸው፡፡»*** *(አል-ሙስተድረክ - አል-ሐኪም (ኢብን ዓባስን በመጥቀስ) 3፡149)*
- «የነቢዩን ቤተሰብ (ኣል-ሙሐመድ) መቀበል ማለት ከጀሐነም እሳት መዳን ማለት ነው፡፡ የነቢዩን ቤተሰብ (ኣል-ሙሐመድ) መውደድ የሲራጥ ድልድይ መሻገሪያ የይለፍ ወረቀት ነው፡፡ ለነቢዩ ቤተሰብ (ኣል-ሙሐመድ) መታዘዝ ማለት ከመለኮታዊ ቁጣና እርግማን መጥጠበቅ ማለት ነው፡፡» *(አል-ሽፋ - 2፡40)*

## *እንከን-የለሽነት (ዕስማህ)*

በሺዓ መዝሐብ እምነት መሠረት ከአደም (ዐ.ሰ) ጀምሮ እስከ ነቢያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያሉ ነቢያት በሙሉ፣ እንዲሁም አሥራ ሁለቱ የነቢዩ ተተኪዎችና ኸሊፋዎችና እሜቴ ፋጢማ አል-ዘህራን ጨምሮ ህይወታቸውን ሙሉ እንከን የለሾች እንደነበሩና አላህን የሚያስቆጣ ምንም ኃጢአትና ስህተት እንዳልፈጸሙ በጥብቅ ይታመናል፡፡ ይህንን ነጥብ በግልጽ ለማየት እንዲረዳን መገንዘብ ያለብን ነገር እነዚህ ሰዎች የሰው ልጆች በሙሉ ይከተሏቸው ዘንድ ተምሳሌት ተደርገው የተሰየሙ ሲሆኑ ስህተት የሚሰሩ ከሆኑ ህዝቡ ስህተታቸውንም የመከተልና የመቀበል ግዴታ ስለሚኖርበት ይህ ደግሞ የነቢያቱንና የመልዕክተኞቹን ተዕማኒነት የሚጻረር አካሔድ መሆኑ ነው፡፡ እንከን-የለሽነት ማለት መጥጠበቅ ሲሆን በኢስላማዊ ቋንቋ ደግሞ አንድን ሰው በራሱ ፈቃድ ከማንኛውም ኃጢአት የመፈጸም ችሎታ የሚያሳጣ ወይም የሚያመክን ሳይሆን ሰውየው በራሱ ኃይልና ፈቃድ ከኃጢአትና ስህተት የመታቀብ ችሎታ የተካነ ማለት ነው፡፡

የነቢያትና መልዕክተኞች ተግባር የአላህን መለኮታዊ መልዕክቶች (መጽሐፍት) ማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆችን ወደ ትክክለኛው መንገድ መምራት ስለሆነ እንከን-የለሽነት (ዕስማህ) ለነቢያቱና መልዕክተኞቹ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ለመላው የሰው ዘር ፍጹም ተምሳሌት መሆን አለባቸው፡፡ ቅዱስ ቁርአንም ሆነ ተፈጥሮአዊ ጥበብ (አመንክያዊ አስተሳሰብ) ይህንኑን ነጥብ ያስረዳሉ፡፡ ቅዱስ ቁርአን እንከን-የለሽነትን አሥራ ሦስት ጊዜ ጠቅሷል፡፡ አላህ ለሸይጧን ሲናገር፦ «***እነሆ ባሮቼ በእነሱ ላይ ላንተ ስልጣን የለህም፡፡ ከጠማሞቹ የተከተለህ ሰው ብቻ ሲቀር ፡፡***» (15፡42) ሰይጣን ለአላህ መልሶ ሲናገር፦ «***(እርሱም) አለ «በአሸናፊነትህ ይኹንብኝ፤ ምርጥ ባሮችህ ሲቀሩ(ነቢያትና ኢማሞች ሲቀሩ)በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡***»» (38፡82)

አንዳንድ የቁርአን አንቀጾች አሉ፡፡ ነገር ግን የላይ ላይ ትርጉማቸውን ብቻ ሳይሆን መቼቱንና ዐውዱን በአንክሮ በመመልከት ትክክለኛ ትርጉማቸውን ማግኘት ይቻላል፡፡ ነቢዩ አደምን (ዐ.ሰ) በተመለከተ የአላህን ግዴታ መመሪያዎች አልጣሰም፡፡ ያልተገበረው መመሪያ ቢኖር አስገዳኝ የሆነ መመሪያ ሳይሆን ጥብቅ ያልሆነ የሚእንደ አደም፣ ሙሳ፣ ዩኑስና የመሳሰሉ ነቢያት ሐጢአት እንደሰሩ ተደርገው የተረዱበት በረታታን ድርጊት ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም በኢስላማዊ አባባል መሠረት ወንጀል ወይም ኃጢአት አልፈጸመም፡፡

**وَلَقَدْ عَهِدْنَا إِلَىٰ آدَمَ مِنْ قَبْلُ فَنَسِيَ وَلَمْ نَجِدْ لَهُ عَزْمًا(١١٥)**

«***ወደ አደምም ከዚህ በፊት ኪዳንን በእርግጥ አወረድን፡፡ ረሳም፡፡ ለእርሱም ቆራጥነትን አላገኘንለትም፡፡***»(20:115)

የሱ ጥፋት ቢኖር የፈቃደኝነት ኃይል (will power) ማጣቱ ነበር፡፡ ነገር ግን መተግበር ያልቻለው የአላህ መመሪያዎች ግዴታ የነበሩ ሳይሆን የሚበረታቱና ተፈላጊ ስለነበሩ መመሪያዎችን ጥሷል የሚያስብል ዓይነት አይደለም፡፡ ውጤቱም የተሰጠውን ዕድል የማጣት ጉዳይ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

**إِنَّ لَكَ أَلَّا تَجُوعَ فِيهَا وَلَا تَعْرَىٰ(١١٨)وَأَنَّكَ لَا تَظْمَأُ فِيهَا وَلَا تَضْحَىٰ(١١٩)**

«***ለአንተ በእርሷ ውስጥ አለመራብና አለመታረዝ አለህ፡፡ አንተም በርሷ ውስጥ አትጠማም፤ ፀሐይም አትተኮስም፡፡***» (20:118-119)

ቁርአን የነቢዩን አደም (ዐ.ሰ) መመሪያ መጣስ ሲጠቅስ የዚህን መመሪያ መጣስ በግርድፉ ሳይሆን በተለየ ዐውድ ነው፡፡ ይኸውም እንደ አደም (ዐ.ሰ) ያለ የነቢይነት ማዕረግ የተጎናጸፈና የህዝብ መሪ ከሆነ ሰው የአላህን ምክር

መተግበር አለመቻል የማይጠበቅ በመሆኑ ይህንን ሁኔታ ለማስቀመጥ ያህል ነው፡፡ ስለዚህ በቁርአን ውስጥ በዚህ ዐውድ መሠረት እንደ ጥፋት ወይም ኃጢአት ሆኖ ተጠቅሷል፡፡

ነቢዩ ሙሳን (ዐ.ሰ) በተመለከተ ደግሞ ቁርአን ሲናገር፡-

**وَلَهُمْ عَلَيَّ ذَنْبٌ فَأَخَافُ أَنْ يَقْتُلُونِ(١٤)**

««*ለእነርሱም በእኔ ላይ (የደም) ወንጀል አልለ፡፡ ስለዚህ እንዳይገድሉኝ እፈራለሁ፡፡*»» (26፡14)

ይህ ክስ የመጣው ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) የሆነን ሰው ገፍቶ በመጣል ሳያስበው በመግደሉ ምክንያት የተከሰተ ነገር ነው፡፡ ይህ የሆነው ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ከሱ ወገን የሆነን አንድ ሰው ለመከላከል ሙከራ ባደረገበት ወቅት ከፈርኦን ወገን የሆነን አንድ ሰው ገፍትሮ በጣለበት ጊዜ ሰውየው ደካማ ስለነበረ በመውደቁ ህይወቱ ያለፈችበት ወቅት ነው፡፡ ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ለመግደል አስቦ አይደለም የገደለው፡፡ ነገር ግን ይህ ድርጊት ከተከሰተ በኋላ ቀደም ሲል የፈርኦን ጭፍራ ይፈልገው እንደነበረ ስለሚያውቅ ከቦታው በመሸሽ ከቦታው መሰወር ነበረበት፡፡ በዚያ ወቅት ተይዞ የፈርኦን ምርኮኛ ለመሆን አልፈለገም ነበር፡፡ ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) የፈርኦንን ጭፍራ አስመልክቶ «*በኔ ላይ ክስ አላቸው*» ብሎ ሲናገር ሰዎቹ በሱ ላይ ያላቸውን ወቀሳ ወይም ክስ መጥቀሱ እንጂ የግድ ክሶቹ እውነት ናቸው ብሎ መቀበሉን አያሳይም፡፡

የነቢዩ ዩኑስ (ዐ.ሰ) ጉዳይም ተመሳሳይ ነው፡፡ ቁርአን ሲናገር፡-

**وَذَا النُّونِ إِذْ ذَهَبَ مُغَاضِبًا فَظَنَّ أَنْ لَنْ نَقْدِرَ عَلَيْهِ فَنَادَىٰ فِي الظُّلُمَاتِ أَنْ لَا إِلَٰهَ إِلَّا أَنْتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنْتُ مِنَ الظَّالِمِينَ(٨٧)**

«ዘንኑን (*የዓሳውንም ባለቤት) ተቆጥቶ በኼደ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ፡፡ በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ጥራት ይገባህ፡፡ እኔ በእርግጥ እራሳቸውን ከበደሉቱ ነበርኩ በማለት ተጣራ፡፡*» (21፡87)

በዚህ መሠረት ነቢዩ ዩኑስ (ዐ.ሰ) ማለት የፈለከው በራሱ ላይ ጉዳት ማድረሱን ነበር፡፡ በራስ ላይ ጉዳት ማድረስ ደግሞ ኃጢአትም ስህተትም መሆን አይችልም፡፡ «በራሱ ላይ ጥፋት የሰራውም» ተከታዮቹ አላህን ይገዙ ዘንድ ለተደረገላቸው ጥሪ በተደጋጋሚ እምቢተኛ ሲሆኑበትና መዘበቻ ሲያደርጉት ትዕግሥት በማጣት ከነሱ በመሸሽ እንደፈለጉ እንዲሆኑ ጥሏቸው በመሄዱ ነው፡፡

ቅዱሱ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ጥፋት እንደጠፉ ተደርገው የቀረቡ የሚመስሉ አብዛኛዎቹ የቁርአን አንቀጾች ጠለቅ ያለ ድብቅ ማብራሪያ ያለቸው ናቸው፡፡ ሁሉንም የቁርአን አንቀጾች ግልጽ በሆነ ትርጉም ብቻ ልንረዳ አንችልም፡፡ ከብዙ የቁርአን አንቀጾች ጀርባ ድብቅ የሆኑ ማብራሪያዎች አሉ፡፡ ይህን አስመልክቶ ቁርአን ሲናገር፡-

**هُوَ الَّذِي أَنْزَلَ عَلَيْكَ الْكِتَابَ مِنْهُ آيَاتٌ مُحْكَمَاتٌ هُنَّ أُمُّ الْكِتَابِ وَأُخَرُ مُتَشَابِهَاتٌ فَأَمَّا الَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمْ زَيْغٌ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَابَهَ مِنْهُ ابْتِغَاءَ الْفِتْنَةِ وَابْتِغَاءَ تَأْوِيلِهِ وَمَا يَعْلَمُ تَأْوِيلَهُ إِلَّا اللَّهُ وَالرَّاسِخُونَ فِي الْعِلْمِ**

«*እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሐፉን ያወረደ ነው፡፡ ከእርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የኾኑ አንቀጾች አሉ፡፡ እነሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው፡፡ ሌሎችም ተመሳሳዮች አሉ፡፡ እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን ለመፈለግና ትርጉሙን ለማዛባት ለመፈለግ*

***ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ፡፡ (ትክክለኛ) ተእዊሉን አላህ እና በዕውቀትም የጠለቁት (ቅዱሱ ነቢይና አህላልበይቱ) ብቻ እንጅ ሌላ አያውቀውም፡፡*** « (3፡7)

በተጨማሪም ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተሰጠው አጠቃላይ ባህርይና ክብር የሚያሳየው ያለጥርጥር ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጥፋት ሠሪዎች መሆን እንደማይችሉ ነው፡፡

የአላህ ነቢያት የፈጸሟቸውን የህግ መጣስ ወንጀሎችን አስመልክቶ በርካታ መሠረተ-ቢስ የሆኑ ሐዲሶች በአንዳንድ የሐዲስ መጽሐፍት ውስጥ ሰፍረው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ኢማሙ ቡኻሪ ሲዘግብ፡-

«በአንድ ወቅት የተወሰኑ የቁሬይሽ ሴቶች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር እያወሩና ድምጻቸውን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድምጽ በላይ ከፍ አድርገው በማውራት ላይ ሳሉ ዑመር እንዲገባ ፈቃድ በጠየቀ ጊዜ ሴቶቹ ተጣድፈው በመነሳት ከመጋረጃው ጀርባ ተጠለሉ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዑመርን በፈገግታ ተቀበሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ዑመር፡- «*የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ዕድሜዎን በሙሉ በደስታ ውስጥ ያኑርዎት*» አላቸው፡፡ ከዚያም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- «*እነዚህ ከኔ ጋር የነበሩ ሴቶች ሁኔታ ገርሞኛል፡፡ ድምጽህን እንደሰሙ ብድግ ብለው ሂጃባቸውን ለበሱ*»» *(ሰሂህ ቡኻሪ፣ መጽሐፈ ዘፍጥረት፣ ሐዲስ 3051፣ ስለ መልካም ባህሪዎች የሚያወሳው ክፍል ውስጥ፣ ሐዲስ 3047፣ መልካም ስብዕናዎች፣ ሐዲስ 5621፡፡ ሰሂህ ሙስሊም - መናቂብ አል-ሰሃባ፣ ሐዲስ 4410፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 1፡171፣ 182፣ 187)*

በተመሳሳይ መልኩ ኢማም ሙስሊም ሲዘግብ፡-

«አቡ በክር ሊጠይቀኝ መጣ (ቅዱሱን ነቢይ ሙሐመድ)፡፡ ከአንሷር የሆኑ ሁለት ሴቶች ከኔ ጋር ነበሩ፡፡ የአንሷር ሰዎች በቡዓዛ ጦርነት ወቅት ይዘምሩ የነበረውን አንዳንድ መዝሙሮች እየዘመሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ልጆቹ ዘማሪዎች

(ዘፋኞች) አልነበሩም፡፡ አቡ በክር ይህንን ባየ ጊዜ እንዲህ አለ፡- «*ምንድን ነው ነገሩ! ይህ የሰይጣን እስትንፋስ የሆነ መሳሪያ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤት ውስጥ ያውም በኢድ ቀን ይዘፈንልኛል!?*» በዚህ ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- «*አቡ በክር ሆይ! ሁሉም ህዝብ የራሱ በዓል (ፌስቲቫል) አለው፡፡ ይህ ደግሞ የኛ በዓል ነው፡፡ ስለዚህ ተዋቸው ይጫወቱ፡፡*» *(ሰሂህ ቡኻሪ - ስለ ጁምዓ ሰላት በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ 897፣ ሰሂህ ሙስሊም - ስለ ዒድ ሰላት በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ 1479፣ አል-ነሳኢ - ሐዲስ 1575፣ 1577፣ 1579፣ ሱነን ኢብን ማጃህ - ስለ ጋብቻ በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ 1888፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐምበል - ክፍል 6፡ 166፣ 186፣ 247)፡፡*

*ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ቁመው በአደባባይ ሽንታቸውን እንደሸኑ የሚጠቅስ ሐዲሶችም ተዘግበዋል (ሰሂህ ሙስሊም - ባብ አል-ሒራብ ወል-ደርቅ የውመል ኢድ፣ ሙስሊም - ኪታብ አል-ጠሓራህ፡ ምዕ. 22፣ ሰሂህ ቡኻሪ፣ ኪታብ አል-ውዱእ ቅጽ 1)*

እውነቱን ለመናገር በመጀመሪያውና በሁለተኛው ኸሊፋዎች እንዲሁም በማንኛውም ተራ ሰው እንኳ ኢስላማዊ ተግባራት አለመሆናቸው የተመሰከረላቸው ድርጊቶች ነቢዩ በግልጽ ይፈጽሟቸዋል ብሎ ማሰብ ለአዕምሮ የሚከብድ ነው፡፡ በመልካም ተምሳሌነት እንከተላቸው ዘንድ በቁርአን የታዘዝንበትና የሰው ልጅ መሪነትን የተጎናጸፉ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ያደርጋሉ ቢባል ማንኛውም ሙስሊም እንዲህ ዓይነቱን ባህርይ አይቀበልም፡፡ በሐዲስ መጽሐፍት አዕምሮ የማይቀበላቸው፣ ተፈጥሮአዊ አስተሳሰብንና ጥበብን የሚቃረኑ በርካታ የሆኑ መሠረተ-ቢስ ዘገባዎች አሉ፡፡

ሌሎች ነቢያትንም በተመለከተ ተመሳሳይ ሐዲሶችን እናገኛለን፡፡ ለምሳሌ፡-
የሞት መልዓክ (መለከል መውት) ወደ ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) መጣና እንዲህ አለው፡- «*የአላህን ጥሪ ተቀበል (ለሞት ተዘጋጅ)፡፡*» ሙሳ የሞት መልአኩን

በጥፊ አጩሎ ዓይኑን አጠፋው፡፡ በዚህ ጊዜ መልዓኩ ወደ አላህ ተመልሶ፡ «*መሞት ወደ ማይፈልግ ባሪያህ ላከኝ፡፡ እነሆ ዓይኔን አጠፋኝ*» አለ፡፡ አላህም ዓይኑን መለሰለት፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ፣ ሐዲስ 1253 (ስለ ለቅሶና ሐዘን በሚያወሳው ክፍል ውስጥ፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ አል-መናቂብ - ሐዲስ 4374፣ አል-ነሳኢ - ሐዲስ 2062፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐምበል - 2፡269፣ 315፣ 351፣ 533)*

የተሰጠውን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ያለን አንድ ሰው ያጠቃ አንድ ተራ ሰው እንኳ አፈንጋጭና አጥፊ ሆኖ ተቆጥሮ ለክስ ይቀርባል፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ባህርይ በተለይ ደግሞ ለዓለም ተምሳሌት ለሆኑትና ህዝብን ሊያስተምሩ፣ ሊመሩና ሊያድሱ ከተላኩት ከአምስቱ ሁለ-ገብ ነቢያት አንዱ በሆነው ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) መሆኑ ፍጹም የማይታመን ነገር ነው፡፡ ወደ አላህ ሊያቀርበው የመጣውን የሞት መላዕከት እንደ ሙሳ ያለ ነቢይ እንዴት እንደዛ ያደርጋል? እንደዚህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች ፍጹም ተቀባይነት ሊያገኙ አይችሉም፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹን ከቁርአን አስተምህሮ ጋር የሚጻረሩ መሠረተ-ቢስ ሐዲሶችን የያዙ መጽሐፍትን ሙስሊሙ ህብረተሰብ ዓይኑን ከፍቶ በአንክሮ ሊመረምራቸው ይገባል፡፡

## *ምልጃ (ሺፋዓ)*

የምልጃ (ሺፋዓ) ጉዳይ በኢስላም ውስጥ አነጋጋሪ ከሆኑ ጉዳዮች ቀዳሚውን ቦታ ከያዙት ርዕሶች አንዱ ነው፡፡ የሺዓ መዝሐብና በሱኒ ውስጥ ያሉ አንዳንድ መዝሐቦች ሺፋዓን ሲቀበሉ ሌሎች ደግሞ አይቀበሉም፡፡ እንዲያው በምልጃ (ሺፋዓ) የሚያምን ሙስሊም አይደለም ይላሉ፡፡ ቁርአን ይህንን ጉዳይ በሦስት መንገዶች ይጠቅሳል፡፡ በመጀመሪያ እንደ 2፡123፣ 2፡254 ያሉ አንቀጾች የሺፋዓን አለመኖር ይጠቅሳሉ፡፡ ከዚያ ደግሞ እንደ 6፡70 እና 39፡44 ያሉ አንቀጾች የማማለድ ጉዳይ በብቸኝነት የአላህ ብቻ እንደሆነና ማማለድ

የሚችለው እሱ ብቻ እንደሆነ ሲያስቀምጡ በመጨረሻ ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱ የምልጃ ዓይነቶች የተለየ አድርገው በኢስላም ውስጥ ያለውን አጠቃላይ የሺፈዓ ጉዳይ ላይ ፍርድ የሚሰጡና የሚያጠቃልሉ አንቀጾችን ያካተተ ነው፡፡ ይኸውም ሺፈዓ የአላህ መብት ብቻ እንደሆነና ነገር ግን እሱ ባሻ ጊዜ ከፍጡራኑ ለፈለገው ሰው እንደሚሰጥ የሚጠቅሱ በርካታ አንቀጾች አሉ፡-

مَا مِنْ شَفِيعٍ إِلَّا مِنْ بَعْدِ إِذْنِهِ ۚ

- «*ከእርሱ ፈቃድ በኋላ ቢኾን እንጂ አንድም አማላጅ የለም፡፡*» (10:3)

مَنْ ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِنْدَهُ إِلَّا بِإِذْنِهِ

- *ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው?*» (2:255)

يَوْمَئِذٍ لَا تَنْفَعُ الشَّفَاعَةُ إِلَّا مَنْ أَذِنَ لَهُ الرَّحْمَٰنُ وَرَضِيَ لَهُ قَوْلًا(١٠٩)

- «*በዚያ ቀን ለእርሱ አልረሕማን የፈቀደለትንና ለእርሱም ቃልን የወደደለትን ሰው ቢኾን እንጅ ምልጃ (አንድንም) አትጠቅምም፡፡*» (20:109)

وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ارْتَضَىٰ (٢٨)

- «*ለወደደውም ሰው እንጅ ለሌላው አያማልዱም፡፡*» (21:28)

لَا يَمْلِكُونَ الشَّفَاعَةَ إِلَّا مَنِ اتَّخَذَ عِنْدَ الرَّحْمَٰنِ عَهْدًا(٨٧)

- «*አልረሕማን ዘንድ ቃል ኪዳንን የያዘ ሰው ቢኾን እንጂ ማማለድን አይችሉም፡፡*» (19:87)

وَلَا تَنْفَعُ الشَّفَاعَةُ عِنْدَهُ إِلَّا لِمَنْ أَذِنَ لَهُ

- «*ምልጃም እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም፡፡* » (34፡23)

በእነዚህ አናቅጽ መሠረት ከአላህ ፈቃድ የሚያገኙ እንደ ነቢያት፣ ኢማሞችና አውሊያዎች በአላህ ፈቃድ መሠረት ሊያማልዱና ሰዎችን ሊረዱ ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ከአላህ ፈቃድ ውጭ የሚሆን ምልጃ ግን የለም፡፡ በዚህ ዓለም ላይ እንኳ ወደ አላህ ተውባ ለሚያደርጉና ይቅርታ ለመጠየቅ ለፈለጉ ሰዎች ነቢያት የማማለድ ችሎታና ፈቃድ እንደነበራቸውና ይህንንም በተደጋጋሚ ያደርጉ እንደነበረ የቁርአን ማስረጃዎች አሉ፡-

وَمَا أَرْسَلْنَا مِنْ رَسُولٍ إِلَّا لِيُطَاعَ بِإِذْنِ اللَّهِ وَلَوْ أَنَّهُمْ إِذْ ظَلَمُوا أَنْفُسَهُمْ جَاءُوكَ فَاسْتَغْفَرُوا اللَّهَ وَاسْتَغْفَرَ لَهُمُ الرَّسُولُ لَوَجَدُوا اللَّهَ تَوَّابًا رَحِيمًا(٦٤)

- «*ማንንም መልዕክተኛ በአላህ ፈቃድ ሊታዘዙት እንጅ አልላክንም፡፡ እነሱም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ ወደ አንተ ቢመጡና አላህንም ምሕረትን በለመኑ መልክተኛውም ለነርሱ ምሕረትን በለመነላቸው ኖሮ አላህን ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ኾኖ ባገኙት ነበር፡፡*» (4፡64)

قَالُوا يَا أَبَانَا اسْتَغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا إِنَّا كُنَّا خَاطِئِينَ(٩٧) قَالَ سَوْفَ أَسْتَغْفِرُ لَكُمْ رَبِّي إِنَّهُ هُوَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ(٩٨)

- የዩሱፍ ወንድሞችም አሉ*፡-«አባታችን ሆይ! ለኀጢአቶቻችን ምሕረትን ለምንልን እኛ ጥፋተኞች ነበርንና» አሉ፡፡ «ወደፊት ለእናንተ ጌታዬን*

*ምሕረትን እለምንላችኋለሁ፡፡ እነሆ! እርሱ መሓሪው አዛኙ ነውና» አላቸው፡፡» (12፡97–98)*

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን አማላጅነት እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡-

- «በቂያማ ቀን በልቡ ውስጥ እምነት (ኢማን) ላለው ሰው አማልዳለሁኝ፡፡» *(ከንዝ አል-ኡማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ - ሐዲስ 39043)*
- «እያንዳንዱ ነቢይ አላህን አንድ ነገር ጠይቆ አገኘ፡፡ እኔ ደግሞ ጥያቄዬን ለህዝቤ አማልድ ዘንድ ለቂያም ቀን አቆየሁት፡፡» *(ከንዝ አል-ኡማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ)*
- «ምልጃዬ የሚሆነው ከሽርክና ዙልም (ጭቆና) በስተቀር ከባባድ ወንጀል (ከባኢር) ለፈጸሙ ሰዎች ነው፡፡» *(ከንዝ አል-ኡማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ)*
- «አማላጆች አምስት ናቸው፡- ቁርአን፣ የቅርብ ዘመዶች፣ አደራ (አማና)፣ ነቢያችሁና የነቢያችህ አህለልቤይት (ቤተሰብ) ናቸው፡፡» *(ከንዝ አል-ኡማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ- ሐዲስ ቁጥር 39041 )*

ሺፈዓህ ማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ኢማሞች (ዐ.ሰ) ከአደጋ እንዲጠብቁን ቀይም ደስታና ስኬትን እንዲያጎናጽፉን መማፀን አይደለም፡፡ ነገር ግን እንደ ነቢያትና ኢማሞች ባሉት ለአላህ ቅርብ በሆኑ ሰዎች አማካይነት ወደ አላህ በመቃረብ አላህን መለመን ማለት ነው፡፡

ቁርአን እንደሚያረጋግጥልን በቂያም ቀን በምልጃ ሰዎችን መርዳት የሚችሉት ከአላህ ፈቃድ የተሰጣቸውና ቃል የተገባላቸው ብቻ እንደሆኑ እንገነዘባለን፡፡ ምልጃ የሚገባቸው ደግሞ በዚህኛው ዓለም መልካም አስተሳሰብና እምነት ያላቸው፣ ከአላህ ያላፈነገጡና በስልጣኑ ያላስተባበሉ ሆነው ምናልባትም በከፊሉ ኃይማኖታዊ ግዴታዎች ትግበራ ላይ ወደ ኋላ የቀሩ ወገኖች ናቸው፡፡

በቂያም ቀን የመልካም ሥራዎቻቸው መዝገብ የመልዕክተኞችን፣ የኢማሞችንና የምዕምናንን ምልጃ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል፡፡

የአህለልቤይት መዝሐብ ስድስተኛው ኢማም የነበሩት ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ(ዐ.ሰ) ሽሒድ በሆኑ ጊዜ ዘመዶቻቸውንና ሰሃቦቻቸውን ጠርተው እንዲህ ብለዋቸው ነበር፡-»እውነት እላችኋለው የሰላትን ጉዳይ ቀለል አድርገው ለሚያዩ ሰዎች ምልጃችን አይደርሳቸውም (ሺፋዓችንን አያገኙም)«፡፡
*(ቢሐር አል-አንዋር፡ 82፡236)*

## ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ኢማሞችን (ዐ.ሰ) ለኢስቲጋሳ (እርዳታ) መጥራት

ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እና ኢማሞችን ለኢስቲጋሳ መጣራት (ኢስቲጋስት አል-ነቢ ወል አኢማህ) ገሃዳዊ ትርጉም ሳይሆን ቅኔያዊ ትርጓሜ ያለው ጉዳይ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርአን ሰዎች አላህን እንዲገዙና ከአላህ እርዳታ እንዲጠይቁ ያስተምራል (ኢያከ ነዕቡድ ወ ኢያከ ነስተኢን)፡፡ ነገር ግን በቅኔያዊ ትርጉሙ መሠረት እርዳታ (ኢስታጋሳ) መጠየቅ የተፈቀደ መሆኑን እናያለን፡፡ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ እንደምሳሌ ማየት እንችላለን፡፡ በነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ታሪክ ውስጥ እንዲህ እናነባለን፡-

**وَدَخَلَ الْمَدِينَةَ عَلَىٰ حِينِ غَفْلَةٍ مِنْ أَهْلِهَا فَوَجَدَ فِيهَا رَجُلَيْنِ يَقْتَتِلَانِ هَٰذَا مِنْ شِيعَتِهِ وَهَٰذَا مِنْ عَدُوِّهِ فَاسْتَغَاثَهُ الَّذِي مِنْ شِيعَتِهِ عَلَى الَّذِي مِنْ عَدُوِّهِ فَوَكَزَهُ مُوسَىٰ فَقَضَىٰ عَلَيْهِ قَالَ هَٰذَا مِنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ إِنَّهُ عَدُوٌّ مُضِلٌّ مُبِينٌ(١٥)**

*«ከተማይቱንም ሰዎቿ በዝንጋቴ ጊዜ ላይ ሆነው ሳሉ ገባ፡፡ በእርሷም ውስጥ የሚጋደሉን ሁለት ሰዎችን አገኘ፡፡ ይህ ከወገኑ ነው፤ ይህም ከጠላቱ ነው፡፡ ያም ከወገኑ የሆነው ሰው በዚያ ከጠላቱ በሆነው ሰው ላይ እርዳታን ጠየቀው (ኢስተጋሰሁ)፡፡ ሙሳም በጡጫ መታው፡፡ ገደለውም፡፡ ይህ ከሰይጣን ሥራ ነው፡፡ እርሱ ግልጽ አሳሳች ጠላት ነውና አለ፡፡» (28:15)*

ብዙ የሐዲስ ዘጋቢዎች ከነቢዩ የተገኘ ዱዓ (ፀሎት) **በማስመልከት «*ጌታዬ ሆይ! እነሆ የርህራሄ ነቢይ በሆነው በነቢይህ ወደ አንተ እዞራለሁ (አላሁመ ኢንኒ አተወጀሁ ኢለይከ ቢ ነቢይከ ነቢይ አል-ረሀመህ)*»** በማለት የሚጀምር ዱዓእ መኖሩን አስተላልፈዋል፡፡ ከዚያም፡- **«*ሙሐመድ ሆይ! ችግሬን ይቀርፍልኝ ዘንድ እነሆ በርስዎ ወደ አላህ እቃረባለሁ*»** እያለ ይቀጥላል *(ኢብን ማጀህ፣ አል-ነሳኢ፣ ቲርሚዚ፣ አል-ሁሰን አል-ሐሲን - ኢብን አል-ጁዝሪ)፡፡*

በተጨማሪም የአብደላህ ኢብን ኡመር አል-ኸጣብ እግር ከጥቅም ውጭ ሆኖ ሊሸከመው የማይችልበት ደረጃ በደረሰ ጊዜ ለልብህ ቅርብ የሆነ ሰው በመጥራት ብትማፀን ጥሩ ነው በተባለ ጊዜ «ዋ ሙሐመዳ» ብሎ ሲጣራ እግሩ ከበሽታው ተፈውሶ ያለ ችግር መራመድ መቻሉ ተዘግቧል፡፡ *(ሺፈዓል አቅሳም - አል-ሰምሑዲ)*

ቅዱስ ቁርአን በትዕግሥትና በሰላት አማካይነት (ሰብርና ሰላት) እርዳታ (ኢስቲጋሳ) እንድንጥይቅ ያስተምረናል፡፡

**وَاسْتَعِينُوا بِالصَّبْرِ وَالصَّلَاةِ**

«***በመታገስና በሶላትም እርዳታን ፈልጉ፡፡***» (2:45)

ሰብር (እዚህ ቦታ ላይ ጾም ማለት ነው) እና ሰላት ወደ አላህ የሚያቀርቡን መንገዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) መጣራት ቅኔያዊ ትርጉም ያለው መዳረሻ ነው፤ የእርዳታና ድጋፍ እንዲሁም የሁሉም ነገር አስተናባሪ አላህ መሆኑን ሁሉም ያውቃልና፡፡

አንዳንድ ሙስሊሞች ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ኢማሞችን መጣራት ከሽርክ ጋር ያቆራኛሉ፡፡ የሰው ልጅ ማንንም ለእርዳታ መጣራት የለበትም ብለው ያምናሉ፡፡ አንድ ተራ ሰው በህይወቱ ውስጥ ችግር ሲያጋጥመው በአካባቢው ያለውን ሌላ ሰው ለእርዳታ መጣራቱ ተገቢና ተቀባይነት ያለው ጉዳይ የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው? ውኃ ውስጥ ሊሰምጥ ያለ ሰው በአካባቢው ያለውን ሰው ለእርዳታ ቢጣራ ይህ ተግባሩ ሙሽሪክ ያደርገዋልን? በተመሳሳይ መልኩ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ኢማሞችን (ዐ.ሰ) መጣራት ሽርክ ሊሆን አይችልም፡፡ በአሁኑ ወቅት በህይወት ስለሌሉ እነሱን መጣራት አይበቃም (አይፈቀድም) የሚለው አስተሳሰብም ውድቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ሺሂዶች ሙታን አለመሆናቸውን ቁርአን በግልጽ ያስቀምጣልና፡፡ በቁርአን ውስጥ ሸሂዶች ህያው መሆናቸውን እንደሚከተለው እናነባለን፡፡

**وَلَا تَحْسَبَنَّ الَّذِينَ قُتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتًا بَلْ أَحْيَاءٌ عِنْدَ رَبِّهِمْ يُرْزَقُونَ(١٦٩)**

«***እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው፡፡ በእርግጥ እነርሱ እጌታቸው ዘንድ ሕያዋን ናቸው፤ ሲሳይም ይለገሳሉ፡፡***» (3፡169)

**وَلَا تَقُولُوا لِمَنْ يُقْتَلُ فِي سَبِيلِ اللَّهِ أَمْوَاتٌ بَلْ أَحْيَاءٌ وَلَٰكِنْ لَا تَشْعُرُونَ(١٥٤)**

«*በአላህ መንገድ ላይ የሚገደሉትን ሰዎች «ሙታን ናቸው» አትበሉ፡፡ በእውነቱ ሕያዋን ናቸው፤ ግን አታውቁም፡፡*» (2፡154)

በአላህ መንገድ ውስጥ ሸሂድ የሆነ አንድ ተራ ሙስሊም ህያው ነው ከተባለ፣ ሸሂድ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ከመላው የሰው ዘር ላይ የላቀ ደረጃ የተጎናጸፉት ታላቁ ነቢይና ቤተሰባቸው እንዴት ሙታን ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ? ቅድሱን ነቢይና ቤተሰባቸውን (አህለልቤይት) መጣራት አላህ ለዓለማት ሁሉ የእርዳታና የድጋፍ ምንጭ መሆኑን አያፋልስም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ለአላህ እጅግ የቀረቡ በመሆናቸውንና አላህ ዘንድ የተለየ ቦታና ደረጃ ስላላቸው እነሱን መጣራት ማለት እሱ በሚወዳቸው ሰዎች አማካይነት አላህን መጣራት ማለት ነው፡፡

## ኢማም መህዲ (ዐ.ሰ)

የመጨረሻው ዘመን አካባቢ ምድር በጭቆና፣ በሙስናና በበደል ከተሞላች በኋላ ኢማም መህዲ ተነስቶ በዚች ምድር ላይ ፍትህ እንዲሰፍን እንደሚያደርግ ሁሉም ሙስሊሞች ያምናሉ፡፡ ነገር ግን በተለያዩ መዝሐቦች መካከል ያለው ልዩነት የኢማም መህዲን ማንነትና አሁን በህይወት ስለመኖሩ ወይም ገና ስለመወለዱ ላይ ያሉ የተለያዩ አስተሳሰቦች ናቸው፡፡ ታላላቅ ምሁራን በአጽንኦት የሚናገሩት መህዲ እንደሚመጣና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህለል ቤይት አባል እንደሆነ ነው፡፡

- ኢማም ቡኻሪ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዘገቡት ሐዲስ፡- «የመርየም ልጅ በመካከላችሁ ሲወርድና መሪያችሁ (ኢማሞችሁ) ደግሞ ከናንተው መሆኑ ምን ይሰማችኋል?» *(ሰሂሀ ቡኻሪ፡- 4፡143)*
- ኢማም ሙስሊም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዘገቡት ሐዲስም፡- «የኔ ህዝብ የመጨረሻ ዘመን ላይ አንድ ኸሊፋ ይገለጣል፡፡ ቲርሚዚና አቡዳውድ በዚህ ሐዲስ ላይ አስተያየት ሲሰጡ ይህ ኸሊፋ መህዲ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ *(ሰሂሀ ሙስሊም - ቅጽ 2፣ ሱነን ቲርሚዚ፣ ሱነን አቡዳውድ፣ 2፡421)*
- አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ፡- «ለመጨረሻዋ ቀን አንዲት ቀን እንኳ ብትቀር ከኔ ቤተሰብ የሆነ ስሙ ከኔ ስም ጋር የሚመሳሰል ሰው ልኮ በበደልና በጭቆና ተሞልታ የነበራቸውን ምድር በፍትህና እኩልነት እስከትሞላ ድረስ አላህ ያችን ቀን ያራዝማታል፡፡» *(ሱነን አቡዳውድ - 2፡421)*
- ኢብን ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ፡- «እኛ አላህ ከዚህ ዓለም ይልቅ የወዲያኛውን ዓለም የመረጠልን አህለልቤይት ነን፡፡ ከኔ በኋላ አህለል ቤይቶቼ ብዙ ችግር፣ መከራና እንግልት ይደርስባቸዋል፡፡ ጥቁር ባንዲራ

የሚያውለበልቡ የሆኑ ህዝቦች ከምሥራቅ እስኪነሱ ድረስ ስቃይ ይደርስባቸዋል፡፡ ባለ ጥቁር ባንዲራዎቹ መብታቸውን ይጠይቃሉ፡፡ ነገር ግን መብታቸው ይካዳል፡፡ ከዚያም ተዋግተው ድል ይቀናቸዋል፡፡ የፈለጉት ይሰጣቸዋል፣ ነገር ግን ይህንን መብት ከኔ አህለልቤይት ለሆነው ምድር በጭቆና ከተሞላች በኋላ በፍትህ ለሚሞላት የኢማምነት መብት ላለው ሰው እስኪሰጡ ድረስ አይቀበሉም፡፡» *(ኢብን ማጀህ፡- 2፡4082፣ 4087)*

- በተጨማሪም ኢብን ማጀህ ከዘገቡት ሐዲስ፡- «መህዲ ከኛ ከአህለል ቤይት ነው፤ መህዲ ከፋጢማ ልጆች ነው፡፡» *(2፡4082፣ 4087)*
- ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ፡- «ስሙ ከኔ ስም ጋር የሚመሳሰል ከአህለልቤይት የሆነ ሰው በእርግጥ ይህችን ዓለም ይገዛል፡፡ የመጨረሻው ዘመን ሊያከትም አንዲትም ቀን እንኳ ብትቀር እሱ በትረ ስልጣኑን እስኪጨብጥ ድረስ አላህ ቀኗን ያራዝማታል እንጂ አይቀርም፡፡ *(አል-ጀሚል አል-ሰሂህ፡ ቲርሚዚ - 9፡ 74 – 75) በዚህ ርዕስ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገዎ - ፊትሀልባሪ - አል-ሐፊዝ 5፡362፣ አል-ሰዋኢቅ - ኢብን ሐጀር አል-ሐይሰሚ፣ 2፡212፣ ሙንተከብ አል-አሳር - አላማህ ቡጥፈላህ ሳፊ (ከ60 በላይ የአህለሱና ሐዲሶችና ከ90 በላይ የሺዓ ሐዲሶችን ያካተተ) ይመልከቱ፡፡*

በሺዓ መዝሐብ መሠረት ኢማም ሙሐመድ ኢብን አል-ሐሰን አል-መህዲ (ዐ.ሰ) የተወለዱት በ255 ሂጅራ (869 ዓ.ክ)፣ በ15ኛው ቀን የሻዕባን ወር በሰሜን ኢራቅ ውስጥ ሰመራ ተብላ በምትጠራው ከተማ ውስጥ ነው፡፡ አባታቸው የዘር ሐረጋቸው ከኢማም ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) የሆኑት ኢማም ሐሰን አል-አስከሪ (ዐ.ሰ) ሲሆኑ የእናታቸው ስም ደግሞ ነርጂስ ይባላሉ፡፡ በምድራችን ላይ የመጨረሻው ኢማም ሲሆኑ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዘር ሐረግ ሰንሰለት እሳቸው ላይ ያበቃል፡፡ በምድር ላይ የአላህ ወኪል መገኘት

ግዴታ እስከሆነ ድረስ በአላህ ፈቃድ እስከአሁኑ ዘመን ድረስ በዚች ዓለም ውስጥ ይኖራል፡፡ ነገር ግን ከህዝብ እይታ ውጭ ነው፡፡ ነገር ግን በመጨረሻው የሰው ልጅ ስልጣኔ ዘመን ዳግም በመገለጥ በጭቆናና ሙስና ውስጥ የተዘፈቀችዋን ዓለም በፍትህና እኩልነት ይሞላታል፡፡

መህዲ ከአሥራ ሦስት ምዕተ ዓመታት በኋላ በህይወት የመኖሩ ጉዳዩ ለብዙ ሰዎች አስተሳሰብ አስቸጋሪ ቢሆንም ቁርአን ግን ከዚህም በላይ በህይወት ስለኖሩት ነቢያት ብዙ ምሳሌዎችን ይሰጠናል፡፡ ለምሳሌ ነቢዩ ዒሳንና (ዐ.ሰ) አል-ኺድር መጥቀስ ይቻላል፡፡ *(ከነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ጋር ያለውን የኺድር ታሪክ 18፡60 – 82 ይመልከቱ)*፡፡

ቅዱስ ቁርአን ሌሎች ሁለት ተጨማሪ ምሳሌዎችን ይሰጣል፡፡ ይኸውም ከሞቱ በኋላ አላህ ስለቀሰቀሳቸው ህዝቦች ያወሳል፡፡ አንደኛው የአስሐቡል ካፍ (የዋሻ ሰዎች) ታሪክ ሲሆን (18፡25 ይመልከቱ) ሌላው ደግሞ የዑዘይር ምሳሌ ነው፡፡ ቁርአን እንደሚከተለው ይተርካል፡፡

**أَوْ كَالَّذِي مَرَّ عَلَىٰ قَرْيَةٍ وَهِيَ خَاوِيَةٌ عَلَىٰ عُرُوشِهَا قَالَ أَنَّىٰ يُحْيِي هَٰذِهِ اللَّهُ بَعْدَ مَوْتِهَا فَأَمَاتَهُ اللَّهُ مِائَةَ عَامٍ ثُمَّ بَعَثَهُ قَالَ كَمْ لَبِثْتَ قَالَ لَبِثْتُ يَوْمًا أَوْ بَعْضَ يَوْمٍ قَالَ بَلْ لَبِثْتَ مِائَةَ عَامٍ فَانْظُرْ إِلَىٰ طَعَامِكَ وَشَرَابِكَ لَمْ يَتَسَنَّهْ**

«***ወይም ያንን በከተማ ላይ እርሷ በጣራዎችዋ ላይ የወደቀች ስትኾን ያለፈውን ሰው ብጤ (አላየህምን)፡- «ይህችን (ከተማ) ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል» አለ፡፡ አላህም ገደለው መቶ ዓመትን (አቆየውም)፡፡ ከዚያም አስነሳው፡- «ምን ያህል ቆየህ» አለው፡፡ «አንድ ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየሁ» አለ፡፡ «አይደለም መቶን ዓመት ቆየህ፡፡ ወደ ምግብህና ወደ መጠጥህም ያልተለወጠ ሲኾን ተመልከት፡፡***» (2፡259)

በተጨማሪም አላህ ነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ)፣ ነቢዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) እና ነቢዩ ዒሳ (ዐ.ሰ) የተለያዩ ተዓምራትን እንዲያደርጉ ከፈቀደ መህዲ ለረዥም ጊዜ በህይወት እንዲኖር ማድረግ አይቸግረውም፡፡ እሱ አላህ ምንም ማድረግ የማይሳነው ጌታ ነውና፡፡

## *ተቂያ (ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ አቋምን ደብቆ የመኖር ጥበብ)*

ተቂያ ወይም ትክክለኛውን አቋም ማሳወቅ አደገኛ በሆነበት ወቅት ማንነትን ደብቆ የመኖር ጥበብ በቁርአን ውስጥ ሦስት ቦታዎች ላይ ተጠቅሷል፡፡

**لَا يَتَّخِذِ الْمُؤْمِنُونَ الْكَافِرِينَ أَوْلِيَاءَ مِنْ دُونِ الْمُؤْمِنِينَ وَمَنْ يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَلَيْسَ مِنَ اللَّهِ فِي شَيْءٍ إِلَّا أَنْ تَتَّقُوا مِنْهُمْ تُقَاةً**

- «*ምእምናን ከሓዲዎችን ከምእምናን ሌላ ረዳቶች አድርገው አይያዙ፡፡ ይኼንንም የሚሠራ ሰው ከአላህ (ሃይማኖት) በምንም ውስጥ አይደለም፡፡ ከእነርሱ መጠንቀቅን ብትጠነቀቁ እንጂ( እልላ አንተተቁ ሚንሁም ቱቃት)፡፡*» (3፡28)

**مَنْ كَفَرَ بِاللَّهِ مِنْ بَعْدِ إِيمَانِهِ إِلَّا مَنْ أُكْرِهَ وَقَلْبُهُ مُطْمَئِنٌّ بِالْإِيمَانِ**

- «*ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው (ብርቱ ቅጣት አለለው)፡፡ ልቡ በእምነት የረጋ ኾኖ የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡* » (16፡106)

**وَقَالَ رَجُلٌ مُؤْمِنٌ مِنْ آلِ فِرْعَوْنَ يَكْتُمُ إِيمَانَهُ**

- «*ከፈርዖንም ቤተሰቦች አንድ እምነቱን የሚደብቅ ምእመን ሰው አለ…* » (40፡28)

እነዚህ ሦስቱ የቁርአን አንቀጾች እምነትና አቋምን በግልጽ ማራመድ አደገኛ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ በድብቅ መኖር የተፈቀደ ስለመሆኑ ማስረጃ የሚሆኑ ናቸው፡፡ ለነቢዩ አህለልቤይት ተከታዮች ምንም ዓይነት ጥሩ አመለካከትና መቻቻል በሌለባቸው ሀገሮችና የዲሞክራሲ ጭላንጭል በማይታይባቸውና ጭቆናና የሰው መብት ረገጣ የተንሰራፋባቸው ቦታዎች እንዲሁም ሰዎች ለእምነታቸው ሲሉ ለግድያ፣ ለዝርፍያ፣ ለእንግልትና ስቃይ በሚጋለጡባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ህይወታቸውን፣ ንብረታቸውንና ሀብታቸውን ለማዳን የተቂያን ጥበብ መጠቀም እንዳለባቸው ቁርአናዊ አስተምህሮ ያረጋግጥልናል፡፡ ተቂያ መትተግበር ያለበት ለአደጋ የሚያጋልጥ ወይም አስፈሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ብቻ መሆን አለበት፡፡ ነገር ግን የሚያስፈራ ወይም ለአደጋ የሚያጋልጥ ነገር ከሌለ፣ ለምሳሌ በአሜሪካና በአውሮፓ ለሚኖሩ ሙስሊሞች፣ ተቂያ መጠቀሙ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ቁርአን 16፡106 በተለይ ይህንን ጉዳይ ይጠቅሳል፡፡ ይህ አያህ የወረደው በመካ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ አንዳንድ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች በአቡ ሱፍያን ስቃይ ይደርስባቸው በነበረ ወቅት እምነታቸውን በልብ ይዘው በምላሳቸው ግን ክህደት (ኩፍር) የማሳየት ሥልት መጠቀም እንደሚችሉ የተገለጸበት ሁኔታ ነው፡፡ እንደ አማር ኢብን ያሲር ያሉ የነቢዩ ታዋቂ ሰሃቦች እንኳ ካፊሮቹ በመካ ውስጥ እጅግ ሲያሰቃዩዋቸው ውስጣዊ እምነታቸውን በመደበቅ በአንደበታቸው የኩፍር ቃል የተናገሩበት አጋጣሚ ነበር የነበረው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዎች ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመምጣት «*አማር ከሃዲ (ካፊር) ሆኗል*» ብለው ለክስ አቅርበውት ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልስ ሲሰጡ፡- «*በጭራሽ! አማር ከራስ ፀጉሩ እስከ የጣቱ ጥፍር በኢማን የተሞላ ነው*» ካሉ በኋላ አማርን ጠርተው ካፊሮቹ ደግሞ የሚያሰቃዩት ከሆነ እምነቱን በገሃድ መካድ እንደሚችል ነገሩት፡፡ ይህ ታሪክ በቁርአን 16፡106 ተፍሲር ውስጥም ተጠቅሷል፡፡

በኢስላም ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቂያን የተጠቀመ ሰው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሆኑ ይህም የሆነው ለመጀመሪያዎቹ የኢስላም ዓመታት ውስጥ ተልዕኮአቸውን ምስጢር አድረገው ይጠብቁ በነበረ ጊዜ ነው፡፡ ለሦስት ዓመታት ተልዕኮአቸውን በድብቅ ይዘው ነበር፡፡ ይዘው የነበሩትን መልዕክትና ተልዕኮ ለመከላከል ሲሉ አላህ ግልጽ እንዲያወጡ እስከሚያዛቸው ጊዜ ድረስ ለቁሬይሾች ሳይተነፍሱ በምስጢር አቆይተው ነበር፡፡ *(ሲራህ - አብ ሒሻም 1:274፣ ታሪክ አል-ጠባሪ 2፣ 216፣ 218፣ አል-ጠበቃቱል ኩብራ - ኢብን ሳዕድ - ገጽ 200)*

ከዚያም ተልዕኮአቸውን እንዲጀምሩ ከአላህ ፈቃድ መጣ፡-

**فَاصْدَعْ بِمَا تُؤْمَرُ وَأَعْرِضْ عَنِ الْمُشْرِكِينَ(٩٤)**

«***የታዘዝከበትንም ነገር በይፋ ግለጽ፡፡ አጋሪዎችንም ተዋቸው፡፡***» (15:94)

ከዚያ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተቂያ ጊዜ በኋላ ተልዕኮአቸውን በግልጽ ጀመሩ፡፡ ህዝቡንም ወደ ኢስላም በገሃድ መጥራት ጀመሩ፡፡ በተጨማሪም ታሪክ እንደሚነግረን አንዳንድ ታዋቂ የተለያዩ መዝሐቦች መሪዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ተቂያን ይጠቀሙ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ ለወደቁት ሰዎች ሰላትን እንዲተዉና በረመዳን ወር ጾምን መግደፍ እንደሚችሉ የሰጡት ፈትዋ ይጠቀሳል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ኢማም ማሊክም አያህ 3:28ን እንደ መረጃ በመጠቀም ከኡመያና አባሲ ሥርወ-መንግሥታት ጋር የጠበቀ የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ ኢማም ሻፊዒም ተገዶ በውሸት በአላህ በመማል ካሳ(ከፋራን) አልከፍልም ብሎ ስላለው ሰው በሰጡት ፍርድ ውስጥ ተቂያን እንደተጠቀሙ ይነገራል፡፡ *(ዲፋዕ ዐንል ካፊ - አል-አሚይ 1:627)* የሙስሊሞችን ደም መከላከል ግዴታ እንደሆነና የሙስሊሙ ደም እንዳይፈስ ለመከላከል ሲባል መዋሸት ግዴታ እንደሚሆን ኢማም አል-ጋዛሊም ዘግበዋል፡፡ *(አህያእ ዑሉመልዲን - አል-ጋዛሊ)*

አንዳንድ ሰዎች ተቂያን እንደ ንፋቅ (አስመሳይነት) አድርገው ያስባሉ፡፡ ነገር ግን ሙናፊቅነት (አስመሳይነት) እምነትን (ኢማንን) ግልጽ አድርጎ ክህደትን (ኩፍርን) ደብቆ መያዝ ሲሆን ተቂያ ደግሞ በውስጥ ወይም በልብ አለመስማማትን ይዞ ውጪውን በማስመሰል መስማማት ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው እራስን፣ ቤተሰብን፣ ንብረትንና ኃይማኖትን ለማዳን ሲባል የሚደረግ ነው፡፡

## *አላህን ስለ ማየት (ሩእየቱላህ)*

የሺዓ መዝሐብ የአላህን መታየት ሙሉ በሙሉ ይክዳል፡፡ ምክንያቱም አላህ ምስልም ሆነ አካል የለውም ብሎ ስለሚያምን ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎች መዝሐቦች አላህ አካላዊ ቅርጽ እንዳለው መቀበል ብቻ ሳይሆን ማንኛውም አካላዊ ነገር እንደሚታይ ሁሉ የቂያም ቀን አላህም ይታያል ብለው ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም አላህ በሆነ ቦታ ተገድቦ አንድ ቦታ ይዞ እንዳለና ከቦታ ቦታ እንደሚንቀሳቀስ አድርገው ይገምታሉ፡፡ የነዚህ አስተሳሰቦች መሠረትም ቁርአን ሳይሆን ሐዲሶች ናቸው፡፡ አንዳንድ ሐዲሶችን ለመጥቀስ ያህል፡-

- «ጌታችን ፍጥረታቱን ከመፍጠሩ በፊት ከራሱ ጋር ምንም ነገር አልነበረውም፡፡ ከሥሩ አየር ነበር፣ ከላይም አየር ነበር፡፡ ከዚያም ዙፋኑን በውኃ ላይ ፈጠረ» *(ሱነን ኢብን ማጃህ - መግቢያ፣ ሱነን አል-ቲርሚዚ - የሱራ ሁድ ተፍሲር፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 4፡11 – 12)*
- በቂያም ቀን፡ «ለአዛብ (ጀሐነም) እንዲህ ይባላል፡- ‘ሞልተሻልን?’ አዛብም ‘ተጨማሪ አለን?’ ትላለች፡፡ ከዚያም የበላይና የተባረከ የሆነው ጌታ እግሩን በውስጧ ይጨምራል፡፡ ይሄኔ ‘አሁን ሙሉ ነኝ’ ትላለች *(ሰሂህ ቡኻሪ - 3፡128፣ 4፡191፣ 4፡129፣ (ከአነስና ሌሎች)*፡፡»

- «ከዕለታት አንድ ቀን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ቁጭ ብለን ነበር፡፡ በዛን ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሙሉ ጨረቃ ተመለከቱና፡ «ልክ ይህችን ጨረቃ እንደምታይዋት ጌታችሁን እንዲሁ ታዩታላችሁ፡፡ በማየታችሁም ምንም ጉዳት አይደርስባችሁም፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - 10፡18፣ 20፣ ኪታብ አውቃት አስ-ሰላት - ሐዲስ 521፣ 539፣ የቁርአን ተፍሲር - ሐዲስ 4473፣ ተውሂድ ሐዲስ 6882፣ 6883፣ 6884፣ ሰሂህ ሙስሊም (መስጂዶችና የሰላት ቦታዎችን በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ 1002፣ ቲርሚዚ ሐዲስ 2474፣ አቡ ዳውድ - ሐዲስ 4104፣ ኢብን ማጃህ - ሐዲስ 173፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 4፡360፣ 362፣ 365)*፡፡

በተለይ የመጨረሻው ሐዲስ የሚያጠነጥነው የሰው ልጆች ከመልካም ሠሪዎችም ሆነ ከሙናፊቆች በአካላዊ ዓይናቸው አላህን ማየት እንደሚችሉ ነው፡፡ አላህን ማየት ማለት አላህ የተወሰነ ቅርጽ (አካል) ያለውና በሆነ ቦታ የሚገኝ ነው ማለት ነው፡፡ ኢማም ማሊክ ኢብን አነስና ኢማም አል-ሻፊዒ ይህንን ሐሳብ ይቀበላሉ፡፡ ኢማም አህመድ ቢን ሐምበል ደግሞ ይህንን እምነት (ሐሳብ) ከኃይማኖቱ መሠረታውያን አንዱ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

የአህለልቤይት ተከታዮች ሐሳብ ደግሞ አላህን ማየት የማይቻል ጉዳይ እንደሆነ ነው፡፡ ይህ አቋም ደግሞ በቁርአንና አመንክዮ የሚደገፍ አስተሳሰብ ነው፡፡ ቁርአን በግልጽ እንዳስቀመጠው፡-

**لَا تُدْرِكُهُ الْأَبْصَارُ وَهُوَ يُدْرِكُ الْأَبْصَارَ وَهُوَ اللَّطِيفُ الْخَبِيرُ(١٠٣)**

***ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)፡፡ እርሱም ዓይኖችን ያያል፡፡***

**وَإِذْ قُلْتُمْ يَا مُوسَىٰ لَنْ نُؤْمِنَ لَكَ حَتَّىٰ نَرَى اللَّهَ جَهْرَةً فَأَخَذَتْكُمُ الصَّاعِقَةُ وَأَنْتُمْ تَنْظُرُونَ(٥٥) ثُمَّ بَعَثْنَاكُمْ مِنْ بَعْدِ مَوْتِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ(٥٦)**

- *««ሙሳ ሆይ! አላህን በግልጽ እስከምናይ ድረስ ላንተ በፍጹም አናምንልህም» በላችሁም ጊዜ (አስታውሱ)፡፡ እናንተም እየተመለከታችሁ መብረቅ ያዘቻችሁ፡፡ ከዚያም ታመሰግኑ ዘንድ ከሞታችሁ በኋላ አስነሳናችሁ፡፡* » (2፡55-56)

**يَسْأَلُكَ أَهْلُ الْكِتَابِ أَنْ تُنَزِّلَ عَلَيْهِمْ كِتَابًا مِنَ السَّمَاءِ فَقَدْ سَأَلُوا مُوسَىٰ أَكْبَرَ مِنْ ذَٰلِكَ فَقَالُوا أَرِنَا اللَّهَ جَهْرَةً فَأَخَذَتْهُمُ الصَّاعِقَةُ بِظُلْمِهِمْ**

*የመጽሐፉ ሰዎች በነሱ ላይ ከሰማይ መጽሐፍን እንድታወርድ ይጠይቁሃል፡፡ ከዚያም የከበደን (ነገር) ሙሳን በእርግጥ ጠይቀዋል፡፡ «አላህንም በግልጽ አሳየን» ብለዋል፡፡ በበደላቸውም መብረቅ ያዘቻቸው፡፡*

(4፡153)

**وَقَالَ الَّذِينَ لَا يَرْجُونَ لِقَاءَنَا لَوْلَا أُنْزِلَ عَلَيْنَا الْمَلَائِكَةُ أَوْ نَرَىٰ رَبَّنَا لَقَدِ اسْتَكْبَرُوا فِي أَنْفُسِهِمْ وَعَتَوْا عُتُوًّا كَبِيرًا(٢١)**

- *«እነዚያም መገናኘታችንን የማይፈሩት በእኛ ላይ ለምን መላእክት አልወረደም፡፡ ወይም ጌታችንን ለምን አናይም አሉ፡ በነፍሶቻቸው ውስጥ በእርግጥ ኮሩ፡፡ ታላቅንም አመጽ አመፁ፡፡* » (25፡21)

- **وَلَمَّا جَاءَ مُوسَىٰ لِمِيقَاتِنَا وَكَلَّمَهُ رَبُّهُ قَالَ رَبِّ أَرِنِي أَنْظُرْ إِلَيْكَ قَالَ لَنْ تَرَانِي وَلَٰكِنِ انْظُرْ إِلَى الْجَبَلِ فَإِنِ اسْتَقَرَّ مَكَانَهُ فَسَوْفَ تَرَانِي فَلَمَّا تَجَلَّىٰ رَبُّهُ لِلْجَبَلِ جَعَلَهُ دَكًّا وَخَرَّ مُوسَىٰ صَعِقًا فَلَمَّا أَفَاقَ قَالَ سُبْحَانَكَ تُبْتُ إِلَيْكَ وَأَنَا أَوَّلُ الْمُؤْمِنِينَ(١٤٣)**

- «*ሙሳም ለቀጠሯችን በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፦ «ጌታዬ ሆይ! (ነፍስህን) አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና» አለ፡፡ (አላህም)፦ «በፍጹም ልታየኝም ግን ወደ ተራራው ተመልከት፡፡ በስፍራውም ቢረጋ በእርግጥ ታየኛለህ» አለው፡፡ ጌታው ለተራራው በተገለጸ ጊዜ እንኩትኩት አደረገው፡፡ ሙሳም ጮሆ ወደቀ፡፡ በአንሰራራም ጊዜ «ጥራት ይገባህ፡፡ ወዳንተ ተመለስኩ፡፡ እኔም የምእምናን መጀመሪያ ነኝ» አለ፡፡*» (7፡143)

አላህን ማየት ለነቢያቱና ለአላህ መልዕክተኛ (ዐ.ሰ) የማይቻል ከሆነ ለሌሎችም ሰዎች በዚህ ዓለምም ሆነ በወዲያኛው ዓለም የማይቻል ነገር ነው ማለት ነው፡፡

በምክንያታዊ (አመንክዮያዊ) አስተሳሰብ መሠረት አንድን ነገር ለማየት ያ ነገር የተለያዩ ባህርያትና ግብአቶች ሊኖረው ይገባል፡፡ በመጀመሪያ የተወሰነ አቅጣጫ ሊኖረው ይገባል፡፡ ለምሳሌ የሚታየው ነገር በተመልካቹ ፊት ለፊት ወይም በቀኝ በኩል ወይም በግራ በኩል መሆን አለበት፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በተመልካቹና በሚታየው ነገር መካከል የተወሰነ ርቀት መኖር አለበት፡፡ ርቀት ካጠረ ወይም ከረዘመ ማየት የማይቻል ይሆናል፡፡ ኃያሉ አላህ ወደሱ አመላክተን ወይም ለይተን ልናየው የምንችል ቦታ የያዘ ቁስ አካል አይደለም፡፡ ቅዱስ ቁርአን፡- «***እርሱም ከባሮቹ በላይ ሲኾን ሁሉን አሸናፊ ነው፡፡ በናንተም ላይ ጠባቂዎችን (መላእክት) ይልካል፡፡ አንዳችሁንም ሞት በመጣበት ጊዜ (የሞት) መልእክተኞቻችን እነርሱ (ትእዛዛትን) የማያጓድሉ ሲኾኑ ይገድሉታል፡፡***» (6፡61) እና «***ጌታቸውን ከበላያቸው ሲኾን ይፈሩታል፡፡ የታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ፡፡***» (16፡50) ቢልም

«ከበላያቸው» የሚለው ሐረግ ኃያሉ አምላክ በኃይሉ፣ በኃያልነቱ፣ በምጥቀቱና ልዕልናው ከባሮቹ በላይና የላቀ መሆኑን የሚያመለክት ነው እንጂ በቦታ፣ በአካባቢ በከፍታ ወይም በማንኛውም ፊዚካል በሆነ የተወሰነ ሥፍራና አቅጣጫ አይደለም፡፡ እንደዚህ ዓይነቶቹ ባህርያት የሱ መገለጫዎች አይደሉም፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በምዕራጅ ወቅት ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ አላህን የተጣሩት፡፡ «አንተ ራስህን በራስህ እንዳወደስከው ነህ» በሚሉ ቃላት ነበር፡፡ ነቢዩ ዩኑስም (ዐ.ሰ) ከጥልቅ ባህር ውስጥ ሆኖ ጌታውን ሲማፀን ያለው፡- «***ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ ክብር ሁሉ ለአንተ የተገባ ነው***» (2፡87) ነበር ያለው፡፡ ነቢዩ ዩኑስን (ዐ.ሰ) በተመለከተ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- «*እሱ ወደ ታች ጥልቅ ባህር ውስጥ የነበረ በመሆኑና እኔ ከፍተኛውን ዙፋን የደረስኩ በመሆኔ ብቻ ወደ አላህ በመቃረብ ረገድ ከሱ የበለጠ ከፍ አታድርጉኝ፡፡ አምላክ በአንድ ቦታና አቅጣጫ ከመወሰን የጠራና የላቀ ነውና*» ብለዋል፡፡

ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ሰዕለብ አል-የማኒ በተባለው አንድ ሰሃባው አንድ ጥያቄ ተጠይቆ ነበር፡፡ ይኸውም ዓሊ (ዐ.ሰ) ጌታውን አይቶ እንደሚያውቅና እንደማያውቅ ጠይቆት ነበር፡፡ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ሲመልስ፡- «*የማላየውን ነገር እንዴት ብዬ ነው የማመልከው?*» አለ፡፡ ጌታውን እንዴት አድርጎ እንዳየ ሲጠየቅም ሲመልስ፡- «*ዓይኖች በገሃድ እይታ አይደርሱበትም፣ ነገር ግን በእምነት እውነታ ልቦች ይደርሱበታል*» ብለው መለሱ *(ነህጀል በላጋ)*፡፡ ሰዎች በገሃድ እይታ ሊያዩዋቸው ያልቻሉ ነገር ግን በህልውናቸው የሚያምኑባቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ በአንድ ወቅት ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ)፡- «*አላህ በቂያም ቀን ይታያልን?*» የሚል ጥያቄ ተጠይቀው ነበር፡፡ መልሳቸውም፡- «*አላህ ከዚህ የጠራና የላቀ ጌታ ነው፡፡ ዓይኖች ማየት የሚችሉት ቀለምና*

*ቅርጽ ያለውን ነገር ነው፡፡ የበላይ የሆነው ጌታ ግን የቀለማትና የአካላት ፈጣሪ ነው፡፡*» የሚል ነበር፡፡

ሌሎች እንደ «እጅ» ወይም «*ፊት*» የመሳሰሉ የአላህ *መገለጫዎች ያ*ላቸው ትርጉም አሌጎሪካል (ምሳሌያዊ/ቅኔያዊ) ትርጉም ነው፡፡ የአላህ እጅ የሚያመለክተው *ኃ*ይልና *ኃ*ያልነቱን፣ ፊቱ ደግሞ የተለያዩ ነገሮችን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በአላህ አንድነትና አሃዳዊነት (ተውሂድ) የማመን የመጀመሪያው እርምጃ አላህ በአካላዊ ቅርጽ እንደማይገለጽና በጭራሽ እንደማይታይ እንዲሁም ልዩና የተለየ እንደሆነ ቁርአን «***እሱን የሚመስል አንዳችም ነገር የለም***» (42፡11) ብሎ በግልጽ እንዳስቀመጠው መረዳት ነው፡፡

## *በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት ማውረድ (ሰለዋት አላ አል-ነቢ)*

ሙስሊሞች በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት እንዲያወርዱ በቁርአን (33፡ 56) *ታ*ዘዋል፡፡ ቅዱሱ ነቢይም (ሰ.ዐ.ወ) ሙስሊሞች እንዴት ሰለዋት ማውረድ እንዳለባቸውና ሰለዋት ሲያወርዱም በርሳቸው ላይ ብቻ ሳይሆን ቤተሰባቸውን (አህለልቤይትን) ጨምረው እንደሆነ በተደጋጋሚ አሳውቀዋል፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

- «ጎደሎ የሆነ ሰለዋት በኔ ላይ አታውርዱ፡፡» ከዚያም ሰሃቦች «ጎደሎ ሰለዋት ምንድን ነው?» ብለው ጠየቁ፡፡ እሳቸውም ሲመልሱ፡- «ጎደሎ ወይም ቆራጣ ሰለዋት ማለት 'አላሁመ ሰሊ ዐላ ሙሐመድ' ብቻ ብላችሁ ስታቆሙ ነው፡፡ ማለት ያለባችሁ 'አላሁመ ሰሊ ዐላ ሙሐመድ ወ ኣሊ

ሙሐመድ' በማለት መሆን አለበት፡፡» *(የናቢዑል መወዳአ - 2፡59፣ አስ-ሰዊዕቁል መህሪቃ - ኢብን ሐጀር - ክፍል 1፣ ምዕራፍ 11)*

- «በነቢዩና አህለልቤይቱ ላይ ሰለዋት ካልተወረደ ሰላት ተቀባይነት የለውም፡፡» *(የናቢዑል መወዳ፡- 2፡59)*
- አብዱላህ ቢን አቢ ለይላን ዋቢ በማድረግ ኢማም ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወደኛ ሲመጡ እንዲህ በማለት ጠየቅናቸው፡- '*በአንቱ ላይ እንዴት ሰላምታ ማለት እንዳለብን ተምረናል፤ ነገር ግን እንዴት ነው በአንቱ ላይ ሰለዋት የምናወርደው?* ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመልሱ፡- «*አላህ ሆይ! ሙሐመድና ቤተሰቡን ባርክ፣ የኢብራሒምን ቤተሰብ እንደባረግክ ሁሉ፡፡ አንተ በእውነቱ ምሥጉንና አሸናፊ ነህና፡፡ በሙሐመድና በአህለልቤይቱ ላይ በረከትህን አውርድ፣ በኢብራሒምና በቤተሰቡ ላይ በረከትህን እንዳወረድክ ሁሉ፡፡ አንተ በእውነቱ ምሥጉንና አሸናፊ ነህና፡፡*»» *(ሰሂህ ቡኻሪ - ሐዲስ 3119፣ 4423፣ 5880፣ ሰሂህ ሙስሊም - ሐዲስ 614፣ አል-ቲርሚዚ ሐዲስ #445፣ አል-ነሳኢ - ሐዲስ #1270፣ 1271፣ 1272፣ አቡ ዳውድ - ሐዲስ #830፣ ኢብን ማጃህ - ሐዲስ #894፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምንበል - 4፡241፣ 243፣ 244፣ አል-ደረሚ - ሐዲስ #1308)*

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦቻቸውን ስለ ሰለዋት ባስተማሩ ጊዜ ቤተ-ዘራቸውን (ኣሊ ሙሐመድን) አካተው በግልጽ አስተምረዋል፡፡ ስለዚህ ሙስሊሞች የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አስተምህሮ ተቀብለው በትዕዛዙ መሠረት በነቢዩና በቤተሰባቸው (አህለልቤይት) ላይ ሰለዋት ማውረድ አለባቸው፡፡

## *ሰላት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ድርጊቶችን በተመለከተ፡-*

### *ውዱእ ሲደረግ እግር ማበስ*

የአህለልቤይት(ዐ.ሰ) ተከታዮች ቅዱስ ቁርአን የሚያስተምረውን መመሪያ በመከተል ውዱዕ በሚያደርጉበት ጊዜ እግርን ከማጠብ ይልቅ በማበስ የቁርአንን መመሪያ ይተገብራሉ፡፡ ቅዱስ ቁርአን፡-

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِذَا قُمْتُمْ إِلَى الصَّلَاةِ فَاغْسِلُوا وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى الْمَرَافِقِ وَامْسَحُوا بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى الْكَعْبَيْنِ**

«***እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርናች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁን፣ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች አብሱ፡፡***» (5፡6) በማለት ያዛልና፡፡

በውዱእ ወቅት እግሮቻቸውን በመታጠብ የውዱኡን ሥርዓት የሚያከናውኑ ሰዎች ማስረጃ የሚያደርጉት «እግሮቻችሁንም» የሚለውን ሐረግ ፊትን ከማጠብ ጋር ሲያቆራኙ የአህለልቤይት(ዐ.ሰ)ተከታዮች ግን «እግሮቻችሁንም» የሚለው ሐረግ ራስን ከማበስ ጋር የተያያዘ ነው ብለው ስለሚያምኑ እግሮች ከመታጠብ ይልቅ መታበስ አለባቸው ይላሉ፡፡ ይህንን ሐሳብ በመደገፍ ኢብን ዓባስ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰሙትን ሲናገሩ፡- በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን እግሮቻቸውን ያብሱ እንደነበሩ ያስታውሳሉ፡፡ *(ውዱእ አል-ነቢ - አል-ሸህርስታኒ)*

ያለጥርጥር ሙስሊሞች ሁሉ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን በዚሁ መልኩ ውዱእ ያደርጉ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመካከላቸው ስለነበሩ በቁርአን ትዕዛዝ መሠረት (4፡59) በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር ጉዳዩን ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለሚያቀርቡ ስምምነት ላይ ይደርሱ ነበር፡፡ በመጀመሪያው ኸሊፋ

በአቡበክር ዘመንም (11–13 ሂጅራ) ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር የነበረው፡፡ የውዱእ አደራረግን በተመለከተ በወቅቱ ልዩነትና አለመግባባት ስለመኖሩ የተዘገበ ነገር የለም፡፡ በሁለተኛው ኸሊፋ በኡመር ኢብን አል-ኸጣብ ዘመንም (13–23 ሂጅራ) ቁርአን ካዘዘው እግር ከማበስ (5፡6) ይልቅ ካልሲ ማበስ ከመፍቀዱ ሌላ ተመሳሳይ ሁኔታ ነበር፡፡ ነገር ግን የውዱእ አደራረግን በተመለከተ አለመስማማት መፈጠር የጀመረው ሦስተኛው ኸሊፋ ኡስማን ኢብን አፋን (23–35 ሂጅራ) እግርን ከማበስ ይልቅ መታጠብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነው፡፡ (ሰሂህ አል-ቡኻሪ፡ 1፡52፣ ሰሂህ ሙስሊም፡ 1፡204) አል-መተቂ አል-ሒንዲ ከንዘል ዑማል በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ *(ከንዘል ዑማል-አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ-9፡443. ሐዲስ #26890)* ሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ቢን ዐፋን የውዱእ አደራረግን በመለወጥ የመጀመሪያው ሰው እንደነበረ ጠቅሰዋል፡፡ በሰሂህ ሙስሊም (ሰሂህ ሙስሊም- 1፡207 – 208) እና በከንዘል ዑማል *(ከንዘል ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ -9፡423 - ሐዲስ #26797)* ውስጥ ዑስማን ቢን ዐፋን እራሱ እንደተናገረው በኸሊፋነቱ ዘመን ከሱ የተለየ መልኩ ውዱእ ያደርጉ የነበሩ ሰሃቦች የውዱእ አደራረጋቸውን ከነቢዩ በያዙት መሠረት እንደሆነ እንደተናገሩ መስክሯል፡፡ በሦስተኛው ኸሊፋ የተነገሩት አሥራ ሦስት ሐዲሶች አዲሱን የውዱእ አደራረግን በተመለከተ እንደሆነ ተዘግቧል፡፡ እነዚህ ሐዲሶች የሚያመለክቱት አዲስ የሆነ መንገድ ማቋቋሙን (የመፍጠሩን) ነው፡፡ እንደ ኢብን ኢቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ ያሉ ዕውቅ የሙስሊም ምሁራን *(ሸርህ ነህጀል በላጋ- ኢብን ኢቢል ሐዲድ- 1፡199 – 200)* ሦስተኛው ኸሊፋ አዳዲስ ነገሮችን በመፍጠር የታወቀ ስለነበረ ይህ አሰራር አዲስ እንዳልሆነ በወቅቱ የተለመደ የፈጠራ አካሄድ የነበረ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ቢን ዐፋን በ35 ሂጅራ ከፖለቲካና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች የተነሳ በሙስሊም አማጽያን ስለመገደሉ የታሪክ ምሁራን በአንድነት የተስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡ ነገር ግን

ሌሎች የሙስሊም ምሁራን ሦስተኛው ኸሊፋ በመጨረሻዎቹ የኸሊፋነቱ 6 ዓመታት ዘመን ውስጥ አንዳንድ ኃይማኖታዊ መመሪያዎችን አስመልክቶ ያመጣቸውን መጤ ነገሮች ከመጀመሪያውና ሁለተኛው ኸሊፋዎች አሠራር ለመለየት ነው ብለው ትንታኔ ይሰጣሉ፡፡

አብዛኛው ሙስሊሞች በኸሊፋነቱ ዘመን ዑስማን የመጀመሪያዎቹን ኸሊፋዎች የሚከተልና የነሱን መንገድ የሚያስፈጽም አድርገው ያስቡት ነበር፡፡ ሦስተኛው ኸሊፋ በሁለተኛው ኸሊፋ ዘመን የተፈጠሩ አዳዲስ ፈጠራዎችን ካስተናገዱት ሰዎች አንዱ ስለነበረ ከቀደምት ኸሊፋዎች በኃይማኖታዊም ሆነ በአዕምሮአዊ ዕውቀት ከማንም አላንስም በማለት እሱም በተራው ቀድሞ ከነበረው ፖሊሲ በመለየት እራሱን የቻለ የፖለቲካ፣ የፋይናንስና በውዱእ ወቅት እግርን መታጠብ የመሳሰሉ ኃይማኖታዊና ህገ-ነክ ጉዳዮች ማስፋፋት ጀመረ፡፡ *(ታሪክ አል-ጠበሪ - 4፡339)*

ምንም እንኳን ዛሬ አንዳንድ ሰዎች እግርን ከማበስ ይልቅ መታጠቡ ለተሻለ ንጽህናና ለበለጠ የጤና አጠባበቅ የተሻለ አድርገው ቢያስቡም ውዱእን ጨምሮ ሁሉንም የኢባዳ ህግጋትን የወሰነው አላህ እግርን የመታጠብ ወይም የማበስ ጥቅምና ጉዳት የበለጠ ያውቃል፡፡ በአንድ ወቅት ኢማም ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ)፡ «ኃይማኖት በሰው ልጅ ሐሳብ (መላምት) ቢሆን ኖሮ እግርን ከላይ ከማበስ ይልቅ ከሥሩ ማበስ የበለጠ ትክክል ይመስል ነበር፡፡ ነገር ግን የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እግራቸውን ላዩን ሲያብሱ አይቻለሁ *(አል-ሙሰነፍ - አቡ ሸይባህ - 1፡30፣ #6፣ ሱነን አቢ-ዳውድ - 1፡42፣ #164)*

***ሰላትን ማጣመር (ጀምዕ ማድረግ)***

በአንድ ቀን ውስጥ (ሌሊትና ቀን ውስጥ) አምስት ግዴታ የሆኑ ሰላቶች አንዳሉና እነዚህ ዕለታዊ አምስት ሰላቶችም የሚከናወኑበት የተወሰነ ጊዜ

እንዳላቸውና ቢያንስ አንዳንድ ጊዜ ሰላቶችን ማጣመር፤ ማለትም የዙሑር ሰላት ከተሰገደ በኋላ ወዲያው አሥርን አስከትሎ መስገድና የመግሪብ ሰላት ከተሰገደ በኋላ የኢሻዕ ሰላትን አስከትሎ መስገድ የሚቻል መሆኑን ሁሉም ሙስሊሞች ይስማሙበታል፡፡ የማሊኪ፣ የሻፊዒና ሐምበሊ መዝሐቦች በጉዞ ወቅት (በሙሳፊርነት ጊዜ) ሰላቶችን ማጣመር የተፈቀደ መሆኑን ይስማሙበታል፡፡ ነገር ግን ለሌሎች ምክንያቶችን ሰላቶችን ማጣመር አይፈቅዱም፡፡ የሐነፊ መዝሐብ ሰላቶችን ማጣመር አይፈቅዱም፡፡ የሐነፊ መዝሐብ ሰላቶችን አጣምሮ መስገድን የሚፈቅደው በአረፋት ቀን ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን የኢማሚያ ሺዓ መዝሐብ ሰላቶችን አጣምሮ መስገድን በማንኛውም ጊዜ (በጉዞ ወቅትም ሆነ ያለ ጉዞ፣ ለምክንያትም ሆነ ያለ ምክንያት - በጦርነት ወቅትም ሆነ በሰላም ጊዜ፤ በዝናብ ወቅትም ሆነ ዝናብ ሳይኖር . . . በማንኛውም ወቅት ይፈቅዳል፡፡ በዚህ ጉዳይ ያለው ክርክር የነዚህ ሰላቶች መጀመሪያና መጨረሻ ወቅት መቼ ነው የሚለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ መቀረፍ የሚችለው ወደ ቁርአንና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች በመመለስ ነው፡፡ በቁርአን ውስጥ ሦስት አንቀጾች (አያዎች) የሰላት ወቅቶችን በተመለከተ የሚሉን አላቸው፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

**أَقِمِ الصَّلَاةَ لِدُلُوكِ الشَّمْسِ إِلَىٰ غَسَقِ اللَّيْلِ وَقُرْآنَ الْفَجْرِ إِنَّ قُرْآنَ الْفَجْرِ كَانَ مَشْهُودًا(٧٨)**

«***ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ፡፡ የጎህንም ሶላት ስገድ፡፡ የጎህ ሶላት ምንጊዜም የሚመሰከርለት ነውና፡፡***» (17፡78)

«እኩለ ቀን» የሚለው የዙሑርና የአሥር ሰላቶች የሚሰገዱበት የጋራ ወቅት የሚያመለክት ሲሆን «የሌሊቱ ምሽት» ወይም «አመሻሽ ላይ» የሚለው ደግሞ የመግሪብና ኢሻዕ ሰላቶች የሚሰገዱበት የጋራ ወቅት ያመለክታል፡፡

«ንጋት» ወይም «ጎህ ሲቀድ» የሚለው ደግሞ የፈጅር (ሱቢሂ) ሰላት ወቅትን ያመለክታል፡፡ ቁርአን በቀላል ቋንቋና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለአምስቱ ሰላቶች ሦስት ጊዜያትን (ወቅቶችን) ያስቀምጣል፡፡ ሰላቶቹ አምስት ቢሆኑም በሦስት ዋና ዋና ወቅቶች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ ዕውቁ የሱኒ ምሁር ፊኽር አል-ራዚ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የቁርአን አያህ ትርጓሜ የተረዱት በዚሁ መልክ ነበር *(ተፍሲር፡-5፡428)*፡፡ በእርግጥ ሰላቶቹ በቅደም ተከተላቸው መሰገድ አለባቸው፡፡ ይኸውም የዙሑር ሰላት መሰገድ ያለበት ከአሥር ሰላት በፊት እንዲሁም የመግሪብ ሰላት መሰገድ ያለበት ከኢሻዕ ሰላት በፊት መሆን አለበት፡፡
ቅዱስ ቁርአን በተጨማሪም እንዲህ ይላል፡-

**وَأَقِمِ الصَّلَاةَ طَرَفَيِ النَّهَارِ وَزُلَفًا مِنَ اللَّيْلِ إِنَّ الْحَسَنَاتِ يُذْهِبْنَ السَّيِّئَاتِ ذَٰلِكَ ذِكْرَىٰ لِلذَّاكِرِينَ(١١٤)**

«***ሰላትንም በቀን ሁለቱ ጫፎችና ከሌሊትም የተወሰኑ ሰዓታት ፈጽም፡፡ መልካም ሥራዎች ኃጢአቶችን ያስወግዳሉና፡፡ ይህ ለተገሳጮች ግሳጼ ነው፡፡***» (11፡114)

ይህ የቁርአን አንቀጽ የሚያወሳው ስለ አምስቱ የግዴታ ሰላቶችና የሚሰገዱበት የተሰወሰነ ጊዜ ማለትም ሦስት ዋና ዋና ጊዜያት እንደሆነ የሙስሊም የህግ ጠበብትና የቁርአን ሙፈሲሮች ይስማሙበታል፡፡ ይኸውም ከነዚህ ሦስቱ ወቅቶች ሁለቱ «በቀኑ መጨረሻዎች» እና ሌላኛውም ደግሞ «ከሌሊት የተወሰኑ ሰዓታት» ናቸው፡፡ የመጀመሪያው «የቀኑ መጨረሻ» የፈጅር ሰላቶች ወቅት ሲሆን ሁለተኛው «የቀኑ መጨረሻ» ደግሞ ከእኩለ ቀን ጀምሮ በጸሐይ መጥለቅ የሚጠናቀቅ ሲሆን የዙሑርና አሥር ሰላት ወቅትን የሚያካትት ነው፡፡ «ከሌሊቱ ሰዓታት» የሚለው ደግሞ የመግሪብና የኢሻዕ ሰላቶች የሚሰገዱበት

ጊዜ ሲሆን ከሌሊት መጀመሪያ አንስቶ እስከ እኩለ ሌሊት የሚዘልቀው ጊዜ ነው፡፡

በሦስተኛው የቁርአን አንቀጽም ተመሳሳይ የጊዜ ክፍፍልን እናገኛለን፡፡ ይኸውም፡-

**فَاصْبِرْ عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ قَبْلَ طُلُوعِ الشَّمْسِ وَقَبْلَ الْغُرُوبِ(٣٩) وَمِنَ اللَّيْلِ فَسَبِّحْهُ وَأَدْبَارَ السُّجُودِ(٤٠)**

«***በሚሉትም ላይ ታገሥ፤ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊትና ከመግባቷም በፊት ጌታህንም ከማመስገን ጋር አወድሰው፡፡ ከሌሊቱም ክፍል አወድሰው ከስግደቶችም በኋላ (አወድሰው)፡፡***» (50፡39-40)

ቀደም ሲል እንደጠቀሱት አናቅጽ ሁሉ ይህ አያም ለአምስቱ የግዴታ ሰላቶች ጊዜያትን የሚያከፋፍልና በዚህኛውም አንቀጽ መሠረት ወቅቶቹ በሦስት እንደሚከፈሉ ሙፈሲሮቹና የፊቂህ ጠበብቶች ይስማሙበታል፡፡ የመጀመሪያው ወቅት ጎህ ከቀደደ በኋላ እስከ ፀሐይ መውጫ ያለው ሲሆን ይህም የንጋት ሰላቶች መስገጃ ወቅት ነው፡፡ ሁለተኛው ወቅት ደግሞ ከእኩለ ቀን እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ያለው ሲሆን ይህ ደግሞ የእኩለ ቀን ሰላት (ዙሑር) እና የቀትር በኋላ ሰላት (ዐሥር) መስገጃ ወቅት ነው፡፡ «ከሌሊት ወቅት» ወይም «ከክፍለ ሌሊቱ» የተባለው ደግሞ ከፀሐይ ግባት እስከ እኩለ ሌሊት የሚቆይ ሲሆን የምሽት ሰላትና (መግሪብ) የሌሊት ሰላት (ኢሻዕ) የሚሰግድበት ወቅት ነው፡፡ «እንዲሁም ከሰላቶቹ በኋላ» የሚለውን ደግሞ ሙፈሲሮች የሱና ሰላቶች (ነዋፍል) አሊያም የሌሊት ሱና ሰላቶች (ሰላት አል-ለይል) እንደሆነ ዘግበዋል፡፡ ነዋፍልና ሰላት አል-ለይል ከግዴታ ሰላቶች ቀጥሎ እጅግ የሚበረታቱ ሰላቶች ናቸው፡፡

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላታቸውን በነዚህ ሦስቱ ወቅቶች ውስጥ አጣምረው ይሰግዱ እንደነበረ ኢማም ቡኻሪና ሌሎችም ዘግበዋል፡፡

***«የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የዙሑርና ዐሥር ሰላቶችን አጣምረው እንዲሁም የመግሪብና ኢሻዕ ሰላቶችን አንድ ላይ አድርገው ያለ ምንም የፍራቻ ጊዜና በጉዞ ላይ ሳይሆኑ ሰግደዋል፡፡»*** *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አውቃት አስ-ሰላት ሐዲስ #529፣ ኪታብ ሰላቱል ጁሙዓ - ሐዲስ #1103፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ ሰላቱል ሙሳፍር - ሐዲስ 1146፣ አል-ቲርሚዚ - ኪታብ አስ-ሰላት - ሐዲስ #172፣ አል-ኒሳኢ - ኪታብ አል-አውቃት - ሐዲስ #585፣ #597፣ #598፣ #599፣ አቡ ዳውድ - ኪታብ አስ-ሰላት - ሐዲስ #1024፣ #1025፣ #1027፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 1፡217፣ 221፣ 223፣ 251፣ 273፣ 283፣ 285፣ 346፣ 351፣ 354፣ 360፣ ማሊክ - ኪታብ ተቅሲር አስ-ሰላት ፊ አስ-ሰፈር - ሐዲስ #300)*፡፡

ኢማም ሙስሊምም ተመሳሳይ ሐዲስ ከተረከ በኋላ በተጨማሪ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላቶችን ማጣመር ለምን እንደፈቀዱ በኢብን ዓባስ ሲጠየቁ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በህዝባቸው ላይ ችግር ላለመፍጠርና ላለመጨናነቅ እንደሆነ መልሰውለታል፡፡ *(ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ ሰላቱል ሙሳፊሪን፣ ምዕ. 6#50 – 54)* በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ኢብን ዓባስ ራሱ ሲተርክ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ሰላቶችን ጀምዕ አድርገው (አጣምረው) ይሰግዱ እንደነበረ ጠቅሷል፡፡ ስለዚህ ቁርአንም ሆነ የነቢዩ ሐዲስ የሚያሳዩት ሰላቶችን አጣምሮ መስገድ የተፈቀደና ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተያዘ መሆኑንና ያለ ምንም ምክንያት ጀምዕ ማድረግ እንደሚቻልና አላህ በምህረቱ ኃይማኖቱን ለምዕምናኑ ገር እንዳደረገ እንረዳለን፡፡

## *አዛንና ሀያ ዐላ ኸይረል ዐመል (ወደበለጠ /ወደ የተሻለ) ተግባር ኑ*

ሙሉውን የአዛን አባባሎች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተማሩት ከአላህ ሲሆን ይህም የሆነው ወደ ሰማይ ያረጉ ጊዜ ነው፡፡ ሰላቶች ግዴታ ሆነው የተደነገጉትም

በዚሁ በምዕራጅ ሌሊት ነው፡፡ በሌላ አባባል ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአዛን አደራረግን በቀጥታ ከአላህ ይዘውት የመጡት ነገር ነው ማለት፡፡ *(ከንዝል ኡማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ - 6፡397፣ አል-ሙስተድረክ አል-ሐኪም - 3፡171)*፡፡

ነቢዩ ባስተማሩት የመጀመሪያው (ኦሪጂናል) አዛን ውስጥ ደግሞ «ሐያ ዐላ ኸይረል ዐመል» የሚለው ሐረግ ነበረበት፡፡ ነገር ግን ኢስላማዊ መንግሥት እየተስፋፋ በነበረበት ወቅት ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ቢን ኸጣብ ይህ አባባል ሰዎችን ከጂሃድ (ትግል) ያዘናጋል ብሎ ስላሰበ ከአዛን እንዲወጣ አደረገ፡፡ ኢማም ሙስሊም ኢብን መስዑድን በመጥቀስ እንደዘገበው ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የአዛንና ዒቃማ አደራረግን ሲያስተምሩ «ሐያ ዐላ ኸይረል ዐመል» የሚል ነበረበት፡፡ ነገር ግን ዑመር ስልጣን ላይ በሆነ ጊዜ ይህንን አባባል ለማስቀረት ችሏል *(ሰሂህ ሙስሊም 1፡48)*፡፡

ሙስሊም በተጨማሪ ሲተርክ ዓሊይ ቢን አቢ ጧሊብና ተከታዮቹ እንዲሁም አብደላህ ቢን ዑመር ይህንን ሐረግ ትተውት እንደማያውቁ ጠቅሷል *(አል-ሲራ ሐለቢያ)፡፡*

ዑመር ቢን አል-ኸጣብ ራሳቸው «ሰዎች ሆይ! በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ ይተገበሩ የነበሩና እኔ ግን አሁን ክልክል ያደረግኳቸውና ሲሰሩ ባይ የቅጣት ፍርድ የማስተላልፍባቸው ሦስት ነገሮች አሉ፡፡ እነዚህም ሙተዐተል ሐጅ፣ ሙተዐተል ኒሳእ እና ሐያ ዐላ ኸይረል ዐመል ናቸው» ብለዋል፡፡ *(ሸርህ አል-ተጅሪድ - ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 1፡49)*

በተጨማሪም ማሊክ ኢብን አነስ በዘገቡት መሠረት አንድ ቀን ሙዐዝኑ (አዛን የሚያደርግ ሰው) ወደ ዑመር ቢን አል-ኸጣብ መጥቶ ለሱብሂ ሰላት አዛን ሊያደርግ ሲል ዑመርን እንቅልፍ ውስጥ ስላገኘው «አስ-ሰላቱ ኸይሩን ሚን አል-ነውም (ሰላት ከእንቅልፍ የበለጠ የተሻለ ነው) በማለቱ ዑመር ይህንን

አባባል ስለወደደ በሱብሂ ሰላቶች ጥሪ (አዛን) ውስጥ እንዲካተት አደረገ። *(ማሊክ ቢን አነስ-ኪታብ አል-ሙወጠዕ)* ኢማም ሙስሊምና አቡ ዳውድ ይህ አባባል በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን በአዛን ውስጥ እንዳልነበረ ይስማማሉ። ቲርሚዚም በዑመር የተጨመረ መሆኑን ያረጋግጣል። *(ሱነን አል-ቲርሚዚ - 1፡64)*

ሺዓዎች ከሁለቱ ሸሃዳዎች በኋላ «አሽሐዱ አነ ዓሊየን ወልዩላህ» የሚል አባባል ለምን እንደሚጨምሩ ብዙ ሰዎች ይገረማሉ። ሁሉም የሺዓ ምሁራን ይህ አባባል በአዛን ውስጥ ግዴታ እንዳልሆነ ያስቀምጣሉ። ነገር ግን ይህ የተጀመረው ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊይን ኸሊፋቸው አድርገው በመረጡበት ዕለት በገዲር ላይ የተጀመረ መሆኑን ያምናሉ።
ሙስሊሞቹ በገዲር ላይ ለዓሊይ ኸሊፋነት የምስክርነት ድምጻቸውን ከሰጡ በኋላ (በይዓ ካደረጉ በኋላ) አቡ ዘር አል-ጊፋሪ አዛን ሲያደርግ «አሽሐዱ አነ ዓሊየን ወቢዩላህ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር ጨመረ። በዚህ ጊዜ ሰዎች ወደ ነቢዩ መጥተው አዲስ ነገር እንደሰሙ ነገሯቸው። ምን አዲስ ነገር እንደሰሙ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲጠይቋቸው «አሽሐዱ አነ ዓሊየን ወሊዩላህ» የሚለውን ዐረፍተ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሰሙ ተናገሩ። በዚህ ጊዜ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓሊይ ኸሊፋ በይዓ በገቡ ጊዜ ይህንኑን አባባል ቀደም ሲል አልመሰከራችሁም ወይ ብለው ጥያቄያውን በጥያቄ መለሱ። ሺዓዎች ይህንን በአዛናቸው ውስጥ የሚጨምሩት እንደ የሚበረታታ ነገር አድርገው እንጂ እንደ ግዴታ ቆጥረውት አይደለም። ይህ አባባል ግዴታ የሆነ የአዛን ክፍል ነው ብሎ በማመን የሚያደርግ ሰው አዛኑ ተቀባይነት የሌለው (ባጢል) ይሆናል።

*በሰላት ውስጥ እጆችን ማጣመር (ተክፊር)*

*‘ተክፊር’* የሚለው ቃል ‘መሸፈን’ ከሚለው የአረብኛ ቃል የመጣ ሲሆን እጆችን በማጣመር ደረት ላይ ማድረግ ደረትን ስለሚሸፍን ይህ ሁኔታ ተክፊር በመባል ይታወቃል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሰላታችሁን እኔ ስሰግድ እንዳያችሁኝ አድርጋችሁ ስገዱ፡፡» በኢማሚያ መዝሐብ መሠረት እጅ አጣምሮ (በደረት ላይ አድርጎ) መስገድ ሰላት ያበላሻል፡፡ ምክንያቱም ይህ የመጁሲዎች ባህል እንደሆነ ስለሚታወቅ ነው፡፡ አል-ካፊ-አል-ከኩለይኒ-3፡ 336፣አል-ተዕዚብ-2፡84፣2፡309)

በሐነፊና በሻፊዒ መዝሐቦች እጆችን ማጣመር የተወደደ (ሙስተሐብ) ነው፡፡ የሻፊዒ መዝሐብ የቀኝ እጅን በግራ እጅ ላይ በማድረግ ከሆድ በላይ ባለው ክፍል ላይ ማድረግ ነው ሲል የሐነፊ መዝሐብ ደግሞ እጆችን ከሆድ በታች አጣምሮ መያዝ ነው ይላል፡፡

*ሰላት ተሰግዶ ሲያልቅ በሦስት ተክቢራ ማጠናቀቅ (ሰላትን ሦስት ጊዜ ‘አላሁ አክበር’ በማለት ማጠናቀቅ)*

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላት የሚያጠናቅቁት በሦስት ተክቢራዎች ነበር፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ኢማም ሙስሊም ኢብን አባስን በመጥቀስ ሲዘግብ «ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላት ማጠናቀቃቸውን የምናውቀው ሦስት ጊዜ ተክቢራ ሲያሰሙ ነበር፡፡» *(ሰሂህ ሙስሊም - 1፡219)*

*አፈር ላይ ሱጁድ ማድረግ*

አፈር ላይ ሱጁድ ማድረግ በምንም መልኩ ያንን ሱጁድ በላዩ ላይ የሚደረግበትን ድንጋይ ወይም አፈር ማምለክ ተብሎ መታሰብ አይችልም፡፡

እንደ አንድ ተግባር በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥ ጠንካራ መሠረት አለው፡፡ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) በሁሉም አኳያ እንድንከተላቸው ደግሞ ቁርአን በጽኑ ያዘናል፡፡ ኢማም ቡኻሪ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን እንደተናገሩ ዘግቧል፡- «ከኔ በፊት በማንም ነቢይ ያልተሰጠ አምስት ነገሮች ተሰጥቻለሁ፡- እያንዳንዱ ነቢይ የተላከው ወደየራሱ ህዝብ ነው፣ እኔ ግን የተላክኩት ለነጭም ሆነ ለጥቁር ለሁሉም ህዝቦች ነው፡፡ ከጦርነት የሚገኝ ምርኮ ለኔ የተፈቀደልኝ ሲሆን ከኔ በፊት ለማንም አልተፈቀደም ነበር፡፡ መሬት ንጹህና የሱጁድ ማድረጊያ ቦታ ሆኖልኛል፡፡ ስለዚህ የሰላት ወቅት በደረሰ ጊዜ ሁሉም ሰው ባለበት ሆኖ መስገድ ይችላል፤ ጠላት የአንድ ወር ያህል መንገድ ርቀት ላይ እንኳን ሆኖ እንዲፈራኝና እንዲርበተበት የሚያደርግ ግርማ ሞገስ አጎናጽፎኛል፡፡ እንዲሁም የሸፊዓ (አማላጅ የመሆን) ዋስትና ተሰጥቶኛል፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - በአፈር ወይም በአሸዋ ውዱዕ ስለማድረግ የሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ #323፣ ሰላት - ሐዲስ #419፣ ኹሙስ - ሐዲስ #2890፣ ሰሂህ ሙስሊም - ስለ መስጂዶችና የመስገጃ ቦታዎች - ሐዲስ #810፣ አል-ኒሳኢ - ውዱእና ተየሙም - ሐዲስ #429፣ መስጂዶች - ሐዲስ #728፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል፣ 3፡305፣ አል-ዳረሚ - ሰላት - ሐዲስ #1353)*

እነዚህ ሐዲሶች በግልጽ እንደሚያስቀምጡት መሬት (አፈር፣ አቧራ ወይም ድንጋይ) የሱጁድ ማድረጊያ ቦታዎች እንደሆኑ ነው፡፡ የኢስላምና የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ታሪክ እንደሚያሳየን በመዲና የነበረው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ በጊዜው የተለያዩ እንጨቶች፣ ምንጣፍና ሌሎች ማሳመሪያ መሣሪያዎች ቢኖሩም መስጂዱ አፈር ብቻ የተነጠፈ ነበር፡፡ መስጂዱ ምንም ዓይነት ስጋጃ ወይም ምንጣፍ ስላልነበረው ዝናብ በሚጥልበት ወቅት ጭቃ ይሆን ነበር፡፡ ይህ በሆነበት ወቅትም ሙስሊሞች ምንም ዓይነት የሚነጠፍ ነገር ሳያነጥፉ ጭቃው ላይ ይሰግዱ ነበር፡፡ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ የነበረው አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ ያየውን ሲተርክ፡- «በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) አፍንጫ

ላይ የዝናብ ምልክትና ጭቃ በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ» በማለት ተናግሯል፡፡ ኢማም ቡኻሪ ከዘገቡት ሐዲስ ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላት በክፍላቸው በሚሰግዱበት ወቅት 'በኹምራ' (ጠጠር የሆነ የአፈር ጭብጥ ወይም ገለባ ነገር) ላይ ይሰግዱ እንደነበረ ጠቅሷል፡፡ እንዲህ ይተረካል፡- »የአላህ መልዕክተኛ በሚሰግዱበት ወቅት እኔ (ከነቢዩ ባለቤቶች አንዷ) አጠገባቸው ጋደም ብዬ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት የወር አበባዬን ባየሁበት ጊዜ ነበር፡፡ ሱጁድ ሲወርዱ አንዳንዴ ልብሳቸው ይነካኛል፡፡ ሱጁድ ያደርጉ የነበረውም በኹምራ ላይ ነበር« *(ሰሂህ ቡኻሪ - የወር አበባ - ሐዲስ #321፣ ሰላት - ሐዲስ #366፣ 487፣ 488፤ ሰሂህ ሙስሊም - ሰላት - ሐዲስ #797፤ አል-ኒሳኢ - መስጂዶች - ሐዲስ #730፣ አቡ ዳውድ - ሰላት - ሐዲስ #560፣ ኢብን ማጃህ - አዛን/ኢቃማ - ሐዲስ #1018፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 6፡330፣ 331፣ 335፣ 336፤ አል-ዳረሚ - ሰላት - ሐዲስ 1338)*፡፡

ሌላኛዋ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት ስትተርክ ደግሞ፡- «ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱጁድ የሚያደርጉበት ወቅት ፊታቸውን ከአፈር ሲከላከሉ ፍጹም አይቼ አላውቅም» ብላለች *(ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 6፡58፤ ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ - 4፡212)*፡፡

በተጨማሪም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች አንዱ የነበረው ዋኢል ሲናገር፡- «*ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱጁድ በሚያደርጉበት ወቅት ግንባራቸውን መሬት (አፈር) እንደሚያስነኩ አይቻለሁ*» ብሏል *(አህካም አል-ቁርአን - አል-ጀሳን - 3፡36፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 4፡315)*፡፡

ሌሎች ሐዲሶች ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦቻቸውን ከመሬት ላይ ውጭ በሌሎች ነገሮች ላይ ሱጁድ እንዳያደርጉ ይከለክሉ እንደነበረ ይጠቅሳሉ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ሰው በጨርቅ ላይ ሱጁድ ሲያደርግ ተመለከቱት፡፡

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰውየው በማመልከት ጨርቁን እንዲያስወግድና ግንባሩን በመሬት ላይ እንዲያስነካ ነገሩት *(ሱነን አል-በይሐቂ - 2፡105፣ አል-ኢሳባህ ሊ መዓሪፈቲል ሰሃባህ - ኢብን ሐጀር - 2፡201)*፡፡

እጅግ ጠራራ በሆነ ጊዜና መሬት በጣም ይሞቅ በነበረበት ወቅት እንኳ የአላህ መልዕክተኛና (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦቻቸው በመሬት ላይ ሱጁድ ያደርጉ ነበር፡፡ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላቅ ሰሃባ የነበረው ጃቢር ቢን አብደላህ ሲናገር፡- «*የዙሑር ሰላትን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር እሰግድ ነበር፡፡ በወቅቱ ከፍተኛ ሙቀት ስለነበረ ጠጠር ለቅሜ እያቀዘቀዝኩ በዛ ላይ ሱጁድ አደርግ ነበር*» ብሏል *(ሰሂህ አል-ኒሳኢ፡ 2፡ 204፣ ሱነን አል-በይሐቂ - 1፡439፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል 3፡327)*፡፡

ሌላኛው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ አነስ ኢብን ማሊክ ሲናገር ደግሞ፡- «*የሙቀት መጠን ከፍተኛ በሆነበት ወቅት ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር እንሰግድ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ጠጠር እንለቅምና ካቀዘቀዝን በኋላ በጠጠሮቹ ላይ ሱጁድ እናደርግ ነበር*» *(ሱነን አል-በይሐቂ - 2፡105፣ ነይለል አውጣር 2፡268)*፡፡

ሌላኛው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ አል-ኸባብ ቢን አረት ደግሞ፡- «*ስለ መሬት ከፍተኛ ሙቀትና ሱጁድ በሚናደርግበት ጊዜ በግንባራችንና በመዳፋችን ላይ ስለሚደርሰው ጉዳት ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቤቱታ አቀረብን፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ግን መሬቱ ላይ መስገዱን እንድንቀጥልበት እንጂ ሌላ ማሻሻያ አልሰጡንም*» በማለት ተናግሯል፡፡ *(ሱነን አል-በይሐቂ - 2፡106)* ፡፡

ሌላኛው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ አቡ ዑበይዳ ሲናገር ሰሃባው ኢብን መስዑድ ከመሬት ላይ በስተቀር ሌላ ነገር ላይ ሱጁድ አድርጎ እንደማያውቅ ይተርካል፡፡ (መጅመዕ አዝ-ዘዋኢድ - 2፡57) ኢባዳ ኢብን ሳሚት የተባለው ሰሃባ ደግሞ ግንባሩ መሬት ይነካ ዘንድ ጥምጣሙን ወደኋላ ያደርግ እንደነበረ ይነገራል *(ሱነን አል-ኩብራ - አል-በይሐቂ - 2፡105)* ፡፡

በመጀመሪያው፣ በሁለተኛው፣ በሦስተኛውና አራተኛው ኸሊፋዎች ዘመን ሙስሊሞች ሱጁድ የሚያደርጉት በአፈር ላይ ነበር፡፡ አቡ ኡመያህ እንደተረከው የመጀመሪያው ኸሊፋ አቡ በክር በአፈር ላይ ሱጁድ ያደርጉና ይሰግዱ እንደነበር ይታወቃል *(ከንዝ - አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ - 4፡212፤ ሱነን አል-ኩብራ - አል-በይሐቂ - ቅጽ 2)*፡፡
መሬት ላይ ሱጁድ ማድረግ የታቢኢኖች (ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለማየት ያልበቁ ነገር ግን ሰሃቦችን የተገናኙ) ሱናም ነበር፡፡ ታዋቂ ታቢኢና ቅን የህግ ምሁር የነበረውና የአብደላህ ኢብን መስዑድ ተማሪ የነበረው መስሩቅ ቢን አጅዳ ከመዲና ጭቃ ወስዶ በመጠፍጠፍ የሱጁድ ማድረጊያ ቱርባ ሠርቶ እንደነበረና በሄደበት ሁሉ (በተለይም በመርከብ ጉዞ ሲያደርግ) ይዞ ይሄድ እንደነበረ ተወስቷል *(አል-ጠበቃት አል-ኩብራ - ኢብን ሰዕድ - 6፡53)*፡፡
ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እጅግ ቅርብ የነበሩት አህለልቤይትም (ዐ.ሰ) አፈር ላይ ሱጁድ የማድረግ ተግባርን በተመለከተ ጽኑ አቋም ነበራቸው፡፡ ይህንን በማድረግም የአያታቸውን የቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና ተከትለዋል ማለት ነው፡፡ የአህለል ቤይት (ዐ.ሰ) መዝሐብ ስድስተኛው ኢማም የሆኑት ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ ሲናገሩ፡- «*ሱጁድ በአፈር ላይና በመሬት ላይ የሚበቅሉ ነገሮች (የሚበሉ ነገሮችና ጥጥ ሲቀር) ካልሆነ በስተቀር ተቀባይነት የለውም*» *(ወሳኢል - አሽ-ሺዓ 3፡592)*፡፡ በግንባር ፋንታ ጥምጣም መሬት ቢነካ ተቀባይነት ይኖረው ይሆን ብለው ሲጠይቋቸው ግንባር መሬት ካልነካ በስተቀር በቂ እንደማይሆን (ተቀባይነት እንደሌለው) አበክረው ተናግረዋል *(ወሳኢል አሽ-ሺዓ - 3፡592)*፡፡ የሳቸው ሰሃባና ተማሪ የነበረው ሂሻም ቢን አል-ሐከም በሱጁድ ወቅት ሰባቱ ቦታዎች (ግንባር፣ እጆች፣ ጉልበቶችና የእግር ጣቶች) በሙሉ መሬት መንካት አለባቸው ወይ ብሎ በጠየቀ ጊዜ ግንባር መሬት እስከነካ ድረስ ሌሎቹ ስድስት

የሰውነት ክፍሎች መሬት መንካታቸው አስፈላጊ አይደለም በማለት መልሰዋል፡፡ ስለዚህ ግንባር መሬት እስከነካ ድረስ ሰዎች መስገጃዎችና ምንጣፎች መጠቀም ይችላሉ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ግንባርን በጨርቅ፣ ምንጣፍ፣ ናይሎን፣ የሱፍ ልብስ፣ … የመሳሰሉ ቀጥተኛ የመሬት ውጤት ያልሆኑ (ለምግብነት የሚውሉና ለልብስ የሚውሉ ነገሮች ሲቀሩ) ነገሮች ላይ ሱጁድ ማድረግ መሬት (አፈር) ላይ እንደማድረግ አይቆጠርም፡፡

የሱጁድ ተቀባይነት ከማግኘት ጉዳይ ባሻገር አፈር ላይ መስገድ ለአንድ አማኝ ጠቃሚ ትምህርትም አስፈላጊ የሆነ ጥቆማ ይሰጣል፡፡ ሱጁድ ማድረግ በራሱ በአላህ ፊት የመተናነስና ከኃያሉ አምላክ ፊት ኢምንት እንደሆንን መግለጫ ነው፡፡ ይህ ተግባር አፈር ላይ ሲሆን ደግሞ ምንጣፎች ላይ ከመስገድ ይልቅ የበለጠ ተጽዕኖ አለው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- «*ፊቶቻችሁን አቧራማ አድርጉ፤ አፍንጫችሁንም በአቧራ ሸፍኑ*» ብለዋል *(አል-ተግሪብ ወል ተህሪብ -1፡581)*፡፡

ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ መሬት ላይ ከመስገድ ጀርባ ያለውን ጥበብ ወይም ፍልስፍና ሲጠየቁ፡- *»ምክንያቱም ሱጁድ ማድረግ ማለት ለአላህ እጅ የመስጠትና በኃያሉ ፊት የመተናነስ መገለጫ ስለሆነ ነው፡፡ ስለዚህ በሚለበስና በሚበላ ነገር ላይ ሱጁድ መደረግ የለበትም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ለሚበሉትና ለሚለብሱት ነገር ባሪያዎች ናቸው፡፡ ሱጁድ ደግሞ አላህን መገዛት ነው፡፡ ስለዚህ አንድ ሰጋጅ በሱጁድ ወቅት ሰዎች በሚያመልኩት ነገር ላይ (ምግብና ልብስ) እና በሚያታልላቸው ነገር ላይ ሱጁድ ማድረግ የለበትም« (ወሳኢል አሽ-ሺዓ - 3፡591)* ፡፡

ነገር ግን ሀሉም ህግ የራሱ የሆነ አፍራሽ ሁኔታ (exception) አለው፡፡ በአንዳንድ ሐዲሶች መሠረት በእሥር ውስጥ ወይም እንደ መርከብ፣ አውሮፕላን የመሳሰሉ ቦታዎችና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ምንም ባዶ መሬት፣ አፈር፣ እንጨት ወይም ቅጠል፣ ወይም ወረቀት በማይገኝበት ቦታ ከሆነ በልብሶቻቸው ጫፍ ላይ ወይም በምንጣፍ ላይ ሱጁድ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ይኸውም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «በሰው ልጅ ላይ ሐራም (ክልክል) ከሆኑ ነገሮች ሁሉ አስገዳጅ ነገር ሲኖርና በችግር ጊዜ አላህ ሐላል (የተፈቀደ) ያላደረገው ነገር የለም፡፡»

## *በከርበላ አፈር ላይ ለምን ሱጁድ ይደረጋል?*

የአህለልቤይት(ዐ.ሰ) ተከታዮች የኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ታላቁ መስዋዕት መዘከሪያና ማስታወሻ በሆነው በከርበላ አፈር (ቱርባ) ላይ ሱጁድ ማድረግን ይመርጣሉ፡፡ ከኢማም ሁሴይን መመሪያዎችና ኢስላምን ከሙስናና ብልሹ አመራር፣ ከውድቀትና ከአምባገነኖች ጥፋትና ጭቆና ለማዳን ካደረጉት ታላቅ ንቅናቄ በላይ አፈሩን አያገዝፉም፡፡

ብዙ የአህለልቤይት ኢማሞች(ዐ.ሰ) ባሉት መሠረት በከርበላ አፈር ላይ ሱጁድ ማድረግ በሰጋጁና በኃያሉ አላህ መካከል ያለውን ሰባቱን መጋረጃዎች ጥሶ እንደሚያልፍ ተናግረዋል፡፡

በተፈጥሮአዊ ጥበብ አንፃርም ሲታይ አንዳንድ ቦታዎች (ምድሮች) ከሌላው እንደሚበልጡና እንደሚሻሉ ይታወቃል፡፡ ይህ እውነታ ደግሞ ኖርማል፣ ምክንያታዊና ሁሉም ህዝቦች፣ መንግሥታት፣ ባለስልጣናትና ኃይማኖቶች የተስማሙበት ነገር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከኃያሉ አምላክ ጋር የተያያዙ

ቦታዎችና ግንባታዎች ሁኔታ ይኸው ነው፡፡ መብታቸው፣ ግዴታቸውና ደረጃቸው የተወሰነና የተጠበቀ የሆነ ልዩ ቦታ ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ በመዲና ያለው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጂድ የራሱ የሆነ ደረጃና ቦታ እንዳለው ሁሉ ካዕባም የራሱ የሆነ ቦታና ደረጃ አለው፡፡ የከርበላ ምድርም እንዲሁ ነው፡፡ ምክንያቱም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ምድር አፈር እንደወሰዱ፣ እንዳሸተቱትና እንደሳሙት ተዘግበዋልና፡፡ የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት የሆነችው ኡሙ ሰለማም የከርበላን አፈር በጨርቋ ቋጥራ እንደወሰደች ተዘግቧል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ለኡሙ ሰለማ ሲናገሩ፡- «*አንዳንድ ከኔው ኡመት የሆኑ ህዝቦች ልጄን ሁሴይንን ኢራቅ ውስጥ እንደሚገድሉ ጅብሪል መጥቶ ነገረኝ፡፡ ከምድሩ አፈርም ትንሽ አመጣልኝ*» ብለው ከነገሯት በኋላ ያንን አፈር ለባለቤታቸው ሰጥተው እንዲህ አሏት፡- «*ይህ አፈር ወደ ትኩስ ደም በተለወጠ ጊዜ ልጄ ሁሴይን መገደሉን በዚህ ታውቂያለሽ፡፡*» ኡሙ ሰላማም አፈሩን ወስዳ ጠርሙስ ውስጥ አደረገችው፡፡ ኢማም ሁሴይን በ61ኛው ሂጅራ ወደ ኢራቅ በተሰደዱ ጊዜ ኡሙ ሰለማ በየቀኑ አፈሩን እያየች ትጠባበቅ ነበር፡፡ አንድ ቀን ወደ ጠርሙሱ መጥታ ስታይ አፈሩ ወደ ትኩስ ደም ተቀይሮ ስታገኘው ዋይታዋን ጀመረች፡፡ የበኒ ሐሺም ሴቶች ተሰብስበው ነገሩን ጠየቋት፡፡ እሷም ሁሴይን (ዐ.ሰ) እንደተገደለ ነገረቻቸው፡፡ እንዴት እንዳወቀች ሲጠይቋት ታሪኩን ነገረቻቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ከርሷ ጋር ለኢማም ሁሴይን ማዘንና ማልቀስ ጀመሩ (*አል-ከሳኢስ - አስ-ሱዩጢ አሽ-ሻፊዒ - 2፡125፤ አል-መናቂብ አል-መጋዚሊ - ገጽ 313፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐምበል - 6፡294፤ ታሪክ አል-ኢስላም - ዲመሽቂ 3፡11፣ አል-ቢዳያህ ወል ኒሃያህ - 6፡230፣ አል-ዐቅደል ፈሪድ - ኢብን አብድ ረበህ - 2፡219፣ ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ 5፡110*)፡፡

ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) የተቀበረበትን ቦታ አፈር ያሸተተ አንድ የበኒ አሰድ ሰው እጅግ አለቀሰ፡፡ ሒሻም ኢብን ሙሐመድ እንደተናገረው፡- «የሁሴይንን የመቃብር ቦታ ለማጥፋት ውሃ በተለቀቀበት ጊዜ ከአርባ ቀን በኋላ ሲደርቅ የመቃብሩን ቦታ ለይቶ ለማወቅ አስቸግሮ ነበር፡፡ ከበኒ አሰድ የሆነ አንድ የገጠር ሰው የአፈሩን ናሙና በተደጋጋሚ እየወሰደ ማሽተቱን ተያያዘው፡፡ ከብዙ ሙከራ በኋላ ቦታውን በሽታው በመለየት ካገኘ በኋላ እያለቀሰ፡- «*ወላጆችህ ለአንተ ቤዛ ይሁኑ! በህይወት በነበርክ ጊዜ ምንኛ መልካም መዓዛ ነበረህ! ከሞትክም በኋላ አፈርህ እንዴት ጥሩ መዓዛ አለው!*» በማለት የሚከተለውን ስንኝ ቋጠረ፡-

በጥላቻና ቅናት ጠላት መቃብሩን ማውደም ይፈልጋል
የአፈሩ መልካም መዓዛ ግን ወደ መቃብሩ ይመራል
ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ሁሉንም ይጣራል፡፡ *(ታሪክ ኢብን አሳኪር - 4:342፤ አል-ኪፋያህ - ሐፊዝ አል-ገንጂ፡ ገጽ 293)*

ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ጭንቅላታቸው ተቆርጦ የተቀበሩበት የከርበላ አፈር ላይ ሱጁድ በማድረግ ቀዳሚውን ቦታ የያዙት ልጃቸው ዓሊ ቢን ሁሴይን ዘይነል ዓቢዲን (ዐ.ሰ) የአህለልቤይት መዝሐብ አራተኛው ኢማምና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የልጅ ልጅ ናቸው፡፡ አባታቸውን በከርበላ እንደቀበሩ አፈር ዘግነው በመውሰድ ካድበለበሉ በኋላ ለሱጁድ ማድረጊያነት ተጠቀሙበት፡፡ ከሳቸው በኋላም ልጃቸው ኢማም ሙሐመድ አል-ባቂርና እንዲሁም የልጅ ልጃቸው ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) እንዲሁ አድርገዋል፡፡ ኢማም ዘይነል ዓቢዲን (ዐ.ሰ) በተናገሩት መሠረት ደግሞ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ ፋጢማ አል-ዘህራ (ዐ.ሰ) ከእንጨት ውቴቶች የተሰራ ሙስበሃ እንደነበራትና ሐምዛ ኢብን አብዱል ሙጦሊብ በኡሁድ ዘመቻ ከተገደሉ በኋላ ከመቃብራቸው ቦታ አፈር ወስዳ

ሌላ ሙስበሃ ሰርታ አላህ  ለመዘከር ትጠቀም እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ሰዎች ይህንን የፋጡማን ልምድ  መሠረት በማድረግ ኢማም ሁሴይን ሸሒድ ሲሆኑ የመቃብራቸውን ቦታ አፈር በመውሰድ ሙስበሃ እየሰሩ እንዲሁ አላህን በመዘከር ይጠቀሙ ጀመር፡፡

## *በሙታን ላይ መስገድ (ሰላት አል-መይት)*

በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን በሞተ ሰው ላይ የሚሰገድ ሰላት በአምስት ተክቢራዎች (አምስት ጊዜ አላሁ አክበር ማለት) ነበር፡፡ አህመድ ቢን ሐምበል ዐብደል ዐእላን በመጥቀስ በዘገቡት ትረካ፡- «ከዘይድ ቢን አርቀም ጋር ሆኜ በጀናዛ (በሞተ ሰው) ላይ ሰግጄ አውቃለሁ፡፡ እናም ተክቢራ ያልነው አምስት ጊዜ ነበር፡፡ አንድ ሰው ከኋላው ተነሳና እጁን ይዞ ምናልባት ረስቶ እንደሆነ ጠየቀው፡፡ ዐብደል ዐእላ ሲመልስ፡- «*በጭራሽ! አቡል ቃሲም ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ተከትዬ (ከኋላ ሆኜ) ሰግጃለሁ፤ እሳቸውም ያደረጉት አምስት ተክቢራ ነው፡፡ እኔም ከዛ ውጭ አላደርግም*» በማለት መለሰ፡፡ (*ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 4፡370፤ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ ሰለዋት አለል መይት፤ ሰሂህ አል-ኒሳዒ - ኪታብ አል-ጀናዛ*)

አስ-ሱዩጢ የተክቢራን ቁጥር ከአምስት ወደ አራት የቀየሩትን የሰሃባ ስም ይጠቅሳል (*አል-ካሚል - ሱዩጢ - 15፡29፤ ታሪክ አል-ኹለፋእ - ሱዩጢ፡ ገጽ 137*)

## *የተራዊህ ሰላቶች*

ኢማም ቡኻሪ አብደላ ኢብን አብደል ቃሪን በመጥቀስ በዘገቡት መሠረት፡- «ከረመዳን ሌሊቶች ውስጥ በአንዱ ሌሊት ከዑመር ቢን አል-ኸጣብ ጋር ወደ መስጂድ ሄድኩ፡፡ ሰዎች ተበታትነው በየግላቸው በመስገድ ተጠምደው አየን፡፡

ሌሎች ሰዎች ደግሞ ከኋላቸው የተወሰነ ቡድን ተከትሏቸው ይሰግዱ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ዑመር አየት አደረገኝና «*እንደኔ እንደኔ እነዚህን ሰዎች አንድ ቦታ ሰብስቤ በአንድ አሰጋጅ ኋላ ሆነው (በጀመዓ) ቢሰግዱ ጥሩ ይመስለኛል*»

አለ፡፡ ከዚያም ሰዎቹን ሰብሰብ በማድረግ በዑበይ ቢን ካዕብ መሪነት (ኢማምነት) እንዲሰግዱ አደረገ፡፡ እንዲሁ በሌላ ቀን አንድ ሌሊት ከሱ ጋር ወደ መስጂድ ስንሄድ ሰዎች ሁሉ ተሰባስበው በአንድ ሰው መሪነት ሲሰግዱ አየን፡፡ ዑመር አየት አደረጋቸውና «ኒዕመል ቢድዓ ሃዚሂ» (ይህች ምንኛ ያማረች ፈጠራ ናት! አለ፡፡) (*ሰሂህ ቡኻሪ - 1፡342*)

በሺዓ መዝሐብ በረመዳን ወር የሚሰገዱ የሱና (ነዋፊል) ሰላቶች የሚሰገዱት በጀመዓ ሳይሆን በግል ነው፡፡

## *የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባዎች*

አብዛኛው የሙስሊም ምሁራን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦችን በተመለከተ «ሰሃባ» ለሚለው ቃል ድፍየና ሲሰጡ፣ «ሰሃባ» ማለት በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን የኖሩ፣ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ነቢዩን ያዩ ወይም ሲናገሩ የሰሙ ሰዎች ወይም ህዝብ ማለት ነው ይላሉ፡፡ በኢስላም አስተምህሮ መሠረት አንድ ሰው ያለ ትክክለኛ ምክንያት ሊወደስም ሆነ ሊኮነን አይገባም፡፡ በቁርአን መሠረት የአንድ ሰው ብልጫነት ወይም ከሌላው የተሻለ የመሆን ነጥብ የሚያገኘው በዘር፣ በእምነት፣ በቀለም ወይም በአካላዊ ገጽታ ሳይሆን ለአላህ ያለው ፍራቻ (ተቅዋ) ነው፡፡

**يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَاكُمْ مِنْ ذَكَرٍ وَأُنْثَىٰ وَجَعَلْنَاكُمْ شُعُوبًا وَقَبَائِلَ لِتَعَارَفُوا إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِنْدَ اللَّهِ أَتْقَاكُمْ إِنَّ اللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ(١٣)**

«***እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡፡ እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው፡፡***» (49፡13)

የደም ትሥሥር፣ ወዳጅነት፣ ጓደኝነት፣ ሀብት ወይም ማህበራዊ ደረጃ ወደ አላህ በመቃረብ ውስጥ ሚና የላቸውም፡፡

ሰሃቦችን በሚመለከት ቁርአን በሁለት ቡድኖች ከፍሎ ያያቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ቡድን እነዛ አማኝ የነበሩትንና ታማኝ የነበሩትን፣ ለኢስላም ሲሉ ህይወታቸውንና ሀብታቸውን መስዋዕት ያደረጉ ምሥጉን ሰሃቦችን ያካተተ ነው፡፡

الَّذِينَ آمَنُوا وَهَاجَرُوا وَجَاهَدُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنْفُسِهِمْ أَعْظَمُ دَرَجَةً عِنْدَ اللَّهِ وَأُولَٰئِكَ هُمُ الْفَائِزُونَ(٢٠)يُبَشِّرُهُمْ رَبُّهُمْ بِرَحْمَةٍ مِنْهُ وَرِضْوَانٍ وَجَنَّاتٍ لَهُمْ فِيهَا نَعِيمٌ مُقِيمٌ(٢١) خَالِدِينَ فِيهَا أَبَدًا إِنَّ اللَّهَ عِنْدَهُ أَجْرٌ عَظِيمٌ(٢٢)

«*እነዚያ ያመኑት፣ ከአገራቸውም የተሰደዱት፣ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው፡፡*
*ጌታቸው ከርሱ በኾነው እዝነትና ውዴታ በገነቶችም ለነሱ በውስጥዋ የማያቋርጥ መጠቀሚያ ያለባት ስትኾን ያበስራቸዋል፡፡*
*በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ (ያበስራቸዋል)፡፡ አላህ እርሱ ዘንድ ታላቅ ምንዳ አለና፡፡*» (9፡20 – 22)

ሌሎች በርካታ የቁርአን አንቀጾችም የበድር ዘመቻ ተከፋይ የነበሩትንና በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ታማኝ ሁነው የዘለቁትን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች በመልካምነት ያነሳሉ፡፡ በበድር ዘመቻ ወቅት የሙስሊሞቹ ቁጥር ከጠላቶቹ ብዛት አንድ ሦስተኛ እንኳ የማይሆኑ በነበሩ ጊዜና መሳሪያቸውም ከጠላት መሳሪያ አንጻር እዚህ ግባ የማይባል የነበረ ቢሆንም በጽናት በመቆም ህይወታቸውን በመሰዋት የሙስሊሞች ምርጥ ተምሳሌት የሆኑ ቡድኖች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የኢስላማዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ተሳተፊ የነበሩ እንደ ኡሙ አማራህ ያሉ የተከበሩ ሴቶችም ነበሩ፡፡ ኡሙ አማራ ለኢስላም ስትል አራት ልጆቿን የሰዋችና የቆሰለውን ልጇን በማከም ላይ ሳለች ጦርነቱ ሲያይል ወደ ውጊያው ገብታ የተፈለመች ጀግና ስትሆን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁኔታዋን በማየት

«*ኡሙ አማራህ ሆይ! አንቺ የቻልሺውን ጉድ ማን ይችል ይሆን!*» ያሏት ሰሃቢት ነች፡፡

ነገር ግን ቁርአን በግልጽ የሚጠቅሳቸው ሌላ ቡድንም አለ - *ሙናፊቆች* (አስመሳዮች)፡፡ በርካታ የቁርአን አንቀጾች ሙስሊሙን ህዝብ ለማጥፋት ያደረጉትን ሴራዎች በማጋለጥ ይኮንናቸዋል፡፡ በቁርአን ውስጥ ሁለት ምዕራፎች በተለይ ሙናፊቆችን በተመለከተ በሰፊው ቀርበዋል፡- አንደኛው ሱራ (ምዕራፍ) 9 (አል-ተውባህ) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ምዕራፍ 63 (አል-ሙናፊቂን) ነው፡፡ «ሙናፊቂን» በተሰኘው ምዕራፍ ውስጥ ሰዎች በውጫዊ ገጽታዎች ወይም በገሃድ በሚያሳዩት ተግባራት ብቻ መዳኘት እንደሌለባቸው ያስተምራል፡፡ መዳኘት ያለባቸው ለአላህ፣ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለሙስሊሙ ባላቸው ታማኝነት መሆን እንዳለበት ቁርአን አበክሮ ይናገራል፡፡

**وَإِذَا رَأَيْتَهُمْ تُعْجِبُكَ أَجْسَامُهُمْ وَإِنْ يَقُولُوا تَسْمَعْ لِقَوْلِهِمْ كَأَنَّهُمْ خُشُبٌ مُسَنَّدَةٌ يَحْسَبُونَ كُلَّ صَيْحَةٍ عَلَيْهِمْ هُمُ الْعَدُوُّ فَاحْذَرْهُمْ قَاتَلَهُمُ اللَّهُ أَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ(٤)**

«***ባየሃቸውም ጊዜ አካሎቻቸው (ግዙፍነታቸው) ያስደንቁሃል፡፡ ቢናገሩም ተሰሚነት ያገኛሉ፤ እነርሱ ልክ ጥቅትቅ ያለ የእንጨት አጥር ግድግዳ ይመስላሉ፡፡ ጩኸት ሁሉ በእነርሱ ላይ ይመስላቸዋል፡፡ እነርሱ ጠላቶች ናቸውና ተጠንቀቃቸው፡፡ አላህ ይርገማቸው፤ (ከቀናው መንገድ) እንዴት ያፈነግጣሉ!***» (63፡4)

በቁርአን መሠረት እነዚህ አላህ የቂያም ቀን የማይምራቸው አፈንጋጮች የነበሩ ናቸው፡-

**سَوَاءٌ عَلَيْهِمْ أَسْتَغْفَرْتَ لَهُمْ أَمْ لَمْ تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ لَنْ يَغْفِرَ اللَّهُ لَهُمْ إِنَّ اللَّهَ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الْفَاسِقِينَ(٦)**

«*ምሕረትን ብትለምንላቸው ወይም ምሕረትን ባትለምንላቸው በእነርሱ ላይ እኩል ነው፡፡ አላህ ለእነርሱ በፍጹም አይምርም፡፡ አላህ አመጸኞችን ሕዝቦች አይመራምና፡፡*» (63፡6)

እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ሰላትን ይሰግዱና ዘካንም ይሰጡ የነበሩ ቢሆንም ይህንን የሚያደርጉት ከሙናፊቅነታቸው የመነጨና ለመታየትና ለይስሙልን ባላቸው ፍላጎት እንጂ ለአላህ ብለው እንዳልነበረ ቁርአን ያጋልጣቸዋል፡-

**وَمَا مَنَعَهُمْ أَنْ تُقْبَلَ مِنْهُمْ نَفَقَاتُهُمْ إِلَّا أَنَّهُمْ كَفَرُوا بِاللَّهِ وَبِرَسُولِهِ وَلَا يَأْتُونَ الصَّلَاةَ إِلَّا وَهُمْ كُسَالَىٰ وَلَا يُنْفِقُونَ إِلَّا وَهُمْ كَارِهُونَ(٥٤)**

«*ልግስናዎቻቸውን ተቀባይ እንዳያገኝ የተደረጉት እነሱ በአላህና በመልክተኛው የካዱ፣ ሶላትንም የተሰላቹ ኾነው በስተቀር የማይሰግዱ፣ እንዲሁም ምጽዋት ሲሰጡ እየጠሉ በስተቀር የማይሰጡ በመኾናቸው እንጂ በሌላ አይደለም፡፡*» (9፡54)

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኋላ ሆነው በሚሰግዱበት ወቅት እንኳ የንግድ ግመሎች ዕቃ ተጭነው መዲና ሲገቡ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባ መስማት ትተው ከሰላታቸው ሰልፍ (ሰፍ) ወጥተው ወደ ጭነቱ የሚሮጡ ለኃይማኖቱ ጉዳይ ያልነበራቸው አስመሳዮች እንደነበሩ ቁርአን ይናገራል፡-

وَإِذَا رَأَوْا تِجَارَةً أَوْ لَهْوًا انْفَضُّوا إِلَيْهَا وَتَرَكُوكَ قَائِمًا قُلْ مَا عِنْدَ اللَّهِ خَيْرٌ مِنَ اللَّهْوِ وَمِنَ التِّجَارَةِ وَاللَّهُ خَيْرُ الرَّازِقِينَ(١١)

«*ንግድን ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተዉህ ሲኾኑ ወደእርሷ ይበተናሉ፡፡ አላህ ዘንድ ያለው ዋጋ ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው፡፡ «አላህም ከሰጪዎቹ ሁሉ ይበልጥ ሲሳይን ሰጭ ነው» በላቸው፡፡*» (62፡11)

የታሪክ እውነታዎች እንደሚነግሩን ከሆነ እነዚህ ሙናፊቆች ሰሃቦችን አሳቻ ቦታ በመከበብ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመግደል እንዳሴሩና በመዲና ውስጥ የርስ በርስ ጦርነት ለመቀስቀስ እንደዶለቱ ቁርአን ይናገራል፡- *(ለዝርዝር መረጃ አል-መጋዚሊ አል-ዋቂዲን 2፡989) ይመልከቱ)፡፡* እላይ የተጠቀሰውን ጉዳይ ቁርአን ሲጠቅስ፡-

لَقَدِ ابْتَغَوُا الْفِتْنَةَ مِنْ قَبْلُ وَقَلَّبُوا لَكَ الْأُمُورَ حَتَّىٰ جَاءَ الْحَقُّ وَظَهَرَ أَمْرُ اللَّهِ وَهُمْ كَارِهُونَ(٤٨)

«*ከዚህ በፊትም ሁከትና ፍትና ለመፍጠር በእርግጥ ፈለጉ፡፡ እነርሱ እየጠሉም ቢሆን እውነቱ እስኪለጥና የአላህም ትዕዛዝ(ድል) በግልጽ እስኪመጣ ድረስ ነገሮችንም ሁሉ ረባበሹብህ፡፡*» (9፡48)

يَقُولُونَ لَئِنْ رَجَعْنَا إِلَى الْمَدِينَةِ لَيُخْرِجَنَّ الْأَعَزُّ مِنْهَا الْأَذَلَّ وَلِلَّهِ الْعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِ وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَلَٰكِنَّ الْمُنَافِقِينَ لَا يَعْلَمُونَ(٨)

*«(ሙናፊቆቹም)እንዲህ ይላሉ »ወደ መዲና ብንመለስ ጠንካራዎቹ (ሙናፊቆቹ) ደካማዎቹን(ነቢዩንና ተከታዮቻቸውን) በእርግጥ ከእርሷ ያወጣሉ»። አሸናፊነትም ለአላህ፣ ለመልክተኛውና ለምእምናን ነው። ግን መናፍቃን አያውቁም።*» (63፡8)

እነዚህ ሙናፊቆች ለአላህ ብለው ሳይሆን ከሌሎች ሙስሊሞች ጋር ለመፎካከርና ለመለያየት ብለው መስጂድ ሰርተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መርቀው እንዲከፍቱላቸው ጋብዘው ነበር። ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ግብዣቸውን እንዳይቀበሉና በሙናፊቅነት ላይ የተገነባውን መስጂድንም እንዲያወድሙ አላህ አዘዛቸው:-

**وَالَّذِينَ اتَّخَذُوا مَسْجِدًا ضِرَارًا وَكُفْرًا وَتَفْرِيقًا بَيْنَ الْمُؤْمِنِينَ وَإِرْصَادًا لِمَنْ حَارَبَ اللَّهَ وَرَسُولَهُ مِنْ قَبْلُ وَلَيَحْلِفُنَّ إِنْ أَرَدْنَا إِلَّا الْحُسْنَىٰ وَاللَّهُ يَشْهَدُ إِنَّهُمْ لَكَاذِبُونَ(١٠٧) لَا تَقُمْ فِيهِ أَبَدًا لَمَسْجِدٌ أُسِّسَ عَلَى التَّقْوَىٰ مِنْ أَوَّلِ يَوْمٍ أَحَقُّ أَنْ تَقُومَ فِيهِ فِيهِ رِجَالٌ يُحِبُّونَ أَنْ يَتَطَهَّرُوا وَاللَّهُ يُحِبُّ الْمُطَّهِّرِينَ(١٠٨) أَفَمَنْ أَسَّسَ بُنْيَانَهُ عَلَىٰ تَقْوَىٰ مِنَ اللَّهِ وَرِضْوَانٍ خَيْرٌ أَمْ مَنْ أَسَّسَ بُنْيَانَهُ عَلَىٰ شَفَا جُرُفٍ هَارٍ فَانْهَارَ بِهِ فِي نَارِ جَهَنَّمَ وَاللَّهُ لَا يَهْدِي الْقَوْمَ الظَّالِمِينَ(١٠٩) لَا يَزَالُ بُنْيَانُهُمُ الَّذِي بَنَوْا رِيبَةً فِي قُلُوبِهِمْ إِلَّا أَنْ تَقَطَّعَ قُلُوبُهُمْ وَاللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ(١١٠)**

«*እነዚያም (ምእምናንን) ለመጉዳት፣ ክህደትንም ለማበርታት፣ በምእምናንም መካከል ለመለያየት፣ ከአሁን በፊት አላህንና መልክተኛውን የተዋጋውንም ሰው ለመጠባበቅ መስጊድን የሠሩት (ከነሱ ናቸው)። መልካምን ሥራ እንጂ ሌላ አልሻንም ሲሉም በእርግጥ ይምላሉ። አላህም እነሱ በእርግጥ ውሸታሞች መኾናቸውን ይመሰክራል። በእርሱ ውስጥ*

*በፍጹም አትስገድ፡፡ ከመጀመሪያ ቀን ይዞ በአላህ ፍራቻ ላይ የተመሠረተው (የቁባ) መስጊድ በውስጡ ልትሰግድበት ይልቅ የተገባው ነው፡፡ በእሱ ውስጥ መጥራራትን የሚወዱ ወንዶች አሉሉ፡፡ አላህም ተጥራሪዎችን ይወዳል፡፡ አላህን በመፍራትና ውዴታውን በመፈለግ ላይ ግንቡን የመሠረተው ሰው ይበልጣልን ወይስ ጎርፍ በሸረሸረው ለመናድ በተቃረበ ገደል አፋፍ ላይ ግንቡን የመሠረተውና በርሱ (ይዞት) በገሀነም እሳት ውስጥ የወደቀ (ይበልጣል)፡፡ አላህም በደለኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡ ያ የካቡት ግንባቸው ልቦቻቸው (በሞት) ካልተቆራረጡ በቀር በልቦቻቸው ውስጥ የመጠራጠር ምክንያት ከመኾን አይወገድም፡፡ አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው፡፡*» (9፡107 – 110)

አንዳንዶቹ ሙናፊቆች ታማኝ ሙስሊሞችን በዘዴ በመቅረብ ትክክለኛ አማኞች እንደሆኑ አስመስለው ለመግባባት ጥረት በሚያደርጉበት ወቅት ሙስሊሞቹ እንዳያምኗቸው አላህ ይነግራቸዋል፡፡

وَيَحْلِفُونَ بِاللَّهِ إِنَّهُمْ لَمِنْكُمْ وَمَا هُمْ مِنْكُمْ وَلَٰكِنَّهُمْ قَوْمٌ يَفْرَقُونَ(٥٦)

«*እነሱም በእርግጥ ከእናንተ ለመኾናቸው በአላህ ይምላሉ፡፡ እነርሱም ከናንተ አይደሉም፡፡ ግን እነሱ (ሙስሊሙን ህዝብ ለመከፋፈል) የሚጥሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡*» (9፡56)

በብዙ አጋጣሚዎችም ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲሰድቡና ሲሳለቁባቸው ታይተዋል፡-

**وَمِنْهُمُ الَّذِينَ يُؤْذُونَ النَّبِيَّ وَيَقُولُونَ هُوَ أُذُنٌ قُلْ أُذُنُ خَيْرٍ لَكُمْ يُؤْمِنُ بِاللَّهِ وَيُؤْمِنُ لِلْمُؤْمِنِينَ وَرَحْمَةٌ لِلَّذِينَ آمَنُوا مِنْكُمْ وَالَّذِينَ يُؤْذُونَ رَسُولَ اللَّهِ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ(٦١)**

«*ከእነሱም (ከመናፍቃን) እነዚያ ነቢዩን የሚያሰቃዩ «እርሱም ጆሮ ነው» (ወሬ ሰሚ ነው) የሚሉ አሉ ፡፡ ለእናንተ የበጎ (ወሬ) ሰሚ ነው በላቸው፡፡ በአላህ ያምናል፣ በምእምናንንም ላይ እምነት አለው፣ ከእናንተም ውስጥ ለነዚያ ላመኑት ምህረት ነው፡፡ እነዚያም የአላህን መልክተኛ የሚያሰቃዩ ለነሱ አሳማሚ ቅጣት አላቸው፡፡*» (9፡61)

በመዲና ውስጥ የነበሩትን ሙናፊቆች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸው አያውቋቸውም ነበር፡፡ የሙናፊቆች አለቃ የሆነው አብደላ ቢን ዑበይን ቢያውቁም አላህ ያለሳወቃቸው ብዙ ሌሎች ሙናፊቆች በመዲና ከተማ በሚገኘው መስጂዳቸው ውስጥ ነበሩ፡-

**وَمِمَّنْ حَوْلَكُمْ مِنَ الْأَعْرَابِ مُنَافِقُونَ وَمِنْ أَهْلِ الْمَدِينَةِ مَرَدُوا عَلَى النِّفَاقِ لَا تَعْلَمُهُمْ نَحْنُ نَعْلَمُهُمْ سَنُعَذِّبُهُمْ مَرَّتَيْنِ ثُمَّ يُرَدُّونَ إِلَىٰ عَذَابٍ عَظِيمٍ(١٠١)**

«*በዙሪያችሁም ካሉት ከዐረብ ዘላኖች መናፍቃን አሉ፡፡ ከመዲና ሰዎችም በንፍቅና ላይ በማመጽ የዘወተሩ አሉ፡፡ አታውቃቸውም፡፡ እኛ እናውቃቸዋለን፡፡ ሁለት ጊዜ እንቀጣቸዋለን፡፡ ከዚያም ወደታላቅ ቅጣት ይመለሳሉ፡፡*» (9፡101)

አንዳንድ ሙናፊቆች ኢስላምንና ሙስሊሞችን ለማጥፋት ባደረጉት ሴራ የተነሳ አላህ ዘለዓለማዊ ቅጣት ቃል የገባላቸውና ለእንዲህ ዓይነቱ አስፈሪ ደረጃ እስከመድረስ የደረሱበት ሁኔታ ስላለ መጥፎዎቹን ከጥሩዎቹ ሳይለዩ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ ያሉትን ሁሉ ማወደስና የአላህን ውዴታ ለሁሉም ማድረግ የማይገባ መሆኑን ሙስሊሞች መረዳት አላባቸው፡፡ ሙስሊሞች ሁሉንም ሰሃቦች ማናቸውንም ብንከተል ወደ ቅን መንገድ የምንመራበት ከዋክብት ናቸው የሚለውን ማስተጋባትና መቀበል የለባቸውም፡፡ ይኸውም ሁሉንም ሰሃቦች ወደ ቅን መንገድ የሚመሩ «ከዋክብት» ናቸው ማለት የለባቸውም፡፡ ኢማም ቡኻሪ እንደሚከተለው ዘግቧልና፡-

*የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡-»በኸውሰር ምንጭ ሁኜ እጠብቃችኋለሁ፡፡ እዛም በፊታችሁ ሁኜ ለአንዳንድ ሰዎች እከራከራለሁ፡፡ ነገር ግን መቆጠብ እንዳለብኝ ይገለጥልኛል፡፡ እንዲህም እላለሁ፡- ጌታዬ ሆይ! እነዚህ እኮ ሰሃቦቼ ናቸው፣ እነዚህ ሰሃቦቼ ናቸው፡፡ ከዚያ ግን «አንተ ከተለየሃቸው በኋላ የፈጠሩትን አንተ አታውቅም» የሚል ምላሽ ይሰሰጠኛል፡፡ (ሰሂህ ቡኻሪ፡- አስደንጋጭ ሐዲሶች (ልብ የሚያቀልጡ ሐዲሶች) በሚለው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ #6089፣ 6090፤ ኪታብ አል-ፊትና - ሐዲስ #6527፤ ሰሂህ ሙስሊም ኪታብ አል-መናቂብ - ሐዲስ #4250፣ ኢብን ማጃህ - ኃይማኖታዊ ተግባራት በሚለው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ #3048 ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡384፣ 406፣ 407፣ 425፣ 453፣ 455፣ 5፡ 387፣ 393፣ 400)*

ይህንኑን ሐዲስ በሌላ በተመሳሳይ አባባል ሲዘግብ፡-

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአንድ ወቅት ሰሃቦቻቸው መካከል በመሆን እንዲህ አሉ፡- »ከናንተ ወደ እኔ የሚመጡትን ሰዎች የከውሰር ምንጭ አጠገብ ሁኜ እጠብቃሉ፡፡ በአላህ እምላለሁ! አንዳንድ ሰዎች ወደኔ እንዳይመጡ

ይታገዳሉ፡፡ እኔ ደግሞ ጌታዬ ሆይ! እነዚህ እኮ የኔ ተከታዮችና ከኔ ኡማ የሆኑ ሰዎች ናቸው እላለሁ፡፡ ከዚያም እንዲህ ይለኛል፡- ከአንተ በኋላ የሡሩትን አንተ አታውቅም፤ ከኃይማኖታቸው በተደጋጋሚ ወደ ኋላ የተመለሱና ያፈነገጡ ናቸው፡፡

አቡ ሙለይካ በዱአቸው ውስጥ፡- «አላህ ሆይ! ወደ ኋላ ከመመለስና ከመፈተን በአንተ እጠበቃለሁ» ይሉ እንደነበረ ተዘግቧል፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ሐዲስ #6104፤ ሰሂህ ሙስሊም - ሐዲስ - 4245)*

አንዳንድ ሙስሊሞች በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ ለነበሩት ማናቸውም ሰዎች ክብር የነፈገ ሰው ሙስሊም ወይም አማኝ አይደለም የሚል አስተሳሰብ አላቸው፡፡ በእርግጥ ታማኝና ሐቀኛ የነበሩትን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች መንቀፍና መተቸት በጥብቅ የተከለከለና ተቀባይነት የሌለው ድፍረት ነው፡፡ ነገር ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዙሪያ ከነበሩ ቡድኖች መካከል ነቢዩ እንኳን የማያውቃቸው ሙናፊቆች መኖራቸው መረሳት የለበትም፡፡ (ቁርአን - 9፡101)፡፡

እነዚህን ሙናፊቆች በመጀመሪያ የረገማቸው አላህ ነው፡፡ በሌላ አባባል እነዚህን ሙናፊቆች የመርገምና የመኮነን ቀዳሚውን ቦታ የወሰደው ኃያሉ አላህ ነው፡፡ በተጨማሪም ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለአላህ ታማኝ በመሆን ይታወቁ የነበሩትን ምርጥ ሰሃቦችን የመርገምና የመሳደብ ባህልን የመሠረተ ከኡመያዎች ኸሊፋ የሆነ ሰው የነበረ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል፡፡ ማንኛውንም ሰሃባ የሚሳደብ ወይም የሚራገም ሙስሊም በከሃዲነት ወይም በኩፍርነት ከተፈረጀ ለዚህ ኸሊፋ የሚሰጠው ኢስላማዊ ፍርድ ምን ሊሆን ነው? ከዚህም ሌላ ደግሞ ለአንድ አስተዋይ የሆነ ሰው ከየትኛው ጎራ መሰለፍ እንዳለበት እስኪቸገር ድረስ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች መካከል ከጊዜ ወደ ጊዜ

እየከፋ የመጣ ልዩነትና አለመግባባት ነበር፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች መካከል የሆኑ ግለሰቦች ለሦስተኛው ኸሊፋ - ዑስማን ቢን ዐፋን መገደል ምክንያት የነበሩ ናቸው፡፡ ዑስማንን የገደሉት የነቢዩ ሰሃቦች የነበሩ ግለሰቦች እንደነበሩ ታሪክ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

*ታዲያ* ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) *ታማኝ* ሰሃቦች *ጋር* በእኩል *መታየት* አለባቸው?

«ሰሃቦቼ እንደ ከዋክብት ናቸው፡፡ *ማናቸውንም* ብትከተሉ (ቅኑን *መንገድ*) ትመራላችሁ» የሚሉ ሐዲሶች የአላህን ውዴታ ለሁሉም ሰሃቦች በጅምላ የሚያደርሱ ከሆነ፣ በሺዓ መዝሐብ መሠረት እንዲህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች ከቁርአን *ጋር* ስለሚቃረኑ ትክክለኛ ተደርገው አይወሰሱዱም፡፡

አንዳንዶቹ ሰሃቦች በስህተት ወንጀል በመሥራታቸው አላህ የይቅርታ ቃል የገባላቸው መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ ሆን ብለው ከአላህ ለማፈንገጥ ሳይሆን በመሳሳት ስለሆነ ይቅርታ የተገባቸው ናቸው፡፡

**وَآخَرُونَ اعْتَرَفُوا بِذُنُوبِهِمْ خَلَطُوا عَمَلًا صَالِحًا وَآخَرَ سَيِّئًا عَسَى اللَّهُ أَنْ يَتُوبَ عَلَيْهِمْ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَحِيمٌ(١٠٢)**

«***ሌሎችም በኃጢአቶቻቸው የተናዘዙ መልካም ሥራንና ሌላን መጥፎ ሥራ የቀላቀሉ አልሉ፡፡ አላህ ከእነሱ ጸጸታቸውን ሊቀበል ይከጀላል፡፡ አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና፡፡***» (9:102)

## *የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች*

የደም ዝምድና ወይም የጋብቻ ትሥሥር ብቻ ጀነት የመግቢያ መንገድና አስተማማኝ የደህንነት ፀጋን ማጎናጸፍ ስለማይችል የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶችም ስለ ሰሃቦች በተባለው ጉዳይ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ አላህ

በቁርአን ውስጥ እንዳስቀመጠው አማኞችን ለስኬትና ለጀነት የሚያበቃ በጎ ሥራዎቻቸው ነው፡፡ ምንም እንኳ ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የመከተልና ሱናቸውን የማወቅ ዕድሉ ቢሰጣቸውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት ወይም ልጅ መሆን ብቻ በቂያም ቀን ስኬትን አያጎናጽፍም፡፡

ኃያሉ አላህ በቁርአን ውስጥ የአላህ መልዕክተኞች (ኑህ እና ሉጥ) ባለቤቶች የነበሩትን የሁለት ሴቶችን ምሳሌ ይጠቅሳል፡-

**ضَرَبَ اللَّهُ مَثَلًا لِلَّذِينَ كَفَرُوا امْرَأَتَ نُوحٍ وَامْرَأَتَ لُوطٍ كَانَتَا تَحْتَ عَبْدَيْنِ مِنْ عِبَادِنَا صَالِحَيْنِ فَخَانَتَاهُمَا فَلَمْ يُغْنِيَا عَنْهُمَا مِنَ اللَّهِ شَيْئًا وَقِيلَ ادْخُلَا النَّارَ مَعَ الدَّاخِلِينَ(١٠)**

«***አላህ ለእነዚያ ለካዱት ሰዎች የኑሕን ሚስትና የሉጥን ሚስት ምሳሌ አደረገ፡፡ ከባሮቻችን ከኾኑ ሁለት መልካም ባሪያዎች ሥር ነበሩ፡፡ ከዱዋቸውም፡፡ ከአላህም ቅጣት (ኑሕና ሉጥ) ሚስቶቻቸውን ምንም ሊያድኑ አልቻሉም፡፡ ከገቢዎቹም ጋር « ወደ እሳት ግቡ» ተባሉ፡፡***» (66፡ 10)

ለብዙ ምክንያቶች ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ብዙ ባለቤቶች (ሚስቶች) ነበሯቸው፡፡ አንዳንዶቹ ባለቤቶቻቸው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ሁልጊዜ መልካም የሆነ ግንኙነት ብቻ እንዳልነበራቸው የታሪክ ምሁራን ዘግበዋል፡፡ ኢማም ቡኻሪ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች አንዷ ከሆነችው ዓኢሻ የሚከተለውን ሐዲስ ዘግበዋል፡-

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዘይነብ ቢንት ጀህሽ (ከነቢዩ ባለቤቶች አንዷ) ቤት በመቆየት ከሷ ቤት ማር ይጠጡ ነበር፡፡ ዓኢሻ ቀጠል አድርጋ ሁኔታውን ስትተርክ፡- »ከሁለታችን አንዳችን ጋር ሲመጡ መጋፊር (መጥፎ ሽታ ያለው እጣን) ትሸታለህ ብለን ልንላቸው እኔና ሀፍሳ (ሌላኛዋ ባለቤታቸው) ተስማማን፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዳቸው ጋር በሄዱ ጊዜ በተማከሩት መሠረት መጥፎ ጠረን እንዳለባቸው ነገረቻቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- «ከዘይነብ ቢንት ጀህሽ ቤት ማር ጠጥቼ ነበር፣ ሁለተኛ እንዲህ አላደርግም፡፡ በዚህ ጊዜ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከማር መታቀብ አስመልክቶ የሚከተለው የቁርአን አያህ ወረደ፡-

**يَا أَيُّهَا النَّبِيُّ لِمَ تُحَرِّمُ مَا أَحَلَّ اللَّهُ لَكَ تَبْتَغِي مَرْضَاتَ أَزْوَاجِكَ وَاللَّهُ غَفُورٌ رَحِيمٌ(١)**

«***አንተ ነቢዩ ሆይ! ሚስቶችህን(እሜቴ ዓኢሻንና እሜቴ ሀፍሳን) ለማስደሰት ብለህ አላህ ለአንተ ከፈቀደልህ ነገር ለምን ትታቀባለህ? አላህም እጅግ መሓሪ አዛኝ ነው፡፡***» (66፡1)

*(ሰሂህ ቡኻሪ (ስለ ቁርአን ተፍሲር - ሐዲስ #4531)፣ ሰሂህ ሙስሊም (ስለ ፍቺ - ሐዲስ #2694)፣ አል-ቲርሚዚ - ስለ ምግብ - ሐዲስ #1574፤ አል-ኒሳኢ - ስለ ፍቺ - ሐዲስ #3367፣ 3735፣ 3896፤ አቡ ዳውድ - ስለ መጠጥ - ሐዲስ #3227፤ ኢብን ማጃህ - ስለ ምግብ - ሐዲስ #3314፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል 6፡221፤ አል-ዳሪሚ - ስለ ምግብ - ሐዲስ #18986)*

በተጨማሪም ቁርአን እሜቴ ዓኢሻንና እሜቴ ሐፍሳን ብቻ አስመልክቶ እንዲህ ይነበባል፡-

**إِنْ تَتُوبَا إِلَى اللَّهِ فَقَدْ صَغَتْ قُلُوبُكُمَا وَإِنْ تَظَاهَرَا عَلَيْهِ فَإِنَّ اللَّهَ هُوَ مَوْلَاهُ وَجِبْرِيلُ وَصَالِحُ الْمُؤْمِنِينَ وَالْمَلَائِكَةُ بَعْدَ ذَٰلِكَ ظَهِيرٌ(٤) عَسَىٰ رَبُّهُ إِنْ طَلَّقَكُنَّ أَنْ يُبْدِلَهُ أَزْوَاجًا خَيْرًا مِنْكُنَّ مُسْلِمَاتٍ مُؤْمِنَاتٍ قَانِتَاتٍ تَائِبَاتٍ عَابِدَاتٍ سَائِحَاتٍ ثَيِّبَاتٍ وَأَبْكَارًا(٥)**

«(እናንተ ሁለቱ የነቢዩ ባለቤቶች ሆይ!)*ወደ አላህ ተጸጽታችሁ የሚትመለሱ ከሆነ -ልቦቻችሁ በእርግጥ (ነቢዩ የሚወዱትን ነገር ለመቃወም) ተዘንብለዋልና ። በእርሱም ላይ ብትረዳዱ አላህ እርሱ ጠባቂው ነው፤ ጂብሪልም ደጋጎቹ ምእምናንም እንዲሁም መላእክቱ ጠባቂዎቹ ናቸው። እናንተን ቢፈታችሁ እንኳ በእናንተ ፈንታ ከእናንተ የበለጡ ሚስቶችን ሙስሊሞች፣ አማኞች፣ ታዛዦች፣ ተጸጸቾች፣ (ለአላህ) ተገዢዎች፣ ጾመኞዎች ፣ፈቶች፣ ደናግልም የኾኑትን ጌታው ይተካለታል።*»(66፡4 – 5)

እነዚህ የቁርአን አንቀጾች እንደሚያረጋግጡልን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች ከምርጥ ሰሃቦች ጎራ ውስጥ እንዳልተካተቱ ነው። ነገር ግን ለፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ያህል ቁጥር ያላቸው ሚስቶችን አግብተው አመጻቸውንና ተንኮላቸውን በትዕግሥት ይዘው ይኖሩ ነበር።

## *ታሪካዊ እውነታዎች*

- ከወንዶች ኢስላምን የተቀበለ የመጀመሪያው ሰው ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ነው። *(ሸርህ ነህጀል በላጋህ - ኢብነል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ - 13፡224)*

ዓሊ እራሱ ሲናገር፡- «*ከዚህ ትውልድ ከነቢዩ ሌላ ማንም ሰው አላህን መገዛት ከመጀመሩ ከዘጠኝ ዓመታት በፊት አላህን ማምለክ የጀመርኩ እኔ ነኝ*» ብሏል፡፡ *(ኸሳኢስ አሚረል ሙእሚኒን - አል-ኒሳኢ - 13፡39፤ እንዲሁም ታሪክ አል-ጠበሪ-2፡316 እና 5፡17 ይመልከቱ፡፡ የሌሎች ሰሃቦችን መስለም ዘመን አስመልክቶ መረጃ ያገኛሉ)*

- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሙስሊሞች መካከል የወንድማማችነትን ትሥሥር ሥርዓትን ሁለት ጊዜ አድርገዋል፡፡ አንደኛው ወደ መዲና ከመሰደዳቸው በፊት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ከስደት በኋላ ነው፡፡ በሁለቱም ወቅት ለራሳቸው ወንድም አድርገው የመረጡት ዓሊ ቢን አቢ ጧሊብን ሲሆን አቡ በክርን ከዑመር፣ ዑስማን ቢን አፋንን ከ አብዱራህማን ቢን ዐውፍ፣ ሐምዛ ቢን አብደልሙጦሊብን ከዘይን ቢን ሐሪሳ፣ ሙስዓብ ቢን ዑመይርን ከ ሰዕድ ቢን አቢ ወቃስ፣ ሰልማን አል-ፋሪስን ከአቡ ዘር አል-ጊፋሪ፣ እና ጠልሓን ከዙበይር ጋር ነበር በወንድማማችነት ያጣመሩት፡፡ *(አል-ጠበቃት አል-ኹብራ - ኢብን ሰዕድ 3፡102)*
- ከጀናባ ንጹህ ያልሆኑ ሰዎች ሳይታጠቡ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጊድ እንዳይገቡ በተከለከለ ጊዜ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጊድ የሚያደርሱ ባሮች ሁሉ ሲዘጉ ሳይዘጋ የቀረው የኢማም ዓሊ ቤት በር ብቻ ነበር፡፡ ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) እና ፋጢማ አል-ዘሕራን (ዐ.ሰ) ይህ ህግ አይመለከታቸውም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በቁርአን (33፡33) የወረደውን አያት አል-ተጥሒር (የንጽህናና የጽድቅና አንቀጽ) ግልጽ የሚያደርግ ጉዳይ ነው፡፡ የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት ሐምዛ በውሳኔው አዝኖ እያለቀሰ ወደ ነቢዩ ሲመጣ የተሰጠው መልስ «*እኔ አንተንም አልከለከልኩም፣ ለሱም አልፈቀድኩም፡፡ የፈቀደለት አላህ ነው፡፡*» የሚል ነበር፡፡ *(አል-ኢሳባህ ፊ መዕሪፈት አል-ሰሃባ - 1፡373፣ አል-ዱረል መንሱሪ 6፡122፣ ወፋእ አል-ወፋእ -*

*አል-ሰምሁዲ - 2፡477፣ ከንዝ አል-ዑማል - አል-መተቂ አል-ሒንዲ - 15፡155 እና ሌሎችም)*

የሁሉም በር እንዲዘጋ ሲደረግ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊን ቤት በር እንደነበረ እንዲቆይ መፈቀዱን አስመልክቶ ብዙ ሰሃቦች እንደተገረሙና ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) በአንድ ኹጥባ ላይ መልስ እንደሰጡበት ኢማም አህመድ ቢን ሐንበል ዘግበዋል፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለጉዳዩ መልስ ሲሰጡ፡- «*የዓሊ በር ሲቀር ሁሉም በሮች እንዲዘጉ አዛለሁ፡፡ በአላህ እምላለሁ! ይህ የራሴ ፍላጎት ብቻ አይደለም፡፡ ከአላህ የመጣልኝ ትዕዛዝ ነው፡፡ እኔም ትዕዛዙን ነው የፈጸምኩት*» የሚል ነበር *(ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡175፣ 2፡26፣ 4፡369)*፡፡

በዚህ ምክንያት ነበር ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ቢን አል-ኸጣብ የሚከተለውን ያለው፡፡ «*ኢብን አቢ ጣሊብ ሦስት ፀጋዎችን የተጎናጸፈ ሰው ነው፡፡ ከእነዚህ ሦስቱ እኔ አንዱን እንኳ አግኝቼ በነበረ ከዚህ ዓለም ህይወት በሙሉ ይሻለኝ ነበር፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን ልጅ ዳሩት፣ እሷም ልጅ ወለደችለት፤ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊ ቤት በር ሲቀር ሁሉንም የመስጂድ በሮች ዘጉ፤ በኸይበር ቀንም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባንዲራ የሰጡት ለዓሊ ነበር*» *(አል-ሰዋኢቅ አል-ሙህሪቃ - ኢብን አል-ሐጀር - 3፡9፣ አል-ሙስተድረክ አል-ሐኪም - 3፡125)*፡፡

## *የሐሙሱ ቀን አሳዛኝ ክስተት*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት ሊለዩ አካባቢ የሮማ ጭፍራ በኢስላማዊ ግዛት ድንበር አካባቢ እየሰፈሩ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ሲቀር ሁሉም ሰሃቦቻቸው መዲናን እንዲላቁና የኡሳማ ቢን ዘይድን ጭፍራ እንዲቀላቀሉ አዘዙ፡፡ አንዳንድ ታዋቂ ሰሃቦች ግን ይህን ትዕዛዝ ሳይቀበሉ ቀሩ፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ደጋግመው ትዕዛዝ

አስተላለፉ፡፡ ነገር ግን ሰሃቦቹ በእምቢተኝነታቸው ፀኑ፡፡ በዕለተ ሐሙስ ማለትም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው አራት ቀናት በፊት ሰሃቦቹ ለሦስተኛ ጊዜ በነቢዩ ቤት ተሰብስበው ሳሉ ዓይናቸውን ገለጥ አድርገው ሰሃቦቻቸው በአልጋቸው ዙሪያ ተኮልኩለው እንዳዩ ውርሳቸውን (ወሲያቸውን) ለመጻፍ ቀለምና ወረቀት እንዲያቀርቡላቸው ጠየቁ፡፡ ከሰሃቦቻቸው አንዱ ግን ወረቀትና ቀለም እንዳይሰጣቸው ከለከለ፡፡ እንዲህም አለ፡- «*እውነት እላችኋለሁ፣ (ይህ ሰው) በሽታው ጠንቶበታል፤ የአላህ መጽሐፍ ለኛ በቂያችን ነው፡፡*» በቤቱ ውስጥ ጭቅጭቁና ንትርኩ እየጨመረ ሲመጣ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ ሰዎቹ ዞር በማለት፡- «*ሂዱልኝ ከዚህ፣ እኔ ባለሁበት እንዲህ ልትነታረኩ አይገባም*» አሏቸው፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - 4፡4090 - ሐዲስ #1229፣ ሰሂህ ሙስሊም - ıı፡ 89፤ አል-ጠበቃቱል ኩብራ - ኢብን ሳዕድ - 2፡36፤ ሚስባሀል ሙኒር - 6፡34)*

አብደላህ ቢን ዓባስ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር፡- «*ፈተናና ኢደጋ የተከሰተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኑዛዜያቸውን እንዳይጽፉ በከለከሏቸው ጊዜ ነው*» በማለት እንደተናገረ ተዘግቧል፡፡ *(አል-ሚላል ወ አል-ኒሐል - ሽህሪስታኒ - ı፡22)*

ሌሎች የታሪክ ምሁራን እንደዘገቡት ደግሞ በዛው ዕለት ያው ሰሃባ «ዝም ባሉት/ተውት (ቅዱሱን ነቢይ)! እየቃዠ ነው በማለት እንደተናገረ ተጠቅሷል *(ተዝኪረቱል ኸዋስ - ሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ፣ ሲርረል ዓለሚን - አቡ ሐሚድ አል-ገዛሊ - ገጽ 2ı፤ ታሪክ ኢብን አል-ወርዲ - ı፡2ı)*፡፡

ይህ ሁሉ የተከሰተው በ (4፡80) እንዲሁም (3፡ı32) የተቀመጡ ግልጽ የቁርአን መመሪያዎች እንዳሉ ሆነው ነው፡፡ ይህ ሰሃባ በዕለተ ሐሙሱ ክስተት ወቅት የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ጥያቄ መቃወሙን ያመነና የተናዘዘ ሲሆን ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በህመማቸው ምክንያት አልጋ ላይ ሆነው ዓሊን (ዐ.ሰ) ለኢማምነት (መሪነት) መጥቀስ ስለፈለጉ ያንን እንዳያደርጉ ለማስቆም እንደሆነ

አምኗል *(ሸርሀ ነህጀል በላጋ - ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ - 3፡114፤ ፈትሐል ባሪ ለላ ሰሒህ አል-ቡኻሪ - ኢብን ሐጀር - 8፡132)*፡፡

ኢማም ቡኻሪ ሰዕድ ኢብን ጁበይርን ዋቢ በማድረግ ከኢብን ዓባስ እንደዘገበው፡- «ያቺ የሐሙስ ቀንማ! ኧረ ያቺ ሐሙስ!» ከዚያም በእምባው ድንጋይ እስኪርስ ድረስ አለቀሰ፡፡ ቀጥሎ፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፡- «*ተቀብላችሁ ከተከተላችሁ ፍጹም ለጥፋትና ለጥመት እንዳትደረጉ የሚረዳችሁን ኑዛዜ እጽፍላችሁ ዘንድ ቀለምና ወረቀት አቅርቡልኝ*» አሉ፡፡ ነገር ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉበት ተጨቃጨቁ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉበት ቦታ ማጨቃጨቅ ተገቢ አልነበረም፡፡ እንዲህም አሉ፡- «*ምንድን ነው ችግሩ ጠይቁት እንጂ!*» እሳቸውም አሉ፡- «*በቃ ተዉኝ! አሁን ያለሁበት ሁኔታ (ችግር) ይሻለኛል፡፡ ሦስት ኑዛዜዎችን እሰጣችኋለሁ፡- ከዓረቢያ ሰርጥ ሙሽሪኮችን በሙሉ አስወጡ፤ ለልዑካን (ወኪሎች) እኔ ስከፍል የነበረውን ያህል አበል ክፈሉ፤ ነገር ግን ሦስተኛውን ኑዛዜ ወይ ሳይናገሩ ቀርተዋል ወይም ተናግረው እኔ ለመርሳት ተገድጄ ይሆናል*» አለ፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታቡልጂሃድ ወል መጋዚ - ሐዲስ #2825፣ ሰሂህ ሙስሊም - ሐዲስ #3089፤ አቡ ዳውድ (ስለ ግብር፣ ምርኮና ግዛት በሚያወሳው ክፍል) ሐዲስ #2634፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡222)*

## *በእሜቴ ፋጢማ አል-ዘሕራ (ዐ.ሰ) ላይ የደረሰው ጭቆናና በደል*

በመዝሐቦቻቸው ልዩነት ሳይገደቡ ሁሉም የሙስሊም ታሪክ ጸሐፍቶች በአንድነት የተስማሙበት ከማይካዱ የታሪክ እውነታዎች ውስጥ አንዱ የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ተወዳጅ ልጅ እሜቴ ፋጢማ አል-ዘሕራ (ዐ.ሰ) በቤቷ ላይ ጥቃት በደረሰ ጊዜ በደረሰባት ጥቃት ምክንያት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ ከሦስት ወራት በኋላ ህይወቷ ማለፉ ነው፡፡ በ18 ዓመት ከ ሰባት ወር ህይወቷ

ለህልፈት ተደርጓል፡፡ በቀብሯ ሥነ-ሥርዓት ላይ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) መቃብር ላይ ሆኖ የሚከተለውን ንግግር ነበር ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያሰማው፡-

***«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነሆ ከኔና ከርስዎ ጋር ለመገናኘት ፈጥና ከመጣችው ተወዳጇ ልጅዎ ሠላምታችን ይድረስዎት! የአላህ ነቢይ ሆይ! ተመረጯ ልጅዎን በተመለከተ ትዕግሥቴ ሁሉ ተሟጧል፡፡ ቀደም ሲል ከርስዎ የመለየት ከባድ ፈተናና ልብ ኢድካሚ ሐዘንን የመቋቋም መሠረት ባይኖረኝ ኖሮ ፍጹም መቋቋም ባልቻልኩ ነበር፡፡ በአንገቴና በደረቴ መካከል ሆነው የመጨረሻዎን እስትንፋስ እንደተነፈሱ በማረፊያዎ ቀብር ውስጥ አደረግኩዎት፡፡ በእርግጥ እኛ ለአላህ ነን፤ ወደ አላህ ተመላሾችም ነን፡፡ እነሆ አሁን አደራው (አማናው) ተመልሷል፤ የተሰጠው መልሶ ተወስዷል፡፡ የሐዘኔ ጉዳይማ ገደብ የለውም፤ ስለ ቀሪ ሌሊቶቼ ከተነሳ እንቅልፍ በዓይኔ አይዞርም፤ አሁን እናንተ ያለችሁበትን ቤት አላህ ለኔም እስኪመርጥ ድረስ እንደሆንኩ እሆናለሁ፡፡ በእርግጥ ልጅዎ ሁሉን ነገር ትነግርዎታለች፡፡ የርስዎ ህዝቦች ተባብረውባት ያደረሱባትን በደልና ጭቆና በዝርዝር ታስረዳዎታለች፡፡ ጉዳዩን በዝርዝር ጠይቋትና ስለሁሉም ነገር ይወቁ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ብዙም ጊዜ ሳይቆይ፣ የርስዎ ትዝታና ትውስታ እንኳን ገና ሳይጠፋ ነው፡፡ ሰላምታዬ በሁለታችሁም ላይ ይሁን! ሰላምታዬም ልቡ የቆሰለና መራር ሐዘን ውስጥ ያለ ሰው ሰላምታ እንጂ የከፋና መጥፎ ሰው ሰላምታ አይደለም፡፡ ከሄድኩኝም ሰልችቼያችሁ አይደለም፡፡ ከቆየሁም አላህ ለታጋሾችና ቻዮች በገባው ቃል ኪዳን ሳላምን ቀርቼ አይደለም፡፡*** *(ነህጀል በላጋ - ኹጥባ #202)*

እሜቴ ፋጢማ (ዐ.ሰ) የሞተችው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ ከሦስት ወር በኋላ ሲሆን ይህንንም ጊዜ የኖረችው በሐዘንና በቁጭት ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኋላ ለአፍታ እንኳን ፈገግ ብላ ታይታ አታውቅም *(አል-ጠበቃቱል ኩብራ - ኢብን ሰዕድ 2፡85)*፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኋላ ከነቢዩ ሰሃቦች አንዱ እላይዋ ላይ በር በመዝጋት አጋጭቷት ልጇን ሙህሲንን እንድታስወርድ ከተደረገች በኋላ ስቃይዋ ቀን በቀን እየጨመረ መጣ፡፡ ከቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የምገባትን ውርስም ተከለከለች፡፡ በተለይም ደግሞ ከመዲና ውጭ የሚገኘውን ፈደክ ተብሎ የሚጠራውን ቦታ «ነቢዮች አያወርሱም» በሚል ሰንካላ ምክንያት ተቀማች፡፡ በኢማም ቡኻሪ ዘገባ መሠረት እሜቴ ፋጢማ (ዐ.ሰ) የሚገባትን ውርስ በጠየቀች ጊዜ የተሰጣት መልስ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «*እኛ የነቢያት ጭፍራዎች ውርስ አናወርስም፤ ትተን የምናልፈው ሰደቃ ነው*» ብለዋል የሚል ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ምንም እንኳ ቁርአን ነቢያት ከሌሎች ነቢያት ውርስ ያገኙበትን ምሳሌዎች ቢያስቀምጥልንም እሷ ግን ተከለከለች፡፡ ከቁርአን ምሳሌዎች ለመጥቀስ ያህል፡-

**وَوَرِثَ سُلَيْمَانُ دَاوُودَ**

«***ሱለይማንም ዳውድን ወረሰ፡፡*** (27፡16)

እሜቴ ፋጢማ በሞተች ጊዜ የቀበራት ባለቤቷ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ሲሆን በቀብሯ ላይ የተገኙት ጥቂት ሰሃቦች ብቻ ነበሩ፡፡ የተቀበረችውም በሌሊት ነው፡፡ ሰላተል መይት የሰገደባትም ዓሊ ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ***«ፋጢማ የኔ አካል ናት፤ እሷን ያስቆጣ እኔን ያስቆጣ ነው»*** ያሉ ቢሆንም ይህ ሁሉ ነገር ደረሰባት (ሰሂህ ቡኻሪ - 3፡35)፡፡ ኢብን ቁተይባ በዘገቡት መሠረት ደግሞ እሜቴ ፋጢማ (ዐ.ሰ) ለአንዳንድ ሰሃቦች የሚከተለውን እንደተናገረች ይጠቀሳል፡- ***«አላህና መላኢኮቹ ምሥክሬ ናቸው፤ እጅግ አስቆይማችሁኛል፣ በናንተ ፍጹም ደስተኛ አይደለሁም፡፡ ነቢዩን***

***(ሰ.0.ወ) ባገኛቸው በናንተ እጅግ ማዘኔንና የደረሰብኝን ሁሉ እናገራለሁ*** *(አል-ኢማማህ ወል ሲያሳህ - ኢብን ቁተይባ - 1:14)*

### ***እውን ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.0.ወ) ከመሞታቸው በፊት የመጀመሪያውን ኸሊፋ ሰላት እንዲመራ አዘውታልን?***

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.0.ወ) ከመሞታቸው በፊት አብዛኛዎቹ ሰሃቦች መዲናን ለቀው የሮማውያኑን ጥቃት ለመመከት የዑሳማ ቢን ዘይድን ጭፍራ እንዲቀላቀሉ ትዕዛዝ አስተላልፈው ነበር፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ሰሃቦች ይህንን ትዕዛዝ ሳይቀበሉ ቀርተው መዲና ውስጥ የቀሩ ሲሆን የዑሳማ ጭፍራ ግን ጁርፍ ተብሎ በሚታወቅ አካባቢ ሰፍረው ነበር፡፡

ነገር ግን ነቢዩ (ሰ.0.ወ) በታመሙ ጊዜ የመጀመሪያው ኸሊፋ በነቢዩ ፈቃድ ሰላት እንዲመራ ተደርጓል ብሎ ያወሩ ሁለት ሰዎች አሉ፡፡ በሌላ አባባል ይህንን ጉዳይ የሚመለከት ሐዲስ ያወሩ ሁለት ሰዎች ናቸው፡፡ ይኸውም አንደኛዋ የመጀመሪያው ኸሊፋ ልጅና የነቢዩ (ሰ.0.ወ) ባለቤት የሆነችው አኢሻና አነስ ኢብን ማሊክ ናቸው፡፡ እሜቴ አኢሻ ስትናገር፡- «*ነቢዩ (ሰ.0.ወ) በጠና ታመው መራመድ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ሆነው ሰላት ለማሰገድ ወደ መስጂድ ሄዱ፡፡ በዚህ ጊዜ አቡ በክር ሰላቱን እያመሩ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.0.ወ) በቦታው ደርሰው አቡ በክር ጎን ተቀምጠው ሰላቱን መሩ*» *(አል-ቢዳያ ወ አል-ኒሃያ - ኢብን ከሲር - 5፡253)፡፡*

ይህ ሐዲስ አቡ በክር ሰላት እንዲመራ ነቢዩ (ሰ.0.ወ) ስለማዘዛቸው ማስረጃ ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.0.ወ) በዛ ሁኔታ ውስጥ እንኳን ሆነው (በጠና ታመው) ከቤታቸው ወጥተው ሰላቱን ራሳቸው መርተዋልና፡፡

ሌላኛው የሐዲስ ተራኪ አነስ ቢን ማሊክ ሲሆን የሺዓ መዝሐብ ይህንን ሰሃባ ገለልተኛ ምንጭ አድርጎ አይመለከተውም፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ወቅት የመጀመሪያው ኸሊፋ መዲና ውስጥ ነበሩ ብለው የሚሉ የታሪክ ፀሐፍት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዕለቱ ቀትር አካባቢ ህይወታቸው ልታልፍ አኢሻ ቢላልን በመጥራት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡ በከር የሱብሂ ሰላት ይመራ ዘንድ እንደሚፈልጉ ለአባቷ እንዲነግር እንዳደረገች ይጠቅሳሉ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን እንዳወቁ በዓሊና አል-ፈድል ቢን ዓባስ ተደግፈው ሰላቱን ለመምራት በዛ ሁኔታ ወጡ፡፡ የመጀመሪያውን ኸሊፋ ቦታ አስለቅቀው ሰላቱን ከመሩ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመስጂዳቸው ውስጥ ወደሚገኘው ክፍላቸው በመመለስ ለአኢሻ፡- «አንቺ ከዩሱፍ ሴቶች (በነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) ዘመን በታሪክ ከሚታወቁ ሴቶች) አንዷ ነሽ» አሏት፡፡ *(ታሪክ አል-ጠበሪ - 2፡439፣ ሲራ ኢብን ሒሻም፡ 4፡303)*

ይህ ታሪክ በተለያየ አባባል በዘጠኝ ተራኪዎች ተነግሯል፡፡ እነዚህም፡- እሜቴ አኢሻ፣ አብደላህ ቢን አባስ፣ አብደላህ ቢን መስዑድ፣ አብደላህ ቢን ዑመር፣ አብደላህ ቢን ማሊክና ሳሊም ቢን ዑበይድ ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ትረካዎች ሁሉ ሲመረመሩ ሁሉም ምንጫቸው ወደ አኢሻ እንደሚመለስ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተራኪዎች ውስጥ እምነት የማይጣልባቸው ግለሰቦች አሉ፡፡ በሌላም በኩል ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡ በከር ሰላት እንዲመራ አዘው በነበረ እንኳ ይህ ምርጫ አቡ በከር በሁለንተናው ጉዳይ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተተኪ የመሆን ዕድል የሚያመለክት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደዓይናማው ኢብን ኡሙ መኽቱም ያሉ ብዙ ሰዎችን ሰላት

እንዲመሩ የወከሉበት ብዙ አጋጣሚዎች ቢኖርም እነዚህ ሰዎች እንደ ኸሊፋዎች ታይተውም ታስበውም አያውቁም፡፡ *(አቡ ዳውድ - ሱነን 1:98)*

ሼክ አል-ኢስላም ኢብን ተይሚያ እንዳስቀመጡት ነቢዩ በህይወት እያሉ በአንድ በተወሰነ ኃላፊነት ወይም ተግባር ተወክሎ መሥራት ወይም ኃላፊነት መቀበል ከሞት በኋላ የተተኪነት ቦታ መያዝን ወይም ኸሊፋ ሆኖ መቀጠልን ሊያመለክት አይችልም፡፡ ቀጠል በማድረግም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደ ኢብን መኽቱም፣ በሺር ኢብን አብደል ሙንዚርና ሌሎችም ሰዎች የጀመዓ ሰላትን መምራትና የመሳሰሉ ሌሎች ሥራዎችን በኃላፊነት እንዲመሩ የመረጡበት ሁኔታዎች እንደነበሩ ይጠቅሳሉ፡፡ አብዛኛዎቹ እነዚህ ሰዎች ነቢዩን ተክተው ለመሥራት ወይም የኸሊፋነት ቦታን ለመያዝ ብቁ ያልነበሩ ናቸው *(ሼክ አል-ኢስላም ኢብን ተይሚያ - ሚንሐጅ አስ-ሱና - 4:91)* ፡፡

በጠበሪ ዘገባ መሠረት ደግሞ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሞት ወቅት አቡ በክር መዲና ውስጥ አልነበሩም *(ታሪክ አል-ጠበሪ 2:439)* ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሽታው ጠንቶባቸው ወደ መስጂድ ወጥተው ሰላት ለመምራት አቅም እንዳጡና ቢላል ጠብቆ ሲያጣቸው፡- «*የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አባቴና እናቴ ለርስዎ ቤዛ ይሁንና ሰላቶቹን ማን ሊመራ (ሊያሰግድ) ነው?* » ብሎ ጠየቀ፡፡ *(ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - 3:302)*

በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) አስጠሩ፡፡ ከዚያም ባለቤታቸው እሜቴ አኢሻ «*አቡ በክርን እንጠራለዎታለን*» አለቻቸው፤ ባለቤታቸው እሜቴ ሐፍሳም፡- «*ዑመርን እንጠራለዎታለን*» አለቻቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጥሪ ለኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ሳይደርስ ቀረ፡፡ ሌሎቹ ሰዎች ግን ነቢዩ

(ሰ.ዐ.ወ) ጋር ቀረቡ። ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ)፡- *«ከዚህ ሂዱልኝ! ስፈልጋችሁ እልከባችኋለሁ አሏቸው፡፡»* ከዚያም ሰሃቦቹ ተመለሱ። *(ታሪክ አል-ጠበሪ - 2፡ 349)*

## *ጀነት የተመሰከረላቸው አሥሩ ሰሃቦች*

በቲርሚዚ ዘገባ መሠረት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለአሥር ሰሃቦቻቸው ጀነት ከወዲሁ እንደተረጋገጠላቸው የተወራ ሲሆን አል-ዘሐቢ ሚዛን አል-ኢዕቲዳል በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ እንደተጠቀሱት ቡኻሪና ሙስሊም ይህንን የቲርሚዚ ዘገባ ውድቅ በማድረግ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፍጹም እንዲህ ብለው እንደማያውቁ ያረጋግጣሉ። ይህ ሐዲስ በተለያየ ደረጃዎች ሎጂክን (አመንክዮን) የሚጻረርና በምክንያታዊ አስተሳሰብ እይታ ቦታ የማይሰጠው ወሬ መሆኑን ለመረዳት አዳጋች አይደለም። ይኸውም እነዚህ ጀነት ከወዲሁ የተመሰከረላቸው ከተባሉት ሰዎች ውስጥ የሦስተኛውን ኸሊፋ ግድያ አዛዦች የሆኑትን ጠልሃና ዙበይር ለምሳሌ እናገኛለን። በዚህ ሐዲስ ውስጥ ግን ለሦስተኛው ኸሊፋ መገደል ዋና ተዋናይ የነበሩትም ሆኑ ተገዳዩ ራሱ ከአሥሩ መሆናቸው ነው። ጠልሃና ዙበይር ማለት የገቡትን ቃል አፍርሰው ህጋዊ ኸሊፋ በሆነው ኢማም ዓሊ ላይ አምጸው ጦርነት የከፈቱበት ግለሰቦች ናቸው። በዚህ ሐዲስ ውስጥ የተካተተው ሌላኛው ሰው ደግሞ ለዓሊ (ዐ.ሰ) በይዓ ማድረግን አሻፈረኝ ያለና ለሙዓዊያ በይዓ ያደረገው ሰዕድ ኢብን አቢ-ወቃስ ነው። ሌላው ደግሞ በሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ቢን አፋን ላይ ያመጸና በኡመያዎች የተገደለው አብዱራህማን ቢን ዐውፍ ነው። ኢብን ዐውፍ ደግሞ ሁለተኛው ኸሊፋ »የዚህ ህዝብ ፈርኦን« በማለት የሰየሙት ሰው ነው። *(አል-ኢማማህ ወል ሲያሳህ - ኢብን ቁተይባ - ገጽ 24)*

ጀነት የተመሰከረላቸው አሥር ሰዎች ብቻ ናቸው የሚለው አስተሳሰብ በራሱ ሚዛናዊ የሆነ አስተሳሰብ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እንደ ሰይድ አል-ሹሐዳእ የተባሉት ሐምዛና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑት ጃዕፈር ኢብን አቢ ጧሊብን፣ ዘይድ ቢን ሐሪሳ፣ ሰዕድ ቢን መዓዝ፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «*ከራስ ፀጉሩ እስከ እግሩ ጣት ድረስ በኢማን የተሞላ*» በማለት ያወደሱት አማር ቢን ያሲርን፣ «*እሱ ከኛ ከአህለል ቤይት አንዱ ነው*» የተባለውን ሰልማን አል-ፋርሲንና ሌሎችን በርካታ በመቶዎች የሚቆጠሩ ታማኝና ጻድቅ ሙስሊሞችን ከማዕዱ ውጭ የሚያደርግ ነውና፡፡ ስለ አሥሩ ጀነት የተመሰከረላቸው ሰዎች የሚያወሳውን ሐዲስ ያወራው ከአህለልቤይት ጋር ጥሩ ግንኙነት ያልነበረው ሰዒድ ቢን ዘይድ ስለሆነ የሺዓ መዝሐብ አይቀበለውም፡፡

## ***አቡ ሑረይራ***

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የቆየው ለሦስት ዓመታት ብቻ እንደነበረ ቢናገርም ከፍተኛውን ቁጥር ሐዲስ ያወራ ሰው አቡ ሑሬይራ አል-ዱሲ ነው፡፡ ሐዲሶቹም 5,374 ሲሆኑ ከዚህ ውስጥ 446 ሐዲሶች በኢማም ቡኻሪ ሐዲሶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ *(አል-ጠበቃት አል-ኩብራ - ኢብን ሰዕድ - 4፡327፤ ሰሂህ ቡኻሪ - 4፡ 239፣ መሕሙድ አቡ ሪያህ 'ሼይኸል ሙዷራ - አቡ ሑሬይራ' በተባለው መጽሐፋቸው ውስጥ አቡ ሑሬይራ ከነቢዩ ጋር የቆየው ለአንድ ዓመት ከዘጠኝ ወር ብቻ እንደሆነ ይጠቅሳሉ፡፡)* አቡ ሑሬይራ ኢስላምን የተቀበለው ከሂጅራ በኋላ በ7ኛው ዓመት ነው፡፡ አቡ ሑሬይራ እራሱ እንደተናገረው ብዙ ሐዲስ በማውራት የሚበልጠው ሰው ቢኖር አብደላህ ቢን ዑመር እንደሆነና ይኸውም የሆነው አቡ ሑሬይራ መጻፍ የማይችል ሲሆን አብደላህ ኢብን ዑመር ግን መጻፍ የሚችል የነበረ በመሆኑ እንደሆነ ተናግሯል፡፡*(ሰሂህ ቡኻሪ -ኪታብ አል-ዕልም-፣፡86)* በእርግጥ አብደላህ ቢን ዑመር ያወራው የሐዲሶች ብዛት 2,630 ሲሆን

ከነዚህም ውስጥ ኢማም ቡኻሪ የጠቀሰው ሰባት ብቻ ሲሆን ኢማም ሙስሊም የዘገበው ደግሞ ሀያ ናቸው፡፡ ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ እራሳቸው ያወሩት ሐዲስ 527 ሐዲሶች ብቻ ሲሆን፣ ዑስማን ቢን አፋን 146 ሐዲሶች፣ አቡ በክር 142 ሐዲሶች፣ የነቢዩ ባለቤት አኢሻ 1,210 ሐዲሶች፣ ጃቢር ኢብን አብደላህ አል-አንሳሪ 1,540 ሐዲሶች፣ አብደላህ ቢን መስዑድ 848 ሐዲሶች፣ አቡ ዘር አል-ጊፋሪ 281 ሐዲሶች፣ የነቢዩ ባለቤት ኡሙ ሰላማህ 378 ሐዲሶች፣ ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብ 537 ሐዲሶች፣ አነስ ኢብን ማሊክ 2,286 ሐዲሶች አውርተዋል፡፡ በተጨማሪም በኢማም ሙስሊም ዘገባ መሠረት በአንድ ወቅት ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ አቡ ሑሬይራን እንደደበደቡት ይጠቅሳል *(ፊቂህ አስ-ሲራ - ሙሐመድ አል-ገዛሊ - ገጽ 41)፡፡* አቡ ሑሬይራ እራሱ ሲናገር፡- «*ዑመር በህይወት በነበረ የሚያስገርፋኝን ብዙ ሐዲሶች ለናንተ አውርቻለሁ፡፡ ዑመር ቢኖር ግን ይደበድበኝ ነበር*» ብሎ እንደተናገረ ተዘግቧል፡፡ *(ፊቂህ አስ-ሲራ - ሙሐመድ አል-ገዛሊ - ገጽ 41)፡፡* አቡ ሑሬይራ በኢስላም ውስጥ በእውነት የተወቀሰና የተኮነነ የመጀመሪያው የሐዲስ ተራኪ (ራዊ) እንደሆነ ይነገራል *(የአረብ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ - ሙስጠፋ አል-ራፊኢ - 1፡278)፡፡* በአንድ ወቅት ዑመር አል-ኸጣብ ለአቡ ሑሬይራ፡- «*የሙስሊሞችን ገንዘብ ለራስህ ወስደሃል*» ብሎ እንደተናገረው ተዘግቧል *(አል-ቢዳያህ ወል ኒሃያህ - ኢብን አል-አሲር - 8፡116)፡፡*
እንዲሁም በአንድ ወቅት ዑመር አቡ ሑሬይራን፡- «*አንተ እጅግ በጣም ብዙ ሐዲሶችን አውርተሃል፡፡ ይህ ደግሞ በትክክል የሚያመለክተው በነቢዩ ላይ ትቀጥፋለህ (ትዋሻለህ) ማለት ነው*» ብሎታል *(ሸርህ ነህጀል በላጋ ኢብን አቢ አል-ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ 1፡360)፡፡* ኢብን ሐጀር አል-አስቀላኒ እንዳሉት ደግሞ በአላህ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መዋሸት ከታላላቅ ወንጀሎች አንዱ እንደሆነ ዑለማዎች በአንድነት የተስማሙበት ጉዳይ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም አልፎ ደግሞ በሌሎች ዑለማዎች መሠረት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ (ስለ ነቢዩ)

ውሸት መናገር ለኩፍር/ከሓዲነት (ኢ-አማኝነት) እንደሚዳርግ አውስተዋል፡፡ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ አንድ ጊዜ ብቻ እንኳን ከዋሸ ሰው ሐዲስ መቀበል ተገቢ እንዳልሆነ አል-ሰምዓኒ ጠቅሰዋል *(አል-ጠሪቅ - አል-ነወዊ - ገጽ 14)፡፡*

አቡ ሑሬይራ ካወራቸው ሐዲሶች ሌላው ምሳሌ በሰሂህ ኢማም ቡኻሪ ውስጥ የሚገኘው ሐዲስ ነው፡፡ ይኸውም ቀጥሎ ያለው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተገኘ የተባለው ሐዲስ ነው፡- «*አንዲት ዝንብ ምግባችሁ ውስጥ ከገባችባችሁ ዝንቧን ሙሉ በሙሉ ምግቡ ውስጥ አስገቧትና ካወጣችኋት በኋላ ምግቡን ብሉት፡፡ ምክንያቱም ዝንብ በአንድ ክንፏ የያዘችው በሽታ ሲሆን በሌላኛው ክንፏ ደግሞ መድኃኒት ስለያዘች ነው*» *(ሰሂህ ቡኻሪ - 7፡22)፡፡* ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፀሐይ እስኪወጣ ድረስ እንቅልፍ ጥሏቸው የሱብሂ ሰላት እንዳመለጣቸው የሚጠቅስ ሐዲስ ኢማም ሙስሊም ከአቡ ሑሬይራ ዘግበዋል፡፡ *(ሰሂህ ሙስሊም - 1፡471፣ 310?)* - ይህ ሐዲስ ግን፡-

**قُمِ اللَّيْلَ إِلَّا قَلِيلًا(٢) نِصْفَهُ أَوِ انْقُصْ مِنْهُ قَلِيلًا(٣)**

«***ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም፤ (ስገድ)፡፡ ግማሹን (ቁም)፤ ወይም ከርሱ ጥቂትን ቀንስ፡፡***» (73፡ 2 – 3) ከሚለው የቁርአን አያህ ጋር የሚጻረር ነው፡፡ የሌሊት ወይም የእኩለ ሌሊት ሰላቶች አምልጧቸው የማያውቁት ነቢይ እንዴት የሱብሂ ሰላት ያመልጣቸዋል!? ቀጠል በማድረግ ሰሂህ ቡኻሪ ውስጥ እንደተዘገበው አቡ ሑሬይራ ሲናገር ሙስሊሞቹ ሰላታቸውን ሊሰግዱ እንደቆሙና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልክ እቃማ እንደጨረሱ በድንገት ጀናባ (ጁኑብ) እንደሆኑ እንዳስታወሱ ተጠቅሷል *(ሰሂህ ቡኻሪ - 1፡77)* እንዲሁም ቡኻሪ ከአቡ ሑሬይራ በዘገቡት ሐዲስ መሠረት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡- ሸይጧን እየተፈታተነኝ *ሥራ* አስፈትቶ አቆየኝ *(ሰሂህ ቡኻሪ - 4፡151)፡፡* ይህ ሐዲስም፡-

إِنَّهُ لَيْسَ لَهُ سُلْطَانٌ عَلَى الَّذِينَ آمَنُوا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ(٩٩)

«***እርሱ በእነዚያ ባመኑትና በጌታቸው ላይ በሚጠጉት ላይ ለእርሱ ስልጣን የለውምና፡፡***» (16፡99) ከሚለው የቁርአን አንቀጽ ጋር የሚጻረር ነው፡፡

ኢማም ሙስሊም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት እሜቴ አኢሻ የሚከተለውን ሐዲስ እንዳወራች ከአቡ ሑሬይራ እንደዘገቡት፡-

»ከዕለታት አንድ ቀን የአላህ መልዕክተኛ ጭናቸው የተገለጠ ሆኖ ቤቴ ውስጥ አርፈው ነበር፡፡ አቡ በክር ወደ ቤቱ ይገባ ዘንድ ፍቃድ ጠየቀ፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንደነበሩ ሆነው (ጭናቸው እንደተገለጠ ሆኖ) እንዲገባ ፈቀዱለትና ገብቶ አናገራቸው፡፡ ከዚያ ደግሞ ዑመር ለመግባት ፈቃድ ጠየቀ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በዚሁ ሁኔታ እያሉ ፈቀዱለትና ገብቶ አናገራቸው፡፡ ከዚያ ደግሞ ዑስማን ለመግባት ፈቃድ ጠየቀ፡፡ ልክ ዑስማን እንዳንኳኳ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሚገባ ተሸፍነው በሥርዓቱ ቁጭ አሉ፡፡ ዑስማን ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አናግሯቸው ከሄደ በኋላ እንዲህ ብዬ ጠየቅኳቸው፡- «*አቡ በክርና ዑመር ሲገቡ ምንም ትኩረት አልሰጧሃቸውም፡፡ ዑስማን ሲገባ ግን እንዴት ጭንዎን ሸፍነው በአግባቡ ቁጭ ሊሉ ቻሉ?*» ከዚያም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመልሱ፡- «*መላኢኮች እንኳ ፊት ለፊቱ ሆነው የሚያፍሩትንና የሚፈሩትን ሰው እኔ ላላፍርና ላልፈራ ነው እንዴ?*» አሉ ይባላል፡፡ *(ሰሂህ ሙስሊም - 4፡1866 ሐዲስ #2401)*

ኢብን ዓረፋ የተባለ ምሁር ስለእንዲህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች ገለጻ ሲያደርግ አብዛኞቹ መሰል ሐዲሶች በዑመያ ሥርወ-መንግሥት ዘመን የተፈበረኩ አሉባልታዎች እንደሆኑ ይጠቅሳል፡፡*(ፈጅረል ኢስላም - ሙሐመድ አሚን - ገጽ 213)፡፡*

ሙዓዊያ ስልጣን ላይ በደረሰ ጊዜ በሥሩ ለነበሩት የአስተዳደር አባላትና የተለያዩ ክልሎች ገዢዎች በጻፈው መመሪያ፡- «*ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) በተመለከተ ለተናገሩት እያንዳንዱ ገድልና ውዳሴ ተመሳሳይ ነገር ለሰሃቦቹም እንዲባል እፈልጋለሁ*» ማለቱ ተዘግቧል *(ለበለጠ ማብራሪያ አል-ኢስቲዓብ - ኢብን አብድልብር 1፡65፤ አል-ኢሳባህ - ኢብን ሐጀር - 1፡154፤ አል-ካሚል ፊልታሪክ - ኢብን አሲር 3፡162፤ ታሪክ አል-ጠበሪ - 6፡77፤ ታሪክ ኢብን አሳክር - 3፡222፤ ወፉእ አል-ወፉእ - 1፡31፣ ተህዚብ - 1፡435፤ ሸርህ ነህጀል በላጋ - ኢብን ኢበል ሐዲድ አል-መዕተዚሊ 1፡176 ይመልከቱ)፡፡*

ሐዲሶች የኢስላማዊ ህግጋት የሁለተኛ ደረጃ ምንጭ እስከሆኑ ድረስ የተራኪዎች ሰንሰለትና አጠቃላይ ይዘቱ በሚገባ መጣራትና መመርመርና ከቁርአን ጋር ማስተያየት ግዴታ በመሆኑ የአንድን ሐዲስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሺዓ መዝሐብ ጥብቅ የሆነ መስፈርቶች አሉት፡፡

## *በሺዓና በሌሎች መዝሐቦች መካከል የሚነሱ ልዩነቶችና አለመግባባቶች*

*عَبَسَ وَتَوَلَّىٰ(١)*

**«*ዐበሰ ወ ተወላ /ፊቱን አጨፈገገ፣ ዞረም*» (80፡1)**

ይህ የቁርአን አያህ በሁለቱ ዋና መዝሐቦች የተለያየ ትንታኔ ከተሰጣቸው የቁርአን አንቀጾች አንዱ ነው፡፡ አብዛኛው የሱኒ ምሁራን ከዓይነ ስውሩ ሰው ፊቱን አጨፍግጎ የዞረው ሰው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደሆነ ሲጠቅሱ የሺዓ ምሁራን ደግሞ ፊቱን አጨፍግጎ የዞረው ሰው ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሳይሆኑ በቦታው ከነበሩ የነቢዩ ሰሃቦች አንዱ ነው ይላሉ፡፡

በሱኒ ምሁራን ዘገባ መሠረት ዓይነ ስውሩ ሰው አብዱላህ ኢብን ኡም መኽቱም ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደ ኡትባህ ኢብን ረቢአህ፣ አቡ ጀህል ኢብን ሒሻም፣ አል-ዓባስ ኢብን አብደል ሙጠሊብ፣ ዑበይና ኡመያህ ኢብን ኸለፍ ያሉ በወቅቱ አማኞች ያልነበሩ ሰዎች ጋር እየተነጋገሩና ልቦቻቸውን ወደ ኢስላም እያቃኑ በነበረበት ወቅት ወደ ነቢዩ እንደመጣ ይነገራል፡፡ የመካ ከተማ ማህበረሰብ መሪዎች ስለነበሩ እነሱ ኢስላምን ቢቀበሉ ሌሎች ብዙ ሰዎች ይሰልማሉ ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከነዚህ ሰዎች ጋር በመነጋገር ተጠምደው እንደነበሩ ሳያውቅ ይህ ሰው ወደሳቸው (ሰ.ዐ.ወ) መጥቶ ንግግራቸውን በመቋረጥ አላህ ካሳወቃቸው ነገር እንዲያስተምሩት ጠየቃቸው፡፡ በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊታቸውን አኮማትረው ከሱ ዞሩ፡፡

የዚህ የቁርአን አንቀጽ የሺዓ ትርጓሜ በስድስተኛው የአህለልቤይት ኢማም የሆኑት ኢማም ጃዕፈር አል-ሳዲቅ (ዐ.ሰ) እንደተናገሩት ግን የወረደው ከበኒ ኡመያ የሆነ ከነቢዩ ሰሃቦ አንዱን በተመለከተ እንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡

ይህ ሰሃባ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጎን ተቀምጦ የነበረ ሲሆን ዓይነስውሩ ሰው ወደ ነቢዩ በመጣ ጊዜ በጥላቻና በንቀት ተሞልቶ ፊቱን አዞረበት *(ተፍሲር መጅመዐል በያን - 10፡437)*፡፡ ይህ ትርጉም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባህሪይ ጋር የሚጣጣም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ምክንያቱም ፊትን ማጨፍገግና ትኩረት መንሳት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባህርይ ሆኖ አያውቁም፡፡ ለሀብታሞች ማዳላትና ደኃዎችን ቸል ማለትም ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባህርያት አይደለም፡፡ አላህ ድካ የሌለውን ከፍተኛ የሞራል ስብዕና ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳጎናጸፋቸው በቁርአን ገልጽዋል፡፡

**وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ(٤)**

*«አንተም ታላቅ **ጠባይ ላይ ነህ፡፡**»* (68፡4)

**فَبِمَا رَحْمَةٍ مِنَ اللَّهِ لِنْتَ لَهُمْ وَلَوْ كُنْتَ فَظًّا غَلِيظَ الْقَلْبِ لَانْفَضُّوا مِنْ حَوْلِكَ فَاعْفُ عَنْهُمْ وَاسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِي الْأَمْرِ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَوَكِّلِينَ(١٥٩)**

«***ከአላህም በኾነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ ልበ ደረቅም በኾንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ አላህ በርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡***» (3፡159)

**لَقَدْ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مِنْ أَنْفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُمْ بِالْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَحِيمٌ(١٢٨)**

«*ከጎሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ ለእናንተ የሚጓጓ፣ ለምእምናን ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ።*» (9፡ 128)

ከኃያሉ አላህ የተመሰከረላቸውን እነዚህን ሁሉ ማስረጃዎች ካየን በኋላ ተልዕኮአቸውን እስከ መጨረሻው ድረስ ለደሃው ክፍል፣ ለተቸገረውና ለተጎዳው ህዝብ ድጋፍ በመስጠት ያጠናቀቁት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከአንድ ዓይነ ስውር ሰሃባቸው ፊታቸውን አጨፍግገው ይዞራሉ ብሎ ማመን እጅግ ይከብዳል፡፡ ህይወታቸውን ሙሉ ድጋፍ ከሚሹት የህብረተሰብ ክፍል በመቆምና ለአቅመ ደካሞችና አካለ ስንኩላን የተለየ ድጋፍና ፍቅር እንደነበራቸው የሚጠቁመውን ታሪክ ወደ ጎን በመተውና የደኃውን ክፍል ህይወት ለመኖርና ሀዘናቸውን ለመግለጽ በርካታ ሌሊቶችን ያለ ምግብ ያሳልፉ የነበሩትን ነቢይ በእንዲህ ዓይነቱ ውንጀላ መውቀስ የማይመስል ነው፡፡ አንዳንድ የቁርአን ተንታኞች ይህ የቁርአን አንቀጽ ሰሃባን በተመለከተ ነው ከተባለ የነቢዩን ሰሃቦች እንደ መሳደብ ይሆናል ብለው ማሰባቸውና የላቀ ስብዕናና ንጽህና ተምሳሌትና የሙዕሚኖች አለቃና መሪ የሆኑትን ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ግን በዚህ አንቀጽ ተወቃሽ ሲያደርግ እንደ ስድብ አለመቁጠራቸው እጅግ የሚገርም አስተሳሰብ ነው፡፡

## *የነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) አባትና የኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) አባት*

በሺዓ አስተምህሮ መሠረት ሁሉም መልዕክተኞች፣ ነቢያትና በመለኮታዊ ትዕዛዝ የተመረጡ ኢማሞች የሚመጡት በተውሂድ (በአላህ አንድነት) ከሚያምኑ አባቶች፣ አያቶችና ቅድመ አያቶች ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ አላህ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲያናግራቸው በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

الَّذِي يَرَاكَ حِينَ تَقُومُ(٢١٨) وَتَقَلُّبَكَ فِي السَّاجِدِينَ(٢١٩)

***»ያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ የሚያይህ፤ (ከቀደምት አባቶችህ መካከል ከሆኑት) በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (የሚያየው ጌታህ) ፡፡«*** (26፡218 – 219)

ከዚህ የቁርአን አያህ እንደምንረዳው የነቢዩ አባት፣ አያትና ቅድመ አያቶች እስከ ነቢዩ አደም (ዐ.ሰ) በሙሉ ከአላህ ጋር የማያሻርኩ በተውሂድ አማኞች እንደነበሩ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ነቢዩ ኢብራሒም (ዐ.ሰ) ከአማኝ አባት የተገኙ አንደሆኑ እንረዳለን፡፡ ታሪክ እንደሚያሳየን አባቱ በተውሂድ አማኝ ሆነው እንደሞቱ ነቢዩ ኢብራሒም በአጎታቸውም አሳዳጊነት ስር ለመሆን እነደበቁና ይህ አጎታቸው በቁርአን ውስጥ አባት ተብለው እንደተሰየሙ እንገነዘባለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሲከላከሉና ሲጠብቁ የኖሩትን ለቁሬይሾች አሳልፈው ለመስጠት አሻፈረኝ ብለው እስከመጨረሻው የፀኑትና እሜቴ ኸዲጃ ከዚህ ዓለም በሞት በተለዩበት ዓመት ውስጥ ያረፉትና ነቢዩም «የሐዘን ዓመት» በማለት የሰየሙት የዓሊ አባት ታላቁ አቡ ጧሊብ አማኝ ሆነው ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ ምክንያታዊ የሆነ አስተሳሰብ ይነግረናል፡፡ በአንዳንድ ሰሂህ በተባሉ ሐዲሶች ውስጥ አላህ እየቀጣቸው ነው ተብሎ የተነገሩ ወሬዎች እንደ ትክክለኛ መቆጠር የለባቸውም፡፡ በጊዜው የነበረው ፖለቲካ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ለመበረዝና ለመፈብረክ ትልቅ ሚና የተጫወተና እንደ ዓሊ ያሉ የኢስላም ታላቅ ሰዎችን ለግድያ ያበቃ ስለሆነ የእንዲህ ዓይነቶቹ ሐዲሶች የትረካ ሰንሰለት መጠርጠርና መፈተሽ አለበት፡፡

የአቡ ጧሊብ መጠሪያ ስም አብደልሙናፍ ወይም ኢምራን ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተልዕኮአቸውን ከመጀመራቸው በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ በአጠቃላይ

ለአርባ ሁለት ዓመታት ከሳቸው ጎን የቆሙና ድጋፍ ይሰጧቸው የነበሩ የኢስላም ባለውለታ ናቸው አቡ ጧሊብ፡፡ እንዲህም ተብሎላቸዋል፡-

»የነቢዩን ሐዲሶች የሚያነብ ማንኛውም ሰው አቡ ጧሊብ ባይኖር ኖሮ ኢስላም ዕድገቱን መቀጠል የማይችል የነበረ እንደሆነ ይገነዘባል፡፡« *(ሸርህ ነህጀል በላጋህ - ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ 1፡142)*

አቡ ጧሊብ ለኢስላም ኃይማኖትና ለአላህ አንድነት እምነት ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ሰጥተው እንደነበረና አማኝ እንደነበሩ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

## *የቅዱስ ቁርአን መበረዝ አሉባልታ*

ከኃያሉ አላህ ወደ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የተወረደ አንድ ቁርአን ብቻ ይገኛል፤ የተጨመረም ሆነ የተሰረዘ፣ የተቀየረም ሆነ የተበረዘ አንድም አያህ የለም፡፡

**إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ(٩)**

«***እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፡፡ እኛም ለእርሱ ጠባቂዎቹ ነን፡፡***» (15፡9)

በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንድ ሙስሊሞች የአህለልቤይት ተከታዮች የራሳቸው የተለየ ቁርአን አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡ ነገር ግን የሺዓ መስጂዶችን፣ ቤቶቻቸውን መይም ኢስላማዊ ማዕከላታቸውን ቢጎበኙና ግለሰቦችንም ቢያገኙ ይህ ውንጀላ መሠረተ ቢስ መሆኑን በተገነዘቡ ነበር፡፡ ከታዋቂ የሺዓ ሐዲስ ዘጋቢዎች አንዱ የሆነው ሙሐመድ ኢብን ዓሊ አል-ቁሚ አል-ሱዱቅ ሲያረጋግጡ፡- «ከኃያሉ አላህ ወደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወረደውን ቁርአን አስመልክቶ ያለንን እምነት ዛሬ በእጃችን ያለውን በሁለቱ ሽፋኖች መካከል ያለውን አንድ ቁርአን መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ የሚጨምርም ሆነ የሚያንስ ቁርአን የለንም፡፡ እኛ ከምንለው ውጭ በኛ ላይ የሚለጥፍ እሱ ውሸታም ነው» *(ኢዕቲቃዳት አል-ሱዱቅ ገጽ 164)*

ቁርአን በትክክል የመተላለፉን ጉዳይ በተመለከተ ሺዓዎች ምንጊዜም ቢሆን ጉዳያቸው አድርገው ነው የኖሩት፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ቁርአንን በአንድ ጥራዝ ሰብስቦ ሳይጨርስ ለሰላት ወቅት ካልሆነ በስተቀር መጎናጸፍያውን እንደማይልበስ ምሎ ነበር *(ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂአል - ሒንዲ - 13፡127)*፡፡

ነገር ግን በአንዳንድ ሰሂህ በተባሉ መጽሐፍት ውስጥ አንዳንድ ዘገባዎች ከቁርአን ምዕራፎች ወይም አንቀጾች የቀሩ ወይም የጠፉ እንዳሉ አድርገው ያትታሉ፡፡ ለምሳሌ ኢማም ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ መሠረት፡- «በእውነቱ አላህ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) በሐቅ ላካቸው፣ መጽሐፍንም በሳቸው ላይ አወረደ፡፡ በሳቸው ላይ በተወረደው መጽሐፍ ውስጥም የመውገር አንቀጽ (አያህ አል-ረጂም) ነበር፡፡ ቀርተን (አንብበን) በጭንቅላታችንም ይዘን (ሐፍዘን) እንዲሁም ተረድተን ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ዝሙት በፈጸመ ባለትዳር ላይ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ህግ አጽንተውም ነበር፡፡ ከሳቸውም በኋላ እኛም በህጉ ሠርተናል፡፡ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ሰዎች ይህን ረስተው በአላህ ኪታብ ውስጥ በድንጋይ የመወገር ቅጣት የለም ብለው አላህ ያስቀመጠውን ህግ በማጥፋት ከመንገድ እንዳያፈነግጡ እፈራለሁ፡፡ ትዳር እያላቸው ዝሙት የፈጸሙ ወንዶችም ሆነ ሴቶች እርግዝና ወይም እራስን መጋለጥ ማስረጃ ከተገኘባቸው በድንጋይ ወግሮ መግደል በአላህ የተቀመጠ ህግ ነው *(ሰሂህ ቡኻሪ - ስለ ቅጣት በሚያወሳው ክፍል - ሐዲስ #6327፣ #6328፤ ቁርአንና ሱንን አጥብቆ መያዝ በሚለው ክፍል - ሐዲስ #6778፤ ሰሂህ ሙስሊም - ስለ ቅጣት በሚያወሳው ክፍል - ሐዲስ #3291፤ አል-ቲርሚዚ - ሐዲስ #1351፣ 1352፣ አቡ ዳውድ - ሐዲስ #3835፤ ኢብን ማጃህ - ሐዲስ #2543፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡23, 29, 36, 40, 43, 47, 50, 55፤ ማሊክ - ሐዲስ #1295፣ 1297፤ አል-ደረሚ - ሐዲስ #2219)*

ሌሎችም ዘገባዎች ቅዱስ ቁርአን ውስጥ ዝሙተኞችን የመውገር አንቀጽ የነበረ ስለመሆኑ በስህተት ይጠቁማሉ፡፡ ኢማም ቡኻሪ ከአንዱ ሰሃባ በዘገቡት መሠረትም ዘርን ወይም ዝምድናን ማጥፋትና መካድ ኩፍር (ከሃዲነት) እንደሆነ የሚገልጽ የቁርአን አንቀጽ እንደነበረ ይተርካሉ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አል-ፈራኢድ - 8፡540)፡፡*

ነገር ግን እንደዚህ የሚባል የቁርአን አንቀጽ እንደሌለ ሁሉም ሙስሊሞች ያውቃሉ፡፡ ከሌሎች ምንጮች የተገኙ ሌሎች ዘገባዎችም በርካታ የቁርአን አንቀጾች እንደጠፉ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ እሜቴ አኢሻ ሲናገሩ ሱራህ አል-አህዛብ (33) በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን 200 አያዎች እንደነበሩትና ነገር ግን ሦስተኛው ኸሊፋ ዑስማን ኢብን አፋን ቁርአንን የመሰብሰብ ሥራ ሲሰሩ 73 አያዎችን ብቻ ማግኘት እንደቻሉ ተተርኳል፡፡ *(ሱዩጢ - አል-ኢትቃን ፊ ዑሉም አል-ቁርአን 1፡63)*

አብደላህ ኢብን ዑመርም ሲናገሩ፡- *«ማንም ሰው ከሙሉ ቁርአን ፍርድ አግኝቼአለሁ ብሎ ሊያወራ አይችልም፡፡ ይህ ሙሉ ቁርአን ስለመሆኑ እንዴት ሊያውቅ ይችላል? በእውነቱ ከቁርአን ውስጥ ብዙ የጠፋ አለ»* በማለት ተርከዋል *(አል-ኢትቃን ፊ ዑሉም አል-ቁርአን - ሱዩጢ 3፡81)*

እዚህ ጋ መጥቀሱ አስፈላጊ ያልሆኑ ሌሎች አስተያየቶችም አሉ፡፡

## የፋጢማ ሙስሐፍ

በአህለልቤይት (ዐ.ሰ) ዘገባዎች መሠረት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ጊዜ ልጃቸው እሜቴ ፋጢማ (ዐ.ሰ) በከፍተኛ ሐዘን ውስጥ ስለነበረች አላህ የሚያጽናናትን መላኢካ ልኮላት እንደነበረና መላኢካውም ወደፊት የሚሆነውን ነገር ይነግራት እንደነበረ ይነገራል፡፡ እሷም በዚህ ብስራት በጣም ትጽናና ነበር፡፡ ባለቤቷ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ደግሞ

ይህንን መላኢካው የተናገረውን ነገር በሙሉ በማስታወሻ ጽፎ ነበር፡፡ እነዚህ ጽሑፎች ሙስሐፍ ፋጢማ በተባለ መጽሐፍ ውስጥ ተሰብስበው ነበር፡፡ ኢማም ሳዲቅ (ዐ.ሰ) ስለዚህ መጽሐፍ ሲናገሩ፡- «*በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሐራምና ሐላል ነገር የለም፡፡ ወደ ፊት ስለሚሆን ነገር ብቻ ነው ያለው*» ብለዋል *(አል-ካፊ አል-ኩለይኒ - ኪታብ አል-ሑጃህ - ገጽ 240)*፡፡ ሌሎች ዘገባዎች እንደሚሉት ደግሞ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ወህይ በወረደላቸው ቁጥር ልጃቸውን ያስተምሩና ነገሩን ሁሉ ይገልጹለት ስለነበረ እሷ ደግሞ ሙስሐፍ ፋጢማ ለመባል በበቃው መጽሐፍ ውስጥ ትጽፍ እንደነበረ ይጠቀሳል፡፡ የአህለልቤይት (ዐ.ሰ) ተከታዮች በአሁኑ ጊዜ ይህ መጽሐፍ የአህለልቤይት መዝሐብ የመጨረሻው ኢማም ጋር እንዳለ ያምናሉ፡፡

ሙስሐፍ ፋጢማ ቁርአን አይደለም፡፡ የአህለልቤይት ተከታዮች ያላቸው ብቸኛው ቁርአን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በህይወት እያሉ የወረደላቸውና በአሁኑ ወቅት በመላው ዓለም ላይ የሚገኘውን ቁርአን ነው፡፡

## *በነቢያትና በኢማሞች አቆራኝቶ ስም ማውጣት*

የአህለልቤይት (ዐ.ሰ) መዝሐብን የሚከተሉ አንዳንድ የሙስሊም ቤተሰቦች ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ እንደ አብደል ነቢ፣ አብደል ረሱል፣ አብደል ሁሴይን፣ አብደል ሪዳ እና የመሳሰሉ ስሞችን ከነቢያትና ኢማሞች ጋር አቆራኝተው መሰየም የተለመደ ነው፡፡ ምንም እንኳ በ ‘አብድ’ የሚጀምሩ ስሞችና ሙሐመድ የተመረጡ ስሞች እንደሆኑ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቢናገሩም ቀደም ሲል የተጠቀሱ ዓይነት ስሞችንም መጠቀም በላይ ላይ ትርጉሙ እስካልታሰበ ድረስ ክፋት የለውም፡፡ በእንዲህ ዓይነቱ ስም የተሰየመ ልጅ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ወይም የኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ወይም የኢማም ሪዳ (ዐ.ሰ)

ባሪያ ነው ለማለት እንዳልሆነና ነቢያቱ (ዐ.ሰ) ወይም ኢማሞቹ (ዐ.ሰ) ፈጣሪዎቻቸው ናቸው ማለት እንዳልሆነ በግልጽ የሚታወቅ ነገር ነው፡፡ ይልቁንስ ለልጆች እንዲህ ዓይነቱን ስም ማውጣት ዕድሜያቸውን ሙሉ ለሰው ልጆች ደህንነት መስዋዕት ያደረጉትን ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ኢማሞቹን (ዐ.ሰ) ማመስገን፣ ማድነቅና መውደድ የሚገለጽበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርአን ራሱ 'አብድ' የሚለውን ቃል «የአላህ ባሪያ» ከሚለው ትርጉም ባሻገር ሲጠቀም እናያለን፡፡ ለምሳሌ «ሚን ኢባዲኩም (ከወንድ ባሮቻችሁ)» የሚለው ሐረግ ባሮቹ ጌቶቻቸውን ያመልካሉ በሚለው ትርጉም እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ እውነተኛው አገልጋይነትና ጌትነት የአላህ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በምሳሌያዊ አነጋገር ወይም በአውደ ትርጉሙ ሲታይ 'አብደል ረሱል' የሚለው ስም የሚያመለክተው በዚህ ስም የሚጠራው ሰው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኩል የአላህ ባሪያ መሆኑን ነው፡፡ የአላህ ቁርአንም እንዲህ ይላል፡-

**وَأَنْكِحُوا الْأَيَامَىٰ مِنْكُمْ وَالصَّالِحِينَ مِنْ عِبَادِكُمْ وَإِمَائِكُمْ إِنْ يَكُونُوا فُقَرَاءَ يُغْنِهِمُ اللَّهُ مِنْ فَضْلِهِ وَاللَّهُ وَاسِعٌ عَلِيمٌ(٣٢)**

«***ከናንተም ትዳር የሌላቸውን አጋቡ፡፡ ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የኾኑትን (አጋቡ)፡፡ ድኾች ቢኾኑ አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል፡፡ አላህም ስጦታው ሰፊ ዐዋቂ ነው፡፡***» (24፡32)

በተጨማሪም »ባሪነት« የሚለው ቃል እንደ አገባቡ ትርጉም ሊሰጠው ይገባል፡፡ እንዲህ ዓይነት አባባሎች በዕለት ዕለት መግባቢያ ውስጥ የተለመዱ ናቸው፡፡ አንዳንዴ ሰዎች «ሰይዲ (የኔ ጌታ)» የሚለውን ሐረግ ለትህትና መግለጫ ሲጠቀሙ ይስተዋላል፡፡ ወይም ደግሞ አንዳንዴ ሰዎች የላይ ላይ ትርጉሙን ሳያስቡ «ጁኢልቱ ፊዳካ (እኔ ለአንተ ልሰዋ)» ሲሉ ይደመጣሉ፡፡

በአረብኛ ቋንቋ ውስጥ እነዚህ አባባሎች ምስጋናና አክብሮትን ለመግለጽ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድን ሰው ‘አብደል ረሱል’ ወይም ‘አብደል ሁሴይን’ ብሎ መሰየም ሽርክ (በአላህ ማጋራት) ሊሆን አይችልም፡፡ አምልኮና መታዘዝ የሚገባው ኃያሉ አላህ ብቻ እንደሆነ ሁሉም ሙስሊሞች የሚስማሙበት ጉዳይ ነውና፡፡

## የነቢያትንና የኢማሞችን መካነ መቃብሮች መጎብኘት

በተመሳሳይ ሁኔታ የቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና የኢማሞችን (ዐ.ሰ) መቃብሮች መንካትና መሳም ያንን ሰው ከአላህ ጋር አሻርኮ ማምለክ (ሽርክ) ሊሆን አይችልም፡፡ በዚህ ዩኒቨርስ ውስጥ ብቸኛ ሉዓላዊነት ያለው አላህ ብቻ በመሆኑ ሙስሊሞች የሚያመለኩትና ዕርዳታ የሚሹት ከሱ ከአንድ አላህ ብቻ ነው፡፡ መቃብሮችን መጎብኘት ለሰዎቹ ያለንን ክብር ከመግለጽ ያለፈ ነገር የለውም፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወይም ኢማሞቹ (ዐ.ሰ) በህይወት ቢኖሩ ኖሮ ሰዎች ከማድነቅና ከመውደድ የተነሳ ከነርሱ ጋር እጅ ይጨባበጡና ይስሟቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ሙታን ስለሆኑና መቃብራቸው የተቀደሰ ሰውነታቸውንና እንዲሁም ነፍሶቻቸውን የያዙ እንደሆኑ ስለሚያውቁ መቃብሮቹን መንካትና መሳም ለመሪዎቻቸው ታማኝነታቸውንና ቃል ኪደናቸውን የሚያድሱበት መንገድ ነው፡፡ ደሪሆቹ ከእንጨት ወይም ከብረት የተሠሩና ምንም ጥቅም ሊያስገኙ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ውዴታውና ክብሩ በውስጣቸው ለያዟቸው የቅዱሱ ነቢይና (ዐ.ሰ) የኢማሞች ነፍሶች ነው፡፡ በተጨማሪም ደሪሆቹ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ለኢማሞቹ (ዐ.ሰ) ያላቸው ቅርበት የተቀደሱና ቅዱስ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

ቅዱስ ቁርአን እንደሚያስተምረን ነቢዩ ያዕቆብ (ዐ.ሰ) ከልጃቸው ከነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) በመለየታቸው ሲያለቅሱ ዓይናቸውን ባጡ ጊዜ፣ ነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) በአንዱ ወንድማቸው አማካይነት ሸሚዛቸውን በመላክ የአባታቸው ዓይን መልሶ ብርሃን ይዘራ ዘንድ ሸሚዙን በፊታቸው ላይ እንዲያደርግ ነገሩት፡-

**اذْهَبُوا بِقَمِيصِي هَٰذَا فَأَلْقُوهُ عَلَىٰ وَجْهِ أَبِي يَأْتِ بَصِيرًا وَأْتُونِي بِأَهْلِكُمْ أَجْمَعِينَ(٩٣) وَلَمَّا فَصَلَتِ الْعِيرُ قَالَ أَبُوهُمْ إِنِّي لَأَجِدُ رِيحَ يُوسُفَ لَوْلَا أَنْ تُفَنِّدُونِ(٩٤) قَالُوا تَاللَّهِ إِنَّكَ لَفِي ضَلَالِكَ الْقَدِيمِ(٩٥) فَلَمَّا أَنْ جَاءَ الْبَشِيرُ أَلْقَاهُ عَلَىٰ وَجْهِهِ فَارْتَدَّ بَصِيرًا قَالَ أَلَمْ أَقُلْ لَكُمْ إِنِّي أَعْلَمُ مِنَ اللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ(٩٦)**

***«ይህንን ቀሚሴን ይዛችሁ ሊዱ፡፡ በአባቴ ፊትም ጣሉት የሚያይ ሆኖ ይመጣልና፡፡ ቤተሰቦቻችሁንም ሰብስባችሁ አምጡልኝ» (አላቸው)፡፡ ግመል ጫኞቹም (ምስርን) በተለዩ ጊዜ አባታቸው «እኔ የዩሱፍን ሽታ በእርግጥ አገኛለሁ፡፡ ባታቄሉኝ ኖሮ (ታምኑኝ ነበር)» አለ፡፡ «በአላህ እንምላለን አንተ በእርግጥ በቀድሞው ስህተትህ ውስጥ ነህ» አሉት፡፡ አብሳሪውም በመጣ ጊዜ (ቀሚሱን) በፊቱ ላይ ጣለው፡፡ ወዲውም የሚያይ ኾነ፡፡ «እኔ ለእናንተ፡- ከአላህ በኩል የማታውቁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን» አላቸው፡፡***

የዩሱፍ (ዐ.ሰ) ሸሚዝ ሰዎች በዛን ወቅት የሚለብሱት ከተለመደ ጥጥ የተሠራ ቢሆንም የዩሱፍን ገላ በመንካቱ አላህ በረከት እንዲኖረው በማድረጉ በአላህ ፈቃድና ስልጣን በረከቱ በሸሚዙ ላይ ተጽዕኖ እንዲያደርግ በማድረግ በነቢዩ ያዕቁብ (ዐ.ሰ) ፊት ላይ በተደረገ ጊዜ ለማየት እንዲችሉ አድርጓቸዋል፡፡

የቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወይም የኢማማን ዓሊን (ዐ.ሰ) ወይም የኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) ደሪሆች ከብረት የተሠራ በመሆናቸው መንካቱ ሽርክ ከሆነ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሙስሊሞች የቅዱሱን ካዕባ ድንጋዮች የሚነኩት ለምንድን ነው? እነዚህ ድንጋዮች ከጀነት የመጡ ናቸው ወይስ ከሂጃዝ የመጡ ተራ ድንጋዮች ናቸው? ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሐጀረል አስወድን (በካዕባ ላይ ያለውን ጥቁር ድንጋይ) እንደሳሙ ሁሉም ሙስሊሞች ይስማማሉ፡፡ ነገር ግን ምንም እንኳ በመካ ጎዳናዎችና በአካባቢው ያሉ ድንጋዮች ከጥቁሩ ድንጋይ የበለጠ ማራኪ ቢሆኑም እየዞሩ የሳሙበት ጊዜ አልተገኘም፡፡ ዛሬ ሙስሊምም ሆነ ሙስሊም ባልሆኑ አብዛኛው ሀገራት ባንዲራ የተቀደሰ ነገር በመሆኑ የተነሳ ወታደሮችም ሲቪሎች ይስሙታል፣ ፊታቸውም ላይ ያደርጉታል፡፡ ይህ ማለት ቁራጭ ልብስ እያመለኩ ነው ማለት ነው?በጭራሽ እንዲህ ሊሆን አይችልም፡፡

ከእነዚህ ምሳሌዎች ጀርባ ያለው ሐሳብ ከድንጋዩ፣ ከመቃብሮቹ (ደሪሆቹ) እንዲሁም ከባንዲራው ጀርባ ያለውን ሐሳብ ማክበር፤ ማላቅና በታላላቅ መሪዎችና ሀገራት የተቀመጡ መመሪያዎች መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፡፡

በኢማም ቡኻሪ ዘገባ መሠረት ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ውዱእ ባደረጉ ቁጥር ሙስሊሞቹ የውሃውን እንጥብጣቢ በመሰብሰብ ለበረከት ሲሉ ፊታቸውን ይቀባቡ እንደነበረ ተጠቅሷል *(ሰሂህ ቡኻሪ - ኪታብ አል-ሊባስ - 7፡199)*፡፡ በተጨማሪም የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ላብ ሳይቀር ይሰበሰብ እንደነበረ ቡኻሪ ዘግቧል፡- «ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተኙ ጊዜ ኡሙ ሰለማ ጨርቅ እስራቸው ታስቀምጥ ነበር፡፡ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰውነት ብዙ ላብ ይወጣ ነበር፡፡ ጠርሙስ አምጥታ ከጨርቁ ወደ ጠርሙሱ ታንቆረቁር ነበር፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንቅልፋቸው ሲነቁ እንዲህ አሏት፡- ኡሙ ሰለማ፡- ይህ ምንድን

ነው?» በዚህ ጊዜ ኡሙ ሰለማ፡- «ይህ ከሽቶአችን ጋር የምንደበልቀው የርስዎ ላብ ነው፤ ሽታውን እጅግ መልካም የሆነ መዓዛ ያለው ይሆንልናል» *(ሰሂህ ቡኻሪ - 'ፈቃድ መጠየቅ' በሚለው ክፍል ውስጥ  - ሐዲስ #5809፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ አል-ፈዳኢል - ሐዲስ #4302፣ አል-ኒሳኢ - ስለ ጌጥና ማጌጥ በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ #5276፣ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - 3፡103, 136, 221, 230, 231, 287, 6፡376)፡፡*

## *ሰደቀላሁል ዓዚም ወይስ ሰደቀላሁል ዓሊዩል ዓዚም?*

በመሠረቱ ሰደቀላሁል ዓዚም (ታላቅ የሆነው አላህ እውነት ተናገረ) ማለትና ሰደቀላሁል ዓሊዩል ዓዚም (ታላቅና የላቀው አላህ እውነት ተናገረ) በማለት መካከል ጭብጥ የሆነ ልዩነት የለም፡፡ እናም ይህ ጉዳይ በሁለቱም አባባሎች መጠቀም የተለመደ እስከነበረ ድረስ በሁለቱ መዝሐቦች መካከል ከሚነሱ ልዩነቶች ቦታ የማይሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በሱኒም ሆነ በሺዓ መዝሐብ በሁለቱም መልኩ መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን የሁለቱም አባባሎች ምንጭ ቅዱስ ቁርአን በመሆኑ በአንዳንድ ሙስሊሞች አዕምሮ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን መቅረፍና 'ዓሊይ' የሚለው ቃል ኢማም ዓሊ ኢብን አቢ ጧሊብን (ዐ.ሰ) ያመለክታል ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ከስህተታቸው ያጸዳቸዋል ብለን እናምናለን፡፡ 'ሰደቀላሁ' የሚለው የመጀመሪያው ሐረግ በቁርአን ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች ላይ እናገኛለን፡-

**قُلْ صَدَقَ اللَّهُ فَاتَّبِعُوا مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ(٩٥)**

«*«አላህ እውነትን ተናገረ፡፡ የኢብራሂምንም መንገድ ወደ እውነት ያዘነበለ ሲኾን ተከተሉ፡፡ ከአጋሪዎቹም አልነበረም» በላቸው፡፡*» (3፡95)

‘ዓሊይ’ እና ‘ዓዚም’ ደግሞ ከዘጠና ዘጠኙ የአላህ ስሞች ውስጥ ናቸው፡፡ በቁርአን ውስጥ አላህ ስሙን ‘ዓዚም’ ከሚለው ቃል ጋር አቆራኝቶ ጠቅሷል (69፡33)፡፡ እንዲሁም ሁለቱን ቃላት አንድ ላይ አጣምሮ ሁለት ጊዜ ጠቅሷል (2፡255 እና 42፡4)፡፡ ‘አል-ዓሊይ’ የሚለው ደግሞ በበርካታ አያዎች ውስጥ ተጠቅሷል *(22፡62፣ 31፡30፣ 34፡23፣ 40፡12፣ 4፡34፣ 42፡51 እና ሌሎችም)*፡፡ ሁለቱን ቃላት (‘አል-ዓሊይ’ እና ‘አል-ዓዚም’) አንድ ላይ አጣምሮ መጥቀስ የኢማም ዓሊን (ዐ.ሰ) ስም በጭራሽ ሊያመላክት አይችልም፡፡ ይልቁንስ ይህ ቁርአን ላይ በመመርኮዝ አላህ በቁርአን ራሱን በገለጸበት መልኩ ኃያሉን አላህ መክበርና ማላቅ ነው፡፡

## *በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና በቤተሰባቸው ላይ በደረሰው አሳዛኝ ክስተት ማዘንና ማልቀስ*

በአጠቃላይ ቅዱስ ቁርአን ማልቀስና ለተገቢው ጉዳይ የሚያለቅሱ ሰዎችን ያወድሳል፡፡ ቅዱሱ ቁርአን በርካታ ነቢያትንና ተከታዮቻቸውን እንዲህ በማለት ይገልጻቸዋል፡-

**أُولَٰئِكَ الَّذِينَ أَنْعَمَ اللَّهُ عَلَيْهِمْ مِنَ النَّبِيِّينَ مِنْ ذُرِّيَّةِ آدَمَ وَمِمَّنْ حَمَلْنَا مَعَ نُوحٍ وَمِنْ ذُرِّيَّةِ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْرَائِيلَ وَمِمَّنْ هَدَيْنَا وَاجْتَبَيْنَا إِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ آيَاتُ الرَّحْمَٰنِ خَرُّوا سُجَّدًا وَبُكِيًّا(٥٨)**

«***እነዚህ እነዚያ አላህ በእነሱ ላይ የለገሰላቸው ከነቢያት ከአዳም ዘር ከኑሕ ጋር ከጫናቸውም (ዘሮች) ከኢብራሂምና ከእስራኤልም ዘሮች***

*ከመራናቸውና ከመረጥናቸውም የኾኑት የአልረሕማን አንቀጾች በነሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ ሰጋጆችና አልቃሾች ኾነው ይወድቃሉ፡፡*» (19:58)፡፡

አንዳንድ አማኞችንም በተመሳሳይ መልኩ ይገልጻቸዋል፡-

وَيَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ يَبْكُونَ وَيَزِيدُهُمْ خُشُوعًا(١٠٩)

«***ኢያለቀሱም በሸንገቦቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ (አላህን) መፍራትንም ይጨምርላቸዋል፡፡***»(17:109)፡፡

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለበርካታ የቤተሰባቸው አባላት እንዳለቀሱ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ ልጃቸው ኢብራሒም ከበርካታ ምሳሌዎች መካከል እንደ አንድ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ኢማም ቡኻሪ ሲዘግብ፡-

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- «*በዛሬው ዕለት ልጅ ተወለደልኝ፡፡ ስሙንም ልክ እንደ አባቴ ስም ኢብራሒም አወጣሁለት፡፡*» ከዚያም የአንጥረኛው አቡ ሰይፍ ባለቤት ወደነበረችው ኡሙ ሰይፍ ላኩት፡፡ ከዚያም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ እሱ ሄዱ፤ እኔም ተከተልኳቸው፡፡ ከዚያም አቡ ሰይፍ በወናፍ በመጠቀም እሳት ይነፋ ወደ ነበረበትና በጭስ ተሞልቶ ወደነበረው ቤት ደረስን፡፡ እርምጃዬን ፈጠን አድርጌ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀድሜ በመድረስ፡- «*አቡ ሰይፍ! አንዴ አቁመው! የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እየመጡ ነው*» አልኩት፡፡ እሱም አቆመ፤ የአላህ መልዕክተኛም (ሰ.ዐ.ወ) ልጁ እንዲቀርብላቸው ተጣሩ፡፡ እቅፍ አደረጉትና አላህ ያሻውን ተናገሩ፡፡ ልጁ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉበት የመጨረሻ እስትንፋስ ሲተነፍስ አይቻለሁ፡፡

የአላህ መልዕክተኛ ዓይኖች እምባ አዘነቡ፤ እንዲህም አሉ፡- «*ኢብራሒም ሆይ! ዓይኖቻችን እምባ አፈሰሱ፣ ልባችንንም ሐዘን ዋጠው፤ አላህ ከሚወደው*

*ነገር ውጭ ግን የምንለው ነገር የለም፡፡ ኢብራሒም ሆይ! በጣም አዝነንልሃል»* *(ሰሂህ ቡኻሪ - ስለ ሐዘን በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ሐዲስ #1220፣ ሰሂህ ሙስሊም - ኪታብ አል-መናቂብ - ሐዲስ #4279፤ አቡ ዳውድ - ሐዲስ #2719፤ ሙስነድ አህመድ ኢብን ሐንበል - 3፡194)*

በተጨማሪም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለአጎታቸው ሐምዛ እንዳለቀሱና እጅግ እንዳዘኑ ተዘግቧል፡- «ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከኡሑድ ዘመቻ በተመለሱ ጊዜ የአንሷር ሴቶች ለተሰውት ባሎቻቸው ምርር ብለው ሲያለቅሱ ባዩ ጊዜ ቆም ብለው እንዲህ አሉ፡- «*ለኔ አጎት ለሐምዛ ግን የሚያለቅስ የለም፡፡*» በዚህ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰዎች ለአጎታቸው እንዲያለቅሱ መፈለጋቸው ተረዱና ማልቀሱን ተያያዙት፡፡ ለሌሎቹ ማልቀሳቸውን አቁመው ሁሉም ለሐምዛ ያለቅሱ ገቡ፡፡» *(ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - ቅጽ 2)*

ለአጎታቸው ልጅ ለጃዕፈር ቢን አቢ ጧሊብና ለልጅ ልጃቸው ኢማም ሁሴይንም (ዐ.ሰ) እንዲሁ ማልቀሳቸው ይጠቀሳል *(ሰሂህ ቡኻሪ - 1፡152፤ ሰሂህ ሙስሊም ቅጽ 1 - ለሞቱት ስለማልቀስ በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የእናታቸውን የአሚናን መቃብር በመጎብኘት እንዳለቀሱና በአካባቢው የነበሩትን ሰዎች እንዳስለቀሱ ተነግሯል፡፡ ሸርህ ነህጀል በላጋ - ኢብን አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዚሊ - 3፡387)*

እሜቴ አኢሻ እንደተረኩት - ሁሴይን ልጅ በነበረ ጊዜ አንድ ቀን መጣና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታፋ ላይ ቁጭ አለ፡፡ በዚህን ጊዜ ጂብሪል ወረደና ከነቢዩ ኡማ የሆኑ ሰዎች እንደሚገድሉት (ሁሴይንን ማለት ነው) ነገራቸው፡፡ ከከርበላ ምድር የሆነ የአፋር ናሙና ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰጣቸውና ቦታውም «አል-ጠፍ» እንደሚሰኝ ነገራቸው፡፡ ጂብሪል ከሔደ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አፈሩን ይዘው ወደ ሰሃቦቻቸው ወጡ፡፡ በቦታውም የነበሩ አቡ በክር፣ ዑመር፣ ዓሊና ሁዘይፋ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያለቅሱ አዩ፡፡ ለምን ያለቅሱ እንደነበረም ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ መለሱ፡-

«ልጄ ሁሴይን በአል-ጠፍ ምድር እንደሚገደል ጂብሪል ነገረኝ፡፡ ይህንንም አፈር ከዛ ቦታ አመጣልኝ፡፡ የመጨረሻ እረፍቱ እዛ ቦታ እንደሚሆንም አጫወተኝ *(አዕላም አል-ኑቡወህ - አል-ማወርዲ አል-ሻፊኢ፤ ከንዝ አል-ዑማል - አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ - የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት የነበረችዋን ኡሙ ሰላማን በመጥቀስ)*

የኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) አሟሟትና አሳዛኝ ታሪክ በአላህ መንገድ ውስጥ የተደረገ ታላቅ መስዋዕትና ወደር የለሽ ትግል መሆኑ ታሪክ ያለ ጥርጥር የመሰከረው ጉዳይ በመሆኑ ለዚህ ኢማም (ዐ.ሰ) ማልቀስና በታሪኩ አሳዛኝ ክስተት ላይ ሐዘንን መግለጽ ወደ አላህ መቃረብን መሻት እንደሆነ
ይታመናል፡፡ ይህንን ማድረግ አላህን ማስታወስና የልጃቸውን እጣ ፋንታ ቀድመው አውቀው ገና ሲወለድ፣ የሚጫወት ህጻን ሆኖ ሳለና የህይወታቸው ፍጻሜ አካባቢ ወቅትም እጅግ ያለቀሱለትን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሱና መተግበር እንጂ ሌላ አይደለም፡፡
ሰዎች ሐዘንና ችግር ባጋጠማቸው ወቅት ለሚወዷቸውና ለሚሳሱላቸው ሰዎች ማዘንና ማልቀስ ተፈጥሮአዊ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ቅዱስ ቁርአን ሲናገር፡-

**قُلْ لَا أَسْأَلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا الْمَوَدَّةَ فِي الْقُرْبَى**

***«በእርሱ (መልክቱን በማድረሴ) ላይ ለቅርብ ዘመድ ውዴታን እንጅ ዋጋን አልጠይቃችሁም» በላቸው፡፡*** » (42፡23)

እላይ የተጠቀሰው የቁርአን አያህ የሚመለከተው አህለልቤይት- ዓሊ፣ ፋጢማ፣ ሐሰንና ሁሴይን መሆኑን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሙስሊሞች በግልጽ ተናግረዋል፡፡ *(ለተጨማሪ መረጃ ስለ አህለልቤይት የሚያወሳውን ክፍል ይመልከቱ፡፡)*
ለነዚህ ግለሰቦች ፍቅርና ርህራሄን ማሳየትና የገጠማቸውን መከራ መቋቋማቸውን በመዘከር ደረጃቸውን መረዳት በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ

በአላህ የተደነገገ ግዴታ ነው፡፡ ከአህለልቤይት አባላት አንድም ሰው የተፈጥሮ ሞት የሞተ የለም፡፡ ሁላቸውም ወይም ተመርዘው አሊያም ለኢስላም ሲታገሉ በሰይፍ ተወግተው የተሰዉ ናቸው፡፡ ላጋጠማቸው አሳዛኝና አስከፊ ክስተት ሐዘን የማይሰማውና የማይታመም ሰው ሊኖር አይችልም፡፡ የአሹራን አሳዛኝ ታሪክ ሰምቶ የማያለቅስ ከቶ ማን አለ?

ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) 72 የሚሆኑ የቤተሰቦቻቸውን አባላትና ተከታዮቻቸውን ለአላህ መንገድ መስዋዕት ሲያደርጉና በአሰቃቂ ሁኔታ ሲገደሉ፣ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች ምርኮኛ ሆነው ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ እየተንገተቱና እየተነዱ ሲወሰዱና በቃላት የማይገለጽ እንግልትና መከራ ሲደርስባቸው፣ የኢማም ሁሴይንና የተከታዮቻቸውን የተቆረጡ ጭንቅላቶች አጅበው በረሃ ለበረሃ ሲንከራተቱ ያየና የሰማ ሰው እንዴት አያለቅስ? ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች እንኳ ይህንን ታሪክ ሲማሩ ተንሰቅስቀው ያለቅሳሉ፡፡ ሙስሊሞች ለቤተሰቦቻቸውና ለዘመዶቻቸው የሚያለቅሱ ከሆነ ለቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች እንዴት አያለቅሱም? ኢማም ሁሴይን (ዐ.ሰ) የሞቱት እንዲለቀስላቸው አልነበረም፤ የኢስላምን መልዕክት ለማዳን ጭቆናንና ሙስናን እንዲሁም ብልሹ አስተዳደርን ሲወጉ ነው ህይወታቸውን የሰጡት፡፡ ነገር ግን ይህ እምባና ሐዘን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) የቤተዘሩን ፋና ለመከተል ቃልኪዳን የሚታደስበት ሰላማዊ መሣሪያ ነው፡፡ ሁሴይንና ሌሎችም የአህለልቤይት አባላት ለደረሰባቸው የግፍ ታሪክና አሳዛኝ ክስተት ርህራሄ ማሳየትና ሐዘን መግለጽ ፈጠራም አይደልም፤ ቢድዓም አይደለም፡፡ ነገር ግን የኢማም ሁሴይንን (ዐ.ሰ) መንገድ መከተልና ከተምሳሌቱ መጠቀም እንዲሁ ከማልቀስ ይልቅ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉም መገንዘብ አለበት፡፡

### *በአንድ ጊዜ ሦስት ፍቺዎች?*

በኢስላም ውስጥ ፍቺ በተቻለ መጠን እንዳይከሰት መከላከል ይገባል፡፡ በአላህ እይታ ህጋዊ ከሆኑ ተግባራት ሁሉ እጅግ የተጠላ ነገር ቢኖር ፍቺ እንደሆነ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መናገራቸው ተዘግቧል፡፡ ፍቺ መፈጸም ያለበት ሌሎች አማራጮች ሁሉ ከተሟጠጡ በኋላ የመጨረሻው አማራጭ ብቻ መሆን እንዳለበት ኢስላም ያስተምራል፡፡ ኢስላም ለፍቺ የሚዳርጉ ጉዳዮች ሲፈጠሩ ቤተሰብ ለአማላጅነት እንዲጠራ ያበረታታል፣

**وَإِنْ خِفْتُمْ شِقَاقَ بَيْنِهِمَا فَابْعَثُوا حَكَمًا مِنْ أَهْلِهِ وَحَكَمًا مِنْ أَهْلِهَا إِنْ يُرِيدَا إِصْلَاحًا يُوَفِّقِ اللَّهُ بَيْنَهُمَا إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا خَبِيرًا(٣٥)**

«*በመካከላቸውም ጭቅጭቅ ብታውቁ ከቤተሰቦቹ ሽማግሌን ከቤተሰቦችዋም ሽማግሌን ላኩ፡፡ ማስታረቅን ቢሹ አላህ በመካከላቸው ያስማማል፡፡ አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነውና፡፡*» (4፡35)

እንዲሁም ፍቺ መፈጸም ያለበት በተለያዩ ሦስት ጊዜያት ሲሆን በእያንዳንዱ ጊዜ መካከል የሦስት ወራት የመጠባበቂያ ጊዜ እንዲኖር ያሳስባል፡፡

**الطَّلَاقُ مَرَّتَانِ فَإِمْسَاكٌ بِمَعْرُوفٍ أَوْ تَسْرِيحٌ بِإِحْسَانٍ**

**فَإِنْ طَلَّقَهَا فَلَا تَحِلُّ لَهُ مِنْ بَعْدُ حَتَّىٰ تَنْكِحَ زَوْجًا غَيْرَهُ فَإِنْ طَلَّقَهَا فَلَا جُنَاحَ عَلَيْهِمَا أَنْ يَتَرَاجَعَا إِنْ ظَنَّا أَنْ يُقِيمَا حُدُودَ اللَّهِ وَتِلْكَ حُدُودُ اللَّهِ يُبَيِّنُهَا لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ(٢٣٠)**

«*ፍች ሁለት ጊዜ ነው፤ (ከዚህ በኋላ) በመልካም መያዝ ወይም በበጎ አኳኋን ማሰናበት ነው፡፡ ቢፈታትም ከዚህ በኋላ ሌላን ባል እስከምታገባ ድረስ ለርሱ አትፈቀድለትም፡፡*

*(ሁለተኛው ባል) ቢፈታትም የአላህን ሕግጋት መጠበቃቸውን ቢያውቁ በመማለሳቸው በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም፡፡ ይህችም የአላህ ሕግጋት ናት ለሚያውቁ ሕዝቦች ያብራራታል፡፡*» (2፡229 – 230)

በሚያሳዝን ሁኔታ አንዳንድ ሺዓ ያልሆኑ ሙስሊም የህግ ባለሙያዎች አንድ ባል ሚስቱን በአንድ ወቅት ሦስት ጊዜ መፍታቱን በመናገር መፍታት እንደሚችል ይፈቅዳሉ፡፡ ይህ ግን የቁርአንን ሐሳብ የሚጻረር ፍርድ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ በሰሂህ ኪታቦችና በሌሎችና (በሲራህ ኢብን ኢስሐቅ - 2፡191) ውስጥ ተዘግቦ እንደምናገኘው በአንድ ጊዜ ዘመን፣ ሶስት የፍቺ ቃለትን መናገር በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን፣ በመጀመሪያው ኸሊፋ ዘመንና በሁለተኛው ኸሊፋ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ዘመን እንደ አንድ ህጋዊ ፍቺ ይቆጠር እንደነበር ተዘግቧል፡፡ ከዚያ በኋላ ነው ሁለተኛው ኸሊፋ በአንድ ወቅት ሦስት የፍቺ ቃላት መናገር ሦስት ጊዜ እንደመፍታት መሆኑን የፈቀደውና ስለዚህም ሚስትም ወደ ባሏ መመለስ እንደማትችል የተፈረደው፡፡ *(ሰሂህ ሙስሊም - ስለ ሦስት ፍቺዎች በሚያወሳው ክፍል ውስጥ - 1፡575፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡314፤ አል-በይሐቂ - 7፡336)*

## *ኹምስ (አንድ አምስተኛ) በኢስላም*

ኹምስ በአላህ የታዘዘና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን የተተገበረ ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ነው፡፡ ኹምስ ማለት አንድ አምስተኛ ማለት ሲሆን በቁርአን ትዕዛዝ መሠረት ከአንድ ሰው ትርፍ ገቢ አንድ አምስተኛው ቁርአን ለደነገገላቸው ክፍሎች መከፈል አለበት የሚል ህግ ነው፡፡

وَاعْلَمُوا أَنَّمَا غَنِمْتُمْ مِنْ شَيْءٍ فَأَنَّ لِلَّهِ خُمُسَهُ وَلِلرَّسُولِ وَلِذِي الْقُرْبَىٰ وَالْيَتَامَىٰ وَالْمَسَاكِينِ وَابْنِ السَّبِيلِ إِنْ كُنْتُمْ آمَنْتُمْ بِاللَّهِ وَمَا أَنْزَلْنَا عَلَىٰ عَبْدِنَا يَوْمَ الْفُرْقَانِ يَوْمَ الْتَقَى الْجَمْعَانِ وَاللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ(٤١)

«*ከማንኛውም ነገር ያገኛችሁት አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልክተኛው፣(ለነቢዩ)የዝምድና ባለቤቶችም፣ ለየቲሞችም፣ ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኛም የተገባ መኾኑን ዕውቁ፣ በአላህና በዚያም እውነትና ውሸት በተለየበት ቀን ሁለቱ ጭፍሮች በተገናኙበት ቀን በባሪያችን ላይ ባወረድነው የምታምኑ እንደኾናችሁ (ይህንን ዕወቁ)፡፡ አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው፡፡*» (8:41)

በአጭሩ ኹምስ ማለት አንድ ሰው ለራሱና ለሚያስተዳድራቸው ሰዎች የሚሆን ወጭ ከወሰደ በኋላ ከትርፍ ገቢው አንድ አምስተኛውን መክፈል ማለት ነው፡፡ ይህም ሁለት እኩል ክፍሎችን ያካትታል፡፡ አንዱ ክፍል የኢማሙ ድርሻ ሲሆን ይህም ለመስጊዶች ግንባታ፣ ለኢስላማዊ ሐውዛዎች (የኃይማኖት ትምህርት ተቋማት) ማሰሪያ፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለአብያተ መጽሐፍት፣ ለሆስፒታሎች፣ ለክሊኒኮች፣ ለወላጅ አልባ ህጻናት ማሳደጊያ ማዕከላት ግንባታዎችና ለቁርአን ህትመት፣ ለሐዲስ መጽሐፍት፣ ለኢስላማዊ መጽሐፍት ለሌክቸሮችና ሌሎች ኢስላምን ለማስፋፋትና ለመጠበቅ የሚረዱ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ማስኬጃ የሚውል ነው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ደሃ ለሆኑ ሰይዶች (የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዝርያ ለሆኑ ሰዎች) የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ ሰዎች ሰደቃ መቀበል ስለማይፈቀድላቸው ነው፡፡

ከተለያዩ መዝሐቦች የተገኙ የታሪክ ማጣቀሻዎች መሠረት ኹምስ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን እንደነበረና በመጀመሪያውና በሁለተኛው ኸሊፋዎች ዘመን እንደተከለከለ ይጠቅሳሉ *(ሱነን አል-በይሐቂ፣ ቅጽ 6፣ 'ሰህም ዚል ቁርባ' በተሰኘው ምዕራፍ ውስጥ፤ ሙስነድ አል-ሻፊዒ፣ ገጽ 187፤ ሱነን አቡ ዳውድ፣ ቅጽ 18 አል-ኹምስ፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡ 320፤ ከንዝ አል-ኡማል-አል-ሙተቂ አል-ሒንዲ፣ 2፡305፤ ሊሳል አል-ሚዛን - 6፡148፤ ሁልየት አቡ ኑዓይም፣ 2፡205፤ ሰሂህ ሙስሊም - 5፡ 198፣ ሱነን አል-ኒሳኢ - ገጽ 177, 178፤ ተፍሲር አል-ጠባሪ - 10፡5)*፡፡

በ8፡41 ውስጥ የተጠቀሰውን «ገኒምቱም» የሚለው ቃል በአህለልቤይት አተረጓጎም መሠረት ከጦርነትም ሆነ ከሥራ ወይም ከንግድ ሆነ ከሌሎች የገቢ ምንጮች የሚገኝ «ማንኛውም ያገኛችሁት ነገር» ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ አምስተኛ የወሰዱት በጦርነት ወቅት ከማረኩት ነገር ብቻ ሳይሆን በሰላሙም ጊዜ ከሌሎች የገቢ ምንጮችም እንደተቀበሉ ታሪክ ይመሰክራልና (ለተጨማሪ ማብራሪያ *ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡314፤ ሱነን ኢብን ማጃህ - ገጽ 839)* ሌሎች ሺዓ ያልሆኑ ምሁራንም ይህንን ሐሳብ ይጋራሉ፡፡ *(ኪታብ አል-ኸራጅ - አል-ቃዲ አቡ ዩሱፍ - ገጽ 25 – 27)*

## *ጊዜያዊ ጋብቻ (ሙትዓ)*

ስለጊዜያዊ ጋብቻ ህጋዊነት መነጋገር ማለት ወጣቱ በዚህ ተግባር ላይ እንዲነሳሳ ማበረታታት ሆኖ ፍጹም መታየት የለበትም፡፡ በቁርአን፣ በነቢዩና በአህለልቤይት ሐዲስ የሚበረታታው የጋብቻ ዓይነት ቋሚ የሆነው የተለመደው ጋብቻ ሲሆን ጊዜያዊ ጋብቻ አማራጭ ሆኖ የሚቀርበው ቋሚ ጋብቻን ለመፈጸም የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠርና አስቸጋሪ ሲሆን እንደ መጨረሻ አማራጭ መወሰድ የሚገባው ሥርዓት ነው፡፡ እዚህ ቦታ ላይ መነሳት

የተፈለገው የእንዲህ ዓይነቱን ጋብቻ ጥቅምና ጉዳት መተንተን ሳይሆን ከቁርአንና ሐዲስ አንጻር ህጋዊነቱን ለማረጋገጥ ነው፡፡

በኢስላም ጋብቻ የተቀደሰ ተቋም ነው - ሁለት ግለሰቦች ተፈቃቅደው፣ እርስበርሳቸው ሊከባበሩ፣ አንዱ የሌላውን ፍላጎት፣ ክብር፣ ፈቃድና ምኞት ሊያከብሩና ሊረዳዱ ቃል-ኪዳን የሚገባቡበት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም ሁለት ዓይነት ነው፡- ቋሚና ጊዜያዊ፡፡ ሁለቱም ተመሳሳይ መመሪያዎችንና ህግጋትን ይጋራሉ፡፡ ሁለቱም የተለመደና የታወቀ የመጠየቅና ጥያቄውን በአዎንታዊ መልኩ የመቀበልና በግልጽ የመፈቃቀድ መግለጫ ሥርዓት መፈጸምን ይሻሉ፡፡ ጋብቻውም- ቋሚውን ቢሆን- ለቅድመ-ሁኔታዎችና ገደቦች ክፍት የሆነ ሥርዓት ነው፡፡ ጋብቻው ቀነ ገደብ የማይደረግበት ከሆነ ቋሚ ያልነው ዓይነት ሲሆን ቀነ ገደብ የተቆረጠለት ከሆነ ደግሞ ጊዜያዊ ጋብቻ የምንለው ይሆናል፡፡

የሌሎች መዝሐቦች ምሁራን በሙተዓ (ጊዜያዊ ጋብቻ) ላይ ተቃውሞ ቢኖራቸውም አንድ ሰው ለተወሰነ የጊዜ ገደብ አንዲትን ሴት ካገባና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እንደሚፈታት ለሴቷ ሳይናገር ሐሳቡን ደብቆ ውሳኔውን ለራሱ ብቻ ምስጢር አድርጎ ከያዘ ጋብቻው ህጋዊ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የሙተዓ ጋብቻን በተመለከተ ሁለቱ ተጋቢዎች ቀደም ብለው በቅድመ-ሁኔታዎቹና ህግጋቱ ላይ በግልጽ ተስማምተው አውቀው ስለሚገቡበት የበለጠ ምክንያታዊ ሆኖ እናገኛለን፡፡ በመሠረቱ ሙትዓ በስምምነት ቀነ ገደብ የተደረገለት (ጊዜያዊ የሆነ) ህጋዊና ኖርማል ጋብቻ ነው፡፡ የዚህ ጋብቻ ቅድመ-ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ለጋብቻው ጥያቄ ማቅረብና (መጠየቅ) ጥያቄውን መቀበል መቻል፣ ለሴቷ ጥሎሽ (መህር) መከፈል አለበት፤ ሁለቱም ወገኖች መስማማት መቻል፣

ሁለቱም የመስማማት ወይም ያለመስማማት መብት አላቸው፤ ሁለቱም አዕምሮአዊ ጤንነት ሊኖራቸው ይገባል፤ ልጃገረዶች ደግሞ የአሳዳጊ ወይም የወላጅ ዕውቅናና ፈቃድ ሊታከልበት ይገባል፡፡ ነገር ግን በጊዜያዊ ጋብቻ (ሙትዓ) ውስጥ በስምምነት ውስጥ ተካቶ ካልተጠቀሰ በስተቀር የውርስና የቀለብ ወጭ ግዴታ የለም፡፡ ይህንን በተመለከተ ቁርአን ሲጠቅስ፡-

**وَالْمُحْصَنَاتُ مِنَ النِّسَاءِ إِلَّا مَا مَلَكَتْ أَيْمَانُكُمْ كِتَابَ اللَّهِ عَلَيْكُمْ وَأُحِلَّ لَكُمْ مَا وَرَاءَ ذَٰلِكُمْ أَنْ تَبْتَغُوا بِأَمْوَالِكُمْ مُحْصِنِينَ غَيْرَ مُسَافِحِينَ فَمَا اسْتَمْتَعْتُمْ بِهِ مِنْهُنَّ فَآتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ فَرِيضَةً وَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ فِيمَا تَرَاضَيْتُمْ بِهِ مِنْ بَعْدِ الْفَرِيضَةِ إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمًا(٢٤)**

«***ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዟቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው፡፡ (ይህን) አላህ በናንተ ላይ ጻፈ፡፡ ከዚህ (ከተከለከሉት) ውጭ ጥብቆች ኾናችሁ ዝሙተኞች ሳትኾኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ፡፡ ከእነሱም በርሱ (በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች ክፍያቸውን መስጠት ግዴታ ነውና ስጧቸው፡፡ ከግዴታው ባሻገር በኋላ በተስማማችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኀጢአት የለም፡፡ አላህ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና፡፡***» (4፡24)

በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ደግሞ በርካታ ሐዲሶች ስለዚህ ጋብቻ ህጋዊነት ይገልጻሉ፡፡ ኢማም ቡኻሪ ሲተርክ፡- የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) መልዕክት አስተላላፊ እነሆ ወደኛ መጣና እንዲህ አለ፡- «እነሆ የአላህ መልዕክተኛ ጊዜያዊ ጋብቻ ማለት የሴቶች ሙትዓ ትፈጽሙ ዘንድ ተፈቀደላችሁ፡፡» *(ሰሂህ ቡኻሪ - ጋብቻ - ሐዲስ #4725፤ ሰሂህ ሙስሊም - ጋብቻ - ሐዲስ #2494፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 4፡47, 51, 55)*፡፡

በሌላ ሐዲስም፡-

«ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ሁነን በአንድ ዘመቻ ላይ ነበርን፡፡ በወቅቱ ምንም ሴቶች ከኛ ጋር አልነበሩም፡፡ እንዲህም አልን፡- 'ራሳችንን ማኮላሸት አለብን እንዴ?' ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን እንዳናደርግ ከለከሉን፡፡ ከዚያም አብደላህ የሚከተለውን የቁርአን አያህ ቀራ፡-

**يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا لَا تُحَرِّمُوا طَيِّبَاتِ مَا أَحَلَّ اللَّهُ لَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ(٨٧)**

«***እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህ ለናንተ የፈቀደላችሁን መልካም ነገሮች እርም አታድርጉ፡፡ ወሰንንም አትለፉ፡፡ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና፡፡***» (5፡87)፡፡ *(ሰሂህ ቡኻሪ - ክፍል፡- የቁርአን ተፍሲር - ሐዲስ #4249፤ ክፍል፡- ጋብቻ -ሐዲስ #4683 እና 4686፤ ሙስሊም - ክፍል፡- ጋብቻ - ሐዲስ #2493፤ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል - 1፡385፣ 390፣ 420፣ 432፣ 450)*፡፡

ኢማም ቡኻሪ በዘገቡት መሠረትም፡-

ከአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ወደ በኒ ሙስተሊቅ ዘመቻ ላይ ነበርን፡፡ ሚስቶቻችን ከኛ ጋር ስላልነበሩ በጣም ተቸግረን ነበር፡፡ ስለዚህ ከሴቶች ጋር ጊዜያዊ ጋብቻ መፈጸም ፈልገን ነገር ግን ዓዝል መጠቀም እንዳለብን ወሰንን፡፡ ከዚያም እንዲህ ተባባልን፡- 'የአላህ መልዕክተኛ በመሐከላችን ባሉበት ሁኔታ አንድ ተግባር ከመፈጸም ለምን አንጠይቃቸውም?' ስለዚህ የአላህ መልዕክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ጠየቅናቸው፡፡ እሳቸውም እንዲህ አሉን፡- «*እንደዛ ባታደርጉም ግድ የለም፡፡ መወለድ ያለበት ነፍስ እስከ የውመልቂያማ ድረስ መወለዱ አይቀርምና፡፡*»

*(ሰሂህ ቡኻሪ - የሺያጭ ዓይነቶች - ሐዲስ #2077፤ ነፃ ማውጣት - ሐዲስ #2356፤ ሙስሊም - ጋብቻ - ሐዲስ #2599፤ አል-ቲርሚዚ - ጋብቻ - ሐዲስ #1057፤ አል-ኒሳኢ - ጋብቻ - ሐዲስ #3275፤ አቡ-ዳውድ - ጋብቻ - ሐዲስ #1855፣ 1856፣ 1857፤ ኢብን ማጃህ - ጋብቻ - ሐዲስ #1916፤ ሙስነድ አህመድ ቢኒ ሐንበል 3፡88፤ ማሊክ - ፍቺ - ሐዲስ #1090፤ አል-ዳረሚ - ጋብቻ - ሐዲስ #2126፣ 2127)*

ኢማም ሙስሊምም በበነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን ጊዜያዊ ጋብቻ ይፈጸም የነበረበትን አጋጣሚዎች በመተረክ *(ሰሂህ ሙስሊም - ጋብቻ - ክፍል 3 - ሐዲስ #15፣ 17)* በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን፣ በመጀመሪያው ኸሊፋ ዘመንና በሁለተኛው ኸሊፋ የተወሰነ ዘመን ህጋዊ ተግባር እንደሆነና ሁለተኛው ኸሊፋ በኋላ ላይ ክልክል እንዳደረጉት ማስረጃዎችን በመጥቀስ ዘግቧል፡፡ ከዚያም ጊዜ በኋላ ቢሆን እንደ ቁርጡቢ ያሉ የሱኒ ምሁራን ህጋዊ ጋብቻ ስለመሆኑ ያመኑበትና ቀጥሎ ያሉ ተተኪዎችና የተተኪዎቹ ተተኪዎች (ሰለፍና ኸለፍ) ህጋዊነቱ ላይ ተስማምተው እንደነበረ ያወሳል *(ተፍሲረል ቁርጡቢ - 5፡132፤ ተፍሲር አል-ጠበሪ)*፡፡

የአህለል ቤይት መሪዎች ደግሞ ቁርአን ላይ በመመስረት ማንም ሰው በፍላጎቱ አንድን ተግባር ሐላል (ህጋዊ/የተፈቀደ) ወይም ሐራም (የተከለከለ) የማድረግ ስልጣን እንደሌለው ይከራከራሉ፡፡ ጊዜያዊ ጋብቻን መሻርና መከልከል አስፈላጊ በሆነ ኖሮ ሁሉን አዋቂው አላህ በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) አማካይነት በከለከለውና በሻረው ነበር፡፡

## ሙተዓተል ሐጅ

ሙተዓት አል-ሐጅ ማለት በዑምራና ሐጅ መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ሙስሊሞች በኢህራም ውስጥ ከተጣለባቸው ማዕቀብ ነፃ ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህም በቁርአን 2፡196 ተገልጽዋል፡፡ ነገር ግን በዑምራና ሐጅ መካከል ባለው

ጊዜ የትዳር አጋር ግንኙነት (የባልና ሚስት ግንኙነት) በሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ቢን ኸጣብ ተከልክሎ ነበር፡፡ ዑመር እንዲህ ብሎ አውጀም ነበር፡፡ «ሰዎች ሆይ! እኔ ግን እንዳትፈጽሙ የምከለክላችሁና ሐራም የማደርግባችሁ እንዲሁም በፈጸመው ሰው ላይ ቅጣት የሚደነገግባቸው በአላህ መልዕክተኛ ዘመን የነበሩ ሦስት ነገሮች አሉ፡- ሙተዐተል ሐጅ፣ ሙተዐት አል-ኒሳእ (ጊዜያዊ ጋብቻ) እና «ሀያ ኸይረል ዐመል» (አዛን ውስጥ)» *(ሸርህ አል-ተጅሪድ፣ ሙስነድ አህመድ ቢን ሐንበል፣ 1፡49)*፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲህም ብሏል፡-

«በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጊዜ የነበሩ ሁለት ዓይነት ሙተዓዎችን እኔ ግን ክልክል አድርጌያቸዋለሁ፤ ሲፈጽም የተገኘንም ሰው እቀጣለሁ፡- እነዚህም ሙተዐተል ሐጅና ሙተዐተል ኒሳእ ናቸው» *(ተፍሲር ፈኽር አል-ራዚ፣ 2፡167፤ ሱነን አል-በይሐቂ፣ 7፡206፤ ቢዳያት አል-ሙጅተሂድ፣ 1፡346፤ አል-ሙሐላ፣ 7፡107፤ አህካም አል-ቁርአን፣ አል-ጀሳስ፤ 1፡279፤ ተፍሲረል ቁርጡቢ፣ 2፡370፤ አል-ሙግኒ፣ 7፡527፣ አል-ዱረል መንሱር፣ 2፡ 141፣ ከንዝ አል-ዑማል፣ 8፡293፤ ወፋየቱል ዐይን፣ 5፡197 እና ሌሎች)*፡፡

*በተጨማሪም ሱዩጢ እንደዘገቡት፡- «ለመጀመሪያ ጊዜ የተራዊህ ሰላትን ያስተዋወቀ፤ አስካሪ መጠጥ ለጠጣ ሰው መቀጫ የነበረውን አንድ መቶ ግርፋት ወደ ሰማኒያ የቀየረ፣ የሙትዓህ ጋብቻን የከለከለ፣ አምስት ተክቢራ የነበረውን የጀናዛ ሰላት ወደ አራት ያወረደና ሌሎች ብዙ ነገሮችን የቀየረ የመጀመሪያው ሰው ዑመር ቢን ኸጣብ ነበር» (ታሪኸል ኹለፋእ፣ ሱዩጢ፣ ገጽ 137)*

ቲርሚዚ በዘገቡት መሠረት ደግሞ «አብደላህ ቢን ዑመር ስለ ሙተዐት አል-ሐጅ ተጠይቆ ነበር፡፡ እሱም ህጋዊ እንደሆነ ተናገረ፡፡ ጠያቂውም ጉዳዩን የከለከለው የአብደላህ አባት መሆኑን ጠቆመው፡፡ በዚህ ጊዜ አብደላህ ቢን

ዑመር ሲመልስ፡- *«አባቴ ከከለከለና የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ደግሞ ከፈቀዱትና ካደረጉት ታዲያ ማንኛውን ነው መከተል ያለብን - አባቴን ነው ወይስ የአላህ መልዕክተኛ መመሪያዎችን»* *(ሰሂህ ቲርሚዚ፣ 4፡38)*፡፡